ሀሒፍ ሲታመር

ከበርታ ከሒይ



ተርጉም
በዮሐንስ ገበረ ጻድቅ

(ተሸሽሎ የተሪበ አራተኛ እትም - ሰኔ 2012 ዓ.ም.)

Scan by Easy Scanner

ህሊና ሲታመር

ከበርታ ክሌይ

ትርጉም

በዮሐንስ ገበረ ጻድቅ

Scan by Easy Scanner

የማስተምር መብት የተርጓሚው ብቻ ነው።

ማሳሰቢያ፡ ሁልጊዜም እኔ ስጽፍ በተቻለ መጠን የሆሀያትን አገባብ ጠብቄና የጎንቱን የአማርኛ ሰዋንና ሥርዓት-ን ተከትዩ ስለሆነ አንባቢ ከፈለገ ትምህርት ሊቀስምባቸው ይችላል። እንደ ሃሰቱ ሀ፣ሐ፣ኀ፤ ሀለቱ ሠ፣ሰ፤ ሀለቱ ጸ፣ፀ የመሳሰሉ ፊደሎች ያለቦታቸው ገበተው ሳይ ያመኛል። እነዚህ ፊደሎች የቋንቋው ወበት ስለሆኑ ጠቢባኑ እንደዚያ ያደረገት ያለ ምክንያት አይሆንምና እንወቅበት። የዚህ ሙያ አውቀት ያላቸው ሰዎች አስተያየት ይስጠበት ከማለት ሌላ የምለው የለኝም።

Scan by Easy Scanner

ምዕራፍ	ርዕስ	ገጽ
	መግቢያም	5
1	ምሥጢረኛዋ ደብዳቤ	8
2	ቦተሉ መቂጥ ምፈት	13
3	የሞት ብሥራ ለሚሰሙ	18
4	ለለመለመለሰ መሄድ	23
5	ከሞት የከፋ	28
6	ዓለሜ ሙሉ ማዘሉ	30
7	«ድንጉጥ ሳገኘው ያ ዐመ ሚኛ ነው»	35
8	ዕውሙ የጠቀመው	39
9	ጠሃቲ	43
10	የመጣሁ አገር ዜና	49
11	የሠታደር ጋሻ መከታ	53
12	ቱናቱኛ ሚስት	60
13	ለምን አጠቸሙ?	64
14	ወጣት ሚስት፣ ሽማግሌ ባል	69
15	የአሳዛኝ ታሪክ መጀመሪያ	74
16	እማ ክፍሳችሙ ይሆን?	79
17	ዘጠንገርረገገ የጽጌረዳ ኦበባ መሃል	84
18	የወዳጅነት ጥክሬ	90
19	ባል ተታለለ	95
20	ጽኑ ፍቅር	97
21	«ሁለም በዚያው መንገድ ያልፋለ»	103
22	«ፋቅር ታግኛለሽ»	106
23	በጣም ዘገየ	110
24	አደገኛ ወዳጅነት	117
25	ከጋብቻ በኋላ ፍቅር	125
26	እንኮን የለሽ ሚስት	131
27	የባል ችንተት	136
28	«ከእንተ ሌላ ሕይወት የለኝም»	140
29	«መጪረሻውን ፈጣሪ ብቻ ነው የሚያውቀው»	144
30	«አፍ ሲያመልጥ»	147
31	«ስለእንተ የነበረኝ እምነት ጐዶፌ»	153
32	የሌላ ሴት ባል	

Scan by Easy Scanner

11	የቪኒርኳ ሠላም	137
10	ልመናስ እምነፈሰሁ	160
9	የኤሊሄር መፈተሻ	171
8	...ክምት የከፋ	176
7	ሰላሰቪ ሚሩ	180
6	ከአሀብስት የከፋ	185
5	የእምላክ ክብር	188
4	የሴት ልጅ ከሀድ ጸጸት	192
3	አጽናኝ	195
2	ንግሥት ልትሆን ትችል ነበር	199
1	ሞት	205
14	የወለዱት ልጅ ሲማሰን	211
15	«እንግዲያውማ አምላኬ እርዳኝ»	216
16	የኤሊኖር ደብዳቤ	223
17	የንጉሥ ደብዳቤ	229
18	ደብዛው የጠፋ ነገር	233
19	አሳዛኝ ታሪክ	237
50	ትዝታ ለመሩት ንጥያት	244
51	የጊዜው ጥያቄ	254
52	ወደር የማይገኝለት ልመና	260
53	ያልተወደደች ሚስት ታሪክ	267
54	ታልፃን ስጠቅት	274
55	ከማድያ የከፋ	280
56	ያጓደኛ ታል	287
57	«የሠራሁት ሥራ ከይቅርታ በላይ ነው»	294
58	መልከም ዜና	302
59	ትልቁ ደብዳቤ	308
60	«መጣሀ ምስጋና ለፈጣሪ»	314
61	ደግም መፈጠጥ	318
62	«ከፈተና ውስጥ በፊሠርኩሽ ጊዜ አብጄ ነበር»	324
63	ለስለሰ ስም መስጠት	332
64	እንደገና ተሳሠፈ	337
65	«ምን ያህል እንደ ተሰታየች አስበው»	344
66	መደምደሚያ	349
67	አስተያየት፣ለሌሎች ሥራዎችፕያማርኛ ያለህምስጋና.....	351....

Scan by Easy Scanner

ትዳር ሁለት ጓደኞች አንዱ ስለሌላው መኖር የሚጀምሩበትና የተወሰኑ የግል ፍላጎታቸውን ለሌላው ደስታ ሲሉ መስዋዕት የሚያደርጉበት በመሆኑ ሁለት በመልክ፣ በባሕርይ፣ ምናልባትም በትምህርት ደረጃ፣ በእድሜ፣ በአስተሳሰብና በአመለካከት የተለያዩ ቢሆኑም መቻቻልን አንግበውና እያዩ እንዳላዩ፤ ሰምተው እንዳልሰሙ ሁነው በእርካታና በሰላምና በፍቅር ለመኖር ሲባል የሚወስዱት እርምጃ መሆን ይኖርበታል። ሁለቱ ተጣማሪዎች ይህን አሳብ በትክክል ተግባር ላይ ለማዋል ከቻሉና ቀን የሚያመጣውን ሁሉ በመጋባትና በመነጋገር ከወሰኑ ለወደፊት ሕይወታቸው ከአለት የጠነከረ መሠረት ጥለዋልና ለረጅም ጊዜ አብረው የመኖር ዋስትና ይኖራቸዋል።

ዮሐንስ ገብረ ጻድቅ

Scan by Easy Scanner

መቅድም

ይህን «Beyond Pardon» የተሰኘውን መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ያነበብኩት በሃምሳዎቹ መጀመሪያ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ ሲሆን ያን ጊዜ ያነበብኩት መጽሐፍ የእንግሊዝኛውን ትጂ ሳይሆን የእማርኛ ትርጉሙን ነው። በእጅግ የማደንቃቸውና የማከብራቸው ደራሲ ክቡር ዶር ከበደ ሚካኤል ይህን መጽሐፍ ከባሬ 56 ዓመት በፊት በሽንሾይ ትእዛዝ ተርጉመው፣ በግዞም መልክ «ከይቅርታ በላይ» በሚል ርእስ ለአንባቢ አቅርበውታል። ክቡርነታቸው መጽሐፉን ያተረጐሙት ፍሬ አሳቡን ሳይለቅ አሳምረው ነው። የእርሳቸው መጽሐፍ ገጽ ብዛት 76 ሲሆን ከዚህ ሙስጥም የራሳቸውን አስተያየት አክለውበታል።

ክቡርነታቸው ከመጽሐፋቸው መቅድም ላይ በሰጡት አስተያየት «መልካም ሥርዓት የተመሠረተለት ሕዝብ ብርታት አግኝቶ ከሌሎች ሕዝቦች በላይ ለመሆን ችሏል።...ስንዴ የዘራ ሰው ስንዴ አጭዶ ሲሰበስብ፣ እንክርዳድ የዘራ ሰው ደግሞ እንክርዳዱን ይሰበስባል አንጂ እንክርዳዱ ወደ ስንዴነት ወይም ስንዴው ወደ እንክርዳድነት አይለወጡም። እንዲሁም ሕፃናት መልካም አስተዳደግ ሲኖራቸው መልካም ሕዝብ ለማግኘት ይቻላል።.....ሕፃናት መልካም አስተዳደግ እንዲያገኙ ወላጆቻቸው ሚልት እናትና አባቶቻቸው በኑሯቸው ሂመን መልካም ባሕርይ ሊኖራቸው ያሻል። እነሱም መልካም ባሕርይ እንዲኖራቸው የኑሯቸው መሠረት የሆነው የጋብቻቸው ሥርዓት መልካም ሕግ ሊኖረው ይገባል። በዚህ ምክንያት የቤተሰብ መሠረቱ የጋብቻ ሕግ ነው። የሕዝብ መሠረት ደግሞ ሕፃናትና ቤተሰብ ናቸው። ይህም መጽሐፍ የተጻፈው የጋብቻ ሕግ የተከበረና የጠበቀ መሆን እንደሚገባው ለማስረዳት ነው» ብለዋል። ይህ አሳብ እኔም ከልብ የምጋራው ነው።

በጋብቻ መፍረስ ምክንያት መሠረቱ የተናጋ ቤተሰብ መቅኖ የለውም። የጋብቻቸውን ሙል ጠብቀው የሚይዋሩ ባልና ሚስት ደግሞ የህብረተሰብ መልክም መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ ሕፃናትን ማፍራታቸው ያጠራጥራል። ስለዚህ አገር እንዲቆናና የህብረተሰብ አባሎች በሙሉ መልክም ኑሮ እንዲኖሩ ከአላባ ድህነት የራቀና በሀሊና ፃኝነት የሚኖር ትውልድ ያስፈልጋል። የዚህ ዓይነቱ ትውልድ ደግሞ በጋብቻ መፍረከረክ ሳቢያ ኩተናጋ ቤተሰብ ይፈጠራል ለማለት ይከብዳል።

በሃሳማችን አልር አልር እንደሚታየው ቢተሰብ ቀውስና መፍረ ያሳሳደገው ልጅ ከባድ ኃላፊነት ካልሰማ ወጣበር ሳደ ቢቀመጥ ሕዝቦን ሊያስተዳድር ሳይሆን ቢቀጣ ይታያል። ይህም ያሚሆነው፣ ክቡር ይሬ ከበደ ሚካኤል እንዳሉት፣ አሚከላ አማእሳኝ፣ እንክርዳድ እንክርዳድነት ሀሊና የሌለውና ይሱንታ የፊለው ዝመልድን ስለሚያፈራ ነው። ስንዴ ሰንዴን ሲተካ የሚከወበር ቤተሰብ ሊሳሙን የሚያከወበር ልጅ ይመሰላል። ሃገሩ ይህ ከሆነ ጋብቻ መከበር ያለበት ሙል ነው። እኛም በዘኔለ ይህን መጽሐፍ ለመተርጎም የተነሳሳሁት ያ እምነት ሰላልኝ ነው። ዘመኑኢድስ ደግሞ ይህን አሳብ የሚደግፍ ይመስለኛል።

ክቡር ዶር ከበደ ሚካኤል «Beyond Pardon » የሚለውን የእንግሊ ዝኛውን ርእስ «ከይቅርታ በላይ» ሲሉ ተርጉመውታል። ከዚህም የተሻለ ትርጉም ሊኖር አይችልም። ግን ጌኤ ይህን ጥከከለኛውን ትርጉምና ከክርነታቸው የተጠቀሙበትን ርእስ አንዳለ የትርጉማን ርእስ ባደርገው እጅግ የተከበሩና የተወደዱትን ደራሲ ክብር የምነካ መስሎ ታየኝ። ምንም እንኳን በሕይመት ባይኖሩም መንፈሳቸው የሚመቅሰኝም መሰልኝ። ስለዚህ የሚደነቃቸውንና የማከብራቸውን የአገሬ ታሳቂን ደራሲ ከማስቀይም ማለታቸውን የሰው አገር ደራሲን ማስተዋመንና በእሳል ባለማቸውም በመንፈስ «ይቅርታ» ማሉቱን መረጥኩ።

የሚስ በርታ ክሌይን መጽሐፍ ስናጤነው በሞላ ጎደል ስለሀሊና ጃኝነት ነው የሚያወራው። የጋስ ጭቅር የቪ ቫንን ሀሊና አሳውሮ ባልጥን ሬስታ ሌላ አኩያዊ የሆነ መልኩመልክም ወንድ ወደደች። ሆኖም በዚያው ሀሊናዋ ጸኝነት ለወደደችው ወንድ ቤተሰብ ደስታጥን መስዋዕት አደረገች። ልዮኔል ደግሞ የስሚት ኃይል ሀሊናውን ሰላላወረበት የጋብቻ ክቡርነትን ረሳ። ያም ድርጊቱ የብዙ ሰዎችን ሕይወት አበላሸ። እርሱም በበኩሉ በሀሊና ውቀላ ሳቢያ ሕይወቱን አደጋ ላይ ጣለ። ስለዚህ የተረፃምኩትን መጽሐፍ ርእስ «ሀሊና ሲታወር» አልኩት።

ሥራችንን በሀሊና ጸኝነት ከመራነው ብዙ ነገሮች ቀና ሊሆኑ እንደሚችሉና ይሱኝታን የእለት ተእለት መመሪያችን ካደረግነው ደግሞ ዓለማችን በመኖሪያነት የሚመችና ኑሮአችንም «ምነው ባልተፈጠርኩ» የሚያሰኝ ሳይሆን የሚጥምና የሚወደድ ሊሆን እንደሚችል አንርሳ። ስለዚህ ሕይወታችንን በይሉኝታና በሀሊና ጸኝነት እንድንመራው ይሁን።

ዮሐንስ ገብረጻድቅ

ምዕራፍ አንድ

ምሥጢረኛዋ ደብዳቤ

ኤሊኖር የጢያና ጨዋታዋን አቁማ ብድግ አለች። በዚያች ሰዓት ምናልባትም ከእርስዋ ይበልጣ ተደላች ሴት በዓለም ላይ አልነበረችም ለማለት ይቻላል። ፕሪና አየመታች ታዜመው የነበረው አሳዛኝና አንጀት የሚበላ ዜማ የልጅነት ሕይወትዋን ለላስታወሳት ዓይኖችዋ እምባ አቀረሩ። ያ የሚያምረው የጥንት መኖሪያዋ ከባህር አጠገብ ስለነበር ውሃ ከማምጣ ጋር ተላትሞ አረፋ ሲደፍቅ በአሳብ ትውስታ ሰላየችው ነበር እምባዋ ያመጣው። ግን እምባው የደስታ እንጂ የሀዘን አልነበረም፣ ምክንያቱም ከዚያ ውብ ሥፍራ ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ የፍቅርን አከርማ የቀጨችውና ከልብ ከሚታሬትረው ሰው ማለት ከዛፊው ባልዋ ከስር ልዮኔል ራይደል ጋር የተዛናንችው።

ይህ ታሪክ የተጀመረበት ቀን ሰኔ 27 ሲሆን ያ ቀን ያለ ወትሮው እጅግ ውብ ነበር። ያ እለት ጸሐይ ዮግ ብሎ የበራበት፣ ምድሪቱ የተሞበችበት፣ ሰማይ የጠራበት፣ አበቦች ፈክተው ንቦች የተንጫጩበት፣ ጽጌረዳዎች መንፈቸውን በነፍ የሰቀቁበት፣ ወንዞች የሞለቡትና የእንግሊዝ ባህር ደምቆ የታየበት እለት ነበር።

ኤሊኖር ደንዎልድ ከሚገኘው ያማሪ ቤትዋ ውስጥ ቁጭ ብላ ነበር ያንን ውብ ትርዒት በአባብ የተመለከተችውና የወፎች ዝማሬ የሰማችው። ይህች ሽንኩርት የመሰለች ውብ ሴት ብዙውን ጊዜ ከዚያ ከአማሪ ቤትዎ ውስጥ ትቀመጣለች እንጂ ወደ ውጭ አትወጣም። ከቤትዋ ውስጥ በምትቀመጥበት ሰዓት ንጹህ አየር ከከፍልዋ ውስጥ በገሩ እንዲገባ ፀውትር መስኮትዋን ወለል አድርጋ ነው የምትከፍተው። መስኮት ሲከፈት መጋረጃዎችን ነፋስ በታይል ያወዛውዛቸዋል። ነፋሱ መጋረጃዎቹን ብቻ ሳይሆን ረጅም ፀጉርዋንም ጭምር ነበር ከወዲያ ወዲህ የሚያንነራት-ተው። በዚያ በሚታምሩና አስተጉ ኳስ በሚመስሉ ዓይኖችዋ በከፈተቻቸው መስኮቶች በኩል ወደ ውጭ ብታፈጥም ወደ እርስዋ የሚመጣ ሰው አልታይ አላት። ሆኖም ግን አካልዋ ብቻ ሳይሆን ነፍስዋም ጭምር የሚጠብቀው አንድ ሰው ነበር። እርሱ ደግሞ የሙሃ ሽታ ሆኖ በመቅረቱ ብት እላለም። የሚወድዱትን ጠብቆ ማጣት ምን ዓይነት ስሜት እንደ ሚፈጥርና እንደሚያሰጨንቅ በዚያ ያለፈ ብቻ ነው የሚያውቀው።

በአሥራ ስምንት ዓመትዋ ነበር ትዳር የያዘችው። ይህ ታሪክ መሃር ሲጀምር የሆያ ሦስት ዓመት ሴት ዕለነበረች የልጅነት ጠዛዋ ጥሩ አልረገፈም። ሰውነትዋ እንደ ዘምዛዛ ዋፍ ቀጠነ ብሎ እንጂ ቀርበሃ ማንድ ቀጭ ያለች መሰሎ ሴት ናት። እነዚህን ያሰፋት በራው የሚመለከታት ወንድ ሁሉ ዓይን የሚያንከራትት ሰውነት ነው ያላት። በእሱቱ በጐሮ ከፈሮ ያጌጠ የሐር ቀሚስ ነው የለበሰችው። ሙሄርዋ ላይ ያማሬ ጌጥ፣ ከተጣስዋ ላይ ደግሞ ሰሚያሚ ቀለም ያለው አበባ ሰክታለች። መለሱ ከመለሰው ጣትዋ ላይ በአልማዝና በሌሎች የከበሩ ድንጋዮች ያሸበረቀ የጋብቻ ቀለበት ሰክታለች። አለባበሰዋ ከሙበትዋ ጋር ተጻምሮ ሲመለከቱት ያወንጾችን ዓይን የሚማርክና የሚስብ ስለነበር በዚያ ሰዓት ያያት ወንድ ሁሉ ሊያፈቅራት፣ ሊመኛት፣ ሊጠብቃትና ሊኮራባት የምትችል እንጂ በጥፊ የሚያጮልጥት፣ በክርን የሚይቁሷትና በእርግጫ የሚያዳጥጥት ዓይነት ሴት አትመስልም። ገና ሲያይዋት ልብ የምትበልብና የሚሳሱላት ሴት ለመሆንዋ ማንም ሊጠራጠር አይችልም።

ግድግዳ ላይ ቁሰትሉ የነበረው ሰዓት ቂኔ ቂኔ የሚል ድምፅ በማሰማቱ ቀና ብላ አየችው። ኩቶኑ አሥር ሰዓት ገደማ ስለነበር «ገና አሥር ሰዓት ነው እንዴ» ስትል ተናገረች። ተጠለችና ደመል ስትያውል ዠጉሩ ላይ ሽበት ጣል ጣል ያደረገበትና ሂንሬ ቢኒት የሚባል የቤት ሠራተኛዋ ከነበረችበት ክፍል ገባ። ከዚያ ቤት ውስጥ ለሁለት ዓመት የቆየ ሠራተኛዋ ነው። ግና ስታየው «ሂንሬ» ብላ ተጣርታ «እርግጠኛ ነህ፣ ከስር ልዮኔል ይተላከ መልእክት ወይም ቴሌግራም አልመጣምን?» ብላ ሰትጠይቀው «ምንም የለም እመቤቴ» ብሎ መልስላት። ወዲያው ተጠለችና «እራት በሰንት ሰዓት ለማትረብ አሰባችኻል?» ስትል ጠየቀችው።

«ጠዲ አንድ ሰዓት ገደማ እመቤቴ» ባላት ጊዜ «እስቲ ከለንደን የሚመጣው ባቡር በስንት ሰዓት እንደሚገባ ጠይቁ» ብላው በማፍጠጥ እየችው። እርሱ ግን ሰዓቱን ያውቀው ናሮ «ባቡሩማ በአንድ ሰዓት ነው የሚገባው፣ ዘግይቶ በአራት ሰዓት የሚገባም ባቡር አለ» ሲል አስረዳት።

«አንግዲያውስ እራት በሁለት ሰዓት ይትረብ» ስትል ትእዛዝዋን ካስተላለፈች በኋላ «እርግጠኛ ነኝ፣ ስር ልዮኔል በአንድ ሰዓቱ ባቡር ይገባል፣ ለማንኛውም እራት እስኪተርብ እስቲ ሻይ ስጡኝ» አለችው።

ባለፈው ሰሞን ባልና ሚስት ቁርስ ቷርቦላቸው እየበሉ ሳለ ፖስተኛ ደብዳቤዎችን ይሆላቸው ይመጣል። ኤሊኖር ደብዳቤዎቹን ስታገላብጥ

Scan by Easy Scanner

ብዙዎቹ የራስዋ ሊሆኑ ለባልዋ የተጻፉ ጥቂት ደብዳቤዎችም እንደነበሩ ታያለች። የራስዋን ደብዳቤዎች ስታገላብጥ ለባልዋ የተጻፉትን ከማን እንደ ተላኩ ልብም አላለቻትም። የራስዋን ደብዳቤዎች አይታ ስትጨርስ «ልዮኔል፣ እመት ትሬዝርን ልትጠይቀን ልትመጣ ስለሆነ በጣም ነው ደስ ያለኝ፣ ብቻ ልጆችዋንም ይዛ በመጣች» አለችው ባልዋን። «ይህንው ደብዳቤ ዴግሞ ከእመቤት ሌሀሚን ነው የመጣው። ሚስ ቤልም እመጣለሁ ብላለች። ትልቅ ግብገር ሊሆን እኮ ነው! የተጠራው ሰው ሁሉ እንድም ሳይቀር ሊመጣ ነው መሰለኝ። የግብገር ወረቀት የተላከላቸው ሰዎች ቁጥር ደግሞ ብዙ ነው» አለች ከእጅዋ ውስጥ የገቡትን የግብገር ጥሪ ምላሽ እንብባ እንደ ጨረሰች።

ለባልዋ ከተጻፉት ደብዳቤዎች መካከል ከእንደኛው ላይ ዓይንዋ በማረፉ «ለእንተም እኮ ብዙ ደብዳቤ ነው የመጣልህ፤ ይህኛው ግን ምን ዓይነት የእጅ ጽሑፍ ነው?» ብላ ጠይቃ ኤንቬሎፑን አተኩራ ተመለከተችው። ፖስታው ወፈር ያለ ሲሆን አድራሻው በችኮላ እንደ ተጻፈ ያስታውቃል። ፖስታውን እንስታ ስጠችው። ያ ደብዳቤ የባልዋን ደረት፣ ከደረቱም አልፎ ልቡን እንደ ጦር ሊወጋው እንደሚችል ያላለመችው ነበር።

«ልዮኔል» አለች የዋህዋ ሚስት። «የጽሑፉ አጣጣል የሴት እጅ ጽሑፍ ይመስላል። የመጣው ደግሞ ከለንደን ነው። የማን ናት ሴት ደብዳቤ የምትጽፍልህ?» ስትል ጠየቀችው። አንስታ የሰጠችው ደብዳቤ ወደፊት የአምስት ሰዎች ሕይወት ሊያበላሽ የሚችል ለመሆኑ ያላሰበችው ነው። ባልዋ ፖስታውን በማንቋሸሽ ተመለከተው። ግን ያ ማንቋሸሽ ከመቅጽበት ተቀይሮ ፊቱ እንደዚያ ሲቀላ አለመመልከትዋ በጀ። ለእርስዋ የተጻፉትን ደብዳቤዎች ስታገላብጥ የባልዋን ገጽታ ልብም አላለችው። ቢሆንም «ለመሆኑ ደብዳቤው ከማን ነው የተጻፈልህ?» ብላ በድጋሚ ስሰትጠይቀው «የምታውቂው ሰው አይደለም» ሲል በቸልታ መለሰላት። ወዲያው ቀጠል አደረገና «አሁኑኑ ወደ ለንደን መሄድ አለብኝ፣ ፋታ የማይሰጥና አጣዳፊ የሆነ ሥራ ስለመጣ በቶሎ መሄድ ይኖርብኛል። ከቻልኩ ዛሬውኑ እመለሳለሁ» አላት።

«በድንገት የሚመጣ ሥራ ደግሞ ምን ዓይነት ሥራ ቢሆን ነው?» ስትል በጠየቀችው ጊዜ ሰር ልዮኔል ሳቅ አለ። ሳቁ ግን የዞረበትና የተጨነቀ ሰው የሚስተው ዓይነት ሳቅ ነበር የሚመልሰው። ሆኖም «ሆድዬ፣ ሊገባሽ የማይችል ዓይነት ሥራ ነው» ሲላት ብድግ ብላ ተነስታ ዓይንዋን በማንከራተት አቀፈችው።

«ልዮኔል፣ የግድ መሄድ አለብህ? ሥራው እስከዚህ አጣዳፊ ነው?» ስትል በማሳዘን ጠየቀችው። እቅፍ አድርጋ በትይዩው ወደ ሳላ ሸርተት ያለ መሰላት። ሆኖም ግን በአሰብዋ የፈጠራችው አንጂ እርሱ ከእርስዋ መሸሸ እውነት ሊሆን እንደማይችል ገመቱች። ስታቅፈው እርሱም አንገትዋ ላይ ይጠመጠማል እንጂ ሰውነቱ ከሰውነትዋ አሸሽቶ አያውቅም።

«ብዙ አልቆይም፣ ከአንድ ሰው ጋር ስለሥራ ጉዳይ ለመነጋገር ነው የምሄደው። ዛሬውኑ ወደ ማታ የምመለስ ይመስለኛል» ሲላት ጥርጣሬ ከሀሊናዋ ውስጥ የማታሰግባ ንጹህ ሴት ስለነበረች ስለደብዳቤው ሲላ ጥያቄ አልጠየቀችውም። እንዲያውም ከነአካቲው ሲላውን ሥራ አቁማ ለባህ የሚያስፈልገውን እቃ ማዘገጃጀት ጀመረች።

«ትልቅ ቦርሳ ባልይዝ ይሻላል፣ ዛሬውኑ ስለምመለስ ብዙም ነገር አያስፈልገኝም» ብሎ ቢናገርም ሰር ልዮኔል አተኩሮ ለተመለከተው ፊቱ ላይ ለውጥ መታየቱ እርግጥ ነበር። እጆቹ እንደ መንቀጥቀጥ፣ ፊቱ እንደ መቅላት፣ መላ ሰውነቱ እንደ መርበትበትና መጨነት ያለ መሰለ። ዝምጅቱ እንደ ተጠናቀቀ እስከ በር ሸኘችው። ርቆ እስከ ሄደ ድረስ ዛፍ ተደግፋ በዓይንዋ ተከተለችው። ወደ አርስዋ ቦር ሲል እጅዋን በማወዛወዝ ተሰናበትችው። ከአጠገብዋ ከመሄዱ በፊት ግን ስምዋት ነበር የሳመችው። ያለ ውትሮዋ ሆድዋን ባር ባር ስላለው በኃይል ነበር የሳመችው። በዚያች ትጽበት እርሱ ያላያት ፊት ግን እስከ አለተ-ሞትዋ አልረሳችውም።

በሚቀጥለው ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ አሥራ አንድ ሰዓት ገደማ ባልዋ በአለቱ ለመመለስ አለመቻሉን የሚገልጽ መልእክት ላከላት ። በሦስተኛው ቀን እንደሚመለስ ግን ጽፎላታል። እንደዚያ ዓይነት ትጠብቀው የነበረው ባልዋ ከቪት በመጣበት ቀን ሳይሆን በሁለተኛውም ቀን እንኳን ሲመጣ ባለመቻሉ እጅግ አነጫነጫት። ሆድዋም ባር ባር አለው።

Scan by Easy Scanner

ምዕራፍ ሁለት

የተስፋ መቁረጥ ምሬት

ኤሊኖር የቀረበላትን ሻይ እየመረራት ጠጣችው። ሻይዋን ጣጥታ ስትጨርስ አሥራ አንድ ሰዓት ይሆናል። ባልዋ ከምሽቱ በአንድ ሰዓት የሚመጣ ቢሆን እንኳን ገና ሁለት ሰዓት መጠበቅ እንደሚኖርባት ተገነዘበች። ለውትሮው ሥራ ትፈጥራለች እንጂ ገም ብላ አትሁመጥም። ባልዋ ሲለያት ደግሞ የመጀመሪያው አይደለም። እንዳሁኑ ጊዜ ግን ሰዓቲ ረዝሞባትና አስጨንቋት አያውቅም።

ከሺቶች ሁሉ የላቀ ሙያ አላት። ፒያኖ እየመታች ሙዚቃ ስትጫወት ሰው ሁሉ ጉድ ይላል። በእል ስትስል ደግሞ ሌላ ናት። መጽሐፍ ማንበብ ከጀመረች ማብሪያ የላትም። ያን እለት ግን ሁሉም ነገር አስጠላት። በለባልዋ በደህና መመለስና ዓይኑን ማየት ብቻ ሆነ ጭንቀትዋ። መላ ጭንቅላትዋ የተሞላውና ልብዋ የተሙሸው በቶሉ መጥቶ እርሱን ማየትና መነካካት በለነበር ብዙ አትበጠበጣት፣ የምትሠራውን አላጣት። ሰዓቱ ተጥ ያለ እንጂ እሙነትሰ ጊዜውን ጠብቆ የሚሄድ አልመሰላትም። ፊትዋ ብድንጓተኛ ደስታ ተፍነክንክ ዓይንዋን በዓይንዋ ወዳየችባቸውና የደስታዋ ምንጭ ወደሆኑት ልጆችዋ ሄዳች። የደስታ እርምጃ እየተራመደች ወደ ሮት ወጣች። የቤቱ ኮሪዶሮች በሚያማምሩ ስእሉችና አበቦች የተጥቡ ቢሆኑም ተና ብላም አላየቻቸው። ልጆችዋ ከነበሩበት ክፍል ውስጥ ገባች።

ከክፍሉ ውስጥ ቁርጥ አባቱን የሚመስለውና ወይፊት የቤቱ አሳዳሪ ይሆናል ብላ ያሰበችውን ወንድ ልጅዋን አንስታ አቀፈችው። ዓይኑ ትንድቡና ፈገግታው ቁርጥ የአባቱን ነው የያዘው። የልጅ አመላካከት ለባልዋ ያላትን ጽኑ ፍቅር ይበልጥ እንዲያገረሽ አደረገው። ልጁ እንደ ተወለደ ሰር ልዮኔል ሚስቱን ለማበደሰት ሲል ሕፃኑን «ጎርዶን» ብሎ በሚስቱ አባት ስም ጠራው። የልጁም ስም በዚያው ጸድቆ ቀረ። ያን እለት እርስዋም «ጎርዶን፣ እናትህ ናፍቃሃለችና እስቲ ጠጋ በልና ሳማት» አለችው። በዚህ ጊዜ ልጁ ዘልሎ ተጠመጠመባት።

ጎርዶን ጤነኛና የደስ ደስ ያለው ማራኪ ልጅ ነው። ከእንግሊዋ ላይ ተጠምቁም በሁለት እጆቹ እንት አድርጎ ያዛት። የእባቱን ዓይን በሚመስለው ዓይኑ አፍጥጦ ሲያያት «እስቲ ሳሙኝ» አለችው እንደገና። ተጥላም «ዛሬ እኮ የእናትህ መንፈስ ከፉኛ ተረብሾአል» ስትለው የእባቱን ከንፈር ሠሚመስሉ ከንፈሮቹ ሳማት፡ እርስዋም ደስ አላት። ባእነዚያ ከትናንሽ ጣቶቹም ፊትዋን ደጠበሰ። ልጅዋንም የአባቱን ያህል ነው የምትወደው።

ልጁ እጅግ በጠም ደስ ከሚል አድሚ ሳይ ነበር የደረሰው። አራት ዓመት ሊሞላው ጥቂት ወራት ነው የቀሩት። አነጋገሩ አነደ ሣር ይሳጭባል። ግርማ ሞገሱ የንጉሥ ልጅ ሥሚያሰኝ ነው። ሥንም እንኳን ቁንጅናውና አኒ ያልኩት ብጅ ይሁን ባይኑ እንዲሞላቁት መንገድ ቢከፍትለትም ቀናፋቂና ሁልጣሩ ልጅ ለመሆኑ በግልጽ ይታያል። እንደ ግንኛውም ልጅ ፍሀሩህ ልብ ነው ያለው። ከጎርዶን ተጥሎ ከልብ የምታፈቅራት ሲት ልጅዋ ወደ ነበረችበት ዮር አለች። ሕፃንዋ ግን እንትልፍ ይሠእት ተኝታለች። ስምዋ ቪክቶሪያ ይባላል። መልክዋ የሚፈነጻ አበባ ሰለሚመስል እናትዋ አምኩጥ አደለች ነው የምትጠራት። እነዚያን የመሰሉ፣ በመልክም ሆነ በጠባይ ይህ ተራቸው የማይባሉ ሁለት ልጆች ከአንድ ቤት ውስጥ መገኘት ብዙ ጊዜ የሚያጋጥም ነገር አይደለም። የሴት ልጅዋን እጅ ተና አድርጋ ሳመቸው። እንደ ማንኛዋም እናት ልጆችዋን ነናስዋ እስኪጠፉ ነው የምትወዳቸው።

«ምነው ዛሬ ፊትም ደስ አላለኝም፣ አመምዎት እንዴ?» በማለት የልጆችዋ ሞግዚት ኤሊኖርን ጠየቀቻት።

«የለም አላመመመኝም፣ ደህና ነኝ። መንፈሴ ግን ትንሽ ተረብሾአል፣ ሆዴም ባር ባር ብሎታል» ስትል መለሰችላት በትሀትና። የኤሊኖር ግርማ ሞገስና ትህትና በእርስዋ ስር የሚተዳደር ማንኛውም ሰው እንዲያደንቃት፣ እንዲያከብራትና እንዲፈራት የሚያደርግ ዓይነት ነበር።

«ምንም ነገር አለመሰማት እኮ መልካም ዜና ነው» አለች ሞግዚትዋ።

ነርዶን የሁለቱ ሴቶች ሠይይት ፍሬ አሳብ ባይገባውም የጨዋታቸውን መንፈስ በመንተራብ ብቻ «እባዬ ዛሬ ይመጣል?» ሲል ጥያቄ ጠየቀ። ጥያቄውን ስትሰማ እናቱ ሳቀች። እናት ከልጅዋ ጋር ስትጫወት ሰውነትዋ ትንሽ ዘና ስላለ ለአሥር ጊዜ ቢሆንም ጭንቃትዋንና የተረበሸ መንፈስዋን ረሳች። ለነገሩማ ከተናዛቂና ሠብ ከሆኑ ልጆችዋ ጋር ከምትጫወት እናት ይበልጥ በስሜት የሚዋዋ፣ አይታን የሚማርክና የሚስብ ትርኢት የለም። ኤሊኖር ከወንዱ ልጅዋ ጋር እየተጫወተች ሳለ አልባሽዋ ሠጥታ እመቤትዋ ልብስ መቀየር አስኝቶአት እንደሆነ ጠየቀቻት። እርስዋን ያስጨነቃት ልብስ መቀየር ሳይሆን ሌላ ነገር ስለነበር መልስም አልሰጠ ቻት። ሆኖም ግን ኤሊኖር ከልጆችዋ ጋር ስትጫወት ሳይታወቃት ሰዓቱ

በቶሎ ሄደላት። ጊዜው በቾል በሚሄዱ በማም ደስ አሰኙ። ከሚሹዋ አንድ ሰዓት ሊሆን ምንም ያህል አልቀረው። ሰዓቱ መድረሱን ሰብኂዝዋ «ለመሆኑ መኪና ወደ ባዙር ግቢያ ሄዷል?» የሚል ነበር ያመጀመሪያ ጥያቂዋ።

መልሱ 'አዎን' የሚል ሆነ። ሆሄይሙ መኪና ግን ከአሜሪ ጊዜ ቆይታ በኋላ ነበር ባጁውን የተመለሰው። ብዙ እንኪን ሰር ልዮኒልን መልእክትም ይዞ አልመጣም። ቢሆንም «ከመሸ በኋላ በሚመጣው ባዙር ይመጣል» ስትል አሰበች። 'ከሁለቶቹው ባዙር ይመጣል' በሚል እምነትም ባልዋ አስዚመዉ ፈስዋን ለማዝናናት ሞከረች። በዚያች ሰዓት ዳንም ባልዋን ለድዳ ብቻዋን ከዚች እንደማትቀር ለራስዋ ታል ገባች።

ከሁለት ቀን በኋላ የተጋበዙት እንግዶች ሁሉ መጥተው ቢትዋ ነው በሰው ሊሆን እንደሚችል በታሰላስል ዘና ብትልም አሁንም ቢሆን ሰዓቲ እየገፋ ሲሄድ በመጠኑም ቢሆን መረበሽዋ አልቀረም። ሁለት ሰዓት ሰላለፊና ልጅችዋ እንቅልፍ ስለያዛቸው ወደ መኝት ክፍላቸው ሂደው እንዲተኙ ነባረቻቸው። የሌሊት ወፍ ዜጩኸት ነፋስ ይሆኣቸው የሚሄደ የደረቁ ቅጠል ዘሽታና በፍጥ የሚሰማው የወሬጅ ውሃ ድምፅ ለመጮዉቱና ሁልም ነገር ስዋ ለዋ ለሚልቁ ምስክሮች ነበሩ።

ከሚያምረው ከፍልዋ ውስዋ ከወዲያ ወዲህ አደለች ተንቀራጠጠች። ከሚንቅላትዋ ውስዋ ያልገባ አሳብ አልነበረም። በመጨረሻ የመኪና ድምፅ ስለሰማች ልብዋ በኃይል መታ። ባልዋ የመጣ ስለመሰላት ፍርሃትዋና ሚንቀሳቅዋ ወዲያው አከተመ። ክቤት እስኪገባ መቃጭ ተስኗት ከነበረችበት ክፍል እየሮጠች መጣች። ስትወጣ በፍን በኃይል በርግዳ ነው የከፈተችው። በጽጌረዳ አበባ ወጻጊጠውና የመኪና መንገድ ወደሚያልፍበት ሥፍራ እየሮጠች ሄደች።

ልክ ናት፣ መኪናቸው ከባቡር ግቢያ ተመልሷል። መኪናው ወደሚመጣበት አትጣፄ ሮጠች። ባልዋ በጨለማ ወደ አርሷ ስትሮጥ ሲያይ ደስ ብሎት እንደሚያቅፋትና ጉንጭዋን እንደሚስም ታውቃለች። ሹፈሩ ሀና'ቱዋን ሰላየ መኪናውን አቁሞ በቶል ከመኪናው ወጣ።

«እመቤቴ፣ ጌቶች አልመጡም» ሲል መርጀውን አረዳት። እጅግ በጣም ስለደነገጠች ሐሙልት መሰላ ከደበረችበት ቆማ ቀረች። መላ ሰውነትዋ በመር ተበሳጨ ያቅሰል መሰላት። ፈትዋ ከመቅጽበት ጥቀርሻ መስለ፡ በፍርሃትም ተዋጠች። ሹፈሩ የሚያጂሊገውን ኦጥዋ ግራ በመጋባት በሙንቀጥ ዓይን አያት።

ከዋቂት ጊዜ ከዚታ በኋላ ሕሚቴ፣ ከሥሩን በኋላ ከወንደን የሚገባ ባዙር የለም» አላት የሚለውን ቢያዉ። ሩሬላ የምላከት ቢ - ብሎ አቆሙን ሳይጨርስ እናስዋ ጣልታ ገዛታ «የለም— ሰቾል መለስችለት ንግግሩን በማቋረጥ። ሆኖም «ከዚር ልዮኒል የመጣ መልእክት ወይም ቴሌግራም የለም» ስትል ጠየቀችው።

«የለም» ብሎ ሊመለስላት «የደረስ አደጋ እንዳለ የስማኸው ነገር አለ?» በማለት ፈላ ጥያቂ መየቀችው።

«ምንም አልሰማሁም። ባቡሩ እንደሆነ በሰላም ነው የገባው። ሲላት «ሰውዬው ግን አልመጣም፣ መልእክትም አልላከም። እንዲያው ግም ነው እንጂ ምን ደባላል፣ ምነስ ማድረግ ይቾላል!» አለችው ስገግታ አነጋገር።

ከቤት ውስዋ ስለሰር ልዮኔል አለመምጣት በማንሳት ውሬተኞች እርስ በእርስ ተንሾኳኩሱ። አመቤቲዉ ግን ከአትክልት ሥፍራ ብቅዋን ከመጂያ ወጂህ አያለች ለረጅም ጊዜ ቁየች። በዚያች ሰዓት በሩቅም ሆነ በቅርበት ለተመለከታት ለድንጋጤዋና ለጭንቀትዋ ወሰን አልነበረውም ብሎ ለመናገር ይቾላል።

ምዕራፍ ሦስት

የሞት ብያኔ ለሚስት

እንደማይኑጋ የስም፣ ነጋ። የጠዋት ሀሐይ ውጋጋን፣ የወሮች ዝማሬ፣ የአበቦች መዓዛና የሚይብረቀርቁው የጠዋት ጤዛ ለተከፋው የኤሊኖር ልብ እፎይታን አስገኙ ያደስታ ምንጭ በመሆን ፈንታ የበለጠ ሠዝና ትካዜ ነበር ያመጡላት። ጉም ከመሬት ከፍ ብሎ ክብ መልይ ነገር እየሠራ ሳለ ለድርቆሽ የሚሆን ሳር የሚያጭዱ አርሰ አደሮች በአካባቢው ኮሚገኝ ሜዳ ደረሱ። በረት ውስዋ ይዳሩ ላሞች ጡታቸው ወተት በኃይል እማቶ ለመታለብ እየተጠባበቁ ናቸው። የነጠር ኑሮ እንቅስቃሴ በዚህ ዓይነት በጠዋቱ እየተሟሟቀ ቢሆንም ቀደም ሲል እንደነገረው ለኤሊኖር ያ መሟሟት ያ ደማረና የደመቀ የዐለይ ብርሃን የወሮች ዝማሬ፣ የወሬጅ ውሃ ማራኪ ድምፅና የልበዎች መዓዛ የሕይወት ተስፋ በማምጣት ፈንታ መርዶ ይዘውላት ነበር ብቅ ያሉት።

ሊሊቱን በሙሉ እንቅልፍ በኑይንም ሳይሆር አደረች። ያደረችውም ፀጉሮን በቅው ሰትጠቀል በኑሙ ነፈሩ የተሞበ ሰሚያዊ ተለም ያለው የሌሊት ልብስዋን ለብሳ ነው። እንቅልፍ አልወሰድ ሰላሳት በአብቦቿው በአፍ ሚዎቿ ተደፍታ ነበር የተኛችው። ከዚያ ወዮታ ነሰፈነበት ቤት ሙስጥ ከመኝታ ክፍልዋ ገበታ በአሳብ ስትዋልልና ባልዋን በንይነብሊናዋ አያያች ብዙ ተቁነጠነጠች። ተወዳጅዋና አጅግ በጣም የምታሞርባት ሮዛ የሙችባል መራተኛዋና የልጆችዋ ሞግሪት ወደ መኝታ ነባናልዋ ሂዳ እንድታርፍ ብዙ ብትጨቃጭቃትም በጊዜ ለመተኛት ፈቃደኛ አልነበረችም። ስለዚህ ወደ መኝታ ክፍልዋ የደደችው በጣም በማይታ ነው።

«እንቅልፍዎ ባይመጣም ዓይኖን ጨፍነው ጋደም ቢሉ እንቅልፍዎም ሊመጣ ይችላል። እንቅልፍ ከመሰድም ደግሞ ቶሎ ይነጋሎታል። ንጋት ደግሞ ጥሩ ዜና ይዞ እንደሚመጣ እልጠራጠርም። እመቤቴ፣ ነገሮች ባሊታሰበና ቡተለያዩ አጋጣሚ ሲደናቀፉ እንደሚችሉ ማመት ይኖርብዎታል። ለምሳሌ ኔቶች የጸፉት ደብዳቤ በፖስታ ቤት ውሯኞች ችልተኝነት የተነሳ ሊሀገደ ይችላል' ብለው ያስቡ። ሌላው ነገር ደግሞ ባቡር ሲያመልጥ ይልታሰበ ሥራ ሊገኮምም ይችላል» አለች ሞግሪትዋ ምነበርዋን በማራብም። ሮዛ ጥሩ ምነር ብትሰጣትም ኤሊኖር ግን አለሰማቻትም። በዚህ ጊዜ ቤኔት የተባለው ምግብ አቅራቢና የቤት ውራተኛዋ ባልቃ ይገባል።

«እመቤቴ» አለ ቤኔት። «እኔ በእርስዎ ቦታ ብሆን ብዙ አልጨነቅም። አደጋ ደርሶ ስር ልዮኔል አንድ ነገር ቢሆኑ ዜናው በትድሚያ የሚደርሰው ከእርስዎ ዘንድ ነው። ጨርሶ ያልታሰበና ያልተጠበቀ ጉዳይ ሊሆን ይችላል ጌቶችን ያህሀያቸው።»

ኤሊኖር ስለሰጡት አስተያየት ሠራተኞችዋን ከመሰነኝች በኋላ እነርሱን ለማበደስት ያህል ፈገግ ለማለት ሞከረች። ሳጥላም ብዙ የማትጨነትና የማትበሳቁ መሆንዋን ገልጻ እነርሱ ሄደው እንዲተኙ አሰናበተቻቸው። የውስዋ ሞንቀትዋን ግን ለማሰናበት አልቻለችም። እንዲያውም ከነአትቴው ወሰጀ ጠልቃ ከመሸ ጀምሮ እስከሚቀጥለው ቀን የቁርስ ሰዓት ድረስ ያለው ጊዜ ለእርስዋ ገሀም ብሎ የቆመ እንጂ የሚሄድ አልመስሰችም።

በሚቀጥለው ቀን 'ደስ ይለት ይሆናል' ባሚል ሞግሪትዋ ልጆቹን ይዘ እናታቸው ወደ ነበረችበት ከፍል ይዛቸው ሄደች። እናትዮ ግን የመናገርም ሆነ የመጫወት ፍላጎት አልነበራትም። እንዲያውም የልጅዋ የጋርዶን ዓይን ነፍስዋ እስኪጠፋ የምትወድደው ባልዋን ዓይን የማየት ፍላጎትዋን በይበልጥ ቀሰቀሰው። የሴት ይጆዋ ፈገግታና ሳቅም እንደ ሞር መጋት እንጂ ደስታ አላመጣላትም።

«ቁርስ ሰበላና ሻይ ስጠሣ ደህና እሆናለሁ» ሰትል ሞግሪትዋን እያየች ተናገረች። «ያኤ...ግሰቴ በቁርስ ሰዓት ልጆቹን ይዘሽልኝ ብትመጪ ይሻላል» ብላ ሞግዚትዋ ወደ ነበረችበት ክፍል እንደትመለስ ነገረቻት። የሚገርመው ግን በድንገት ፈትዋ ተቀይሮ የብርሃን ፍንጣቂ ታየበት። ቁርስ ለመቅረቡ ያሚገልጽ ደወል ስለተደወለ ኤሊኖር ከአሳብዋ ነቃች። በአሳብ ያየችው ነገር ነበር ማለት ነው እንደቢያ የሰመጣት። ከፎቅ ወደ ምድር ቤት ወረደች። ቀደም ሲል ሮዛ ልብስ በማልበስ በትረዳትና ልብስዋን በታስማሙርሳት ደስ ያሚል ዜና በመንገር ስላዋራቻት ደስ ብሎአት እንደ መበርታት አሰች።

«የፖስተኛው መምጫ ሰዓት ደርሷል። እርግጠኛ ነኝ፣ የሆነ ጥሩ ዜና ይዞ ይመጣል» ስትል አልባሽዋ አጽናናቻት።

ቁርስ የሚበላበት ክፍል በሰፊ የመስታወት በርና በሙላ እቃዎች ያጌጠ ሰለነበር በጣም ያምራል፤ ልብን ያሳልሳል። ከፊት ለፊት የነበረው የአትክልት ሥፍራ በመስታወቱ በር በኩል ስሚታይ ውበቱ ሳይወዱ በግድ ዓይንን ይስባል። ከአትክልቱ መሀል ወደ ሰማይ እየተመነጠቀ የሚረጭ ሰው ሠራሽ ፏቴቴ አለ። ከፏቴቴው ዙርያ የለመዱ እርግቦች ውሃ ይጠጣሉ። እመት ኤሊኖር ለመትሮው ይህን ቦታ በጣም ትወደውና እያየችውም ትደሰትበት ነበር።

ቤኔት ደብዳቤዎችን ከፖስተኛው ተቀብሎ ኤሊኖር ከነበረችበት ከፍል እየተቻኮለ ገባ። ኤሊኖር ግን ራስዋን ለመቆጣጠር መስና ስለነበር ብዙም አልተቅበጠበጠችም። ሆኖም ፖስታዎቹን ለማየት መሳ ሰውነትዋ መንስፍስፉንና በተለይ አጅችዋ መንቀጥቀጣቸውን ቤኔት ይገነዘባል። ከዚያ በፊት እንደዚያ ከሀሊናዋ ጋር ስትታገል አይቶአት አያውቅም። በልብዋ ፈጣሪዋን በጸሎት እንደምትማጠን አልተጠራጠረም። ቀና ብሎ ሲያያት መንግሥተ-ሰማይ ውስዋ እንደሚበራ ልዩ ብርሃን ፊትዋ በድንገት ሲፈካ፣ መሳ ሰውነትዋ ሲፈነድቅ ተመለከተ። አርስዋም ደብዳቤዎቹን ከየች በኋላ ፈትዋን ወደ እርሱ አዙራ አየችው።

«አይዞህ ቤኔት፣ ይህኛው ደብዳቤ ሰር ልዮኔል የላከው ነው» ብላው ባልዋ የላከውን ደብዳቤ አስቀርስታ ሌሎቹን ከመሬት ማለቻቸው።

የተቀመጠችበትን ወንበር ወደ ኋላ ብመለጠጥ እጅግ አድርጋ ከሞትወደዉ ባልዋ የተላከውን ደብዳቤ ማንበብ ጀመረች። ታስታውን ከመትደድዋ በፊት ግን የታሸገውን ኤንቬሎፕ ሳመችው። በሚስቱ ላይ የሚደያ ፈታያ የሚበይነውን ደብዳቤ ነው በእነዚያ በሚያማምሩ ከንፈሮችዋ የሳመችው። የተጻፈላትን ደብዳቤ ማንበብዋን ቀጠለች።

«ኤሊኖር ይህን ደብዳቤ በታነብ በሣም አንደምትደነግጪ አውቃለሁ፣ ከአሁን በኋላ እኔ ከሩቅ በታ ነው የምሆነው። የመጪሪሻው ጉዟሀና ታማኝ ሚስቴ እንደሆንሽ አውቃለሁ። ሆኖም ግን እኔ ከአንቺ የተለየሁት ለዘላለም ነው፣ ዳግም አንገናኝም። ከዚህ ውሳኔ ላይ ስደርስ መሳሰቢን እየታውቱንና ማንም ሳያስገድደኝ በራሴ ፈቃድ የፈጸምኩት መሆኑን እወቂልኝ። የማልረባ ሰው ብሆንም ከልብ እንደምታፈቅሪኝ የምጠራጠረው አይደለም። ደህን ይብዳቢ ነገስብሽበት ሰዓት ጀምሮ ግን እጅግ እንደምትከፊ ዳግሞ አውቃለሁ። ከምወዳቸውና ከሚወዱኝ ልጆቼ የምለየው ልቤ የደም እምባ እያነነበ ነው። ነገር ግን እጣ ክፍሌ ሆኖ ራሊ ገና ስሜቴን ለመቆጣጠር ባለመታደሌ ምንም ለማድረግ አልቻልኩም። አንቺ ለእኔ እንደ መልአኬ ነበርሽ። አሁንም የመልአክ ያህል ንጹህ ሴት መሆንሽን እያወቅሁ ነው ጥሬሽ የምኮበልለው። ከአንቺ ተለይቼ የምሄደው እንዳንቺ እጹብ ድንት ሳልሆን ፍጡር ሰዋቼሽ እንደምሄድ ይገባኛል። የእኔን በደል፣ የእኔን ታጥያት ጋዜጣ ላይ ወጥቶ ከምታነቢው እኔው ራሴ አሰቀድሚ ብነግርሽ ይሻላል ብዬ ነው ይህን አስከፊ ደብዳቤ የጻፈኩልሽ።

«ኤሊኖር ይህን ደብዳቤ የምጽፍልሽ እኔ ልሁን ወይም በእኔ ላይ የበፈረው ርክስ መነፊስ ይሁን ለመለየት አልቻልኩም። አንቺን ተናፋቂዋን ሚስቴን፣ ተወዳጅ ልጆቿንና ያማረ ቤቴን ትቼ ለዘላለም መጥፋቴ ስለሆነ ደህና ሁኚ። አገሬንም ሞምር ወደ ኋላ ብዬ ከአገር ስጠፋ ግን ብቻዬን አይደለሁም። እነዚህን አስከፊ ቃላት ስታነቢ እጅግ አድርገሽ እንደምትጠይኝ እርግጠኛ ነኝ። የዘመኔ ሞልፊቶች እንዲጫወቱብሽና እንዲሳለቱበሽ ትቼሽ ከምኮበልል ያን እኔን ያፈቀረውን ልብሽን እኔው ራሴ በጩቤ ተርትሬው ብጠፋ ይሻል ነበር። ለማንኛውም ብቻዬን ሳይሆን ከሌላ ቴት ጋር ነው አገራችንን ለቅቂ የምወጣው። ወንጀለኛዋ ማብረ አበፊ ቀኒጅኖና የሊንዋ አመቤት ቪቫን ናት። ስምዋን ምናልበት የማታውቂው ይሆናል፣ ለንደን ኩትማ ሙስዮ ነው የተገናኘነው። ከተዋወቅን ሁለት ወይም ሁለት ወር ተኩል ቢሆን ነው። መጪሪሻው ይሽሙ ነው ኤሊኖር» አለ ቀጠለና፣ «ይቅርታ የማይገባኝ ሰው በመሆኔ ይቅርታ አድርጊልኝ ብዬ

አልጠይቅሽም። ታጥያቴንም ለማስተባበል አልሞክርም። የእኔ ወንጀል፣ የእኔ ታጥያት ከይቅርታ በላይ ነው። ባለፉት ጥቂት ቀናት የፈጸምኩት ጥፋትና ያደረስኩት በደል ማንም ከሚጠብቀው በላይ ነው። ይህም አዲስ ነገር ባለመሆኑ ቀደም ሲል በሹን የተጀነገና በጽሑፍ የሰፈረ ነው።

«ኤሊኖር፣ ከእኔ በቀር አንዲህ ያለ ሌላ ርካሽ ፍጡር በሕይወት ለመኖሩ አጠራጠራለሁ በሚል እምነት እኔን ለመርሳት ሞክሪ። ዳግም ባንቺ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ በመግባት አልረብሽሽም። ከአሁን በኋላ በዓይኔ የማሳየው ተናፋቂው ልጄ ሳርዶን ወራሺ ይሁን። እርሱ ነፍስ አውቆ የቤታችንን ታላፊነት እስክ ተረከበ ድረስ ከፊለማሽ ከቢታችን ሙስጥ መቀመጥ ትቺያለሽ። እኔን ወራጃውን ወነድ ለመርሳት ሞክሪ ከማለት በስተቀር ሌላ የምለው የለኝም። በእነዚያ ሙብ ዓይኖችሽ እንድታነቢያቸው እነዚህን አሳፋሪ ቃላት ስጽፍ በአንድ ወቅት በዚህ ዓለም ላይ የኖረ ፈሪና የሚታዘንለት ፍጡር ለመሆኔ እንደምትገነዘቢ ተሰፋ አደርጋለሁ። ቅንጅዋ፣ ተናፋቂዋና ታማኝዋ ባለቤቴ ለዘላለም ደህና ሁኚ። እኔ ወደ ጨለማና ወደ ሞት ስለሆነ የምሄደው ደህና ሰንብቺ። ሳልወድ በግድ ደህና ሁኚ ብዬ ልሰናብትሽ።»

ከዚያ ከተቀመጣችበት ሙብ ሥፍራ ሳትነቃነቅ እፍቃሪዋን ሚስት ለመግደል ፈታድ የተሰጣቸው ጨካኝ ቃላት በዚሁ ተጠቃለሉ። እነዚያ ቃላት ነበሩ በኤሊኖር ሕይወት ላይ የሞት ብያኔ የወሰኑት።

ምዕራፍ አራት

ላለመለስ መሄድ

ኤሊኖር ደብዳቢውን በእጅዋ እንደ ያዘች ከነበረችበት ሥፍራ ሳትነቃነቅ ለረጅም ሰዓት ከዚያው ጌች ብላ ቀረች። ነገር ግን ከንፈሮችዋ አመድ የተነፋብቸው አሸቦ መሰሉ እንጂ አላሉቀሰችም። ከድንጋይ የተጠረበ ሐውልት እንኪን እንደዚያ ንቅናቄ ሳያሳይና ድምፅ ሳያሰማ ጸጥ ብሎ ሲቀመጥ አይችልም። ብቻዋን ከነበረችበት ክፍል ቀረች እንጂ ለእርዳታ ሰው አልጠራችም። ሳትነቃነቅ የቆየችበት ሰዓት በጣም ረጅም ሲሆን በዚያች ቅጽበት ጨርሶ በድን ነበር የመሰለችው።

ደብዳቢውን ጥብቅ አድርጋ እንደያዘች ባልዋ ከእርስዋ መለየቱን እንጂ አለመሞቱን ለራስዋ ለመንገር ታነለች። ሞቱ አሰከፊኑ ቢመጣላት እርር

Scan by Easy Scanner

ድብዙ ኽህወትኡ ውዳቤ ነበረ፣ ግን ኣብዚ ጉዳይ ብሓደ ኣጋጣሚ ጥራይ ኣይኮነን ዝፍለጥ። ከባቢኡ እቲ ኣብ ኣስመራ ዝነብር ዝነበረ ሓደ ኣርመንኛ ዝዛረብ ሰብ ኮይኑ ንሱ ድማ ኣብ ሓደ ሆቴል ኣብ ሓላፍነት ስለዝነበረ ኣብ ሆቴሉ ዝነብሩ ኣብ ዝተፈላለዩ ኣጋጣሚታት ኣብ ሆቴሉ ዝተኻየዱ ኣኼባታት ስለዝነበረ ኣብ ኣስመራ ዝነብሩ ኣርመንታት ብዙሓት ስለዝነበሩ

እጅር ተኝቶ የፍትርን አዘርግ እንደሚቀጭ በእሳብ ስታይ አብዙ በማኙ ጽንናት፣ ሀሊናዋም ያንን ለመቀበል ክፉኛ ተሳነው።

በዓለማችን ሙስና ጽሞትር የሚከሰት የተሰየ የስቃይ መድሪክ አለ። ለምነሊ ለምን የሞኑና ገራሹ ነጭ ርማብ ከሠተመድ ሙስና ገዛቡ ይሰቃያ፣ የርጠኩክ ይቅር፣ ለምን ንጹሠኖና የኖህዋ እፍቃሪ ሴት ባልፈጸመችው ኃጥያት እፍራና በሙነትዋን እስማትቃ የስቃይ ኑር ትኑር! ለምን የዚህች ቆንጅና እድለቢስ ሴት የደስተና የፍትር ኑር በሰቆቃና በህዘን ይለጠጣ!

የሚገርመው ግን ደሀን የመከራ ጽዋ የቀመስች ሴት እርስዋ ብቻ አለመሆንዋ ነው። ልክ እንደ እርስዋ ቦተዋቡ፣ እንደ እርስዋ ያፈቀሩ፣ እንደ እርስዋ ታማኝና ገራገር የሆኑ በሺህ የሚቆጠሩ ሴቶች ዘመትር ከእርስዋ ይበልጣ ይስቃያሉ። ለምን? ምን መልስ አለሙ!

ብዙ ግይነት ሀዘንና ስቃይ አለ። በምት መራራነት መድበን፣ በቅናት አለንጋ መገረፍ፣ በረጅም ጊዜ ሕመምና ቁንቃት መጠውለግና ሌላም ሌላም ስቃይና ህዘን አለ። ነገር ግን አጅግ በጣም አድርገው ከሚወዱትና 'ደህ ሰው የእኔ ብቻ ነው' ብለው ከሚቆጥሩት ፍጥረኛ መጉደፍ የተነሳ ከሚመጣ ህዘንና ስቃይ ይበልጥ ልብን ሮሚያቆስልና ርህራሄ በተሰየው ጭካኔ ሕይወትን ከመቅጽበት ሮሚያበሳሽ ነገር የለም። ቢሆንም ከዚህ ቢቃላት ቀባብተው ሊሸፍኑት ከማይችሉት ስቆታ ላይ ቦሐይ ብርሃንዋን መነከቱን ቀጠለች፣ የሌትዮም ሕይወት እንዲሁ ቀጠለ።

«አመቤቱ፣ መኪናውን ይዤ የምሄድበት ቦታ አለ?» ብሎ ቮፈሩ ኤሊናርን ሲጠይቃት «ያለም» በማለት መልስ የሰጠው ድምፅ ማንኑት ለማወቅ እስኪሳነው ድረስ ኤሊናር ተለወጠችበት። ሽማግሌው አባዳሪ ጌታው የት እንዳለና ምን ወደ ሷላ እንዳስቀረው ለማወቅ በጣም ቢፈልግም አመቤቱን ለመጠየቅ አልደፈረም። ምናልባት ያቺ ደግዋና አሳዛኝዋ ሴት 'የምትነገረኝ ነገር ይኖራል' በሚል ግምት ለጥቂት ደቂቃዎች ከአጠ ንብዋ ቆሞ ጠበቃት። እርስዋ ግን እንኪን የሆነ ነገር ልትነግረው የእርሱ ከዚያ መናር እንኪን ረቢታ ፈጠዛ ነው የቀረችው።

«ደሀን ነገር ሆኖል፡ እነዚህን ሀብታሞች እንድ የሚሳቸው ይጥፋ! እዚህ አመቤቲቱ ልባቸው ሊፈነዳ ነው፣ እርሳቸው ግን ከዚያ ካማሬ የለንደን ከተማ ውስጥ እየዝኩ ይዝናናሉ። ቢሆንም አከ ይህ የመጀመሪያቸው ነው» አለ ሽማግሌው ቢያሳስል ከልጅቱ ሞገዚት ጋር ተገናኙ።

«ወዲያው እንደተመኙ በችኮላ «ጌቶች ሆት ነው ያሉትና» ብሳ ስትጠይቁው «ምንውቶው ነገር የለም» ሲል መስሰሳት። «እሳነሽ የማየው ነገር ሁሉ ደስ አይልም። እግዜ ከትድም ጀምሮ ብዙሻውን ከነበሩበት ቁጭ እንዳሉ ናቸው። ሁኔታቸውን ሲያዩት እጅግ ያስከፋል፣ የሆነ ነገር ሆነዋል። ይቅርታ ጠይቀሽ ታሩግሪያግሙ!» ሲል አማከራት።

«ደህላል፣ ሁኔታቸውን ሳየው እኔም አላማረኝም» ብላ ሞገዚትዋ የህዘንና የጭንቀት ፊት እያሳየች አመቤትዋ ወደ ነበረችበት ከፍል ሄደች። የአመቤትዋን ፊት በማየት ብቻ ኤሊናር ምን ያህል እንደ ተከፋችና እንደ ተከታየች አመተች። በህዘን ለመብከንከንዋ ራትዋ ታሳት ምስክር ነበር።

«መይኦ እመቤቴ» ብላ በመሮህ ለቅሶዋን ለታታችው። የሆነ መዋር ነገር ሰምተዋል፣ አይደል?» ብላ ስትጠይታት አመቤትዋ ቀና ብላ በፈዘዘ ግፎን አየቻት።

«አልተሳሳትሽም፣ አሰታቲ ቢና ነው የሰማሁት» ብላት ወጣትዋና ቆንጆዋ ሴት ሌላ ተጨማሪ ቃል ሳትናገር ከወዲያ ወዲህ አደሰች ተንቆራጠጠች። ከዚያም በድንገት ከሞገዚትዋ እግር ስር በእፍ ጢምዋ ቀደፋች።

ምዕራፍ አምስት

ከሞት የከፉ!

«አሙቁዋለሁ፣ አሙቁዋለሁ» ስትል ሞገዚትዋ ሮጎች። «ከጌቶች ወይም ስለጌቶች የሆነ መዋር ነገር ነው የሰሙት። አመቤቴ እንደሆነ የጌቶች ነገር አይሆንላችሙም» አለች ቀጠለችና። የተገለፈለፈውንና የጠሮቸረውን የአመቤትዋን «ድንትላት ቀና ለማድረግ ሞከረች። የኤሊናር ትላልት ዓይኖች ፈጥጠውና ፈገሠው ሲቀሩባት ሞገዚትዋ በጣም ደነገጠች።

«አመሞት እንዴ? ምንድነው ነገሩ? ምን አጋጠምዎት? ስትል ድምፅ ዋን ከፍ አድርጋ ጠየቀቻት። ቀጥላም «ልክ እኔ ካጠገብም ስቆም ነው ሀሊናዎን ስቱው የወደቁት» ብላ ስትናገር አመቤቲቱ ኑቃች።

«ለምን አሞኛል። መዋርም ነገር ነው የደረሰብኝ። መርዶ ነው የተረዳሁት። ምኑ ይደበቃል፣ ነገ ዓለም ሁሉ ሊሰማው። ባለቤቴ አኔን ጥሎ ካገር ወጥቷል» ስትላት ሞገዚትዋ ግራ ተጋባች። ከአፍሮር ጊዜ ዝምታ በኋላ «እርስዎን ጥለው ነው የኮበለሉት? እርስዎን ጥለው ጠፉ?

Scan by Easy Scanner

እኔን ትቶ ሄደ ነው የሚሉት?» በማለት አሳብዋን ስትደጋግም «አልጎ ሳይመለስ ትቶኝ ኮብልሏል» ብላ እመቤቲቱ መለሰችላት።

«የኮበለሉት ከሌላ ሴት ጋር እንዳይሆን!» ባለቻት ጊዜ «ባይገርምሽ፣ የኮበለለው ከሌላ ሴት ጋር ነው» አለቻት በመረረና ዝቅ ባለ ደምፅ።

«ወይ የእኔ እመቤት! እኔ አፈር ልብላሉት» ብላ ሞገዚትዋ አቀርቅራ ቀረች። ድንጋጤዋ ለቃላት የከበደ ነበር። እጎዳገና «ወይ የእኔ እመቤት!» ካለች በኋላ በኃይል ተነፈሰች። ቀጥላም እመቤትዋን አተኩራ እያየች «አሁን ምን ይባላል፣ ምንስ ይደረጋል» ስትል ተናገረች።

«እኔ እንጃ፣ ታሪኩ ግን ይኸው ነው» አለች እመቤቲቱ በገሃታ። «እውነትሽን ነው፣ አሁን ምን ይባላል፣ ግራ የሚያጋባ ነገር እኮ ነው፣ባሉት ሲሞቱ ሚስቶች ይቀብሯቸዋል። ከመቃብራቸውም አጠገብ ቁጭ ብለው አምርረው ያለቅሳሉ። የእኔ ባል ግን አልሞተም። ቢሆንም ለእኔ እንደ ሞተ ያህል ነው። እና አሁን ምን ልል ነው፣ ምንስ አደርጋለሁ? ምንስ ልሆን ነው? በአንድ ወቅት ከእኔ ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ታሪክ የሰማሁ ይመስለኛል። ሆኖም ግን የሰማሁት ታሪክ ከእኔ ጉድ የተለየ በመሆኑ እውነት አይመስለኝም።ያንን ታሪክ ስሰማ 'አንድ ቀን የእኔም ተራ ሊሆን ይችላል' ብዬ በውኔም ሆነ በሕልሜ አስቤው አላውቅም» ስትል ቀባጠረች።

እድለቢስዋና ረዳተቢስዋ ሴት በእድሜ ወደምትበልጣትና ጠና ወዳለችው ወደ ልጆችዋ ሞግዚት ዓይንዋን በማዞር በጭንቀት ዓይን እየቻት። በሕይወት ዘመንዋ ብዙ ነገር ያየች ሴት በመሆንዋ አንድ መላ የምትፈጥርላት መሰላት።

«እርግጠኛ ኖት፣ አልተሳሳቱም። የነገሩኝ ነገር እኮ ሊያጨኑት እውነት አይመስልም። ሰር ልዮኔል እንኳን እርስዎን፣ የረገጡትንም መሬት የሚወዱ ሰው ናቸው። አንዳንድ ጊዜ በሰው ለመጫወትና ለማፌዝ ሲባል እንዲህ ያለ ወሬ ይወራል እኮ» አለቻት።

«ቀልድ አይደለም፣ እውነት ነው» በማለት ኤሊኖር ስትመልስላት «እንግዲያውማ እመቤቴ አባትዎ ቢመጡ ይሻላል፣ መልእክተኛ ቶሎ ብለው ይላኩ» ስትል አሳብዋን አካፈለቻት።

«አባቴ ይህን ወሬ ሲሰማ በጣም ነው የሚያዝነውና የሚደነግጠው፣ በጣምም ይከፋዋል» አለች ግራ የፈጋባችው ኤሊኖር።

«ከእርሳቸው የተረበ ዘመድ ስለሌለ ቢመጡ ይሻላል። ጊዜ ሳያጠፉና ሳያመነቱ መልእክተኛ ይላኩ። አገር ወሬውን ሳይሰማ እርሳቸው ከእርስዎ ጋር ቢሆኑና ስጠያቂም እርስዎ ሳይሆኑ እርሳቸው መልስ ቢሰጡ ይሻላል። ስለዚህ ቴሌግራም ቢልኩላቸው» ስትሳት «ጥሩ አሳብ ነው፣ አንቺ የምትዪው ሳይሻል አይቀርም» አለች ኤሊኖር ሀዘን እየተሰማት። «አሁኑኑ ቴሌግራም እልካለሁ። አንቺ ደግሞ አሁኑኑ ወደ ልጆቺ ሂጂ፣ አባቴ እስኪመጣ ምንም ነገር እንዳይሰሙ» ስትል አስጠነቀቀቻት።

ሞግዚትዋ ያንን የተከራና በሀዘን የተጨማለቀ ፊት ከማየት በቶሎ መሄዱን ትመርጥ ስለነበር ሂጂ ስትባል እጅግ ደስ አሳት። ስለዚህ ሳታመነታ እመቤቲቱን ተሰናብታ ከዚያ አስፈሪ ሥፍራ ወጥታ ሄደች። እመቤቲቱ ደግሞ በቶሎ አንድ ነገር ማድረግ እንደለባት ከጨዋታቸው ተማረች። የደረሰባትንም መጋፈጥ እንጂ ከነገሩ መሸሽ እንደሌለባት አመነች። ከሰፈው ዓለም ውስጣ ብቻዋን ለመቅረትዋም እያወቀች ሄደች። ከነበረችበት ሥፍራ ተነስታ ወደ ቤተመጻሕፍት አመራች። ሆኖም መላ ለውነትዋን የሚወጥር ጭንቀት ስለተጠናወታት በሕልምዋ የምትራመድ እንጂ በውንዋ ለመሆኑ መለየት ተሳናት። እስከነኑሩዩ በሕይወት መኖርዋንም ተጠራጠረች። ቢሆንም ትንቀሳቀሳለች፣ ትናገራለች። ነገር ግን ማሰብ መቻልዋን ስታጤን ወጥታዋና እርጋታዋ ራስዋንም አስገረማት።

«ድንገት አንድ ሰው ከመሬት ተነስቶ ልቤን በጩቤ ቢቦጠርቀው ከዚህ ይበልጥ ያመኝ ይሆን?» ስትል ራስዋን ጠየቀች። ከቤተመጻሕፍት ቁጭ ብላ ለአባትዋ የምትልከውን ቴሌግራም ስትጽፍ፣ በመጀመሪያ ስምዋንና የአባትዋን አድራሻ ጻፈች። የቴሌግራሙ ፍሬ አሳብ የሚከተለው ነበር።

«አባዬ፣ በእስቮኒይ ካለሁበት እንድትመጣልኝ እፈልጋለሁ። ከባድ ነገር ደርሶብኛልና በቶሎ ድረስልኝ፣ እንጸትዘገይ።»

ቴሌግራሙን ጽፋ እንደ ጨረስች ደወል ደወለች። ቤኔት የተባለው አሽከርዋ ከተፍ አለ። በእለቱ እርሱ ብቻ ቢታዘባት ደስ ይለዋል እንጂ አይከፋውም። ቴሌገራሙን ሰጠችው።

«አሁኑኑ የሚላክ ቴሌግራም ነው። ወደ ክፍሌ እንደ ሄድኩ ለሮባ ንገራት። ከእሁን በኋላ ማንም መጥቶ እንዲረብሸኝ አልፈልግም። አባቴ እስኪመጣ ማንንም አላነጋግርምና ከክፍሌ ውስጥ ማንንም እንዳታስገቡ። እስከዚያው ብቻዬን ለመሆን ነው የምፈልገው» ስትል አዘዘችው።

Scan by Easy Scanner

ምዕራፍ ስድስት

ዓመፃ ሙሉ ማዕበል

የኤሊኖር አባት ወደ ልጃቸው ቤት እየገሰገሱ ሲሆን ቅንጅቱ ልቧቸዉ በሀዘን ተውጣ የእርሳቸውን መምጣት በመጠባበቅ ላይ ናት። ሀሳቧ እስኪናገሩ እቡቱ አንዴት ብላ የሰር ልዮኔል ባለቤት ልትሆን እንደ ቻለች በጥቂቱም ቢሆን እንነጋገር።

የኤሊኖር አባት ሚስተር ዣርዶን የትውልድ ሐረጋቸው ከታላላት የሰመ ዘር ግንድ ሲሆን ከዚተሰበሰቧቸው ታላላት ሰዎች መካከል በሕይወት ያሉት እርሳቸው ብቻ ናቸው። አገራቸው እስከድተሳንድ ቢሆንም ከእንግሊዞች ጋር በጋብቻ በመተሰሳራቸው ለበጮ ደህል እንጂ እርሰቸው 'እስኮቲሽ ናቸው' ለማለት አያስደፍርም። በባህሪያቸውም 'እንግሊዝ ናቸው' ለማለት ግን ይቻላል። ሚ/ር ዣርዶን ለእንግሊዝ የባህሪይ ምሰዋነት አንደ ምሳሌ የሚቆጠሩ ሲሆኑ የሚኖሩት ከእንድ ትልቅ ጥንታሚ ቤት ውሰዋ ነው። በአካባቢው ትልቅ እርሻ አሳቸው። ሁለት ጊዜ ነው ሚስት ያገቡት። የመጀመሪያ ሚስታቸው ገና ባልፈር ስትባል ተናፋቂ ሴት ነበረች። በልጅነትዋ ነው በወሊድ ምክንያት የሞተችው። እናትዮ በወሊድ ምክንያት ስትሞት ልጅዋ ኤሊኖር በሕይወት ናደች። የኤሊኖር እናትነ አለ አይደለ፣ ውብ ግን ለዘህ የተረገመ ዓለም የማትገባ የሚልዋት ዓይነት ሴት ነበረች። በጣም ቁም ነገረኛና ጪዋ ሴት ሆና ሳለ በልጅነትዋ ተቀጪች። ባልዋ እንደ አምላክ ነበር የሚያመልኳት። እጅግ ታታሽና ረጋ ያለች ሴት ሰለነበረች ባልዋንም እንዲሁ የረጋና ምሬቱን ዮሞጠ ሰው እንዲሆን አሰተዋዕያ አደርጋለች። ባልዋ በእርስዋ ምክንያት መልወጣቸውን በተገነበቡ ቁጥር እጅግ ይገረሙ ነበር። ከእህያ ጋር የዋለ የእህያን፣ ከጪዋ ጋር የዋለ የጪዋነት ባህሪ መቅሰሙ አይቀሬ ነውና ባልዮ የበለቤታቸውን ባህሪይ መረቡ።

ሚስተር ዣርዶን ይህቺን ተናፋቂ የሆነችዋን ሴት ባጡ ጊዜ እጅግ አዘኑ ለዓመታትም ማቅ ለብሰው ኖሩ። በመጨረሻ ግን በእንድ ባሉተጠቦቀ አጋጣሚ የብዙ ሀብት ወራሽ ከሆነችና እኒ ላንግተን ከተባለች ሴት ጋር ተገናኙ። እንዘህ ሰው ሰሚስታቸው ሞት ምክንያት ብዙ ቢያዝኑም መልካቸው ብዙም አልተንሰቄለም ነበርና ሴትዮዋ ወደደቻቸው። መጠነኛ የሆነ የአደሚ ልዩነት ቢኖራቸውም ተጋቡ። እንዳጋጣሚ ሆኖ የእኚህ ሰው ሁለተኛ ሚስትም ከሞላ ጎደል ጥሩ ሴት ነበረች ለማለት ይቻላል።

ሴትዮዋ በእንደንድ ንዝር ሳይ ሐሰትና የሥነምብር ባህርያ ሲኖራት በዙዙ ነገርዎ ሩህሩህ ነበራች። ሥሉኝ የሆነ ተንኮል ግን በውሳኔዋ ነበር አግለጫ ይቻሳል። ቢሆንም ቢታገሰዉን በማስተዳደር ረገድ ባለመ ይ ጎ። ያንን ማዙር ቤት ሰው አይተጋና ሐሰሥው ነበር የያዘችውህ ታማኝ፣ አመኔተኛና ረጋ ያለች ሴት ብትመስልም ጉልፎ አልፎ ግልፍ እንደሚሳዞ ጎረቤት ሁሉ ያውቃል። በዚህም የተነሳ አንዳንድ ጊዜ ባልዋ ገራ ያገዘቸዋል። ቢሆንም ሰውዬው በማይታገሱው እገም ጠተን ባህርያ ይሰደል። ኒንጂ ብዙም አያዘወሯም። እርስዋም ሚስቲቱ ተከናንቦ እያደርሳስሁ ብሰው ከቢታቸው ሲመሙ ስጥና ቀጳሙታ ትተበሳቸዋለች። የባፊሙስ ምቤ የሚያስመታ ነው። ባሌበት ሰዓት ደግሞ ከመትጽበት ታኮርፍቸዋለች። ከዘመናት በኋላም ቢሆን የጠባይዋ መለዋወጥ ምክንያት ምን እንደሆነ ሊደርሰበት ባይችሉም አገል ጠባይዋን ሰለተቀበሰት አሪፈም መረረ ባልና ሚስት በጀስታ ለመኖር ቻሉ።

የቤት ሠራተኞች እመቢታቸውን ማለት ሚሰዮ ዣርዶንን ይወዳሉ። ኤሊኖር ግን ሴትዮዋን ለመጥደድ ብዙ ብትሞክርም ልታፈትራት አልቻለችም። ሴትዮዋም ብትሆን ልጅትዋን ከልብ የማፍቀሩ ነገር አልሆነሳትም። ግን በሁለቱ መካከል ይፋ ያወጣ ጥላቻ አልነበረም። ልጅትዋ ያእንጀራ እናትዋን ከሥታዘዝና ጠባይዋን ለማሳመር ከመሞከር ወደ ኋላ አሳሰችም። የኢናትዋን ቦታ በመውሰድዋ ግን ልብዋ ጠሳት።

የሚስተር ዣርዶን ሁለተኛ ሚስት ከእንጀራቸዉ የመጣ ልጅ ቢኖራት ደስ ባሳት፣ ግን መሐን ሰለነበረች ልጅ አልወለደቻም። በዚህ ምክንያት ነበር ኤሊኖርን የጠላቻት። ቢሆንም በትናት ሳቢያ ልጅትዋን ብትጠሳትም ኤሊኖር ማግኘት የሚገባትን ሁሉ ከማሟላት አልቀዙጠበቸም። አባትዋና የቤት ሠራተኞች ግን እጅግ በማም ሰለሚወዷትና በለሚያከብርዋት ዘውትር ጥቅራቸውን ይገልጹላታል፤ አንድ አምላክም ያይጥታል።

ልጅቷ አሥራ ሰባት ዓመት ሲሞላት መልክዋ እየወጣ ሄዶ በአገሩ ውስዋ እሱ ከሚባሉ ቆንጆጅት አንድዋ እየሆነች መጣች። መልክዋ ሲፈነዳ የተቃረበ ጽጌረዳን መሰለ። ጌቃትዋና አመተትዋ የሚያስቀና ነበር። ጤናዋም የተሟላ ስለነበር እምቢተ ነበር የምትመስለው። እንዲህ አምራና ጀምቃ በታዮችበት ጊዜ አባትዋ አንድ ቁን ወደ አደን ሥፍራ ይዘዋት ይሄዳሉ። ከዚያ ሥፍራ ደግሞ ክሌላ ቦታ የመጡ ሌሎች ብዙ ሰዎች ነበሩ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ሰር ልዮኔል ራይዳል አንዱ ነበር።

Scan by Easy Scanner

ሰር ልዮኔል ይህችን ልጅ ገና ሲያያት በፍቅር ወደቀሳት። እርስዋም ገና ስታየው ወደደችው። የሁለቱ ፍቅር በፍቶተ-ሥጋ ጥማት ላይ ያተኮረ ሳይሆን ጸር ድንበር ሲደረግለት በማይቻልና ከውስጥ ፈንትሎ በሚወጣ የሁለት ሰዎች መፈላለግ፣ መሳሳብና መመኘት ላይ የተገነባ ነበር። ከቪዛም በላይ አንዱ ሌላውን የማምለክ ባህርይ የታከለበት ፍቅር ስለነበር ሰር ልዮኔል ከአንድ ዓመት በላይ ተከታተላት፣ አባበላት፣ አሽኮረመማት፣ ተጻራት። በዚህ ጊዜ ለፍቅራቸው ወሰን አልነበረውም። በዘመኑ ከሁለቱ ለሆኑ ፍቅር የላቀ ሌላ የፍቅር ታሪክ አልተጻፈም። ከእነርሱም ወዲያ ያማረበት ቆንጆ ለአሳር ነው ተባለ።

ያያቸው ሁሉ ይደሰትባቸዋል፤ እነርሱም ተደሳቾች ነበሩ። ከተፋቀሩ እንደ ልዮኔልና እንደ ኤሊኖር ነው ተብሎ ተወራ። ጎረቤትና መንደርተኛ ሁሉ ቀናባቸው። ልባቸው በፍቅር ብርሃን ፈክቶ ሁለቱም ባልተናነሰ መልኩ እየፌነደቁ ከጎጥ ጎጥ፣ ከመንደር መንደር ሳይቀራቸው ሁሉንም ተምነሽንሸበት። ዘለሉ፣ ወጡ፣ ወረዱ፣ ተቃቀፉ፣ ተጻሩ፣ ተሳሳሙ። ከዚያ ወዲያማ ምሉ ቅጡ፣ እንዲያው ገም ነው እንጂ ህቅ ህቅ፣ ያገ ሰቀቅ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ሞክረዉት። ስለዚህ በሁሉም ነገር ተደሰቱበት ግለቱ ይበቃል። በመጨረሻ ተጋቡ። የሠርጋቸው እለት አልማገና ወርቅ ሳይቀር ስጠታ ጎረፈላቸው፤ ለዉም ጉድ አለ። በእለቱ የእንጀራ እናትዋ በአልማዝ ያሸበረቀ ስጦታ ስትሰጣት ግን ትንሽ ቅር የሚያሰኝ ንግግር ተናገረቻት።

«ልጄ እኔ እንደሆነ ነብር ይመስል ቱሉ ግልፍ ይለኛል። ይገርምሻል፤ ከማህፀኔ የወጣ ልጅ ስለሌለኝ ነው መሰለኝ ገና ሳይሽ እናደድ ነበር። ብቻ አሁን እርሱን እንተወውና ይሽውልሽ ለልዕልት የሚገባ ስጦታ ነው የገዛሁልሽ። የማያልቅበት ቸር እምላክ ጋብቻሽን ይባርከክ። ደስታ፣ ጤናና የኑሮ ብርታት ከእንቺ አይለዩ።»

ለማንሻውም የጋብቻቸው ሥነሥርዓት የደመቀ ነበር። ወሐይዋ በጎሱን ለማክበር የተዘጋጀች ይመስል ደምቃ ዋለች። አበቦች ደግሞ በቂ የፀሐይ ብርሃን ስላገኙ በእለቱ እጅግ ፈኩ። ሳቅረሞቹም ለዚያች ቀን በመብቃታቸው ሶሚታቸው ግንፍሎ ደስታ ከፊታቸው ላይ ወለል ብሎ ታየ። የተጠራው ሰው እጅግ ብዙ ስለነበር ታቦት በሚነግስበት እለት ካልሆነ በቀር እንደዚያን ቀን ሰው ሲበዛ ታይቶ አይታወቅም። ከሥነሥርዓቱ በኋላ ሰው ሁሉ ለለመጣው ተጋባኝ ብዛት ብዙ እወራ።

ኤሊኖርም በዚያች ቡተረገመች ሀዘንዋ እለት የሠርግዋ የነበረውን ሁኔታ ታወሳትና ወደ ኋላ ተመልሳ እንደ ሕልም በሞሳንሞል አየችው። «የዚያ ሁሉ ፌንጠዚያ፣ የዚያ ሁሉ ደስታ መጨረሻ ይህ ሆነ» ስትል ብዙ ቆዘመች። ሳይታወቃት እምባዋ ከጉንጮችዋ ላይ እንደ ጎርፍ ፈሰሰ።

የጋብቻቸው ሥነሥርዓት የተፈጸመበት ጥንታዊው ቤተክርስቲያን፣ በአካባቢው የነበረው የዛፍና የአበባ ዓይነት፣ በደስታ ፌንድቆ ከወዲህ ወዲያ ሲቅበዘበዝ የነበረው የአባትዋ ፊትና ዓይን፣ ሙሹሮቹ እጅግ እምሮባቸውና ደምቀው ሲያይዋቸው፤ እነርሱም በተራቸው የዚያን ዓይነት እድል እንዲገጥማቸው በመመኘት ከወንድ ወንድ ያማርጡ የነበሩት ሚዜ ሦች ገጽታ፣ ሙሽራው በፍቅር ጠምብዞ ፊቱ ሲፈካ ያሳየው ፈገግታ፣ እንደሚጨመቅ ልብስ አልፎ አልፎ እንቅ አድርጎ የያዘው ለስላሳ እጅዋና ሌላም ሌላም ነገርዋ ሁሉ ወደ ኋላ መለስ ብላ በዓይነ-ህሊና መስታወትነት በአላብ ቃኘችው። የፈረንጆች ባህል ነውና በጋብቻቸው ማግስት ተያይዘው ለጫጉላ ሽርሽር ከአገር በመጥፋት ለመዝናናት ያደረጉት ጉዞም ቁልጭ ብሎ ታያት። በእለቱ ሜዳ ለሜዳ ሲሮጡ ልቦናዋ የተሞላውና ትሰማው የነበረው ድምፅ የአንድ ሰው ብቻ ነበር....ያአዲሱ ባልዋ ድምፅ። መላ አካልዋንና ነፍስዋንም ሙምር ለፍቅረኛዋ ስለሰጠች በወቅቱ ከእርሱ ወዲያ ሕይወት እንደሌለ አምና ነበር የተቀበለችው።

በሠርጋቸው ሰሞን ከሽርሽር ቦታ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የቤት ሠራተኞችና ዘመድ አዝማድ አንድም ሳይቀር መጥቶ በሀገሩ ባህል መሠረት ሲዘፍንን ሲጫወት፤ ሲበሳና ሲጠጣ የነበረው ሁካታ፤ አባትዋና የእንጀራ እናትዋ በደስታ ፌክተውና ተውጠው ሰዉን ሁሉ እጅ ሲነሱ፤ ሙሽራው የሙሽራዋን እጅ ይዞ ከቤት ሲገባና ሌላ ሌላውንም ሁሉ አሁንም በአላብ ስላየቸው እምባዋ አልቆም አላት።

በጊዜው ኤሊኖር ከባልዋ ፍቅር ሌላ ለምንም ነገር ደንታ አልነበራትም። ዓመት አልፎ አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር «መጪው ዓመት የሰላም፣ የፍቅርና የደስታ አድርግልን» ብላ ትጸልያለች። ኑሮአቸው በፍቅር የተሞላ ቢሆንም አልፎ አልፎ ባልዋ በሥራ ምክንያት ይሰደታል። በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ ወደ ለንደን ከተማ ይሄዳል። ሰር ልዮኔል ለሥራ ጉዳይ ወደ ለንደን በሄደ ቁጥር ከባልዋ ጋር አብሮ የመሄድ ወይም አገሩን የማየት ጉጉት አልነበራትም። በመጨረሻ ሲሄድ ግን ምክንያቱ አይታወቅም፤ እርስዋ ሳትሆን ባልዋ አብራው እንድትሄድ ፌልጎ ነበር። ሆኖም ሴት ልጃቸው ሕፃን ስለነበረች ኤሊኖር እርስዋን ጥላ ለመሄድ አልፌለገችም።

Scan by Easy Scanner

«በሚቀጥለው ዓመት ግን አልቀርም፣ አብሬህ እሄዳለሁ» አለችው መጎንጅ ከመጀመሩ በፊት። እርስዋ አልሄድም ብትልም እርሱ የሚሄድበት ቱዳይ የሚቀርብት ዓይነት ስላልነበረ ብቻውን ሄደ። የሚገርመው ደግሞ በዚህ ጉዞው ነበር ያ መሆን የሌለበት ክህደት የተፈጸመው።

ኤሊኖር በትዳርዋ የረካችና የመጨረሻዋ ተጀላች የቤት እመቤት ነበረች። አምስት ዓመት ሙሉ አብረው ሲኖሩ አንድም ቀን ተሳልቷት ወይም አስቀይሟት አያውቅም። ክፉ አልተናገራትም፣ በነገር አልሳነቱለትም፣ ኑጋ ጠባ የፍትር አዘርማ ነበር የሚያሲታቸፋት። ስለዚህ አውን በመጨረሻ ባልዋ ላይመለስ ጥሎአት ሲሄድ ድንጋይ ሆኖ ብትቀር፡ ብትታመምና ልብዋ በሀዘን ብዛት ቢፈርጥ የሚገርም ነገር አይሆንም።

ምዕራፍ ሰባት

«ድንግል ባገኘው ያ ሰው ሚሻ ነበር»

የማያልፍ የለምና አንድ ቀን አለፈ። መጥፎ ነገር እንደ ደረሰ ደግሞ የቤቱ ሰው ሁሉ አውቋል። በዚህም ልጆቹ እንኳን ሳይቀሩ የቤቱ ሰው ሁሉ ችሰሙ ተሰበረ። በአንድ ወቅት አምርሮና ደምቆ የነበረው ቤት የተመረረ ከተማ መሰሉ ከመቅጽበት እጅግ ጭር አለ።

«እማዬ ስላመመሽ ሚጯታ ሁሉ አስጠልጅታል» አሉ ልጆቹ። ኅርጾነ ግን «አባዬ፣ አይመጣም እንዴ?» ሲል ደጋግሞ በመጠየቅ አሰቸገረ። አባቱ ብዙ ጨዋታ አስለምዶት ስለነበር የእርሱ ነገር አይሆንለትም። ሆኖም እያለቀሰ ሲያስቸግር ምግዚትዋ በመቆጣት ዝም አሰኝትው።

ኤሊኖር በጠዋት ከርቅ ወደ ምድር ቤት ወረዳች። ፊትዋ ገርጥቷል። ሰውነትዋ ጠሙልጓል። ልብን ከሁለት የሚከፍል ሀዘን እርሷንትዋን ለመጠ ያቺ ቆንጆ ሴሳ ሴት መስላለች። ጠበቃው ዓይንዋን ብዩ ጊዜ እጅግ ደንግጠ «አሁን ጉዳዩን ባነሳባት እገድላታለሁ» ሲል አሰበ። ሚስተር ፍርተን የሕግ ባለሙያ ሲሆን የመጣው የኤሊኖር አባት ዜናውን እንደ ሰሙ በአስቸኳይ ወደ ልጃቸው ቤት እንዲሄድ በቴሌግራም ሰለጠየቁት ነው። ኤሊኖር ቱሰፋ በቆረጠ አመለካከት ቀና ብሳ ዓይን ዓይኑን እያየች በእጅዋ ይዛው የነበረውን ጋዜጣ አመላከተችው። በዚያች ሰዓት አባትዋም መጥተዋል።

«ዓለም ሁሉ ወሬውን ሰምታለ! ድምግችንን ዝግ አድርገን መወያየቱ ዋጋ የለውግ» በማለት ሲናገሩ «አባዬ ክቢታችንን ይዘሽኝ ብትሄድ ይሻላል።

መሞቱ ካልቀረ ከዚያው ብሞት ይሻለኛል። አልቻልሁም። ሁሰቱ ወንዶች በአንጋገሮዋ በሚታየው ስለተነሳ ከተቀመጠበት ብድግ ብለው ጠበቃው ወንበር ሲያስተካክልላት አባትዋ እጅዋን ይዘው ከወንበሩ ሳይ አስውጥ ዋት። አንርሱም አጠገብዋ ሁነው ከግራ ቀኝ ቆመ። አባትዋ በጥን እጃቸው ትከሻዋን በግራ አጅትው ሳንበስ ብለው አንድ አጅዋን ያዙ።

«አይሆሽ ልጅ፡ እኔ አለሁልሽ» አሉ አባትዋ አንዳበታቸው አየተንቀጠ ቀጠ። «እመኚኝ፣ ይሕይወት እስካለሁ ድረስ አንቺንና ልጅችሽን መንከባከብ አደቅተንም። ብዙ መናገር እንደማይሆንልኝ የምታውቂው ነው። ልትሚ በፈታዩ ሁሉ ግን ነመንኛውም ነገር አጠብቅሻለሁ፣ የከዳሽን ደግሞ አሰቀለሞለሁ። ማንኛውንም ቁሰል የሚወግሃው ቆራጥነት ስለሆነ ኤሊኖር መበርታት አለብሽ» ሲሉ መከሯት።

«የእኔ ጉድ የሚጠግኑትና የሚረሰት አይደለም» አለች ኤሊኖር ስትመልስሳቸው። «ልቤ ከመድማት አልፎ ቆስሎአል።»

«ለማንኛውም እስቲ አሁን ጋዜጣው የሚሰውን እንሰማ» ባልዋት ጊዜ ጋዜጣውን ለሚሰተር ፍርተን ለጠቻውና ስለባልዋና ስለራስዋ የተጻፈበትን ሥፍራ አያመለከቱት። ድምውን ከፍ አድርጎ አነበበው። በሚቀጥለው አኳኋን ነበር ጋዜጠኛው ዜናውን ያቀረበው።

«በተደላደለ ኑሮ ላይ የቸፈጸመ ደባ።» በጋዜጣው ላይ የሰፈረው ጽሑፍ ርእስ መሆኑ ነው። «ወጣትዋና ቆንጆዋ ሴት ወይዘሮ፣ ባልዋንና ቤትዋን ጥላ ከአገር በመነሣለልዋ ዓለም ሁሉ ተገርሞአል። መገረም ብቻ ሳይሆን የአገሩ ሕዝብ ነገሩ አልጋባ ስላለው ግራ ተጋብቷል። ይህ ታሪክ የሚወራላት ሴት የዘመናችን ንግሥት ተብሳ የተወሳላት ናት። አብሯት የነበለለው ሰው መልዘመልክም፣ አዋቂና ወጣት ክበርቴ ሲሆን የሚያሳገኘው እርሱም በበኩሉ ቆንጆ ሚስቱንና ልጆቹን ጥሎ ነው ከእርስዋ ጋር የሄደው። አንደሚወራው ከሆነ ሁለቱ ፍቅረኛች ከአገ ፊት በመቅረብ የፍቺ መብት ከጠየቁ በኋላ ከኮበለሉበት አገር ተጋብተውና ባልና ሚስት ሆነው ወደ አገራቸው ይመለሳሉ ይባላል። ስለዚህ አሳገኝ ደባ ተጨማሪ ዜና እንዳገኘን በሚቀጥለው አትማችን እናወጣዋለን።»

«ሚሪ ፍርተን» አሉ አባትዋ ግራ በመጋባት። «ምን ማድረግ ይሻላል?» ብለው ሲጠይቋት ምን ማድረግ እንደሚሻል ጠበቃውም እርግጠኛ አልነበረም። እርሱም በበኩሉ ግራ ተጋብቶ ለተወሰነ ጊዜ ዝም አለ።

ቢሆንም ግን ጊዜ ወለደ እንጂ በሕግ አኳያ ምን መደረግ እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል። ደፍሮ ለመናገር ግን አልፈቀደም። የሴትዮዋን ሞራልና የቤተሰቡን ስም ማስከበርን በተመለከተ አሳብ ለመሰጠት ተቸገረ።

«ኤሊኖርም ብትሆን ምን መደረግ እንዳለበት የምታውቅ አይመስለኝም። እኔም 'እንደዚህ ቢሆን ይሻላል' የምለው አሳብ የለኝም። ሰለዚህ ኖርተን አንደ መርከብ መቅዘፊያ አንተው ብትመራን ይሻላል» ሲሉት «ቢለኝጋርዎ ሕግን ተመርኩዞ እርምጃ ቢወሰድ ይሻላል ለማለት የፈለጉ መሰለኝ። እንዲህ ያለ ጉዳይ ሲገጥም ከመታገስ በስተቀር አማዳፊ እርምጃ የሚያስወስድ ሌላ አማራጭ ያለ አይመስለኝም» በማለት መለሰላቸው።

«አንድ ነገር መደረግ ግን አለበት። ልጅ በህዘን ብዙት ልብዋ መቁሰሱን እያየሁ ዝም ብዬ ልቀመጥ አልችልም። ያ አረመኔ ደግሞ ከትጣት ሊያመልጥ!እንዴት ተብሎ? የሚሆን አይደለም።»

«ከሰሜቱማ ሲመለስ በሚገባ ይቀጣል» አለ የሕግ ባለሙያው በቀዘቀዘ እንደበት። «ነገሩ ከእመት ኤሊኖር መጻፍ ሰር ነው ያለው። ደብዳቢውን ብቻ እንደ ማስረጃ በማቅረብ ፍቺ ለመጠየቅ ትችላለች» ብሎ ጠበቃው ሊናገር ፈለም» አለች ኤሊኖር በዓይንዋ እየገረመመቻቸው። «በምንም መንገድ ባሌን አልፈታውም።»

«እንግዳያውማ ሰር ልዮኔል መቼም ቢሆን ቪቫንን ሲያገባ አይችልም» ሲሳት ኤሊኖር ዞር ብላ ጠበቃውን በማፍጠጥ አየችው።

«ለሙ ጌታዬ» አለች፣ «ሰው የሚያወራውን ገባገነኝኬ ሁሉ ወደዚህ አያምጡብኝ። እኔ በእግዚአብሔር ትእዛዝ አምናለሁ። እንዴት ተብሎ ነው የእኔ ባል ሌላ ሴት የሚያገባው?» ብላ ስትጠይቀው «ሕግ አንቺን ነፃ ሲያወጣ ነዋ ኤሊኖር!» ሲል መለሰላት።

«ሕግ ነፃ ሊያወጣኝ አይችልም። ማንም ቢሆን እግዚአብሔር ያወጣውን ሕግ የማፍረስ ሥልጣን ስለሌለው ይህ ሥልጣን ለሰው ልጅ ሊሰጥ አይችልም። እግዚአብሔር አንድ ያደረጋቸውን ባልና ሚስት ሰው ሊለያያቸው አይችልም» ስትለው «ግን እኮ» አለ ሚ/ር ኖርተን፣ «ያንን መሓላ፣ ያንን እግዚአብሔር ያጣመረውን ጉዳይ ያፈረሰው ባልሽ ነው።»

«ሊያፈርሰው አይችልም» አለች ተስፋ ለመቁረጥዋ ፊትዋ ላይ እየተነበበ። «አይችልም፣ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየውም።»

«እንግዲያውማ በትክክል ገብተኛ ከሆነ የጋብቻችሁ ውል እንዲፈርስ ጉዳዩን ከሕግ ፊት ለማቅረብ አትፈልጊም ማለት ነው?» ብሎ ሲጠይቃት «በፍጹም ሚ/ር ኖርተን፣ ጨርሶ የሚታሰብ አይሆንም» አሰኘው።

«ይህን ብታደርጊ ግን በአገራችን ሕግ መሠረት ባልሽን መርታት እንደሚችቺና ከባልሽ ጋር የነበለሽውም ሴት ባልዋ ቢፈታትና ባልሽ እርሰዋን ቢያገባ አንቺ ደግሞ ፍቺው ከተፈጸመ በኋላ ሴሳ ባል የማግባት መብት እንደሚኖርሽ አያውቅሽ ነው ክሰ ለመመሥረት የማትፈልጊው?» ብሎ ሲጠይቃት «አውቃለሁ» ስትል መለሰችለት። ይህን ጊዜ «በእኔ በኩል ግን ሕጉ የሚፈቅድ ለመሆኑ ለማሳሰብ እንጂ አንቺን ለመገፋፋት አንዳልሆነ ይገባሻል፣ አይደል?» ብሎ ጠየቃት።

«ይገባኛል» አለችው ፈጋ ባለድምፅ። «ግን አሁንም ቢሆን ፍቺ የሚባለው ነገር የሚሆን አይደለም። ባሌ ጥሎኝ ቢኮበልልም እኔ ቃሌን ጠብቄ እኖራለሁ፣ መጠበቅም ግዴታዬ ነው። የጋብቻዬ ውል እንዲሰረዝ ፍርድ ቤትን አልጠይቅም፣ ሌላም ባል አላገባም። የዚህ ዓይነት አሳብ ሲነሳ እንኳን ይዘገንነኛል። ባለቤቴ ላይመለስ ጥሎ ሂዷል። ልጆቼንም ጥሎ ነው የሄደው። እኔ ግን ቃሌን አክብሬ እኖራለሁ።»

የኤሊኖር ልብ በህዘን ብዛት ስለተጨማለቀ ከመጠን በላይ ቆስሏል። ህዘኑ ምን ያህል ልብዋን እንዳቆሰለው ግን አልተገነዘቡላትም። እርስዋ ባልዋን እጅግ በጣም ነው የምትወደው። ልብዋ አርሱን ለማግኘት ፈልጎ ሲያገኘው ስላልቻለ ከዚያ ጭንቀት ቶሎ ለመገላገል ነበር የምትፈልገው። አባትዋና የሕግ ባለሙያው የሚያወሩላት ግን ስለፍቺና ሌላ ባል ስለማግባት ነው።

«እስካሁን መቼስ ወሬው ተባምቶ የአገሩ ሰው ሁሉ ሳይሰማው አልቀረም» አሉ አባትዋ ሚስተር ጎርዶን። «ኖርተንን፣ አንተ ብዙ ሰው ታውቃለህና ለመሆኑ ይህ የሌኑ ከበርቴ በመባል የሚታወቀውና የልጂን ባል ያስኮበለለችው ሴት ባል ማነው?» ብለው ሲጠይቁት «ስለሰውዬው ብዙ አላውቅም፣ ግን በእድሜ ከስልሳ ዓመት በላይ የሆነው ሽማግሌ ሲሆን ሀብት የተትረፈረፈው ጌታ የጌታ ልጅ መሆኑንና የሚኖረውም አርነስ ከሚባል ሥፍራ እንደሆነ አውቃለሁ» ሲሳቸው «ስለባለቤቱስ ስለቪቫን የምታውቀው ነገር አለ?» በማለት ጠየቁት።

«የለም፣ ፎቶግራፍዋ ግን አምና ለንደን ከተማ ውስጥ በየሱቁ በራፍ ተሰቅሎ እንዳየሁ ትዝ ይለኛል። ሲበዛ ቆንጆ እንደሆነችና የእስፖኝ

Scan by Easy Scanner

ደም እንደሳትም ሰምቻለሁ። ስሥራ ጉዳይ ወደ ለንደን ከተማ ስሁሰትና ስሦስት ወራት ሄጄ ሳለ ያያት ወንድ ሁሉ ምራቁን እንደሚውጥሳትና እንደሚመኛት ሲወራም ሰምቻለሁ።»

የሁለቱን ሰዎች ጨዋታ ኤሊኖር መሬት መሬት እያየች ትሰማለች። ሚስተር ፍርተን ስለሴትዮዋ የተናገሩት ሁሉ ለኤሊኖር አጅግ መራሪ ነበር። ባሳንጣዋ ሴት ያያት ወንድ ሁሉ በሠበትዋ የሚማረከና ከእርስዋ ይበልጥ ቆንጆ መሆንዋን መስማቱ አጅግ ነበር የከፋት። ለማነኛዋም ሴት ቢሆን ከንቺ 'ባሳንጣሽ በቁንጅና ትበልጣለች' የሚለው ዜና ለመሸከም ቀላል እንዳልሆነ ማንም የሚያውቀው ነው። የምትወደው ባልዋ ከጢያት አጅግ ከተዋበች ቆንጆ ሴት ጉያ ገብቱ ሲወሸቅ በዓይነ-ህሊናዋ ባያቸ ጊዜ አላቡ ዘነናት። ሁለቱ የሚፈጅሙት ትርኢትንም ለመቀበል ተቸገረች።

«ሊገላታለሁ» ብሳ ሳይታወቃት ድምፅ እሙቱታ ሰትናገር አሳትቀ «ገሳገልሻት ግለት ነበራ» አሉ ። «ወይኒ ልጂ፣ ያባቴ እምላክ ያንገብግባትና አንገበገበችሽ አይደል? እደሆሽ ልጂ። ሰማህ ኖርተን፣ ያን አታሳይ አንድ ቀን ባሸንው እርሱ ሳይቀድመኝ እኔ ቀድሜ እገድለዋለሁ።»

«ጌታዬ፣ ቆይ እስቲ ረጋ ይበሉ፣ አሁን የመገዳደል ነገር ምን አመጣው» አለ ጠበቃው። ሚሀር ነርዶን ደወል ደውለው የቤት ሠራተኛዋ እንድትመጣ አዘዙ። ሠራተኛዋ ሳትዘገይ በቶሱ ከተጥ አለች።

«ሮዛ፣ ልጂ ከባድ ሜንቀት ውስጥ ነው ያለችው። አተኩሬ ሳያት ሀሊናዋን የሳተችም ይመስለኛል። ምነው እናትዋ በኖረችሳት! እኔ እንደሆነ እንዴት ብዬ እንደማደናናት እንኒን አላውቅም» ሲልዋት «ሀዘንዋ ከባድ በለሆነ ምን ብለው ነው የሚያጽናንዋት» አለች ሠራተኛዋ ማልታ ገብታ። «እንዲያው አያድርስ ነው እንጂ ምን ለማለት ይቻላል። እስከ ዛሬ ከገጠ ሙኝ ነገሮች ሁሉ የዛሬው ይበልጥ የከፉ ነው። እርግጠኛ ነኝ፣ ሰር ልዮኔል ኤሊኖርን ጥሱ የሄደው ፍቅሩ አልቆበት ስላልሆነ ወደፊት ይጸጸተዋል።»

«እንደሚጸጸተውማ የታወቀ ነው» አሉ ሚስተር ሳርዶን። «ወነዶች ይህን የመሰለ ወራጽና አስጸያፊ ተግባር አስከፊጸሙ ድረስ አገራችን ሰላም የሰፈነባት አገር አትሆንም።»

ምዕራፍ ሰምንት

ሰው የጠበቀው

ግና ከመጀመሪያው ወሬው እንደ ሳዶድ አሳት ከመቅጽበት በየአገሩ ስለተሰራጨ መላ የአገሩ ሰው ሰማው። ሁሉም ሰው በመገረምና በመጀነት ነበር ዜናውን የሰማው። ቀድሞ የሰማው እርስ በእርስ ሲወያይ ዜናውን ዘግይቶ የሰማው ማመን ሰሳቃተው «ሊሆን አይችልም» በማለት ተከራከረ።

ሰር ልዮኔል እንደ ሞዴል የሚጠቀስ የባሉቾ ሁሉ ተምላሌት ነበር። ኤሊኖርም ለባልዋ ታሳየው የነበረውን ፍቅርና ችሰጠው የነበረውን አክብሮት በመመልከት ሌሎች ሴቶች ይቀኑባት ነበር። ቤታቸውም ሰሳምና ፍቅር የበራበት ስለነበረ እንደ ሞዴል ቤት ነበር የሚታየው። በዚህም የቱነሳ የቤተሰቡ ታሪክ የሰማ ሁሉ ያከብራቸዋል፣ ይቀናባቸዋል። ለዚህም ነው በሀብረተሰቡ ዘንድ ዜናው እንደ መብረቅ የሚማታ እንጂ ተራ ዜና ሆኖ ያልታየው። መልኬመልካሙና አመለ-ሸጋው፣ ወጣቱና ሀብታሙ ባል ቆንጆዋንና ታማኝ ሚስቱን ጥሎ መኮብለሱ ሀብረተሰቡ ሳይ አጉል ጠባሳ የሚተው ነው የመሰለው ሀብረተሰቡ። በተጨማሪም ሀብረተሰቡ 'በወንዶች ሳይ ጥቁር ነጥብ የሚጥልና የማይረሳ ወንጀል ሆኖ ነው' ያየው።

የቤተሰባቸው አባል ሁሉ ወሬውን እንደ ሰማ ሚስተር ሳርዶን አወቁ። ነገር ግን ሁሉም ለእመቤታቸው ማዘናቸውን ሲገነዘቡ በጣም ደስ አላቸው። ሠራተኞቹ ከወትሮው ይበልጥ ኤሊኖርን ይንከባከብዋታል፣ ያሰደስታታል ያሉትን ሁሉ ያደርጉላታል። የባልዋን ስም በክፉ አያነሱም። ድንገት ስለ ቤቱ ጌታ ያነሱ እንደሆነ የሚያወሩት በሹክሹክታ ነው። ከዚያ አስከፊ ድርጊቱ በፊት ሰር ልዮኔል ሁሉንም ይረዳቸው ስለነበር 'ከእርሱ የተሻለ አሳዳሪ የትም አይገኝም' የሚል እምነት ነበራቸው። ሰር ልዮኔል ለሰው አዛኝ፣ ቸርና ሩህሩህ ሰው ነው። የለጠ እንደሆነ የሚያረካ እድርጎ ነው። ሰው በልቶ የሚጠግብ አይመስለውም። የሚያለዝነው ግን ያ ትልቁ ሰው እንደዚያ ተዋርዶ የአሽከሮቹ መሳለቂያ ሲሆን ማየቱና መስማቱ ነበር።

ሕግ አዋቂው ሚስተር ፍርተን ከዚያው እንዳለ ደብዳቤ በስንደን በኩል ይመጣለታል። ደብዳቤውን እርሱ አሁን ወዳለበት የሳከው ለንደን የሚገኘው የጠበቃው ቢሮ ሲሆን የደብዳቤው ጸሐፊ ሰር ልዮኔል ነው። የደብዳቤው ፍሬ አሳብና አጻጻፍ ሲገመገም ደስ ብሉት የሚኖር ሰው አጻጻፍ እንዳልሆነ በግልጽ ይታያል። እንዲያውም ቀን የጨለመበትና

Scan by Easy Scanner

የተቸገረ ሰው የጸፈው ጽብሸቢ ለመሆኑ አያወራጥርም። ዝርዝር ውስጥ ላይገባ ድግን ባለ መልኩ የተጻፈ ጽብሸቢ ቢሆን መነሻው ፖሪዕ ከተማ ነው። ወደ ሩቅ አገር እንድሚሄድና ምናልባትም ወደ እንግሊዝ አገር ሳያመሌስ ጎሙ ሊቆይ እንደሚችል ሰር ልዮኔል በደብዳቤው ገልጾአል። «ያውም ከተመለስኩ» ሥሊል ቅልም አክሰብተዋል።

ከርስቡ የሚገኘው ገቢ እሁል ለሁለት ተከፍለ። ግማሹ ለፊው እንዲሆንና ቀሪው ለባለቤቱ ለኤሊኖር እንዲሰዋ በደብዳቤው ያዝዛል። ዝዉው ግጫት እስከ ስልሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር ሊደርስ እንደሚችል ያውቃል። በጊዜው ይህ ገንዘብ በጣም ብዙ ሀብት ነው። የአርሱ ድርሻ ግንህ ዝኒ እንዲሆንለት ሲጠ ፎት እርሱ ገንዘብ ባስፈለገው ጊዜ ከዘንህ ሊያወጣ እንደሚችልም ይናገራል። የሚሉት ድርዓ ግን በቅጥታ ለእርስዋ በእጅ እንዲሰዋ በደብዳቤው አደራ ያላል። ልጀችው እድጎና ራሱን ችሎ ቤተን ማስተዳደር እስከ ፆለ ድረስ ባለቤቱ ከፈለጎች ከዚታቹው ውስዋ ለመቀመጥ እንደምትችል ይጠቅሳል። ምሮቱን ሞግራሮ እንዲያደርጉ የባለቤቱ አባቅ ሚስተር ጎርዶንን በጣም የሚወደው ዛደኛው ስር ዴልዘና ሚስተር ፕርቦን እንዲሆኑ በመጨረሻ አዕደደቶ ሚሉቀንና ልጆቹን እንዲጠብቁለትም እንዚህኑ ሰዎች አደራ ሰጣለት ይሻልናል። በመጨረሻም ለማንኛውም ጊዳያ መሻዣ ኢሊኖር መሠን እንዳለዋት ጠቅሶ ልጅ እድጎ ጋብቻቱን መረጠዋ እስከዅስ ድረስ ፈራጅ ቆራጭዋ እርስዋ እንደሆነች በደብዳቤው አመክሮ ያሰነግባል።

«እንደሚመስለኝ የመመለስ አሳብ የለውም» ካለ በኋላ ወሰቃው ሚስተር ፕርቀን ብዙም ሳይቆይ ወደ ለንደን ተመልሶ ይሄዳል። ከመሃዱ በፈት ግን መደረግ ያለበትን ሁሉ አዘጋጅቶ ነው ዮተሊያቸው። ለእመቤት ኢሊኖር የሰጣት ምክር ለንቢው ቤትዋን ለቅቃ ከለላ ባታ ጊዳ እንድትኖር ነበር። ምክሩ ግን በደበልኖ አስከፋት አንጂ አልጠቀማትም። እርስዎ ቢሆን ያን ቤት እጅግ ይወደው ስለነበር ይህን ሲናገር ውስዋ ውስጠን ሳያበጨጌንቀው አልቀረም። «ሞኝነቱና ንዴቱ ለነዙ ሳያሰጣት አይቀርም፣ ግና ከዚህ ቤት ሳትመጣ እንስትሞት» ሲል አሰላሰለ ሚስተር ፕርቦን።

ሰሙኤው ከእንኤሊኖር ቤት ከሄደ በኋላ አባትዋ የሚጨነቡትንና የሚያደርጉትን ስላጡ እጅግ ተቅበጠበጠ፣ ተጨነቀ። ሦን ማድረግ እንዳለባቸው ለይቶ ማወቅም ተሳናቸው። ልጀቸው የሞት ጥላ እንዳንጎጦበት በተገነዘቡ ጊዜ ብቻዋን ቸተዋት ወደ ቤታቸው ለመመለስ አልፈለጉም። እንዲያውም ወደ ባለቤታቸው መልክታቸ ልከው በቶሌ እንድ-መጣላቸው ጸለዩ። ሆኖም ጥሪት በላመጣ መልእክተኛ ወዲያው ከመላኔ ተመለሰ።

«ወይዶት እንዲህ ትባን ይሆንን የደረሰውንስ በዚህ ጎድነት ተበብ ቸተበለዋለች ብሎ ለመተንበይ ያስቸገራል» ሲሉ ሽማሃለሙ አሰሰ በጽሳቸው ተንጋግሩ። «ይናውን ባለበት ስትሰማ እንዴት አድርጋ ትቀበለው ይሆን፣ በቅጣ ግንፍሳ አዋደይን ብላ ትሮግህ ይሆን ወይስ ለኢሊኖር አገሩ ጊዜ ሳታጠፋ በቶሌ ወደዚህ መጥታ ከጎደነት፣ ታጉናኛት ይሆን አርስዋም ራስዋ በጥያቄቂ ያበኝ የሃጥል ጎድነት ሰት ናት። ለመሆኑ እንዴት አድርገን ነው የምንገነገራት» ሲሉ አጉራን ይዘው ሲላመን በመልቀት ብዙ አሰላሰሉ፣ ቀዘሙ። በመጨረሻ ኢሊኖር እየደከመቸ ሂደትና ሕመሙ ጠናባት። በዚህ ጊዜ ነበር ሽማሃሌሙ አባትዋ ጊዜ ሳያጠፉ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባቸው ዮተንዘበት። ልጀቸው ግን 'ይህን አድርጉልኝ፣ በዚህ ውጡ በዚህ ሙሩዱ' እያለች ሳታሰጉገር እንዲያው ጽዋ ለዋ ብላ ነው የምትተኛው። የሆድዋን በሆድዋ እምታ ይህ ነው ዝም የምትለው። የምትሞላ እንዳናገበባት ግን ፈትዋ በግልጽ ይናገራል፣ ደመስክራል። ሰውንትዋ ድርት ብሎ መገዮ ጠፍቷል። መትሮ ከዓይንዋ ውስዋ ይፍለቀለቅ የነበረው የሕይወት ብርሃን እየመሻመነ ሂደ። እስዚያ ሙብ የነበሩ ከንፈሮችዋ ፈገግታ ተለያቸው፣ ኢሰሃፍና አዛኙ አባትዋ ሊያጽንዋትና ሊያባብሷት በሞክሩ ቸዋር የምትሰጣቸው መልስ አንድ ሆነ።

«በሕይወት ብዙም የምቆይ አያመስለኝም፣ ልቤ ቀስ አያለ ሰለሚደማ ወደ ሞት የሚያዘነም ይመስለኛል። ቢሆንም እናንተ ብዙ አትረበሹ።»

አባትዋ ምንም እንኳን «ተይ እንዲህ አትበይ፣ ይሀና ነሽ» ብለው ቢናገሩም ያያትና የሰማት ሁሉ የምትሊው ነገር ከእውነት የራቀ እንዳልሆነ ስለሚያውቅ ማንም ለማስተባበል አልሞከረም። ህዘንዋ የከፋ ስለነበር አንድ ቀን ልብሞን ሲያዶርጠው እንደሚችል ሁሉም ገምቷል።

አጅግ በጣም የሚያሳዝነው ግን ከትንሹ ልጅዋ ከጎርዶን ፊትዋን ስታዞር ማየቱ ነበር። ልጅ ቀርዋ አባቱን ይመስላል። ዓይኑ፣ ዋርሱ፣ ድምፁ፣ አመለካከቱ እንኳን ሳይቀር ከአባቱ ጋር ሙሉ ለሙሉ አንድ ዓይነት ናቸው። ልጁ ብቻ ብሎ ግና ሊያያት ሰማይ ምድሩ ይዞርባታል፣ ልብዋ ከሁለት ዮተከፈለም ይመስላታል። ታዲያ ልጅዋን ምን ታድርገው? እንዳትሸሸው ልጅዋ ነው፣ አንዳችቀርበው ጥሎአት የሄደውን ነፍስዋ አሰዚጠፋ የምትወደውን ባልዋን ያስታውሳታል።

በእርግጥ ኢሊኖር ዐሉይ አንጀ ሙታው ቅጠል በየሰኑቱ እየሟሸሸች ነው። ማንንም አላነጋግርም ብላ ስለመሰነች የቅርብ ዓደኞችዋና ወዳጆችዋ

Scan by Easy Scanner

እንኳን ሊያይዋት ሲመጡ ልታነጋግራቸው አትፈቅድም። ከቅርብ ጓደኞችዋ ጋር ብትገናኝና ብትጫወት እንኳን ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም ሀዘንዋን ሊያረሳስዋትና ከትካዜ ሊያርቅዋት ይችሉ ነበር። እርሰዋ ግን ዉዋቃቸው ቀርቶ ጓደኛቸውን ለግየት እንኳን አልፈለገችም።

ሀዘንዋ ከማንኛውም ሰው ሀዘን ጋር የተሰተካከለ አልነበረም። የማታ ማታ ሥራዋ በር ቆልፎና አልጋ ሙሰጥ ተወሽቆ ማልቀሰ ነው። ናትርዮና ሀዘንዋ ከእምባ ጋር ታጥቦ የሚወጣ እየመሰላት የዘወትር ሥራዋ ሚነባት ሆነ። ቀን ቀን ተሰሩ ቆርጣና በሠዘን ተጨማልቃ ነገር እየበላች ምንም ላትናገር ቆዝማ ሰለምትቀመጥ አንዱ ቀን ዓመት ይሆንባታል።

«አልጋ ላይ ተጋድመው ግድግዳና ጣራ እያዩ ሲቆዝሙ አንድ ቀን በዚያው እንዳይቀሩ» በማለት ሞግዚትዋ አባትዋን አሰፈራራቻቸው። «ከዚህ ጭንቀትና ብስጭት እንዲገላገሉ አንድ ነገር መደረግ ያለበት ይመሰለኛል» አለቻቸው። ይህን ሲሰሙ ሚስተር ጎርዶን ደንግጠው ባለቢታቸው በቶሎ እንዲመጡ መልክተኛ ላኩ። ሚስታቸውም ሳይዘገዩ ወዲያው ከተፍ አሉ። የኤሊኖር አባት የባለቤታቸውን ውስጣዊ ስሜት ለማወቅ ሰለተቸገሩ የሴትየዋን ሁኔታ በጥንቃቄ ማጤን ጀመሩ።

ሳሉን ቤት ከሚሸነው ሶሩ ላይ ተጋድማ መጽሐፍ ለማንበብ እየሞከረች ላለ ነበር የእንጀራ እናትዋ በድንገት ኤሊኖር ከነበረችበት የገቡት። ሁለቱ ሴቶች ሲገናኙ እንዴት እንደተያዩና እንዴት ብለው እንደ ተሳሳሙ ሚስተር ጎርዶን እሰከ ሕይወታቸው ፍጻሜ አልረሱትም። ኤሊኖር መጽሐፉን ለይሰሙላ ያህል ይዛው ነበር እንጂ እርስዋ ታልመው የነበረው በደስታ ሰለኖረችበት የልጅነት ዘመንዋና ለባልዋ ስለነበራት ብርቱ ፍትር ነበር። የእንጀራ እናትዋ ሲገቡ ያንን የገረጣ ፊትዋን ቀኖ አድርጋ አየቻቸው።

«እኔ ኤሊኖር ነኝ እንዳትዪኝ! ወይኔ ልጄ! ምንድነው ያደረጉሽ? ምን ቢያስነኩሽ ነው እንዲህ የተሰዋወጥሽው?» ብለው ሲናገሩ ኤሊኖር ከተኛችበት ለመነሳት ሞከረች። ሆኖም ሴትዮዋ ቀድመው ጎንበስ በማለት ከነበረችበት እቅፍ አድርገው ሳምዋት። ቀጥለውም «በጅኑ ነው ያቆለሉሽ! አልቅሰሽ ይውጣልሽ እንጂ ሰው አትሆኚም። ወይኔ ልጄ፣ ከዚህስ ደረትሽን በጦር ወግተው ቢገሉሽ ይሻል ነበር» አሉ የእንጀራ እናትዋ።

የእንጀራ እናትዋን ከልብ አፍቅራ ስለማታውቅና አነጋገራቸውም ደስ ሰላላት ከነበረችበት ተመልሳ ተኛች። ከዚያም ግንባርዋን ወደ ደረትዋ በማሰጠጋት ጥቅልል አለች። ከእንጀራ እናትዋ ጎደኝ ማን እምባ ዱብ ዱብ ሲል በተመለከተች ጊዜ በጣም ገረማት።

«ከንፈን የታመታች ዶሮ ማለቴ የተቀጠፈች አበባ መሰለሽ የለም እንጂ» በማለት ሴትየዋ ንግግራቸውን ቀጠሉ። «እንዴት አንድ ወንድ አናታሪዋንና ቀንጆዋን ጨዋ ሴት እንዲህ አድርጎ ይጫወትባታል» ካሉ በኋላ ፊታቸውን ወደ ባላቸው አዞሩ።

«ምነው አስካሁን ባትልክብኝ» አሉ በዝግታ ኤሊኖር እንደግትስማ አድርገው። «ከዚህ ተደም ብትል ጥሩ ነበር። እንዲህ ያለውን ፈተና መቋቋም ወንዶች የት ትችሉበትና ነው አስካሁን ሳይላክብኝ የቀረው? በለውዬው ፍትርና ንዴት ልብዋ ሲፈርጥ ምን ቀረው! ነፍስዋ ልትከዳት አይደለም እንዴ! ይኼኔ አሥር ጊዜ ስሙን በከራ እያነሳችሁ ሳትጫወቱባት አልቀራችሁም። ወንዶች ስትባሉ እኮ ይህን የመሰለ አስቸጋሪ ነገር ሲገጥም መላ የመፍጠር ወይም ምን መደረግ እንዳለበት አታውቁም።»

«እግዚአብሔር ይባርክሽ፣ እውነትም ታውቅበት የለም እንዴ» አሉ ሚስተር ጎርዶን ከጭንቃቸው የተገላገሉ መስሉአቸው። ያን እለት ማታ የኤሊኖር ሕመም ትንሽ መለስ ብሎ አደረ።

ምዕራፍ ዘጠኝ

ጠያቂ

የኤሊኖር አባት ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም መንፈሳቸው ስለተረጋጋ መፍትሔ የተገኘ መሰላቸው። ባለቢታቸው በዚያ ጥበብ በተሞላበት አያያዝ ከቀጠሉና እንደዚያ ፍቅራቸውን እያሳዩ ከተንከባከብዋት ኤሊኖር እንደምትበረታና ደህና እንደምትሆን አመኑ። ሴትዮዋም ትህትና በተሞላበት አንደበት አጫወትዋት፣ ረጋ ባለመንፈስ መከርዋት። የፍትር ጥናት ማለት ምን እንደሆነ ስለሚያውቁ መነሳት ያለበትን እያነሱ፣ መነሳት የሌለበትን እየተዉ ኤሊኖርን ከአላብ ለማዘናጋት ብዙ ጣሩ። ከእንዲት የእንጀራ እናት ከሚጠበቀው በላይም የተቻላቸውን ሁሉ አደረጉ። ባልዋ ከጠላትና ከክዳት ሴት ልብ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የፍትር ብርታት፣ የተስፋ መቁረጥ ጽናትና የመንፈስ ድቀት ምን እንደሆነ ማየት ስለቻሉ በዚያው አኳያ ስሜትዋን የምትለውጥበትን መንገድ በመቀየስ የኤሊኖርን ጭንቀት ለመቀነስ ብዙ ታገሉ።

Scan by Easy Scanner

አሰላፍርም ምንም አንኳን ሙሉው ርዝመት ባይከለሰ ሰሙኑትም በህዝብ ላይ ላሰ ሁሉ ፈጣሪ ሕሉም አንጻራዊ አስፈላጊነት ዞኒያዩርነ መደገ

በተሞላበት እንደበት ነው። ብዙ ጊዜ አብረው ሲተመጩም ገጾ ይሳሳል እንጂ በነገር አይነኳኳትም። ወዳጆችዋና ጎረቤቶችዋ እንዲከበደቷቸው ከልብ ቢፈልጉም ዝምታንና ብቸኝነትን መምረጥዋን ሰላውቁ ብዙም አላሰቸገሯትም። ሰው ለማኅጋር እንደማትፈልግና ብትፈልግም ረኽይ ታሪክ ለመስማት አቅም እንዳልነበራት ደርሰውበታል። ቢሆንም አርሰቀ ብዙ ቢደክማትም የእለት ተእለት ተግባርዋን ባለመርሳት የተጉኅነን ሁሉ ትፈጽማለች። መሠራት ያለበት ሁሉ እንዲሠራ ትእዛዝ ትሰጣለች። የልጆችዋን ሁኔታና ደህንነት ትከታተላለች። ከባድ ሀዘንና የህፍረት ማኅ መከናነብ ማለት ምን እንደሆነ ብትረዳም ለማሰመሰል ያህል የደረሰባትን ዋጥ ለማድረግና ደህና መስሎ ለመታየት ትሞክራለች። ሆኖም ግን ልብዋ ውስጥ ደመል እየደመሰ ያሰቸገራትና ዘወትር ከጭንቅላትዋ ሙሰጥ የማይጠፉ ጥያቄዎች ነበሩ። እነርሱም፡- «መለሳዬ፣ የእኔ ፍትር፣ ምነው እንደዚህ ጉድ አደረከኝ? ምነው ጥለኸኝ ኮበለልክ?» የሚሉ ናቸው።

እባትዋና የእንጀራ እናትዋ ከቤትዋ እያሉ አንድ ደልተጠበቀና እንግዳ የሆነ ነገር ይደርሳል። ባልና ሚስቱ ከቤት ወጣ ለማለት ፈልገው ኤሊኖር አብራቸው ወጣ እንድትል ይጠይቋታል። እርስዋ ግን ስላልፈለገች ከቤት ቀረች። ከቤት ውስጥ ብቻዋን ቁጭ እንዳለች ሠራተኛዋ ቤኔት የእንድ ሰው ስምና አድራሻ የተጻፈበት ካርድ እምጥቶ ከሰጣት በኋላ «አንድ ሰውዬ ከቤት ካልገባሁና እርስዎን ካላነጋገርኩ እያለ አሰቸግረን እመቤቴ» ሲል በመጨነቅ ይነግራታል።

ኤሊኖር ካርዱን ተቀብላ እየችው። ስሙን ባየች ጊዜ መላ ሰውነትዋ ተረበሸ። ፍርሃት፣ ፍርሃት አሰት። ከመቀመጫዋ ብድግ ብላ ተነሳች። እጅዋን በእጅዋ ጨብጣ ጩሂ ጩሂ አለች።

«አልፈልግም፣ ማንንም አላነጋግርም» በማለት ተኮሳተረች። «በፍጹም አይደረግም፣ የማይሆን ነገር ነው» አለች። ካርዱ ላይ የተጻፈው ስም ባልዋን የነጠቀቻት ሴት ባል ስም ነው። እንዴት እንደሆነ ሳይገባት ቀና ሰትል ሰውዬው ከአጠገብዋ ቆመዋል።

«ሺህ ጊዜ ይቅርታ አጠይቃለሁ» አሉ ሽማግሌው። «እሺ ብላ ታነጋግሪኛለች ወይስ አምቢ ብላ ችመልሰኝ ይሆን እያልኩ ነው ከሩቅ አገር ስፈራ ስቸር የመጣሁት። አሁን ግን በምንም መንገድ ቢሆን ሳላነጋግራት አልሄድም በሚል ነው ማንም ሳይፈቅድልኝ ሰተት ብዬ ከቤትሽ የገባሁት። ለማንኛውም ለአጭር ጊዜ እንኳን ቢሆን እድሱን

ልትሰጪኝ ትጢያለሽ? ብዙ አለቶይም፡፡ ግን ተመለስና ከዚህ ቤት ሙጣ ነልሽኝም አምቢ አልልም፡፡ ብቻ ከሩት አገር መምጣቴን አትርሺብኝ፡ ብርቱ የሆነ ጌዛይ ነበራኝ» ብለው ነገራቸውን ሲያራዝሙ «አያበግሆች ነው» አለምቶሙ ሬታ ብለ መንፈስ፡ ይህን ጊዜ ቤኔት ጥሱ-አቸው ወጣ፡፡

ምዕራፍ ኦስር

የውጭው አገር ዜና

«ምናልባት አንግዳ የሆነ ነገር ላይሆንብሽ አይተርም፡፡ በእርግጥም እኔ አንቺን ፍለጋ መምጣቴ ለማንም ቢሆን ግር የሚያሰኝ ነው፡፡ ሆኖም በእንቺ ላይ የደረሰው ጥቃት ከእኔው ጋር ሲነጻጸር የአንቺ የከፋ ነው» ብለው ሉርድ ሊን ሲናገሩ «አሱን ባናነሳው ይሻላል» አለች ኤሊኖር እጆችዋ እየተንቀጠቀጡ፡፡ «ይህ ነገር ሲነሳ መላ ሰውነቴ ይረበሻል፡፡»

«ካልተመያየንበት ብዬ እኔም ድርቅ አልልም፡፡ እኔንም እንዲሁ ስለሚረብሸኝ የደረሰውን አንበቶ ዘርዘር አድርጎ መነጋገሩን እኔም የምፈትደው አይደለም፡፡ መልእክተኛ ክምልክብሽ እኔው ራሴ ብመጣ ይሻላል ብዬ ነው ተነሰቼ የመጣሁት፡፡ ለመሆኑ ስለወደፊቱ ምን አስበሻል?»

«የወደፊቱ አሳቤ?» ሰትል የጠየትዋትን መልሳ ጠየቀች፡፡ «ማን ምን ለማለት ፈልገው ነው ይህን ጥያቂ የሚጠይቁኝ?» ሰትል ጥያቄው በትክክል እንዲገባት ሴላ ጥያቂ ጠየቀቻቸው፡፡

«ከቶኛ ነው የተበደልሽው፡፡ እና ለዚህ ለደረሰብሽ በደል ማካካሻ የመጠ የት አሳብ አለሽ?» ብለው ሲጠይቋት «ከማን ነው ማካካሻ የምጠይቀው! ለደረሰብኝ በደል ማንም ቢሆን በብታት ሊክሰኝ አይችልም፡፡ ከእጁ አምልጦ ለወጣ ነገር ጀግም ከማን ነው ካሣ የምጠይቀው?»

«ለማለት የፈለግሁትን ነገር በትክክል አላበቀመጥኩም መለለኝ፣ ካሣ ማለቴ አልነበረም፡፡ የተፈጸመው በደል ማንኛውም ሰው ቢሆን በገንዘብ የሚሸፍነው አይደለም፡፡ ለማለት የፈለግኩት ሁለቱን ከሃዲዎች ለማስቀጣት ምን እርምጃ ትወስጀለሽ ማለቴ ነበር፡፡»

«ማስቀጣቱም ቢሆን ዋጋ አይኖረውም፡፡ እንዲህ ላለው ከባድ ወንጀል ማንም ቢሆን በአጥጋቢነት ሊቡቀል አይችልም» ስትላቸው በዝረም ትኩር ብለው አይዋት፡፡

Scan by Easy Scanner

«ምንም ዓይነት እርምጃ አልወስድም ነው የምትዪው? ያ ሁሉ ሚሊዮን ያ ሁሉ ከህይትና በደል ተሸክመሽ ዝም ብለሽ ታልፊዋለሽ? ነግሩን ሁሉ ዝም ብለሽ ተቀብለሽ ታልፊዋለሽ?»

«ይኸው ነው አሳቤ ሎርድ ሊን።»

ሽማግሌው ይህን ሲሰሙ ቃል ሳይተነፍሱ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም ብለው ተቀመጡ። ከዚያም «መቼስ ዝምታው በራሱ ትልቅ ትጣት ሊሆን ይችላል» ካሉ በኋላ አሁንም ለተመለከ ጊዜ ዝም አሉ።

«ፍቺ መጠየቁ ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ ይሁን አይሁን የምለው የለኝም። ስለሞራል ኮሞና ስለክብር መነሳትም እንዲሁ የምሰጠው አስተያየት አይኖረኝም። ነገር ግን የምለው ነገር ቢኖር እኔዚህ ሁለት ወንጀለኞች ከጊዜ በኋላ እኩይ ተግባራቸው ተረስቶ ሲጋቡ እንደሚችሉ ነው። ህብረተሰቡም ወንጀላቸውን ረስቶና ከግህበረሰብ ውስጥ አስገብቶ ይቀበላቸው ይሆናል። ለወላቶች፣ ለቆንጆዎችና በሕይወት ዘመናቸው ኦሮ ለተሳካላቸው ቢያጠቆም ምህረት እንደሚደረግላቸው ሁሉ ለእነርሱም ምህረት ይደረግ ይሆናላ» አሉ እንደ መናደድ ብለው።

«ሊሆን ይችላል» አለቻቸው። ሌሊናር እንዲህ ብላ መመለስዋ ምናልባት ስለጉዳዩ ቀደም ብላ ማሰብዋን ያመላክታል።

«ወደፊት፣ ማለቴ ከብዙ ዓመታት በኋላ ከበልሽ ጋር ድንገት ብትገናኙ ምን ታደርጊያለሽ? በብዙ ሺህ የሚቆጠር ገንዘብ በካሣ መልክ እንዲከፍልሽ ትጠይቂዋለሽ? ልጆቻችሁ ካደጉ በኋላስ ድንገት ቢገናኙ ምን የሚያደርጉ ይመስልሻል?» ሲሉ ተደራራቢ የሆኑ ጥያቄዎችን ጠየቅዋት።

አሳቡ ስለዘገነናት እንደ መናደድ አደረጋት። ቢሆንም ስሜትዋን ተቆጣጥራ ወደ ሰውዬው ጥያቄ ተመለሰች። «አስቤበታለሁ» አለች አሳቡ ልክ በጦር እንደ ተወጋ ሰው ስሜት እየጎዳት። «ልናገረው ግን አልፈቅድም።»

«አሳብሽ እኔንም ከሙሳኔ አሳብ ሳይ እንድደርስ ይረዳኛል» አሉ ሎርድ ሊን ቀጥለው ሲናገሩ። «'ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስዱ ነግሩን ናቅ አድርጎ መተው ይሻላል' የምትዪ መሰለኝ። እኔም ብከለውና ባስፈርድበት በብዙ ሺህ የሚቆጠር የካሣ ገንዘብ ላስከፍለው እችላለሁ። ነገር ግን ገንዘቡም የደም ገንዘብ ይሆንና 'ሚስቱንና ስሙን ለገንዘብ ሸጠ' ሊያስብልብኝ ይችላል። ነዚ መስርቺ እኔ ብፈታ፣ እንኢምረትም አርግጠኛ ነኝ፣ አርሰዋ ነፃ ትወጣለች። ሌለው ምክንያቅ ደግሞ ጭበድ ቤት ስንኳት ወፈው በይበልጥ ተጋንዛ ሊወራ ስለሚችል ከአሁኑ ይበልጥ መሸማቀቅ ይሆናል። በማለት ሲነገሩ ኤሊኖር ሳሳባቸው ለመለሚማትዋ እጅ በመንሳት አረጋገጠ ችላቸው። ሎርድ ሊን ንግግራቸው ቀጠሉ።

«ከሙሳኔ አሳብ ሳይ ከመድረሴ በፊት ያእንቺን አሳብ ልወቅ ብዬ ነው» ሲልዋት «የእኔ አሳብ ከአርስም አሳብ የተሰየ አይደለም። አድራጎታቸውን በመታወም ምንም ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ አልተበጋጀሁም» አሰኝቸው።

«አሳብሽ ያሚያረካ ነው» አሉ ሎርድ ሊን፡ «ስለከጻችኝ ባለቤቴ ምን ማድረግ እንዳለብኝና ቁርጥ ካለ አሳብ ሳይ ለመድረስ የእንቺ አሳብ ረድቶኛል ለማለት እችላለሁ። ባለቤቴ በሰሜ በመጠቀም ከትብያ ተንስታ ታዋቂ ሴት ሆና ነበር። ስሜንና ክብሬን የራስዋ በማድረግ ብዙ ተጠቅመችበት። ስንጋባ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በእርስዋ ስም ባንክ አስቀምጬላታለሁ። መቼስ ወደፊት መቸገርዋ ስለማይቀር በገንዘቡ ትጠቀምበት እንጂ እኔ አሁን ገንዘቡን መልሺ አልላትም። ምንም እንኳን አሁን ነገሮች ቢለዋወጡም፣ በእንድ ወቅት ጌታ የነበረች ሴት በገንዘብ እጦት ምክንያት እንድትቸገር አልፈልግም። ነገር ግን በምንም መንገድ ጭማሮ ዓይንዋን ለማየት አልፈልግም። እኔ እንደሆነ በአድሜ የገፋሁ ሰው ስለሆንኩ የቀረኝ እድሜ ውስን ነው።

«አሁን እኔ ወዳንቺ የመጣሁት እርጅና ሳይጫጫነኝ ልያት በሚል ሲሆን ሁለታችንም ተመሳሳይ የሆነ በደል ደርሶብናልና ነገሩን እንዴት ነው የያዘችው? ምን ዓይነትስ እርምጃ ለመውሰድ አቅዳለች? እስቲ በአካል እንገናኝና ምን እንደምትመስልም ልያት። እርስዋን ከድቶ የእኔን ሚስት የቀማኝ በምን ምክንያት እንደሆነ ለማወቅም ፈልጌ ነው ወዳንቺ የመጣሁት።» በመጨረሻ ሎርድ ሊን የተናገርዋቸው አስከፊ ቃላት የኤሊኖርን መሳ ሰውነት ለማርበትበታቸው ሽማግሌው ተገነዘቡ። ቢሆንም ንግግራቸውን ቀጠሉ።

«እንቺ አሁን ምን እንደምትፈልጊ አውቄአለሁ። ድፍረት ባይሆንብኝና አድናቆቴን ለመግለጽ ያህል ብቻ ለማለት የፈለግሁትን ብናገር። ባለቤቴ እኔን ጥላ ክሴላ ወንድ ጋር ብትኩበልል ይህን ያህል አያስደንቅም። እኔ እድሜ የከዳኝ ሽማግሌ፣ ጊዜ ያለፈብኝና የወጣትነት አፍላ ደስታ የራቀኝ ሰው ነኝ። በሚስቴ በጣም አቀና ስለነበር ጨክኜባታለሁ ለማለት

እችላለሁ። ወጣት ናት፣ ቆንጆ ናት። ለውበትዋ ወደር ስለሌለው እጅግ በጣም ታምራለች። የማይመኛት ወንድ የለም። ሆኖም ግን በእኔ ንጥት ባለቤቴ ከአንቺ ይበልጥ ደግም አይደለችም። ታዲያ ባለቤትሽ እንቺን በእርስዋ እንዴት ብሎ ሊለውጥ እንደ ቻለ ለእኔ ግልጽ አይደለም።»

«ምክንያቱን ግሃት ይህን ያህል ለውጥ አያመጣም» ስትላቸው ሎርድ ሊን ከሊሳቸው ውስጥ አንድ ደብዳቤ አውጥተው «ስለሰር ልዮኔል መነገር ያለበት አንድ ጉዳይ አለ» አልዋት። «ሰውዬው ፈሪ ሰው አይመስልም። እሺ ደብዳቤው ይቅር፣ አሳሳይሽም። ፍሬ አላቡን ግን ልነግርሽ እችላለሁ። ፖሪስ ከተማ ሆኖ ደብዳቤ ጻፈልኝ። በደብዳቤውም እኔ በባለቤቴ ላይ ያደረስኩትን በደል፣ እርስዋም ደስታ የተሊያት ቆንጆ መሆንዋንና በዚያች ሰዓትም ባለቤቴ ከእርሱ ጋር መኩብለልዋን በመግለጽ ጽፎአል። ደብዳቤው ከእንግሊዝ አገር በወጡ ማግስት እንደ ተጻፈ ያስታውቃል። ምክንያቱም 'ደብዳቤው ሲደርስዎ እኛ መንገድ ላይ እንሆናለን። ምናልባት እኔን ማግኘት ከፈለጉ ለአንድ ሳምንት ወይም ለአሥር ቀን ያህል ፖሪስ ከተማ ሞሪስ ከሚባል ሆቴል ውስጥ እንቆያለን' የሚል ቃል አክሎበታል። ከዚያም የፈለግኩትን ውሳኔ እንድወስንና የሚመቸኝን አሳብ እንድሰነዝር ለእኔ ነው የተወው። ነገር ግን እኔን የገረመኝ ነገር የደብዳቤው አጻጻፍና የቃላቱ አመራረጥ ደሰ ያለው ሰው የሚጽፈው ዓይነት ደብዳቤ ሆኖ አሳገኘሁትም። ጠቅሳላ ይዘቱ ምሬት ምሬት ይሸታል።

«ሰር ልዮኔል አቅሙ በፈቀደ መጠን ማንኛውንም ካሣ ለመክፈል ዝግጁ እንደሆነ ከጠቀሰ በኋላ እኔ ከፈለግኩ ከየትኛውም ቦታ ልንገናኝ እንደምንችል ጠቁሞኛል። እኔ ግን በዚህ አልተስማማሁም። በዚህ እድሜዬ ለገንዘብ ብዬ ስንከራተት አልፕንም። ብከሰው እንኳን ራሱን ለማዳን ሲል ክርክር ውስጥ እንደማይገባ ከጻፈ በኋላ ጥፋተኛ ለመሆኑና ለዚህም ቅጣት እንደሚገባው ገልጾልኛል። ቢሆንም ለጻፈው ደብዳቤ መልስ አልሰጠሁትም። ጠበቃዬ መልስ እንዲሰጠውና መልሱም በቀላሉ ያገኛትን ሴት ይዞ ለመቀመጥ እንደሚችል ገልጾ እንዲጽፍለት ነግሬዋለሁ። በተጨማሪም ከእሁን በኋላ ከእኔ ጋር ምንም ዓይነት ግኙኝነት እንዳያደርግ አስጠ ንቅቂዋለሁ።»

«እርስዋስ አልጻፈችም» ብላ ስትጠይቃቸው «የለም አልጻፈችም፣ ወደፊትም አትጽፍም» ሲሉ መለሱላት በመማረር።

«ከፈተድሽልኝ ሌላ አንዲት የመጨረሻ ጥያቄ ልጠይትሽ። አሁን የምጠ ይቅሽ ጥያቄ ሁለታችንንም የሚመለከት ስለሆነ ልጠይትሽና መልሱን ብትሰጪኝ። ባለቤትሽ ባደረሰው ጥፋት ተጸጽቶ ቢመለስ ይቅርታ ታደርጊለታለሽ?»

ለተመሰነ ጊዜ ዝም ብላ ዓይን ዓይናቸውን ካዮች በኋላ «እምን፣ ይቅርታ አደርግለታለሁ» ስትል መለሰችላቸው።

«ተመልሶ ከቤትሽ እንዲገባስ ትፈቅጂለታለሽ? ከአሁን በኋላስ አብራችሁ ትኖራላችሁ?» ሲሉ ጠየቅዋት የመገረም ገጽታ ከፊታቸው ላይ እየታየ።

አሁንም ለተሠሰነ ጊዜ ዝም አለች። በአሳብ ተውጣ በአካል እንጂ በመንፈስ እንደሌለች ሞልጥ ብላ ነጎደች። የገረጣውንና ቆንጆ ፊትዋን ቀና አድርጋ ሎርድ ሊንን አየቻቸው። ከዚያም ዝቅ ባለ ድምፅና ረጋ ባለ ስሜት ተዋለ ያለውን ተናገረች።

«የለም፣ አይመስለኝም። ይህንን እንኳን አላደርገውም። ሆኖም ግን አሁንም ቢሆን በፍቅር አወደዋለሁና ፍቅሬ እስከ አለተ-ሞቴ አይለየውም፣ አብረን ግን አንኖርም። እርሱ የበጠሰውን ገመድ እኔ እንደገና ለመቀጠል ስለሚከብደኝ ለዘላለም እንደ ተበጠሰ ይቀራል።»

«አመሰግናለሁ ኤሊኖር፣ ምንም ነገር ሳትደብቂ የልብሽን ገልጠሽ ነው የነገርሽኝ። አዋቂና ብልህ ሴት እንደሆንሽ የምጠራጠረው አይደለም። የሚያሳዝነው ግን አንቺ ከእኔ ይበልጥ ብዙ ትሰቃያለሽ። ልጆች ስላሉሽ በልጆችሽ ምክንያት ብዙ ነው የምትቸገሪው። ሲያድጉልሽ ደግሞ በእነርሱ ትጽናኛለሽ፣ እኔ ግን ልጅ የለኝም።»

«ወንዱ ልጃችን ቁርጥ አባቱን ነው የሚመስለው። በተለይ ዓይኑማ ከአባቱ ዓይን ጨርሶ አይለይም» አለች ዝቅ ባለ ድምፅ። «ዓይኖቹ ባዩኝ ቁጥር ልቤን ከሁለት ነው የሚተረትሩት። እርስዎ እንዳሉት ልጆቼ እስኪያድጉ በሕይወት ለመኖሬ በጣም ነው የምጠራጠረው።»

«ሀዘን ጊዜ ሊወስድና እድሜውም ሊረዝም ይችሳል። ከጊዜ በኋላ ግን ሁሉም ነገር ይረሳል። ፈጣሪ የሰጠን ትልቁ ፀጋ የቆየውን የመርሳት ኃይል ነው» አሉ ሎርድ ሊን ለመሄድ እየተነሱ። «ተቀብለሽ በትህትና ስሳናገርሽኝ ከልብ አመሰግናለሁ። ገር ሴት ስለሆንሽ የልብሽን ገልጠሽ፣ ምንም ነገር ሳትደብቂ ስላጫወትሺኝ እድናቆቴና ምስጋናዬ የላቀ ነው።

Scan by Easy Scanner

ምናልባት ዳግም እንገናኝ ይሆናል። ግን ከአኔም ይበልጥ ለእንቺ ያስጎ ብዙ እንደሌለ ብገልጽልሽ ደስ ይለኛል። ይህንንም የምለው አንቺን ሰመበንላ ላደሆን ከልቤ እንደሆነ ተረጂልኝ። ከየኩሽና ትግር ከጀመርንበት ሰንቅ ጀምሮ 'ይህ አንዴት ሊሆን ቻለ?' እያልኩ ራሌን ደጋግሚ ጠይቀዋለሁ። በነገራችን ላይ አንድ የረሳሁት ነገር፣ የቅርብ ዓደኛዬ በቅርቡ ከሥራስ ተመልሶ መቀድል። በለጉዳዩ ተደም ብሎ የስግሙ ነገር አልነበረም። ከሥሩስ በፊት ግዛፅ እዝር ብዙ ቆይቷል። አሌነሰንድሪያ ላይ ስር ልዮኒ ልዓ አማንቱት ስላምታ ተለዋወጠዋል።»

«አሌነሰንደሪያ» አለች ኤሊኖር ፎነ ብላ ውስዋ ውስጡን ሀዘን እየተሰማት። ከአለበችው በላይ አገር ጥሎ መሄዱን ስታውት ተገረመች።

«ትንሽ ግር የሚያስኘውና ግራ የሚያጠፋው ግን ዓደኛዬ እንደሚለው ስር ልዮኒን ከዚያ ሥፍራ ያጣኘው ብቻውን ነው» ሲልዋት «ብቻውንና» ስትል ኤሊኖር በመገረም ጠየቀቻቸው።

«ይኸው ነው ያስኝ ዓደኛዬ። ነገር ግን እርሱ የተሳሳተ ይመስለኛል። ዓደኛዬ አልነሰንደሪያ ውስጥ የቆየው ለዎሰት ቀን ሲሆን በአነዚያ ሦስት ቀናት ሰር ልዮኒን አንድም ቀን ከሴት ጋር አላየውም። እንዲያውም እርሱ ካረፌበት ሆቴል ውስጥ የሴት እንግዳ እንዳልነበረች አረጋግጦ ነው የነገረኝ።»

«ግራ የሚያጋባ ነገር ነው» አለች ኤሊኖር። «ዓደኛሽ መሳሳት አለባቸው» ስትላቸው «ይመስለኛል» ሲሉ መለሱላት። «እንዲያው ልንገርሽ ብዬ ነው እንጂ ምን ይጠቅማል ብለሽ። ለማንኛውም ቢበቃን ይሻላል፣ እኔ ልሂድ። ደህና ሰንብቺ» ብለው ሎርድ ሊን ከጨጉዋ ወጥተው ሄዱ።

ሎርድ ሊን እንደ ሄዱ የኤሊኖር ልብ በኃይል መታ። ይህ መጥር አጋጣሚ የደረሰባት በስኔ መር ሲሆን ከዚያ ወዲህ ጥቂት ሳምንታት ነው ያለፉት።

«እና ያዲያ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ከሴትዮዋ ጋር ተጣልተው ተለያይተዋል ማለት ነው?» ስትል ራስዋን ጠየቀች። መልሱን የሚሰጣት ግን አላገኘችም።

ምዕራፍ አሥራ አንድ

የጠያቂር ጋሻ መዘታ

የሊንዋ እመቤት ማለት የቪኳን ታሪክ ብዙም የተለመደ ዓይነት ታሪክ አልነበረም። አባትዋ ኑሮ ስለሰለቸው በራሱ ፍላጎት በወጣትነት እድሜው ወደ አሰሪኛ አገር ሄዶ የአንድ ፖለቲካዊ ንትናቴ አባል ይሆናል። አባል በመሆኑም ከሠርነት ውስዋ ዝ። ሰውሄው በተፈተሮው ምንም ነገር የማይፈራ ደፋር አንግሊዛዊ ሲሆን አሮኖልድ ዊልሱን ይባላል። ዊልተን ከዚህና ቤተሰብ የተመለደ በመሆኑ መጠነኛ የሆነ ሀብት ነበረው። ሀብቱን ለንትናቴው ዓላማ መስጎት ተጠቀመበት። አዚያው እስፖኛ ውስዋ እያለ እናትና አባት ከሊላትና የአሰሪኛ ተወላጅ ከሆነች ልጅ ፍቅር ያዘው። አርቆ ሳያይና ሳያስተውል ስሚት አስገድዶት ልጅትዋን የትዳር ጓደኛው አደረጋት። ልጅትዋ ግን ከልብ ወደደችው። ከፍቅርዋ ብዛትም የተነሳ ልትሞት ስታማጥር ከመሞትዋ በፊት በመጪረሻ የተናገራቻቸው ታላላ 'ፊትሀን እያየሁ ልሙት' የሚሉ ነበሩ።

ባልና ሚስት ትዳር መሥርተው ለእንድ ዓመት ያህል አብረው ሲኖሩ ከቦታ ቦታ እየተንከራተቱት ከአጠገቡ ሳትለይ ከእርሱ ጋር ቆየች። በዚህች አጭር ጊዜ ውስጥ ግን በደስታ ነበር የኖረችው። በመልክ ደግሞ ሲበዛ ቆንጆ ሰለነበረች ያያት ሁሉ ያደንቃታል። ስምዋ አሱንታ ይባላል። ይህቺ ልጅ ከባልዋ ዊቅር ሊላ የምታስበውና የምታልመው ነገር ሳይኖራት ዓለምን በባልዋ ፍቅር የለመነች ሴት ናት። ዓለምን ረስታና የባልዋን ፍቅር ብቻ አንግባ በዓለም ላይ ለተመሰነ ጊዜ ኖረች። የሚያሳዝነው ግን ሴላ ነገር ከመሪናዋ ውስዋ ሳይገባና መልክዋ ሳይረግፍ በልጅነትዋ ተቀጨች። ልብዋ በፍቅር እንደ ተሞላ ቅናትንና ምቀኝነትን ሳታውቅ፣ ንጹህ ልብ እንደ ያዘች ነው የሞተችው። የሞተችውም የመጀመሪያ ልጅዋን ማለት ቪቫንን ስትወልድ ነው።

ልጅ ሲወለድ ማልቀስ የተለመደ ነውና ቪቫንም ስትወለድ እጅግ አምርራ አለቀሰች። እምርራ ያለቀሰችው አደጋ የማታያትን እናትዋን ስላጣች ሲሆን ይችላል፣ እውነታው ግን አይታወቅም። እናትዋ በሞተችበት እለት ሌላ መጥፎ አጋጣሚ ደረሰ። ቡልት የፖለቲካ ተቀናቃኞች መካከል ከባድ ጦርነት ይከፈታል። የቪቫን አባት የአንዱ ተፋላሚ ወገን አባልና የሽምበል መር አጉዥ ስለነበር ሳይወድ በግድ ወደ መር ግምባር መሄድ

Scan by Easy Scanner

ነበረበት። ስለዚህ ከቤቱ የሚስቱን ሬሳ ትቶ ጠሩን እየመራ ወደዚያዉ ሄደ። ታሪኩን ይበልጥ አሳዛኝ የሚያደረገው ደግሞ ከሄደበት አለመመለሱ ነው። ጦር ሜዳ ላይ በመጀመሪያ ከወደቁት መካከል እርሱ አንዱ ሆነ።

በጦርነቱ ከተሳተፉ ሌሎች ሰዎች መካከል ሻለቃ ሌስተር የሚባል ሌላ እንግሊዛዊ ነበር። ሻለቃ ሌስተር የሻምበል ዊልተን የቅርብ ወዳጅ ሲሆን በእድሜ ግን ሻለቃው ይበልጠዋል። ሻለቃው ብዙ ሀብት የነበረው ሰው ሲሆን ሰፊም የእርሻ ቦታ ነበረው። ሆኖም ከአንድ ቦታ ተቀምጠው እርሻውን አሰፋፍቶ ለመኖር የሚፈልግ ሰው አልነበረም። እንዲያውም ከነአካቴው የገጠር ሕይወት አይስማማውም። ስለዚህ ባለቤቱን በታላቅ በመደለል ከነበረበት ገጠር ወጥቶና ወደ እስፖኝ አገር ሄዶ የጦር አባል ሆኖ እንዲኖር ባለቤቱን ለመናት። ከጦርነት ውስጥ ገብቶ ከመዋጋት ለምን እርሻውን እያሳረሰ በሰላም ለመኖር እንዳልፈለገ ባለቤቱ ሲገባት አልቻለም። ሆኖም የቅርብ ጓደኞችዋ የባልዋን ፈቃድ እንድትፈጽም ስለመከርዋትና ምናልባትም የጦርነት ሕይወት ሲሰለቸው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደ ቤቱ ይመለሳል በሚል እምነት የባልዋን ጥያቄ ተቀብላ ወደ ፈለገበት እንዲሄድ ፈቀደችለት።

ሻለቃው ጦር እየመራ ለረጅም ጊዜ ቢዋጋም እንደ አድል ሆኖ አንድም ቀን የመሳሰል አደጋ አልደረሰበትም። ከሻምበል ዊልተን ጋር የተዋወቁትና ጥሩ ወዳጆች የሆኑት እዚያው እስፖኝ አገር ውስጥ ነው። እነዚህ ሁለት ጎበዝ ወታደሮች ከባዕድ አገር ሄደውና በሌላ አገር ሰው ጉዳይ ውስጥ ገብተው ለመዋጋት በመወሰናቸው ሰው ሁሉ ይገርመው ነበር። ከሁለቱ ጓደኞቹ አንደኛው ካርሊስት የተባለው ጠረኛ ቡድን የተነሳበትን ዓላማ ስለሚደግፍና በንትፍቱው ስለሚያምን ነበር ከጦርነቱ ውስጥ የገባው። ሌላው ግን ስለዓላማቸው ደንታ ባይኖረውም በሕይወቱ አዲስ ነገር የማየት ፍላጎትና ጉጉት ስለነበረው ብቻ ነበር ከጦርነቱ ውስጥ የገባው።

ሻለቃ ሌስተር የጋራና ሸንተረር ሕይወት አጅግ በጣም ያስደስተዋል፤ ያረካዋል። ከቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ የተንደላቀቀ ኑሮ መኖር በጣም ያሰጠላዋል። አዲስ ነገር የማየት ፍላጎቱ ብርቱ ስለነበር ጦር ሜዳ ውስጥ ወጊያ ተጀመረ ያሉት እንደሆነ ወደዚያ ለመሄድ ግምባር ቀደም ሚና የሚጫወተው እርሱ ነው። በተወሰነ የጦር ግምባር ውጊያው ተፋፍሞአል፤ አይሉአል ያሉት እንደሆነ ወደዚያ ለመሄድ ይጣደፋል። ፍርሃት የሚሉት ነገር አያውቀውም። የጉብዝናውን ያህል ደግሞ ቸር ሰው ሲሆን ጓደኞቹን

በጣም ይወድዳል። ለጓደኞቹ የማያደርገው ነገር አልነበረም። እንዳጋጣሚ ሆኖ ሻምበል ዊልተን ተመትቶ ሲወድቅ ሻለቃ ሌስተር ከአጠገቡ ነበር። ሁለቱ ወታደሮች ከተተራረቡ ጥቂት ወራት አልፎአል። ጓደኛው ተመትቶ ከፈረሱ ላይ ሲወድቅ ሲል ሻለቃ ሄስተር ዘልሎ ያዘው። «እጀን ዘርግቼ አንደሞት ከመሬቱ ላይ አስተኛኝ» ብሎ ሻምበል ዊልተን ለመነው። ሻለቃ ሌስተርም ቃል ሳይተነፍስ በዝምታ ከሳር ላይ አስተኛው።

«ዶን ካርሎስን ካገኘኸው» አለ ዊለተን በደከመ ድምፅ። «እርሱና እኔ ላመንበት ዓላማ በመሞቴ ደስ ብሎኝ እንደሞትሁ ንገረው።»

ዶን ካርሎስ የንትናቲው መሪ ነበር። ሻለቃው እጁን እንዲይዘው አንድ እጁን ዘረጋለት። «የጦር ሜዳ ጓደኛዬ» አለ፤ «ባለቤቴ ዛሬ ጠዋት አርፋለች። ሕፃን ልጅ ጥላብኝ ነው የሞተችው። ስለዚህ ልጄን እንደ ልጅህ አይተህ አሳድግልኝ። እንድትጠብቅልኝም በፈጣሪ ስም አደራ ብዬሃለሁና ልጄን እርዳለልኝ።»

«አምላክ ይርዳኝ እንጂ ተገቢውን እንክብካቤ አደርግላታለሁ፤ እንደ ልጄም አሳድጋታለሁ» ሲል ደጉ ሻለቃ ቃሉን ሰጠው። «ልጅ ስለሌለኝ እርስዋ ልጄ ትሆናለች» አለው ቀጥሎም። ለመሞት የሚያጣጥረው ጓደኛው ሻምበል የሰጠውን ተስፋ ሲሰማ ፊቱ እንደ ፀሐይ ብርሃን ፈክቶ ገጽታው ላይ የደስታ ስሜት ታየ። «አሱንታ» ሲል ጮኸ። አሱንታ የሚለቱ ስም እንደሆነ ተነግሯል። ሆኖም ቃሉን ሳይውጥ ነፍሱ ከሥጋው ተለየች።

ሻለቃ ሌስተር አስከሬኑን ለማንሳት ጊዜ አልነበረውም። የጠላት ጦር እየተቃረበ ስለነበር የጓደኛውን ሬሳ ከዚያው ጥሎ የወገን ጦር ወዳለበት እየሮጠ ሸሸ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ግን ከአጭር ጊዜ ከባድ ውጊያ በኋላ የጠላት ጦር ስለተሸነፈ በተራው ወደ ኋላ አፈገፈገ። በሚቀጥለው ቀን ሻለቃው የጓደኛውን አስከሬን ከወደቀበት ስላገኘው ወደ ከተማ አስወስደው። ባልና ሚስት በአንድ ጀምበር ከአንድ መቃብር ውስጥ በአንድነት ተቀበሩ። ስለአሟሟታቸው ታሪክ በስማቸው ከቆመው ሐውልት ላይ በእጭሩ ተጻፈ። ሻለቃው የቆንጆዋን እናት ጪቅላ ልጅ ሲያይ በጣም ደነገጠ። የሚያደርገውን ቢያጣ ሕፃንዋን ብድግ አድርጎና አቅፎ ሳማት።

«የእኔ ልጅ ትሆኛለሽ፡ በሕይወት እስካለሁም ተንከባክቤ አሳድግሻለሁ፤ እጠብቅሻለሁ» ሲል ለራሱና ለፈጣሪው ቃል ገባ። ቃሉን ለማክበርም ስለልጅትዋ አስተዳደግ ከጓደኞቹ ምክር ጠየቀ። ባገኘውም ምክር ተጠቅሞ

Scan by Easy Scanner

ጋፅንዓ ከሚባል ስፈር ቤት ተከራይቶና ሞግዚት ቀጥሮ ሕፃንዋን በሞግዚትዋ ጠባቂነት ከዚያ እኖራት። በሳምንት የተወሰነ ግንዘብ እንደሚከሩላት ከሞዝሪትዋ ጋር ከተስማሙ በኋላ ልጅትዋን ለማሳደግ የሚያስፈልጓ ቁሳቁስና የቤት እቃ አሟላላት። ከዚያም ለሚስቱ ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ ሬዥም ደብዳቤ ለመጻፍ ቁላሳት አድርበት ሳለ በድንገት ወያ ጦር ግምባር በአስቸኳይ እንዲሄድ ትእዛዝ ተሰጠው። ምርጫ በላልነበረው ደብዳቤውን ሳይጽፍሳት ወደዚያ ተነስቶ ሕዶ። ከጦር ግምባር ሳይመለስ ብዙ ወራት አለፉ። እነዚያ ወራት ቁላል ጊዜ አልነበሩም። ቢሆንም ቀደም ሲል እንደ ተነገረው ሻለቃው የውጣ ውረድ ሕይወት ስለሚያስደሰተው ብዙም አልተከፋበትም።

አንደ ሻለቃ ሄለተር ያሉ ሰዎች ከሞቀ ቤት ሕይወት ይልቅ የእንግልት ኑሮ ሲያስደስታቸው ማየቱ ያበደንቃል። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ከቦታ ቦታ መንከራተት፣ በወሐይ ሙቀት መቃጠል፣ ጸጥት ቁልቁለት መውጣትና መውረድ፣ አደገኛ ከሆነ ቦታ መገኘት፣ ጭንቀት የበዛበት የስቃይ ኑሮ መኖርና ጀብጹ መሥራት ያረካቸዋል። ሻለቃውም እንግዲህ እንደዚህ ያለ ሕይወት ነበር የሚያረካውና የሚያበደበተው። በዚህ ዓይነት የስቃይ ኑሮ እየኖረ ጀብዱ በመሥራቱ በራሱ እጅግ የሚኩራራ ሰው ሆኑ። በመጨረሻ ግን አርሱም የመቁሰል እደጋ ደረሰበት። ቁሰሉ ክባድ ስለነበር ሐኪሞች ሊመረምሩትና ሁናቴውን ሊያጤኑ ምናልባትም ለሞት ሊዳርገው ይችላል የሚል እምነት አደረባቸው። ወደ ኋላ ግን የግራ እጹ እስከ ክርኑ ቢቆረጥ ሕይወቱ ሊተርፍ እንደሚችል ደረሱበት።

ሻለቃው መርዶውን ሲሰማ እጅግ ዘገነነው፣ የሚሞትም መሰለው። ባለቤቱ ትልው የነበረው ነገር ትክክል እንደሆነ በዚሁ አወቀ። የጦር ሜዳ ሕይወት ወደ ሞት ሊያደርስ፣ ካልሆነም አካለ-ጎደሉ ሊያደርግ እንደሚችል በወትር ትነግረው ነበር። አሁን እንግዲህ ስለቆሰለ ወደ ቤቱ መመለስ እንዳለበትና ያ ያስደሰተው የነበረው ሕይወት ማክተሙን ሲገነዘብ እጅግ አዘነ።

ሳይታወቅው እምባ ከጉንጮቹ ላይ እንደ ጎርፍ እየፈሰሰ በቅሰቅ ብሎ አለቀሰ። የዚያ የጀግንነት ሕይወት አክትሞ ከቤቱ ሲመለስ ሌሎች እየደነፉትና እየተንከባከቡት የሌሎች ተጠዋሪ ሆኖ እንደሚኖር በአሳብ በታየው ጊዜ እጅግ በጣም ተከፋ። ስቃይ ምኞቱ የነበረው ጀግና ወታደር ከቤት ሊውል ሆነ። ከአልጋ ለመውረድ አንኳን ያለ ሰው ድጋፍ ለመንቀሳቀስ ባለመቻሉ ብዙ ተረበሸ። በዚህ ሁኔታ እያለ ሳብዙ ላምንታት እንደሚቆይ ሲገነዘብ እጅግ ቢያዝንና ቢከፋም የደረሰውን ከመቀበል ውጭ ሌላ አማራጭ አለነበረውም። ወደ ሐኪሞቹ ዞር ብሎ የሚከተለውን በፈገግታ ተናገረ።

«ጓደኞቼ አርኖልድ ቪልተን ሕያመቱን ለዶን ክርሎስ ንትናቴ ስጠ። ሼኔ ደግሞ አንድ እጅጉ ለንትናቴው መስዋዕት ሳደርግ መከሩት የለብኝም።»

ነገሩ ሁሉ በዚሁ አለቀ። የሻለቃው እጅ ተቀረጠ። ቁራጣውና ቀራጩ ጀግና ሻለቃም የእጁ መቅረጥ ተቀበለው እንጂ ብዙም አልተከፋበትም። ሕይወትን በቆራጥነት መምራት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ስለሆነ ይህን መቀበል የግድ ነው የሚል እምነትም አደረበት።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ቀኖተኛ ሚስት

በሕይወት ዘመን የሚፈራረቁ ደስታና ሀዘን የሕይወት ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ዘወትር ሀዘን በደስታ ሲተካ ደስታም በሀዘን ይተየራል። ሻለቃው ለባለቤቱ ሊጽፍ አሰቡት የነበረው ደብዳቤ በጊዜው ሳይጻፍ በመቅረቱ ባለቤቱ ስለዝርዝር ነገሮች ወሬ ሳትሰማ ትተራለች። ሆኖም ግን አልፎ አልፎ ጦር ሜዳ ውስጥ ምን እንደ ገጠመው አጠር ያለ ማስታወሻ በጥቂ ሰማሽ ወረቀት ስለላከለት በመጠኑም ቢሆን ስለጦርነቱ ሁኔታ ሰማች። ዕለትዓንጥ ቪቫን ግን ምንም አታውቅም። እርሱም ከዚያ አደለ ያነሳሳት ነገር አልነበረም። 'ስንገኛኝ በገዘርዝር አጫውታታለሁ' በሚል ጉዳይን ቾላ አሰው። እንዲያውም 'በደብዳቤ ከመንገር በአካል ማስረዳቱ ይሻላል' በሚል እምነት ነበር ስለልጅትዋ ደብዳቤ ሳይጽፍሳት የቀረው። ቁይቶም ስለዚህ ጉዳይ ሲያበሳስል ይኸው እንደሚሻልና የልጅትዋ ጉዳይ እስከዚህም ከባድ አለመሆኑን ያምናል። ደጉ ሻለቃ 'ይህ ነገር ቤቲ ውስጥ ጭቅጭቅ ሊፈጥር ይችላል' የሚል አሳብ ከጭንቅላቱ ውስጥ ገበቶ አያውቅም።

የቪቫን ሞግዚት አንድትሆን የቀጠራት ሴት ባልዋን በጦት ያጣች እንግሊዛዊት ወይዘሮ ናት። ባልዋ ከሞተ ቆይቷል። የሞተውም እዚያው አስፖኝ አገር ውስጥ እንደ አነሻለቃ ሌሰተር ከጦርነት ውስጥ ገብቶ ጦር ሜዳ ሲዋጋ ተመትቶ ነው። ሴትዮዋ ባልዋ ከሞተ በኋላ ከዚያው ቀረች እንጂ ወደ አገርዋ አልተመለሰችም። ቪቫንን ከልብ ነው ያፈቀረቻት።

ልጅትዋ፣ ሞግዚትዋና ሻለቃው ከቢታ ቢታ እየተዘዋወሩ ለጥዙ ዓመታት
ነው አብረው የቆዩት። አብረው በመኖራቸው ሰዎች ያገረሙ. እንጅ
ለሻለቃው ምንዋም አልነበረችም። ቤትዋ መልኩጥሩ ሰላልነበረች ሰዎች
ማግታቸው አልቀረም። ሕፃንዋ ግን ሁሰት ዓመት ሲሞላት እጅግ ሰላግረኝ
ያያት ሁሉ ተማረከላት። በዚያ እደሜዋ ሳሙኝ፣ ንክሱኝ የሚያሰኝ ጌንጭ
ነበራት።

ሻለቃው ወደ አገሩ በተመለሰ ጊዜ ብቻ ነበር እንግዳ የሆነ ነገር
መፈጸሙን የተገነዘበው። ሊተበሉት መኪና ይዘው ወደ ባቡር ጣቢያ
የመጡት ሠራተኞች ልጅ የያዘች ሴት ይዞ በመምጣቱ ለመገረማቸው
ከፈታቸው ላይ አነበበ። የሠራተኞቹ ፈተነ የሹፈሩም ሞምር፣ አተኩሮ
ሲያጤን ነበር ነገሩ የነነከነው። ባለቤቱ ነበረች እንዲተበሉት ሥረቱኞቹን
የሰከፉቸው።

ሹፈሩ ከልጅነቱ ጀምሮ ነባልና ሚስቱ ቤተሰቦች ቤት ተቀጥሮ ነበር
ያደገው። ሻለቃው ልጅና ሴት አስከትሉ በመምጣቱ ሹፈሩ አይቶትና
ሰምቶት የማያውቅ እንግዳ ነገር ሆነበት። 'እንዴት ሊሆን ይችላል' በሚል
በሜት አፍጥጦና አፉን ከፍቶ በተመለከተው ጊዜ ነበር ሻለቃው ሰለጉዳዩ
በቁንቁት ማሰብና ማስላሰል የጀመረው።

«ታዲያስ ቲቤት፣ ምነው አፈጠጥክብኝ! ሁላችሁም ደህና ናቸሁ? ቤት
ደህና ነው?» ሲል ሻለቃው ሹፈሩን ሲጠይቀው መለሰ ሳይሰጠው እርሱ
ሌላ ጥያቄ ጠየቀው።

«ጌታዬ ሴትዮዋና ልጅትዋ አብረውን ነው ወደ ቤት የሚሄዱት?»

«አዎን፣ አብረውን ነው የሚሄዱት። ሕፃንዋ ጡት ያጠባችት የመንፈስ
ልጄ ናት» ብሎ ሻለቃው ሲመልስለት «እሺ ጌታዬ» አለ ሹፈሩ ግራ
በተጋባ አነጋገር። የድምፁ ቃና 'አኔ የለሁበትም' የሚል ቅላፄ ነበረው።
ለሻለቃው ግን ሕፃንን ጡት አጥብቶ እንደ ልጅ ለማሳደግ ከቤት ይዞ
መምጣት እንግዳ ነገር ሆኖ አልታየውም። እድሜ ለመከረው ሹፈር ግን
ሚስትን ከቤት አስቀምጦ ሕፃን ልጅ ይዞ መምጣት በጣም የሚያስከፋ
ነገር መሆኑን በሚገባ ገብቶታል። ከአጭር ጊዜ ዝምታ በኋላ «ጅን፣
ሄስተር ደህና ናት?» ሲል ሻለቃው ጠየቀ። ወ/ሮ ሄስተር የሻለቃው
ባለቤት ሲሆኑ ደህንታቸውን ለማወቅ ፈልጎ ነው እንጂ የተለየ አሳብ
ከሞንትላቱ ውስጥ ገብቶ አልነበረም።

«ደህና ናቸው። ብሎ መለሰ ሹፈሩ ሞኗኮቱ። ጉሮሮ በጥሩ አሞታው።
የነገሩ እንግዳነትና አሳሳቢነት ሻለቃው አውቋም በኋላ ላይ
ሊሆንም 'ምኑ ላይ ይሆን ሞግይሳስበውን ልጅና ሞግዚት ይዞ መምጣት
ሲል ሻለቃው ማሰላሰሉ አልቀረም።

መኪና ውስጥ ከሙግታቸው በፊት ሉሞንዋ ደስ ብሎአት ከመጻ
ወዲህ ሮጠች፣ ከት ከት ብላ ስታ እንዲ ጥሻ ቦረቀች። እናትና አባትዋ
በሕይወት ኖረው ደህን ቢያዩ እንዴት ደስ ባለቻው! ይህን የደስታ ትኳበት
ለማየት ባለመታደላቸው ሻለቃው እጅግ አዘነ። እርሱ ግን በሕይወት
ኖሮ ይህን ለማየት በመብቃቱ ውስጥ ውስጡን ደስ አለው። በዓለም ላይ
ያለ የአባንዋ ዘመድና ወዳጅ አርሱ ብቻ መሆኑን በተገነዘበ ጊዜም ያቺ
ደስ የምትል ልጅ የአርሱ አንጡራ ሀብት መሆንዋን አረጋገጠ። ደህም
ደስታውን በእሣፍ ከኖ አደረገው።

«ይህቺ ልጅ እህ የእኔ ልጅ ናት። እግዚአብሔር ይመሰንትና የእኔ
ልጅ በለሆነች አቸጫ በፊቀደ ሠጠን ሁሉ እንከባከባታለሁ፣ አሳድጋታለሁ»
ሲል ለራሱ በድጋሚ ቃል ገባ።

ሻለቃውና ሁለቱ እንግዶች እንዲሁም ሠራተኞች ከመኪናቸው ውስጥ
ገብተው ወደ ቤታቸው አመሩ። ቤታቸውም ቅርብ በለነበረ ከጥቂት
ደቂቃዎች በኋላ ደረሱ። ከገቢያቸው ውስጥ ሲገቡ ከዚያ የነበሩ ትላልቅ
ዛፎች ስላልተቆረጡ እንዳሉ መሆናቸውን አየ። ከቤቱ ግርጌ ከሚፈስሰው
ወንዝ ላይ የነበረው የእንጨት ድልድይም እንዳልፈረሰ ተገነዘበ። የሰሩና
የባቱ ማማር እንዲሁም የግቢውን ሰፋት ዳግም ከረጅም ጊዜ በኋላ
ሲያየው የደሰታው ብዛት እምባውን አስመጣው። ቤት፣ ቤት ነውና ከቤ
ቱ በመመለሱ እጅግ ደስ አለው። የመጣበት መኪና ከቤቱ በራፍ ሲቆም
ባለቤቱ ከቤት ውስጥ በር አጠገብ ቁሞ ብላ እንደምትጠብቀው ጠረጠረ።
እውነትም ባለቤቱ ባለዋ በሩን ከፍቶ አስኪገባ በጉጉት ነበር የምትጠ
ብቀው። ከቤት ውስጥ የቆየችውም ከሠራተኞችዋና ከሹፈሩ ፊት ፍትርዋን
ለመግለጽ ከባለቤትዋ አንገት ላይ ሰትጠመጠም ለመታየት ሰላልፈለገች
ነው። ሻለቃው ከቤት እንደ ገባ ጊዜ ሳትሰጠው አቅፍ አድርጋ በመያዝ
ስሩ የተኑሎለ አስኪመስለው ሳመችው። ናፍቆትዋን ለማሳየትም ልብስ
ታጥቦ ከመሰጣቱ በፊት በታይል እንደሚጨመቅ ሁሉ እርስዋም የባልዋን
ደረት ከደረትዋ ጋር አጣብቃና በእጅትዋ አንገቱን አንቃ ይዛ በተጅላት
ሁሉ ጨመቀችው።

Scan by Easy Scanner

«እንኳን ደህና መጣህልኝ፡ ዳግም ግን አትለየኝ» ስትል ተግጠናችው፡፡ ከዚያም የጋለው ስሜትዋ ቀዝቀዝ ሲልላት ባልሞን ሉሎ አደረገችው፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ቆራጣ እጅን ያየችው፡፡

«የእኔ ደም ይፍሰስ» አለች ፎክ ብላ፡፡ «ደምህን ጠራርጌ እንዳላጥብልህ እንኳን ከአጠብህ አልነበርኩም» ስትል በህዘኔታ ተናገረች፡፡ ሻለቃው ይህን ሲሰማ በስሜት ተሞጠ፡፡ እርሱም ቤተሰው እንት አድርጎ በማሰቡ በድጋሚ ምጥቀ አድርጎ ሳማት፡፡ እንደተቃቀፉ ፊትዋን ስታነብር ልጅትዋንና ሞግዚትዋን አየቻቸው፡፡ ግራ ተጋብታና ደንግጣ ፈገፍ ቀረች፡፡ ድንጋጤው ሲለቃት «ሻለቃ፣ ይህቺ ቤት ደግሞ ማን ናት?» ስትል በለዘቢ እንደበት ጠየቀችው፡፡ ጥያቄው አጭርና ቀላል ቢሆንም አመድ ጥያቂ ጓደኛው ከአስፖኝ ተራራ ላይ ወድቆ ከሙሞ በፊት የተናገረውን አስታወሰው፡፡

«ባለቤቱ ባሬ ጠዋት ሞታለች፤ የሞተችውም ጨቅላ ልጅ ጥላብኝ ነው፡፡ ልጁን ወስደህ የራስህ ልጅ ታደርጋታለህ?»

አሳቡ በለጋነት አድሜዋ ስለተቀጨችው የሕፃንዋ እናት ያመጣው ሚስቱ ለጠየቀችው ጥያቄ መልስ ሳይሰጣት ፈዝዞ ይቀራል፡፡ ይህን ጊዜ «ሻለቃ፣ 'ይህቺ ቤት የማን ናት?' ብዬ እኮ ነው የጠየቅኩህ» ስትል ጥያቄዋን ደገመች፡፡ አሁን ግን የድምዕዋ ቃና ከስተርተር ያለ ሰለነበር ሻለቃው ሕፃንዋን ከሞግዚትዋ ተቀብሎ ከባለቤቱ ክንድ ላይ ለማሳረፍ ሞከረ፡፡ ሚስቱ ግን ሕፃንዋን ለመቀበል ዝግጁ በሳልነበረች እጅትዋን አልዘረጋችለትም፡፡ እንኳን እጆችዋን ልትዘረጋ ፊትዋም ፈገግ አላለ፡፡ ሻለቃው ልጅትዋን እንደ ያዘ ቀረ፡፡

«ሌስተር ልጅ አኮ የለንም» አለ የሚለውን ቢያጣ፡፡ «ልጅ እንድትሆነ» ብዬ ጡት ያጠባኋት ልጄ ናት፡፡»

«ልጅ እንድትሆንን?» ስትል ባልዋ የተናገረውን በደገመች ጊዜ «ቦነ በሌሊት፣ ሌሊት በቀን እንደሚተካ ሁሉ የእኔ በእንቺ፣ የእንቺ ደግሞ በእኔ መተካት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ሕፃንዋ ልጅሽ ትሆናለች» በማለት ሻለቃው አሳቡን አካፈሳት፡፡ ቀጥሎም «መቼም እንቺን የሚያስከፉ ነገር እንደማልሠራ የምታውቂው ነው፡፡ ልጅትዋን እወዳታለሁ፤ አንቺም እንድትወጂያት አፈልጋለሁ» ሲል ተማጠናት፡፡ የባለቤቱ ፊት ግን አሁንም አልተፈታም፡፡

«የማን ልጅ እንደሆነ፣ እንኳን እኮ አላውንዝብንም» አለችው በቀበቀበ እንደበት፡፡ ባለቤቱ ይህን ስትናገር እጅን ተደጋጋሚ የሞተውና ሚዳ የቀረው ሃይኛው ቅዝ አለው፡፡ ሃይኛው ሕያውነ ከማሰሩ በፊት የተናገራቸውና በፍትር የተሞሉ ቃላት ትርጅ አሙተተው ድቅን አሉበት፡፡ ባልና ሚስት ሲጨኑታጨቁ ሞግዚትዋ ክቅመኛበት ሳትነቃነት እንጽሮተቋረች አንባትዋን ይፍታ ቀረች፡፡ በባልና ሚስት ጉማገር ማን በማም ተናዳለች፡፡ የሴትዮዋ አነጋገርና አተባበል የጠበቀችው አልነበረም፡፡ በር የሰደደ ፍቅር በቅናት አንድዶ እሙሬ እንደሚያደርግ ባለመጣንዘብዋም «ምን ዓይነትዋ ጨካኝ ሴት ናት» ስትል አሰበች፡፡

ሕፃንዋ ወደ ሚስስ ሌስተር እያየች እጅዋን ዘረጋችላት፡፡ እርስዋ ግን ያላየች በማስመሰል ፊትዋን አዞረችባት፡፡ አሁንም ህስተርተር ባለ አንደበት የሚከተለውን ቢጋለ ቁጣ ጠየቀችው፡፡

«የማን ናት ልጅ? እንዴት ብለህ ነው ጡት በማጥባት ልጅህ ያደረግካት?»

«የሻምበል ሺልተን ልጅ ናት፡፡ ሻምበል ሺልተን ከጋለንባ የጦር ሜዳ የወደቀ ጀግና መኩንን ሲሆን በሕይወት እያለ ጥሩ ጓደኛዬ ነበር፡፡ ባለቤቱ ይህቺን ልጅ እንደ ተባላላለች በጠዋት ሰዓት ስትሞት እርሱም በእለቱ አመሻሽ ላይ በጥይት ተመትቶ ከጦር ሜዳ ወደቀ፡፡ ኑፍሱ ከሥጋው ከመለየትዋ በፊት የዚህችን ልጅ እደራ ጥሎብኝ ነው የሞተው፡፡ በዚያች ቅጽበት ነው ልጁን ልጄ ሁና እንደማሳድጋት ቃሌን የሰጠሁት፡፡»

ባለቤቱ የጓደኛውን ታሪክ ስትሰማ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ዝም ካለች በኋላ ሌላ ጥያቄ አነሳች፡፡

«ታዲያ ለምንድነው ይህን ገልጸህ ያልጻፍክልኝ?» ብላ ስትጠይቀው ምክንያቶን ገልጾ ለማስረዳት ሞከረ፡፡ ሆኖም የተናገራቸው ቃላት እንኳን እርስዋን እርሱንም የሚያሳምኑ አልነበሩም፡፡ «ባል ልጅ ይዞ ሲመጣ ቀርቶ እንግዳ ለመጋበዝ ሲያስብ እንኳን ባለቤቱን ማማከር አለበት፡፡ ምንም ሳይናገሩ ክቤት ልጅ ይዞ መምጣት የሚይታሰብ ጉዳይ እንደሆነ ነው የሚገባኝ» ብላ የተናገራቸው ቃላት ሁሉ አለማኝ እንዳልሆኑ ገለጸችለት፡፡

«እኔማ» አለ ሻለቃው፤ «ያንቺና የእኔ ልብ አንድ እንደሆነ ሙቼ ነሞ ልቤ የፈቀደው ሁሉ ያንቺም ልብ ይፈትደሞል ብዬ አስቤ ነሞ» ካለ በኋላ

Scan by Easy Scanner

«ለመሆኑ ለተወዳጁ ጓደኛዬ ልጅ ልትራራላትና ልታዝንላት የሚገባ ነገር አይመስልሽም?» ብሎ ሊጠይቃት «አይመስለኝም» አለችው ፊርጠም ባለ እንደበት። «በማም ነው ያስገረምከኝ። ቀደም ብለህ ብታስጠነቅቀን ጥሩ ነበር። እንትም እንደምታውቀው አንድን ቢሙ በድንገት የማፍቀር ጠባያ የለኝም» አለች በዝግታ ንግግርዋን በመቀጠል። «ማህፀኔ ለምልሞ ልጅ ባለማፍራቴ ብዙ እረበሻለሁ፣ እጨነቃለሁ፣ እናደዳለሁ። የእንተ ልጅ ይቡ መምጣት ደግሞ ይበልጥ ሊረብሸኝ እንደሚችል ማሰብ ነበረብህ። ቀደም ብለህ ብታስጠነቅቀኝ መልካም ነበር።»

«ወቸ ጉድ» አለች ሞገዚትዋ። «ጌታዬ፣ እሜቴ ሕፃንዋን ካልፈለግዋት እኔ ልውሰዳት። አሁን እንደምሰማው እሜቴ መቼም ቢሆን ይህቺን ሕፃን ሊያፈቅሩ የሚችሉ አይመስለኝም። ስለዚህ ሕፃንዋን እኔ ይዣአት ብሄድ ይሻላል። ለዚህ የሚከፈለኝ ጎንዞብ ደግሞ አይኖርም። የትም ያትም ብዬ ሥራ ስለማላጣ እርስዋን ማለዳማ አያትተኝም። እምላክም ይህንን እያየ ዝም ስለማይል አሱ ይረዳኛል። ይህቺን ጽጌረዳ የመሰለች አምቡጥ አልቀበልም ብሎ መመለስ መላእክትን አልቀበልም እንደ ማለት ያህል ነው። በዚያ ላይ ደግሞ የሙት ልጅ ናት» ብላ ስትናገር «ይህቺ ደግሞ የማን ናት ሞተሚጣ» ስትል ሴሰተር ተናገረች።

«'ይህቺ' ተብዬ የምጠራ ሴት አይደለሁም፤ የሕፃንዋ ሞግዚት እንጂ» ስትል ኖራ ኮስተር ባለ አንደበት ሰትመልስላት «ሽለቃ፣ ማንኑትዋን ጠየቅሁ እንጂ ሌላ ያልኩት ነገር የለም» አለች ሌስተር የሴትየዋን አመላለስ በመናቅና ምንም ነገር እንዳልተባለ በመቁጠር።

«ምነው ሊስተር፣ ማን እንደሆነች እያነገረችሽ!የሕፃንዋ ጠባቂና ሞግዚት ናት አኩ» በማለት ከመለሰላት በኋላ ወደ ኖራ ፊቱን አዙሮ «ኖራ፣ ባለቤቴ ጊዜ አግኜታ የሆነውን እስከምትቀበለው ሕፃንዋን ይዘሽ ከሚፋጥለው ከፍል ውስጥ ብትቆዪ» አላት። ከዚያም «ጄን አራት ሳታቀርብ አልቀረችም» ብሎ ከክፍሉ ወጥቶ ሄደ። ባለቤቱም ሌላ ነገር ሳትናገር ተከተለችው። ልጅትዋንና ሞግዚትዋን ግን ጸንም አለናገረቻቸውም።

ሞግዚትዋ ልጅትዋን ይዛ ከተባለው ክፍል እንደ ሄደች የቤቱ ጠባቂና አሽከር እንርሱ ከጸቡሩነት ክፍል ገብቶ በቃላት ለመገለጽ በማያስቸግርና ልብን በሚመስጥ ስሜት ሕፃንዋን አተኩሮ ተመለከታት። ከልጅትዋ እግር ሰር ተንበርክኩ እንደበቱን የሕፃን በማስመሰል አዋራት። ኖራ ልጅትዋን የሚወድ ሰው ስላገኘች እጅግ ደስ አላት። ከደስታዋም ብዛት የምታወራውን

ስታውት የልጅትዋን ፈረን ስስሙዬሙ ዘክዘነቀለች። እናትዋ በመሊደ ምክንያት እንደ ሞተች፣ የሞታችውም ከሶስ የምታዉቀው ባልዋን ፊት ለፊትዋ እንደሆነና በእሰቱ አባትዋ ከመር ሚጻፍ መሙይጠን፣ ሕይወቱ ያለፈውም የሻለቃውን ልጅ ተንከባክቦ እንደሆነ፣ ሻለቃውም ልጅትዋን እንደ ራሱ ልጅ ሊያሳድጋት በዚያኑ ጎጃበት ቃል መግባቱን እምባ እየተናነቃት በዝርዝር አስረዳችው።

ባልዋ ሚስት ብፅጫውን ሲሆኑ «ቤቱን ደህና አድርገሽ ነው የጠበቅሽውና የተንከባከብሽው» በማለት ካሞካሻት በኋላ «ስለልጅትዋ የሰጠሽው አስተያየት ግን ቅር አሰኝቶኛል፤ ምን አለ ልጅትዋን እንደ ልጃችን ቆጥረን ብናሳድጋት?» ብሎ ሻለቃው ባለቤቱን ሲጠይቃት መልስ አልሰጠችውም። ግን ከገጾታው በላይ ትስጥዋ እንደ ተሰበረና ሰሚትዋ እንደ ተጎዳ ተገነዘበ።

«ያአባትዋ ነፍስ ከለበሰው ሥጋ ልትለይ ስትል አባትዋ እንዲት ብሎ አንዳዮኝና እናትዋ ደግሞ ከሞተች በኋላ ያሚያነሳት አጥታ ከመሬት ላይ እንዲች ብሳ ተንጋልላ በተኛች ጊዜ ምን ትመስል እንደ ነበረ ብታዪ ኖሮ ልጅትዋን ከመውደድና ከማሳደግ ወደ ኋላ አትይም ነበር» ሲል በማስተዛዘን አናገራት። ባለቤቱም ይህን አሳዛኝ ታሪክ ስትሰማ ዓይኖችዋ በእምባ ተሞሉ። ከዚያም ቀና ብላ አያየችው «አልገባህም» ብላ ተንሰቅስቃ አለቀሰች። «ምን ያህል በልጅትዋና በአናትዋ እንደ ቀናሁ አንተ አልታየህም። እንደምታውቀው እኔ ከማህፀኔ የወጣ ልጅ የለኝም። አንተ ደግሞ አሁን ልጅ ይዘህ መጥተህ ውደጂያት ትለኛለህ። ወንዶች ስትባሉ ሁሳችሁም ምንም ነገር አይጠቅሁም። በማም ነው የምትገርሙኝ።»

«አረ ተዪኝ፣ በማም ነው የሚገርመው። እኔ በዚህ መንገድ መች አየሁት፣ ነገሩ ሁሉ የገባኝና ሁኔታዎችን ያገናዘብኩት ገና አሁን ነው» አለ ሻለቃው ረጋ ብሎ። «በትድሚያ ማሰብ የነበረብኝ ስላንቺ ደህንነትና ስሜት መሆን ነበረበት፣ ግን አላደረግሁትም። ልጅትዋን በየሽ ቁጥር ስሜትሽ ከሚነካ ኖራ ልጅትዋን ይዛት ትሂድ» ብሎ ሲናገር «የለም፣ ይህማ አይሆንም» አሰችው እርስዋም በህግታ እንጋገር። «አንተ ልጅትዋን ትወዳታለህ። ጓደኛህም የአደራ ቃል ጥሎብህ ነው የሞተው። ምንም እንኳን ሴት ባትሆንም ጡትህን አጥብተህ ልጅህ አድርገሃታል። ከአሁን በኋላ ወደ ኋላ መመለስ አይቻልምና እኔ የተዎለኝን ሁሉ ልሞክር» ስትለው ሻለቃው እጅግ ደስ አለው።

Scan by Easy Scanner

«እንግዲያውማ ልጅትዋን ለማፍቀር ጥራት ታደርጊያለሽ» ባላት ጊዜ «እሞነራለሁ» በትል መለስችለት። ሆኖም ግን «እርግጠኛ አይደለሁም» በትል አስጠነቀቀችው። ሻለቃውም ሌላ የተለየ አሳብ ሰያተርብ ነጎዱ በዚሁ ተቋጨ። ሻለቃውም በዚሁ ረኩ።

«እንደሚሆንልሽ አልጠራጠርም፣ የእኔ ማር» ሲል አቶሳመሳት። ሆኖም ግን ሚስስ ሌስተር እስክ መጨረሻው አልሆንላትም። የቪቫን የመደፈት ሕይወት መበላሸትም ምክንያት የሆነው ይኸው ሳይሆን አልቀረም፣ የሊንዋ እመቤት የሆነችዋና ከሰር ልዮኔል ጋር የነበለለችው ይህችው ሕፃን ናት። ሚስስ ሌስተር ልጅትዋን በመቻል በጥሩ እያያዝና ርህራሄ በተሞላበት ስሜት ልታሳድጋት ብዙ ሞከረች። ልታፈቅራትና ልትወዳት ግን አልቻለችም። አትክልቶች ያለ በሐይ ብርሃን ለመኖር እንደማይችሉ ሁሉ ልጅትዋም ያለ ፍቅር ለመኖር ተገደደች።

ሦስራ አሥራ ሦስት

ለምን አጣሳችሙ?

በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ከቢታቸው ውስጥ የሚወራው ወሬ ተመሳሳይ ነበር። ሚስስ ሌስተር የሚጠበቅባትን ሁሉ ፈጸመች። የቤ ቱን ሰው ለማስደሰት ያህል ብቻ ልጅትዋን ተነከባከበቻት። ከልብ በመነጨ ፍቅር ግን አልጠያያቃትም። ቢሆንም ቀን አያሰፈ ሰሂደ ልጅትዋ የሻለቃው የሕይወት ብርሃን እየሆነች በመሄድዋ የቤተ ሰው ሁሉ ወደዳት። ከአናትዋ የወረሰችው ባህርይ ሳይሆን አይቀርም፣ ሰው የማፍቀር ጠባይ በልጅትዋ ላይም ጎልቶ ታየ። ማንም ሰው ፍቅር ካሳያት አርሰዋም አጸፋውን ትመልሳለች። ያም ስሚትዋ በተሳሳ በሰው ፍቅር አንድትማረክ መንገዱን ከፈተላት። ከሰው ፍቅር ሌላ እስክዚህም የሚሰባት ነገር አልነበረም። ኖራንና ሻለቃውን ከልብ በመነጨ ፍቅር ወደታቸው። ከሁለቱ አንደሆቸው ምንም ነገር ቢጠይቁ ፈጥና የምትታዘበቸው አርሰዋ ናት። ሚስስ ሌስተር በታማት ግን እንደ ግመል ሽንት ወደ ጓላ ነው የምትልላት። ሌስተር እንደማትወዳት ልቦናዋ ስለሚያውቅ ለአርስዋ ደንታ አልነበራትም። ስለዚህ ይሉ ያልወጣ የድብብቆሽ ጨዋታ በሴትዮዋና በቪቫን መካከል የሚነሃደድ የዘወትር ትርዒት ሆነ።

ሚስስ ሌስተር በልጅትዋ ትቀናለች። ቅናትዋ ከልጅ እጠት ጋር የተዛመደ ከመሆኑም በተጨማሪ ባልዋ ልጅትዋን ከመጠን በላይ ስለሚወዳት በዚህም ቅሬናለች። የልጅትዋ በነልዋ መወደድ እስክዚህም ባያስነሳትም ሞግዚትዋ ከልጅትዋ ጋር የነበራትን መቀራረባና መፈቃቀር ስትመለከት ግን ብዙ ያስነሱታል። ደስም ልጅትዋ ሳይ እንደትጨነና እንድታስቀይማት ሌላው ምክንያት ሆናት።

ልጅትዋ ተፈጥሮ ውበት የቸራት አመሌሽጋ ከመሆንዋም በላይ ሞገስ ያልተለያት ተበጥባጭና ንቁ ልጅ ስትሆን ዓይኖችዋ እጅግ ማራኪ ናቸው። ደም ግባትዋ የሚስብ ስለነበር ያያት ሁሉ ሳማት፣ ነክሰት፣ አቀፈት፣ አሻሻት የሚያስኝ ብርቱ ሰሜት በውስጡ ቅፈጥርበታለት። የድምፅዋ ነገርማ ባይነሳ ይሻላል፣ ከሙዚቃ የጣፈጠ ነው። ጉንጮችዋ ላይ የሰረሳይ አካልዋ ሳይወዱ በግድ የወነድ ሁሉ ዓይን ያንዘራትታል። በዚህም የተነሳ አሳዳሪዋ ዘወትር አተኩሮ ሲመለከታት 'አንድ ቀን በእጉ የተከበረ ሻህ ይንበረከክላታል' እያለ ዘወትር ይተንብያል።

«ታያሳችሁ» ይላል ሻለቃው። «እነዚያ የሰረሳዱ ጉንጮችዋ ከአታት አንድ ቀን የሚያደርሱትን ጥሩት ልብ በሉ» ብሎ ሲናገር «ምን አለ እንዲህ አያልክ ባትቀባጥር። የዚህ ዓይነቱ ከንቱ ንግግር ልጅትዋን በይበልጥ ስለሚያበላሻት አርባነቢስ ነው» በማለት ሂስተር ባልዋን ትዘልፈዋለች።

«ምንም አትሆንም» ሲል ሻለቃው ይመልሳል። ቀጥሎም ወዲ ጄን ፈቱን በማዞር «ጀን፣ ግድ የለም ተያት፣ የፈለጋትን ታደርግ» ይላታል።

የልጅትዋ ውበት ሻለቃውን ከልብ ያበደስተዋል። ንጉትዋ የመንፈስ ደስታን ያጎናጸፈዋል፤ ከመጠን ያለፈ እርኒታንም ይስጠዋል። የሻለቃው ያፍላና የስሜት ተባዥ የሚሆንበት ዘመን በማለፉ የእስት ተእስት ሕይወቱን የሚተሩው ያለፈ ሕይወቱን በማስታወስ ነበር ለማለት ይቻላል። ከጊዜው አብዝቸውን ሰኑት የሚያጠፋው ከቤት ውስጥ ደመቀመዋ ሲሆን ከቤት ወጣ የሚልበት ጊዜ እጅግ ውስን ነበር። በዚያን ጊዜ ቀሚያበደስተው ነገር ቢኖር ጥሪውን እየሚገ የግል እርሻውን መታጎንትና ማስተዳደር ሲሆን ከባለቤቱና ጡት ካጠባት ልጅ ጋር ቁጭ ብሎ ማሙጋትም ያስደስተዋል። ጋዜጣ ማንበብም የእስት ተእስት ሱሱ ነበር።

ቪቫን የሕይወቱ ፎራ ስትሆን ከቤቱ ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ይበልጥ ለእርስዋ ነበር እንደ ዓይን ብሌን የሚጨነቅላት። ከሚስስ ሌስተር ሌላ ያያት ሰው ሁሉ ስለሚያፈቅራት የሻለቃው ልጅትዋን መውደድ እስክዚህም የሚደንቅ ነገር አልነበረም። ቪቫን ገፍው ከገነና ከታወቀ ትምህርት ቤት

ገብታ የሚያነሪ ትምህርት ቀሰሙች። ተፈሣሮ ሙልክ ብቻ ሳይሆን የቸራት በአንፍንጅ ነጠም ልዩ ችሎታ ለማሏታል። ለምሳሌ በሙዚቃ በሣም ገበዝ ስለነበረች ስትዘፍን በአገሩ የታወሉ ዘፋኞችን ታስንታለች። ድምፁመረዋ በመሆነዋ የጠራና ታናው የሚስጥሞ ድምፅ በማውጣት ሰዉን ሁሉ ታፈዘልች። ሻለቃው የተሊያዩ ቋንጀዎችን ስለሚናገር ፈረንሳይኛና ጀርመንኛ አስተምሯታል። ብዙ ጊዜ ሁሉቱ የሚያወሩት በእንግሊገኛ ሳይሆን በእነዚህ ሁለት ቋንቋዎች ነበር።

ልጅትዋ እድሜዋ እየጨመረ በሄደ ቁጥር በይበልጥ እያማረባትና ሣርማ ሞገስዋ እየፈካ መምጮ መልክዋ ገሃድ ይወጣል። በአሥራ ሰባት ዓመትዋ 'ኢንግሊገ አገር ውስዋ ከቪቫን ዊልቶን የሚበልጥ ቆንጆ የለም' እየተባለ ተወራ። ቅንድብዋ የንግሥትን፡ ከንፈርዋ ሊፈነዳ የተቃረበ ጽጌ ረዳን፡ ፈገግታዋ የጠዋት ሀሐይ ፎራን እያመሰለ በመሄዱ ሰው ሁሉ ተገረመ። የማታ ጀምበር ከሙሃ ላይ ቢያርፍ የሚያምረውን ያህል እርስዋም እንዲሁ አማረች፡ ደመቀች፡ ተናፋቂ ሆነች። ሻለቃው ይህን ማራኪ ውበት በተመለከተ ቁጥር እንደ ልጁ ሊያሳድጋት መወሰኑ አሰደሰተው እንጂ አሳጸጸተውም። በእንድ በኩል ውበት ታላቅ ፀጋ የመሆኑን ያህል በሌላ በኩል ግን ገፀይ መሆኑን ቢረዳም በውበትዋ ከከፍተኛ ቦታ ልትደርስ እንደምትችል አልተጠራጠረም። ያም ሆነ ይህ በሕይወት ዘመንዋ ተደላች እንድትሆን ከልቡ ይመኝላታል። አንዳንድ ጊዜ ሁለቱ ቁጭ ብለው ሲጫወቱ ሳይታወታቸው ብዙ ሰዓቶችን ያሳልፋሉ። በጭውውታቸው ወቅት ለሕይወት መመሪያ ሊሆንዋት የሚችሉ አሳቦችን በማካፈል እውቱት ሊያስጨብጣት ብዙ ምክሯል።

ቪቫንም ብዙ በማንበብ እውቱት ለመጣበዮት ታላለች። ሙዚቃ በመጫወት ብዙ ሰዓቶችን ታሳልፋለች። ከሩት ለሚባለዉ ነገር ልቦናዋ ውስዋ ቦታ አትሰጠውም። ህዝንና ጭንቀትም ከእርስዋ የራቁ ናቸው። ስለዚህ ሕይወትዋ ገሳ ካለበት እንደ በቀለ ባፍና አበባ የለመለመ በመሆኑ ዘወትር ተደላች ናት። ቢሆንም አንድ የሚጠበቅና ሊሆን የሚችል አደጋ ከፊትዋ ላይ መጋረጡ አልቀረም። አደጋው ከሠበትና ከታመቀ ስሜት የሚፈልቅ ሲሆን የእርስዋም ስሜት እንደ ታመቀ ነው የኖረው።

'ያ የታመቀ ስሜትዋ ዮት ያደርሳት ይሆነ?' የሚለ ጥያቄ ቢነሳ መልስ የሌለው ጥያቄ ይሆናል። በእርስዋ እድሜ ያለች ማንኛዋም ቆንጆ ልጃገረድ የሚጠብቃት አደጋ የዚሁ የታመቀ ስሜት ውጤት ሊሆን

አንደሚችል ግን ማንም የሚያውቀው ነው። ይህንኩ የዚህ የታመቀ ስሜት ውጤቶ ሊሆን በሚችለውና ሰዎች ካበር ብለው በሚጠሩት የበቡት ኃይል አደጋ የሚጠቁት ሁሉም ቆንጆ ልጃገረዶች ሰላልሆኑ ቪቫንም ከዚህ ዓይነቱ አደጋ ልታመልጥ ትችል ይሆናል ብሎ ማሰፋም ይቻላል። ሆኖም ማን ፍቅር ማንኛዋንም ቆንጆ ልጃገረድ ሊያጠፋና ከህሉ ነገር ሳይ ሊጥል እንደሚችል አሙን ነው። ቆንጆዪቱ ቪቫን ቸርና መሐሪ የሆነው አምላክ ከዚህ ነፋ መትሰጥት እንዲጠብቃት ፈጣሪዋን በጸሎት ተማጥናው ይሆናል፡ ማን አይታወትም። የሕይወትዋ መጪረሻ የሚወሰነው በሚገጥማት የፍቅር ዓይነት እንደሆነ ለማወቅ ግን አስከዚህም የሚከብድ ነገር አይደለም።

አኑል ሰው መሠደድ ከአገል ቦታ ሳይ ይጥላል። 'የውሻ ጓደኛ አር ያበላል' እንዲሉ ከማይሆን ሰው ጋር ዣጥማ ሕይወትዋ ይዘቅጣል ወይስ መልክም ሰው አጋጥሞአት ሕይወትዋ ይለመልማል? በዚያች ሰዓት ከፈጣሪ ሌላ ይህን ሊያውቅ የሚችል ማንም አልነበረም። ይህቺ ቆንጆ የአባት እንክብካቤና የእናት ፍቅር በሚያስፈልጋት ጊዜ ብቻዋን የቀረች የሙት ልጅ መሆንዋን አንርሳ።

አሥራ ስድስት ዓመት የሞላት ቆንጆና ለማላጋ ወጣት፡ ማር፣ ግፋጭ፡ ደመ-ፍስ፡ በአክል ትልቅ ሴት ሆኖም ልጅ፡ መላ አካልዋ በስሜት የተዋጠ፣ አየር የምትጪብጥ፡ በጭለንጭል በሚታይ ሕልም የተኮፈሰች፡ በወጣትነት ተስፋ የተሞላች፡ ለአፈቀራት ንግሥት፡ ለወደደቹው ትሁት መስሎ ለመታየት የማትሆነው አልነበረም። ስለዚህ ሁሉም ናት ማለቱ ይበቃል። ሁለመናዋ የሚወደድ፣ የሚፈቀር፡ ብሉኝ፣ ግመጡኝ፣ እትሳሱልኝ የምታሰኝ፣ ከማፍቀር አልፎ እንደ እምላክ አምልኩኝ የምታስብል። ይህ ነው እንግዲህ የቪቫን ገጽታ።

የሊኑ መስፍን በፍቅርዋ ሲነደፍ የቪቫን እድሜ አሥራ ሰባት ዓመት ነበር። ገና ሲያያት 'ሚስቴ መሆን አለባት' ሲል ወሰነ። ባለብዙ ሀብት ስለነበረ ማንንም በገንዘቡ ሊገዛ እንደሚችል እምነቱ ነው። ሻለቃው በድንገት ባይሞት ኖሮ የሊኑን መስፍን እታገባውም ነበር። የጣንት ወዳጅዋና ያሳደገቻት ሩሀሩህዋ ሞግዚት ባል አግብታ ቪቫን ከነበረችበት አካባቢ ርቃ ሄዳለች። ስለዚህ የሊኑ መስፍን በፍቅር በወደቀላት ጊዜ ቪቫን 'የእኔ ነው' የምትለውና ከሰንዋ የሚቆም ሰው ከአጠገብዋ አልነበረም። ስለዚህ ሕይወትዋን ትመራው የነበረው እርስዋ በመሰላት ብቻ ሲሆን አሳብ ሊያስለውጥ የሚችል የበሰለ ምክር የሚሰጣትና የምታምነው ሰው

Scan by Easy Scanner

ከዓንዋ አልነበራትም። ሁሉንም ነገር የምትጋፈጠው ብቻዋን ነው። ያ ከነ ጊዜ ነው እንግዲህ መስፍኑ ከቸች ያሉት። ምርጫ ስላልነበራት በአሥሬ ሰባት ዓመትዋ ነው የሊኑ መስፍን በመባል የሚታወቀውንና በእድሜ በብዙ ዘመን የሚበልጣትን ሽማግሌ ያገባችው።

ምዕራፍ አሥራ አራት

ወጣት ሚስት፣ ሽማግሌ ባል

የሊኑ መስፍን ሠላትዋን ቆንጆ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያደ አድሚው ሃምላ ዓመት ሰለነበር ቪቫንን በሰላሳ ሦስት ዓመት ይበልጣታል። ይህ በእገሩ ዝናው የገነነ አባውንት 'ሃንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ' ነውና ልቡ የፈቀደውን ለማግኘት የሚያስችል ሀብትና ገና ነበረው። ስለዚህ 'እንግሊዝ አገር ውስጥ እርስዋን የምታስንቅ ቆንጆ የለችም' እስከ መባል የደረሰችዋን ወጣት የትዳር ጓደኛው ሊያደርጋት ተመኘ። ይህም በሕይወት ዘመኑ ሊፈጽማቸው ከቀዳቸው ምኞቶች አንዱ ሊሆን ምሮቱም ተሳካለት።

የሊኑ መስፍን ሻለቃውንና ቪቫንን ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙቸው ከአንድ ግብገር ቦታ ሲሆን ያ ግብገር ለምስኪኖች ግንዘብ ለመሰብሰብ ሲባል የተደረገ ነበር። መስፍኑ የተትረፈረፈ ሀብት ያላቸው ሰው በመሆናቸው የእርሳቸው ችሮታ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ማንም አልተጠራጠረም።

ማንኛውም በእድሜ የገፋ ሰው ከእራት በኋላ በሚደረግ የዳንስ ጨዋታ ለመሳተፍ እንደማይፈልግ ሁሉ መስፍኑም ከእራት በኋላ ወደ ቤታቸው ለመሄድ አቅደው ነበር። ሆኖም የእራት ሰዓት አልፎና መስፍኑ በማ ተሰላችተው ሳለ ሻለቃው፣ ባለቤቱንና ቪቫንን አስከትሎ መስፍኑ ከነበሩበት ክፍል ይገባል። ሻለቃውና ቤተሰቦቹ ሰዓት አሳልፈው ነበር የመጡት። እንሽለቃ ሰውዬው ከነበሩበት ክፍል ሲገቡ ከእዚያ የነበረው ሰው ሁሉ ዓይን ቪቫን ላይ አረፈ። የመስፍኑም ዓይን እንዴ ነበር።

ቪቫንን እንደገና ለማስተዋወቅ ያህል ከሚገባው በላይ ሽንቃጣ ስትሆን ጉራጊዎች ቅቢ ሲያነጥሩ እንደሚጠቀሙበት ማማሰያ ከወጥበጥ ቀጠን፣ ከዳሊዋ ሰፋ፣ ከዙመትዋ ዘለግ ያለች መለሎ ወጣት ናት። የጽጌረዳ አበባ ምሰል ከለበሰችው ነጭ ቀሚስ ላይ ጣል ጣል በመደረጉ ከውበትዋ ሌላ ያም ጌጥ ሳይወዱ በግድ እዩኝ፣ እዩኝ የሚያሰኝ ነበር። ቪቫን ከነፍሱ ውስጥ እንደ ገበች ከወጣት እስከ ሽማግሌ የሁሉም ዓይን ተንከራተተ የሁሉም ልብ ተመኛት። የሁሉም ምኞት 'ከእርስዋ ጋር አድሬ ሲነጋ በምትኩ' ሆነ። የመስፍኑን ያህል ታደነቃትና የተመኛት ሰው ግን ከዚያ ከፍል ውስጥ አልነበረም። 'እስከ ዛሬ ይህቺን ልጅ የሚሰቀጥል ቆንጆ ሴት አላየሁም፣ ይህቺ ልጅ ሚስቴ ትሆናለች' ሲሉ ለራሳቸው ቃል ገቡ።

'ሳጣሚዎች በሰንኖቻቸው የሚያወድሰዋት፣ አገሪሪዎች በድምጣቸው የሚያንሳራጉርሳት፣ ሰዓሊዎች በአሳብ የሚነድፏት ቆንጆ ሴት ማለት ይህቺ ልጅ ናት' ሲሉ የሊኑ መስፍን በአሳብ ዋገሩ። ልባቸው ከአካላቸው ተመንጭቆ ወጥቶ ከቪቫን መጸፍ ሰር ወደቀ። ጠቅላላ ውበትዋም ተጠቃለሎ የተለየ ቅርጽ አወጣና ከእንጎላቸው ውስጥ ቤት ሠርቶ ቀጭ አለ። ስለዚህ ሳይወዱ በግድ ከዚያ የነበረ ሰው ሁሉ እስኪታዘባቸው ድረስ አፈጠጡባት።

መስፍን ሲባል የትም ቦታ መስፍን ቢሆንም ትንሽ ከተማ ውስጥ ግን እንደ ንጉሥ የሚታይበት ጊዜ አለ። የሊኑ መስፍን ጉዳይም እንዲሁ ነው። ስለዚህ እንደ ንጉሥ የሚታዩት የሊኑ መስፍን በልጅትዋ ውበት መማረካቸውን ከዚያ የነበረ ሰው በተገነዘበ ጊዜ ቪቫን ከመቅጽበት የክፍሉ ንግሥት ሆነች። የአሥራ ሰባት ዓመትዋ ወጣት ስለሕይወት ምንነት ብዙም ስለማታውቅ ያ በእገሩ የታወቁ ሀብታም በእርስዋ ውበት እንደዚያ መፍነክነካቸውን ስታይ ምን እንደምትሠራ ሳታውቅ አአፋውን መለሰችላቸው። በእለቱ በዓይን ከማመንዘር ውጪ ሌላ የሆነ ነገር የለም።

በሚቀጥለው ቀን መስፍኑ ልጅትዋ ከምትኖርበት ሰፈር ሄደው ከተዋወቅዋት በኋላ ያባብልዋት ጀመር። ምንም እንኳን በእድሜ የገፉ ሰው ቢሆኑም ቁመናቸው ያማረ ስለነበር ለጊዜውም ቢሆን የሚመኙት ዓይነት ወንድ ሆነው ነው ያገኘቻቸው። 'ምነው ሼባው' ብሉ የሚያበሪማና የሚያሸሽ ዓይነት ወንድ ሆነው ስላላገኘቻቸው ፊት አልነሳቻቸውም። እርሳቸውም በዚህ በጣም ተደሰቱ።

ሻለቃው፣ ባለቤቱና ቪቫን ከቤቱ መጥተው እራት እንዲጋበዙላቸው በጠየቅዋቸው ጊዜ ልጅትዋ ከደስታዋ ብዛት ሲቃ ያዛት። እንደ ማንኛዋም ሴት ውበትዋ ሲደነቅ በመስማትዋና ወደፊት ሊገጥማት የሚችለውን የተንዳሳቱ ሕይወት በዓይነ-ሀሊናዋ በታያት ጊዜ ስሜትዋ ቱዘበራርቆ በደስታ ሰከረች። ከነአካቴው በመጨረሻ የትዳር ጓደኛቸው እንድትሆን ጠየቅዋት። ጨካኝ ጥያቄ ቢሆንም መካሪም ሆነ አማራጭ ስላልነበራት ጥያቄያቸውን ተቀበለችው። እድግ በጣም የሚያሳዝነው ግን ስለሕይወት፣

ስለፍቅርና ስለኑሮ ውጣ ውረድ ምንም አለማወቅዋ ነው። ስለምንም ነገር አለማወቅ እንኴት ጠጥር ነው! ብታውቅ ኖሮ አትሳሳትም ነበር። የእድሜ መቀራረብና በትምህርት ደረጃ ብዙ አለመራራት ተቻችሎ ለመኖርና ለትዳር በደስታ መዝለቅ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች እንደሆኑ ብዙ አሳብ አልነበራትም።

ለውጤው ህብት ቢትረፈረፍባትና ገናናው የገነነ ቢሆንም ሻለቃው በድንገት ባይሞት ኖሮ እድሜያቸውን በሚዮት ብቻ ቪቫንን አሳልፎ አይሰጣቸውም፣ እርስዋም እታገባቸውም ነበር። ስለሻለቃው አሟሟት፣ በለሚስቱና ስለጡት ልጅ ህዘን ዘርዝሮ ለማስረዳት መሣከር በታሪኩ ሂደት አንባር ጥቅም ስለማይሰጥ ዝሙ ብሎ ማለፉ ይሻላል። ሆኖም መሰፍኑ በአጋጣሚው የተጠቀመ መሆኑን፣ እንድታገባቸው ልጅትዋን ደጋግሞ መጠየቃቸውን፣ እርስዋም እሺ ማለትዋን፣ እንዲሁም ሚስስ ሴስተር የምትወደው ባልዋን በማጣትዋ ብታዋን መቅረትዋን በተገነዘበች ጊዜ በልጅትዋ ላይ የነበራት ቅናት ማገርሸቱን መጥቀሱ ለታሪኩ መሟላት አስተዋጽዖ አለው።

ቪቫን ለቀረበላት ጥያቄ እጅዋን እንድትሰጥና እሺ እንድትል ሴስተር ገፋፋቻት። አባውንቱን ብታገባ ቆንጆዋ ልዕልት ተብላ እንደምትወራ ደጋግማ በነገረቻት ጊዜ ቪቫን ጓጓች። ሴትዮዋ የምትላት ነገር ሁሉ ትክክል ስለመሰለት አባብዋን አልጠላቸውም። በሌትዮዋም አቀራረብ ተታለለች። ለነገሩማ በወጣት ዘመኑ ፍቅርን በተመለከተ ማነው የማይታለል፣ ስለዚህ መጥፊያዋ ወደ ሆነው የሕይወት አዘቅት ሰተት ብላ ገባች። ወደፊት ሊገጥማት ይችል የነበረውን እውነተኛ ፍቅር እንዳታይ የሰውሌው ህብተና ዝና ጋረደባት። ሚስስ ሌስተር ደግሞ የማለሳለያ ጊዜ አልሰጣቻትም። እንደ እውነቱ ከሆነ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከቢተመቅደሱ ፊት ለፊት ከሊኑ ሠርጭን ጋር እስከ ቆመች ድረስ ምን እንደምትሠራ አልታወቃትም። ቤተክርስቲያን ውስጥ ባልዋን ቁና ብላ ስታያቸው ከብዙ ዓመታት በፊት የሞተችው እናትዋ ትዝ አለቻት። እናትዋ ለመሞት ስታታጥር የባልዋን ፊት አያየች እንድትሞት የጠየቀችውን አስታወሰች።

«እንደ እናቴ ያን ዓይነት ጥያቄ የምጠይቅበት ጊዜ ይመጣ ይሆን?» ስትል ለማሳጋዋና ቆንጆዋ ሙሽራ ራስዋን ጠየቀች። ጥያቄው ሞንትሳትዋ ውስጥ በነባ ጊዜ መላ ሰውነትዋ ተንቀጠቀጠ፣ ልብዋም በኃይል መታ። ያገኘችው መልስ ግን «የለም፣ አይመጣም» የሚል ሆነ። ወደ ኋላ ለመመለስ

የሚይቻልበት ሰዓት ነው፣ ጊዜው አልፎአል። ነገር ግን የቤተክርስቲያኑ ሥነሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ የተደረገው ድል ያለ ግብግና ፈንጠዚያው ቀደም ሲል ከሞንትሳትዋ ውስጥ ገብቶ የነበረውን መሞሮ አሳብ አስረሳት። ከጋብቻዋ ቀን በኋላም ቢሆን ነገሮቹ ሁሉ እንዲሁ እየተረሱ ሄዱ።

አሥራ ሰምንት ዓመት ሲሞላትማ ውበትዋ በይበልጥ ፈነ። በዚያ እድሜዋ በአባሩ የታወቀች ቆንጆና ገናዋ የገነነ ልዕልት ስለሆነች ባልዋ ሰጣም ተኩራሩባት። በዚህም የተነሳ የጠየቀችውን ሁሉ ከመፈጸም ወደኋላ አላሉም። 'እምቢ አይሆንም' የሚለውት ጊዜ አልነበረም። ማጋጌጮችዋና ልብሶችዋ ብልጫ ያላቸው ነበሩ። የመንሸራሸሪያ ሠረገላዎችዋም ሆኑ መኪናዎችዋ የአንደኛነት ደረጃ የያዙ ናቸው። ዘውተር ውድ የተባለ ቀሚስ የምትለብሰው እርስዋ ብቻ ነበረች። ለግብግ ሰው የጠራች እንደሆነ ድግስዋ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ዓይነት ሲሆን ሰዉ ሁሉ የሚያወራው ስለእርስዋ ሆነ። ሁሉም በየፊናው ስለሊንዋ እመቤት ውበት፣ ቁንጅና፣ ሙያ፣ ግርማ ሞገስ፣ ለዛ ያለው ድምፅና የማንሳራግር ችሎታ እያነሳና ሌላም ሌላ ነገር እየጨማመረ ያወራል፤ ይተቻል፤ እርስዋንም ይመኛል። በዚሁ ሰበብ የእርስዋ ልብም ከአንድ ሊሬጋና ሲረካ አልቻለም።

ሰው ሁሉ ግብግ እያዘጋጀ ቤቱን እንድታይለት ጋበዛት። እርስዋም ብዙ ተጋባጉዎችን እየጠራች ግብግ ማዘጋጀቱን ቀጠለችበት። መስፍኑ ግን በግብግው ብዙም አይደሰቱም ነበር። ሆኖም ስሜታቸውን ዋጥ እያደረጉ ተቻውሞ አያሰሙም። እንዲያውም ከነአካቴው አንጻንድ ጊዜ ቤታቸው ሲደገስ 'የፈለግሽውን ሰው መጋበዝ ትቺያለሽ' ይሏታል። አንዳንዴም 'አንቺ ወደ ግብግው ቦታ ብቻሽን ሂጺ፣ እኔ እዚሁ ከቤት እሆናለሁ' እያሉ ከቤት ስለሚቀሩ የምትሄድበትና የምትጋብዘውን ሰው እርሰዋው ራስዋ ነበረች የምትመርጠው። ይኼ ደግሞ ለባልና ሚስት ሕይወት ጤንኛ አካሄድ አይደለም። ለማንኛውም ተቅበጥባጩና ተሰፋ የቆረጠው ልብዋ በለሠ ጋጋታና ማባሪያ በሌለው ግርግር ውስጥ ደስታ ሲፈልግም ሊያገኘው አልቻለም። ጊዜ እያለፌ ሲሄድም ሌሎች ያገኙት እርስዋ ያጣችው አንድ ነገር እንዳለ እየታወቃት ሄደ።

መስፍኑ ቤተኞቻቸው ሁሉ ለእርስዋ ደግ ሥራ ከመሥራት ወደ ኋላ አላሉም። የፈለገችውን ሁሉ አሟሉላት፣ እርስዋም የፈለገችውን ሁሉ እንድታደርግ ነፃነት ያለ ገደብ አስታቀፍዋት። ይህም ለመልካም ትዳር መሰፈን ጠንት ሲሆን እንደሚችል የሚጠረጥሩት አይደለም። በእርስዋ

Scan by Easy Scanner

በኩልም ቢሆን ባልዋ ሳይሆን አባትዋ ሊሆኑ የሚችሉ ሰው ስለነበሩ አልረከቧቸውም። ያ ሁሉ ደግነት አፈር ድሜ ስለጋበ ልትመልሳቸው አልቻለችም። ለገዝዘብና ለገፃ ብሎ ብል ከማግባት ይልቅ ሳጥትር ብሎ ባል ማግባት እንደሚሻልና ልዩነቱ ምን ላይ እንደሆነ አየተራዳኛ የሄደችው ጊዜው ከመሸ ነበር።

ቪቫን በአደግዝጅዋ ቦታህ ሴት ስትሆን እንደ ልጅ የጠራ ልብ ነው ያላት። በሽማግሌ ባልዋና ዘመትር ከዘትዋ በሚመጡ መልኩ-መልካም ወጣቱ ወንዶች መከበል ብዙ ልዩነት እንዳለ በትጡ ገባች። ስለዚህ ወጣት ወጣትን ቢወድ እንደሚሻል በሚገባ ተግነዘበች። ሆኖም ይህ አሳብ ልብዋን ቢያሸፍትባትም ለባልዋ ታማኝ ነበረች። ልብዋ ግን መከጀል አልቀረም። እንኳንደግ ጥፉ ብረሪ ብረሪ ያሰኛታል። ልብዋ ከልብ የሚመደሙን ሰው ከፉኛ ተመኘ። ሲሳሙ ቢቀር አሳጽኒዋ ወይም አባትዋ በሕይወት ቢኖሩ እንኳን አብታዊ ፍቅርዋን በሚርክት ትጽናና ትረካ ነበር፡ ያም አልሆነም። በዚህም የተነሳ ሁሉም ነገር በቶሎ ይሰለቻትና ነገር ዓለሙ ሁሉ ያስጨሰት ጀመር።

ቪቫን የምትወደውን ሰው ፈለገች፣ ግን አላገኘችም። ልጅ ቢኖራት እንኳን ምናልባት ሁናቴዋ ይለወጥ ነበር። ሳቅርዋን አንደ ዝናብ ሀዛ ከሚሀሀንዋ ከመጣ ልጅ ሳይ ብታዘንብ መጥፎ ሕጋሚያዎችን በዚያ ታነሳስ ነበር ለማለት ይቻላል። ሆኖም አምላክ በልጅ ዛጋ አላደላትም። መስፍኑን ለማፍቀር ብዙ ብትሞክርም ደህም ሊሆን አልቻለም። ቢሆንም ሚታ ሚታ አትፋቸው ትተኛለች።

ከመጋበታቸው በፊት የትዳር ጓደኛ እንድትሆናቸው ጠየቅዋት እንጂ በመነከሳቸው የፍቅር ጉዳይ ተንስቱ አያውቅም። በዚያን ጊዜ የልጅነት ስሜት አስሂዳት ሳታጤንና ሳታመዛዝን ከመቀመጫዋ ብድግ እያለች በመደጋገም ስትሰማቸው ሰውይው እጅግ ይገረሙና ይደንግጡም ነበር። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ለንግሥት ቪክ የሚገባና በእጅ ሥራ የተዋበ ከአልማዝ የተሠራ የአንባትና የጆሮ ጌጥ ገዝተው ሲሰጥት ባለውለታዋ መሆናቸውን ለመግለጽ ከአንገታቸው ላይ ተጠምቀማ በአደባባይ ምጥዋ አድርጋ ሳመቻቻው። በዚህ ጊዜ ከአርስቶ ይበልጥ አርሳቸው ስላፈሩ ወደ መራት አቀርቅረው «አያስፈልግም ነበር» ካልዋት በኋላ «ስሜትን አደባባይ ማውጣት ተገቢ አይደለም» አልዋት። ከዚያ በኋላ አርሳቸውን መሳም አቆመች። ደግም አርሳቸውን አለመሳምዋ ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ስትል ራስዋን ጠየቀች እንጂ መልስ አላገኘችለትም።

መስፍኑና ባለቤታቸው ቪቫን ለን ተገለሎ በሚጠራ አጋር ትልት ቤት ነበራቸው። ሆኖም ከዚያ ቤት አልፎ አልፎ እንጂ በድሚነት ያሚኖሩበት አልነበረም። ወይዚያ ቤት በሚሄዱበት ጊዜ የሚጋብዟቸው ስዎች እጅግ ዮተመረጡ የመሳፍንትና የመኢንነት ዘሮች ብቻ ናቸው። ከዚያ ቤት ያሚደረግ ግብግና የሚረገጥ ጽንኩራ እንዲያው ዝም ብለው የሚያደንቁት እንጂ ቢታሳት ለመግለጽ የሚሞክሩት ዓይነት አልነበረም። የሊንዋ እመቤት ግን በዚህም አትደሰትም ነበር። ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የሕይወታቸው ገጽታ አረረም መረረ በኑሮአቸው ገፉበት፣ ጊዜው ደግሞ እንዲያው ዝም ብሎ እያለፈ ሄደ እንጂ የቆጠበት ትጽበት የለም። በአንድ ወትት የፀደይ መራት በመጣ ጊዜ ባልና ሚስት ያን ትልት ቤት ለትተው ወደ ለንደን ከተማ ተመለሱ።

ምዕራፍ አሥራ አምስት

የአሳዛኝ ታሪክ መጀመሪያ

ለንደን ከተማ ውስጥ የምትኖር የባልና ሚስቱ የቤት ጓደኛ በሚያዝያ ወር ድግስ ደግሳ የተለያዩ ሰዎች አራት እንዲበለሳት ትጋብዛለች። ይህቺ ሴት የተዋጣላት ባለሙያ በመሆንዋ ሰው ሁሉ ሙያዋን ያደንቃል። ዝግጅቱ ከባድና እጅግ የተጋነነ ስለነበር በሚቱጥሉት ጥቂት ቀናት ስለማብሰሉ ሰው ብዙ አወራ። ሴትዮዋ ደግሞ የምትጋብዝቸው ሰዎች በአገሩ አጅግ የታወቁ ምርጥ ወይዛዝርትና መኳንንት ሲሆኑ የምትኖርበት ቤትም ጉድ የሚያሰኝ ነው። በአካባቢው እርሱን የሚያስንት ሕንፃ የለም። የቤቱ ግቢም በአበባ ያሸበረቀ ስለሆነ በጣም ያምራል።

የአለቱ የክብር እንግዳ አዲሲቱ የሊንዋ እመቤት ቪቫን ነበረች። ቪቫን እንደ ልማድዋ ከፉኛ ዘንጣ መጥታ ስለነበር ተጋባኝዎ ሁሉ አደነቃት፣ ከማድነቅ አልፎም እግዚር ባለው ቱን እንዴት ብሉ እንደሚያገኙት ሁሉም በየፊናው እቅድ አወጣ። እርስዋን ከጭንትላቱ ውስጥ እያስገባም ከሚገባው በላይ ቋመጠ፣ ልግፊውንም በአሳብ አዝለከረከ። ቪቫን ባል ካገባች ወጺህ እንደዚያን አለት አምሮባት አያውትም። አለበስዋ ቀላል ስለነበረ የሸፈተን ልብ በዚያው የሚያስቀር ነው። የወንዱ ዓይን ሁሉ እርስዋን እየተከተለ መንከራተቱን በተገነዘበች ጊዜ እንደ ሚንኛሞም ሴት ውስጥ ውስጡን ደስታ እንክት አደረጋት። ቀደም ሲል ባልዋ የገዙላት አልማዝ ከደሬትዋና ከጅሮዋ ላይ ተንሰራፍተው እንደ ጠዋት ፀሐይ ያበራሉ።

በሕልም ካልሆነ በስተቀር እንደዚያ ያለ ውብትና ቁመናው የተስተካከለ ፍጡር እንደ መስቀል ወፍ ቆይቶ፣ ቆይቶ ብቅ የሚል እንጂ በወትሮ ሥርዓቷ አይደለም። ለዚህም ነው ከዚያ የነበረ ሁሉ የሚያየው ነገር አዲስ ስለሆነበት «ከየት የፈለቀች ውብ ፍጡር ናት» እያለ ያደነቃትና የፈዘዘለት። አንዱ ሌላው እስኪታዘበው ድረስ ይሸኮረመማል፣ ያያል፣ ያፈጣል፣ እኒ እበልህ፣ እኔ እበልዋ እያለ ሁሉም ይቅለሰለሳል፣ የማይሆነውን እየሆነ ራሱን ያቁላል። 'እባክሽ ልብሽ ይራራልኝ' በማለት የሚጣጠን ይመስል ወደ እርሱ ዞር ባለች ቁጥር ድዱን እያሰጣ ይገለፍጣል። አንዳንዱም እግዜር ብሎለት ካናገረችው በቀም በመሸናት ቡሪውን ያረጥባል ቢባል ግጋንን አይሆንም። እርስዋ ግን እያየች አታይም፣ እየሰማች አትሰማም። ለሁሉም ደንታ አልነበራትም። ቢሆንም አንድ ነገር እንደሚፈላግ ሰው ዓይንዋ ከወዲያ ወዲህ መቀበዝበዙ አውነት ነው።

እርኪስትራው ለበለሰ ያለ ሙዚቃ አሰማ። ሙዚቃው ወደሚሰማበት አቅጣጫ ዞር ባለች ጊዜ እስከ በእድሜዋ ሙሉ የማትረሳውንና እያንዳንዷን ድርጊት የምታስታውሰው ነገር ይሆናል። ከቁመቱ ዘለግ፣ ከሰውነቱ ቀጠን ብሎ የሸንቀጠና ረቀቅ ያለ መልክ-መልካም ወንድ ሚድግዳ ተደግሮ ቆሞ በሩቁ ታያለች። ወዲያው ከዚያ በፊት ተሰምቶአት የማያውቅ ስሜት ሰውነትዋን ይወረዋል። ምስኪንዋ ቆንጆ የመጥፊያዋ ሰዓት መቃረቡን ሳትገነዘብ ሰውዬው ላይ አፍጥጣ ተረች።

መልኩ-መልካሙ ወንድ ፊቱን በፈገግታ አስውቦ፣ ቁመናውን ባመረ ልብስ አስጊጦ እርሱም በተራው በሩቁ አያች። ዓይናቸዉ ትላልቅ ሲሆኑ ጥርሰ-ፍንጭት ነው። የሚያሳፍር ወይም ለመደበቅ የሚፈልገው ሰውነት ሰላልነበረው የተደገፈውን ሚድግዳ ለቀቅ በማድረግ ከፊት ለፊትዋ ቀጥ ብሎ ቆመ። ፊቱ ላይ የደግነት ምልክት ስለተንጸባረቀበት እዩኝ እይኝ የሚል መልክ አንጂ ሽሽኝ የሚያሰኝ መልክ አይደለም ያሰመ። አየተገላመጠ ከዚያ የነበረውን ሁሉ በዓይኑ ቃኘ። ይህ ሰው ሰር ልዮኔል ራይዳል ይባላል። ሰር ልዮኔል ራይዳል በዙም ሳያጥርና ብዙም ሳይንቀዋለል መካከለኛ ቁመት ያለው ሽንቃጣ ወንድ ሲሆን ኩትክሽው ሰፋ ብሎ ከወገቡ ሽንቀጥ ያለ ሰውነት አለው። እንደ ሴት ስልክክ ያለ ቆንጆ ባይሆንም ሐመናው ማራኪና የወንዳ-ወንድ ምልክት በገፍ የሚታይበት ስለሆነ ያለ ውዴታ በግድ ዓይንን ይማርካል። ገና ከሩቁ ሲያዩት ደምግባቱ እንደ ማማኑት ይሰባል። አተኩረው ሲመለከቱትማ ከንይኑ ወይም ከሌላ የሰውነቱ ክፍል የሚመንጪው የሆነ ነገር ሳይታወቅ በጠራ ምሽት እንደሚታይ ከከብ

ወይም ጨረቃ ዓይንን ማርኩ 'ነበከትኑ አዩኝ፣ አጥሩብኝ' የሚያሰኝ መልክ ነው ያለው። ያ ምንጩ ያልታወቀው ሰበት ነበር የሊንዋ እመቤ ቅን ዓይን እንደ ማግኔት ያሳበውና ጥምብርብርጥን ያወጣው። ያ ሰበት ነበር ገና ስታየው ልብዋን ከሥሷት የሰነጠቀው። ያ ድንገተኛ ሰበትና ስሜት ነው ባጣማምቾ ዮጭትር ዋንሰሰ ብለው ያሚጠሩት። ከዚያ በፊት ጭትር የሚሉት ነገር ያሳከነፈው ንጹህ ልብዋ እንደዚያ በመጥነከነኩ ቪቫን እጅግ ግራ ተጋባች። 'ምን ጉድ ነው?' በተል ራስዋን ጠየቀች። ልምዱ ስላልነበራት ለጠየቀቸው ዋያቄ መልስ አሳጣችሰትም።

እስከዚያን ጊለት ድረስ ብዙ ወንዶችን አይታለች፣ በተለይም ዓይናቸው ተጎልቶ እስኪወጣ የሚያፈጠጥባት ወንዶች። እንደዚህኛው ወንድ ግን ጥምብርብርዋ እስኪወጣ ያሰደነገጣት፣ የማረካትና ከመትጽበት ልብዋን ያሸፈተባት ወንድ አጋጥሞአት አያውትም። ከሰር ልዮኔል ራይዳል ላይ ማፍጠጥዋን ቀጠለች። በአካባቢዋ ከነበሩት ወንዶች መካከል እንዱ አብረው እንዲደንሱ ጠየቃት። ሆኖም የእርሱን ጥያቄ ረበታ እርሰዋ ሌላ ጥያቄ ጠየቀችው። ሰውዬው ኮሎኔል ኸንት ይባላል።

«ኮሎኔል ኸንት፣ ከእዚያ ጥግ ከመጋረጃው አጠገብ የቆመውን ሰው ታውቀዋለህ?» ብላ ስትጠይቀው «አዎን አውቀዋለሁ፣ ሰር ልዮኔል ራይዳል ይባላል» ብሎ መለሰላት ኮሎኔል ኸንት። ምክንያቱ ሳይታወቃት የለሙዬው ሰም እንደ ሙዚቃ ጣፈጣት። ያ ስም ነበር ልብዋንና ነፍስዋን ግራ በሚያጋባ መልኩ መላ ሰውነትዋን የሚወር ስሜት የፈጠረባት።

«ሰር ልዮኔል ራይዳል አልከኝ! ለመሆኑ የት ነው የሚኖረው?» ስትል ስትጠይቀው «ደንዎልድ ከሚባል ሥፍራ የሚኖር ይመስለኛል» ሲል በቸልታ መለሰላት።

«ደንዎልድ! እሰ ደግሞ የት ነው የሚኘው?»

«በትክክል እንኳን አላውቀውም፣ ግን ኪንት ክፍለ-ግዛት ውስጥ የሚገኝ መንደር ይመስለኛል።»

«ታዲያ ሰውዬው ከዚህ ምን ይሠራል?» ብላ ስትጠይቀው ጥያቄዋ አስገርሞት ቀና ብሎ ተመለከታት። ያገሩ ወንድ ሁሉ የሚንበረከክላትና 'የዘመኑ ውብዋ ንግሥት' እያለ የሚጠራት ቆንጆ እስከዚህም ገናው ባለገነና ከገጠር አካባቢ በመጣ ግለሰብ መማረክዋ እጅግ አስገረመው።

Scan by Easy Scanner

«አይ ሰውዬው እኮ እስከዚህም በአገሩ የታወቀና ሰሙ የገነነ በሙ አይደለም» ሲል እጅግ በማንቋሸሽ ከመለሰላት በኋላ ገጠር ሙሳ እንደሚኖርና የግሉ የሆነ ሰፊ እርሻ እንዳለው ነገራት።

ወጣትዋ ቆንጆ «ትዳር አለው?» ስትል ጠየቀችው አነጋገሯና ድምፅዋ በመንገት ስሜት መዋጡን ለራስዋም እየታወቃት።

«አልፎ አልፎ ቢራ ከምጠጣበት ክበብ፣ ሙስጥ ከመግናኘታችን ሌላ እስከዚህም ብዙ አንተዋወቅም። ትዳር ይኑረው አይኑረው የሰማሁት ነገር የለም» በማለት መልሰላት ኮሎኔሉ ስለራሱ ማውራት ጀመረ። የሊንቋ አመቤት ግን ስለራሱ የሚያወራው ወሬ ብዙም አልጣማትም።

«ኮሎኔል፣ ከጓደኛህ ጋር አስተዋውቀኝ» በማለት ቪቫን በድፍረት ስትጠ ይቀው «ምነዋ፣ ፍላጎትሽ እንደ ሕግ የከረረ ሆነብኝሳ!» ሲል በሚሽሚጠቀ መለሰላት። ሆኖም ግን ኮሎኔሉ ሳያመነታ በቀጥታ ሰር ልዮኔል ወዳለበት ሄዶ ትከሻውን ነካካው።

«እንግሊዝ አገር ውስጥ ለቁንጅናዋ ወደር የማይገኝላት ቆንጆ ቤት ከእንተ ጋር ለመተዋወቅ ትፈልጋለች» ሲለው «ኩራት ኩራት አለኝ» ሲል ሰር ልዮኔል መለሰለት እየሳቁ። ቀጥሎም «የሊንዋን አመቤት ማለትህ ነው? ብዙ ሰው ስለቁንጅናዋ ሲያወራ ሰምቻለሁ። አንዳንዶቹማ ዘፍኙ እንደሚለው 'ከአርሰዋ ጋር አንድ ቀን አድሬ በማግስቱ በሞትኩ' ይላሉ መሰለኝ» በማለት እንዲ ቀልድ አድርጎ ተናገረ።

«ለአንተ መቼም ትልቅ ክብር ነው» አለ ኮሎኔል ሽንት የሀዘን ሰሜት እየተሰማው። «የአንተን እድል ለማግኘት ያላቸውን ሀብት በሙሉ መስዋዕት ቢያደርጉ ቅር የማይላቸው ብዙ ሰዎች ከዚህ ቤት ውስጥ እንዳሉ አውቃለሁ። ገና ስታይህ ስላንተ ማንነት ለማወቅ ብዙ ጥያቄዎችን ነው የጠየቀችኝ።»

«ጥሩ ጥሩ ነገር እንደ ነገርካት ተሰፋ አደርጋለሁ» ብሎ ሰር ልዮኔል በተናገረ ጊዜ «የማይሆን ነገር ብንግራት 'ልተዋወቀው' ብላ ሰው የምትልክ ይመስልሃል?» ሲል ኮሎኔሉ በቱራው በአንክሮ ጠየቀው። «ስላንተ መልካምነትና ደግነት ከግማሽ ሰዓት በላይ ማውራት ነበረብኝ። ከዚያ በኋላ ነው 'አስተዋውቀኝ' ብላ የጠየቀችኝ» ሲለው ሰር ልዮኔል ራይጸል አስከዚህም ሰሜት አልሰጠውም።

«ብዙም ሳንቆይ 'ባለሙለታዬ ነህ' ብለህ ታመስግነኛለህ» አለ ኮሎኔል ሽንት እንደ መግረር ብሎ። ሰር ልዮኔል ወዲያው ፈጥኖ «ኤሳት እንኳን አይበግረኝም» አለ አሁንም እየሳቁ። ሆኖም በእነዚያ ትላልት ዓይኖችዋ ትኩር ብላ በታየው ማንቫውም ወንድ በቆንጆ ሴት አይታ በቅላሉ እንደሚፈታ ሁሉ እርሱም ስሜቱን ሰመግታት ስላልቻለ ምንም ሳይታወቀው በተላሉ እጁን ሰጠ።

በተራው ቂና ብሎ ቆንጆዋን ሴት አተኩሮ ባያት ጊዜ የእርሱም ልብ እንደ እርስዋው ከሁለት ተከፈለ። የልቡ ጎመታት ቅሉ ቶሎ በል ያሉት ይመስል በጣም ፈጥኖ ድው ድው ይል ጀመር። እርሱም በተራው እንደ እርስዋው ከቱጥጥር የሚያደርግ አንድ ዓይነት ስሜት ወረረው።

«ምንድነው ጉዱ? ምን ነክህ? ምን ሆንክ?» ተብሎ ቢጠየቅ «እኔ እንጃ» ብሎ ከመመለስ ሴላ ለማስረዳት አይችልም። ነገር ግን «ብቻ... አለ አይደል፣ አንዲያው ዝም ብሎ ቁንጅት፣ ጥብብ የሚያሰኝ ነገር! ሰዎች ፍቅር ወይም የፍቶተ-ሥጋ አምሮት ብለው የሚጠሩት በሽታ ይሆናላ!» ብሎ ሊመልስ ይችል ይሆናል። ታዲያ ለእርሱ እኮ ፍቅር እንግዳ ወይም አዲስ ነገር አይደለም። እርሱኑቱን የሆነ ነገር ሲያርበተብተው በእነዚያ ልብን ከሁለት በሚሰነጥቁና በሚቅበዘበዙ እንከብል ዓይኖችዋ አሁንም ሳቅ እያለች አፍጥጣ ስታየው እርሱኑቱን አፈር ድሜ አስጋጠችው። ይህን ጊዜ ነው «እንዴት ያለች ቆንጆ ናት! ደም ግባትዋ ደግሞ ውሃ የሚያደርግ አይደለም እንዴ?» ሲል ራሱን የጠየቀው።

ከነበረችበት ሄዶ ሲተዋወቃት ኮሎኔል ሽንት የሆነ ነገር እንዳሳት አስተዋለ። እርሱም ለመስማት በሚያዳግት ድምፅ ዝግ ብሎ አናገራት። ከዚያ በኋላ ኮሎኔሉ እጅ ነስቱ ከአጠገባቸው ሾር አለ። ሁለቱ ብቻቸውን ሲቱሩ ለጥቂት ደቂቃዎች በመፋጠጥ ዝም ዝም ተባባሉ። በተለይ ቆንጆዲትዋ አመቤት ቃል ሳትተነፍስ ዓይን ዓይኑን እያየች ዝም ብላ አፈጠጠችበት። በሕይወትዋ ለመጀመሪያ ጊዜ የምትለውን አጥታ ፈዘዘች።

በመጨረሻ ግን «እንዴት ነው፣ ዓይን አውጣ ሴት ትወደለህ?» ስትል ጠየቀችው። ቀጥላም «ምን ዓይነትዋ ዓይን አውጣና ደፋር ሴት ናት እንደምትለኝ አልጠራጠርም። ብትልም የተሳሳትክ አይመስለኝም። ዓይን አውጣ ሴት ባልሆን ኖሮ 'አስተዋውቀኝ' ብዬ ኮሎኔል ሽንትን አልክብህም ነበር» ስትለው «ደስ የሚል ዓይን አውጣነት ነው» አላት።

Scan by Easy Scanner

«ሆነም ቀረም ዓይን አውጣ ሴት ትወዳለህ?» ስትል በድጋሚ በጠየቀችው ጊዜ «የዚህ ዓይነትዋን ዓይን አውጣ ሴት ከአሁን ቀደም አጋጥማኝ እንደሆነ ማስላሰል ይኖርብኛል። ብቻ እኔም ራሴ ዓይን አውጣ ስለሆንኩ 'ዓይን አውጣ ሴት እወዳለሁ' ብዬ ከመለስኩ ራሰ-ወዳድ ሊያሰኝ ነው። ብቻ.....ለማንኛውም ይህን ያመጣሽውን አሳብ እንርሳውና አሁን የምንሰማው ሙዚቃ እጅግ አድርጌ የምወድደው ዓይነት ሙዚቃ ስለሆነ 'አብረን እንደንስ' ብዬ ብጠይቅሽ ግብጥቦን ትቀበያለሽ?» አሳዛኙ ታሪክ የተጀመረው በዚህ ዓይነት ነበር።

ምዕራፍ አሥራ ስድስት

እጣ ክፍላቸው ይሆን?

ከግማሽ ሰዓት በኋላ አሁንም እንደ ተጣበቁ ናቸው። አሁን ግን ከነበሩበት ክፍል ወጥተው ከቋቋቴ አጠገብ ነው የቆሙት። ቋቋቴው ውሃ ወደ ሰማይ ስለሚረጭ ከቋቋቴው የሚረጨው ውሃ ገላቸውን አራሰው፣ ግን አልተሰማቸውም። የነበሩበት አካባቢ በአበባ ያጌጠ ስለነበር መዓዛው ያውዳል። አቋቋማቸውና የግቢው ማማር አንደ ሙዚቃና እንደ ውበት ስሜት የሚነካ ዓይነት ስለነበር የማሰብ ችሎታቸውን ጋረደባቸው። ለዚህም ነበር እንደዚያ ከክፍሉ ሲጠፉና ተቃቅፈው ሲወጡ 'ሰጪ ምን ይለናል' ብለው ለማሰብ ያልቻሉት።

«ቀደም ሲል ከነበርክበት ግድግዳ አጠገብ ለምን ያህል ጊዜ ነው ቆመህ የነበረው?» ብላ ስትጠይቀው «ብዙ አልቆየሁም» ሲል መለሰላት።

«ባጋጣሚና በእጣ ፈንታ ታምናለህ?» ብላ ስትጠይቀው «አንዳንዴ» አላት። ለረጅም ጊዜ እፈልገው የነበረውን ነገር አሁን አገኘሁት በሚል አመለካከት እርሱን ትኩር ብላ ማየቱን ቀጠለችበት። አይታዋ ኃይለኛ ስለነበረ ልቡን ሰለበው።

«ወደ ግብጥው ቦታ ስመጣ» አለች፣ «ያለውዴታዬ ሠራተኞቼ አሁን ያጌጥኩባቸውን ጌጣጌጦች እንዳደርግ ለመነችኝ። እኔ ለማድረግ የፈለግሁት ሌላ ጌጥ ነበር። የአንገት ጌጤ ላጠልቀው ስል ከእጄ ተፈትልኮ ስለወደቀ ከላዩ ላይ የነበሩትና ከከበሩ ድንጋይ የተሠሩ ፈርጦች ተሰበሩ። በዚህ ጊዜ ሠራተኞቼ በአጉል እምነት የተጠመዱች በመሆንዋ አሟረተችብኝ። 'ውይ' ብላ ከፎኸች በኋላ 'እሜቴ ይኼ የመጥፎ አጋጣሚ ምልክት ስለሆነ ከግብጥው ቦታ ባይሄዱ ይሻላል' ስትል ሙነረችኝ። እኔ ታዲያ ሳትሀብት እንጂ ምክርዋን አልተተበልኩትም። እኔ የምፈልገው 'ከፈተድኩበት ቦታ መሄድና ልቤ የፈቀደውን ማድረግ ነው፣ ምን ይመጣ ብለሽ ነው ብዬ አፈገዛኩባት። ስለዚህ በአልማዝ ያሸበረቀው ሌላውን ጌጥ አምጥታ እንድታደርግልኝ አዘዝኳት። አሁንም ጌጡን ጠበት አድርጋ ሰታስተካክልኝ ከላዩ ላይ አንድ ነገር ተሸረፈ። በዚህ ጊዜ እኔ ክት ብዬ ሳቅሁ እንጂ አልተናደድኩም። ሠራተኞቼ አሁንም ድምፅዋን ከፍ አድርጋ 'አረ ተዉ አይሆንም፣ ዛሬ እኔ አላማረችም። እመቤቴ የመጥፎ አጋጣሚ ምልክት ስለሆነ ከግብጥው ቦታ ባይሄዱ ይሻላል'» ስትል ነገርዋን አጥብቃ ለመነችኝ። እኔ ግን አሁንም አልሰማኋትም። ከክፍሌ ወጥቼ ደረጃ ስወርድ ከባለቤቴ ጋር ተገናኘን። እርሱ ብቅ ሲል እኔ ቦግ ያለ መብራት ከነበረበት ደርሼ ስለነበር የመብራቱ ጨረር ካጠለኩት አልማዝ ላይ በማረፉ በጣም ተንጸባረቀ። ባለቤቴ ያንን አንጸባራቂ መብራት ሲያዩ ሳቅ አሉ።

«'እንደ ፀሐይ ነው የምታበሪው፣ አምሮብሻል። ገላሽ ላይ የበራው ብርሃን መልካም አድል ይዞልሽ ይመጣል' ሲሉ ተናገሩ። እኛ አሁን ከሁለቱ ትንቢት የማንኛቸው የተፈጸመ ይመስልሃል?»

«የባለቤትሽ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ» አላት። ክፉ ነገር ይደርሳል ብዬ ለማሰብ አልፈልግም፣ ማለቴ ሠራተኞሽ እንዳለችው።»

«እኔ እንኳን በእጣ ፈንታ አምናለሁ» አለች የሊንጥ እመቤት። «ከዚህ ግብጥ ቦታ አንድ ነገር እንደሚሆን በልቤ አምኜ ነበር» ስትለው «ታዲያ አሁን የሆነ ወይም የደረሰ ነገር አለ እንዴ?» ሲል ጠየቃት።

«አምን ደርሷል» አለችው ዓይንዋን እየሰበረች። «አምን ሆኖአል፣ ከአንተ ጋር ተገናኝቻለሁ» ባለችው ጊዜ «ምሽቱ ለአንቺ እጅግ የተለየ ምሽት እንደሆነ አድርገሽ ነው የምትናገሪው» አላት።

«ለእንተስ?» ብላ ጠይቃው በለመደችው የማንኛውንም ወንድ ልብ በሚያሸፍት ዓይን አየችው። እይታዋ ልብዋ እንደተማረከለት በጉልህ አሳየው። ምን ብሎ እንደሚመልስላት ግራ ተጋባ። ጥቂት ቆይቶ ግን «ለእኔም የተለየ ምሽት እንደሆነ አውቃለሁ» አላት እያተደናበረ።

ለምን እንደዚያ አጥብቃ እንደ ጠየቀችው ለማወቅ ፈልጎ ሊጠይቅ ያሰበውን ከምላሱ ጫፍ አድርሶ መለሰው። ስር ልዮኔል በመሠረቱ ክፉ

Scan by Easy Scanner

ሰው አይደለም። ሙቾስ የማንኛውም ሰው ሙሉ ሙሉ ሙሉ

እያንዳንዱ የደም ሰርም በደስታ የፈካና የደንደነ መሰለው። ስለዚህ የተጣ ናውቱውን መንፈስና ሊቃ ከስውነቱ ስጥ ለማስወጣት የሚችል መስሌት ሚንቅላቱን በኃይል ነቀነቀው። ነገር ግን የሆነ አፍዝ አደንግዝ አስታቅፋው ስለሄደች ሊያስወጣው አልቻለም። ከጠራ ሰማይ ላይ የሚብለጨለሪቤና የሚንጸባርቁ ከዋክብትን ቀና ብሎ ባየ ጊዜ እነዚያ የተዋቡ ዓይኖችዋን አስታወሱት።

«አይ ውበት፣ አይ አፈጣጠር! እንከን የማይወጣለት ገላ! የእግልኒት ከንፈር ወይስ የሰው! ታዲያ ይህቺ ሁሉንም አሚልቶ የሰጣት ሴት ምን እንደዚያ አፍነከነካት? ምነው ተቅበጠበጠችሳ!።» ከሰር ልዮኔል ሚንቅላት ውስጥ የሚሳወስ አሳብ ነበር።

የት እንደሚኖር ስትጠይቀው መኖሪያው አፖርተማ ውስጥ እንደሆነ ነገራት። በዚህም ወንዱላጤ እንደሆነ ገመተች። «አፖርትማ ውስጥ መኖር አይደብርም?» ብላ ስትጠይቀውም እንደማይደብርና ቁጥራቸው በዛ ያለ ወንዶች እንደሚደሱቱበት ሲነግራት እየተመላለሰ እንዲጠይቃትና ከቤ ትዋም እንዲመጣ ጋበዘችው። ከቤትዋ መጥቶ እንዲጠይቃት የጋበዘችው ቪላ ቤት ውስጥ መኖር ምን ያህል እንደሚጥም ለማሳየት ነበር።

«በቋሚነት የምትኖረው ግን ደንዎልድ ከተባለ ሥፍራ ነው፤ አይደል?» ብላ ጠየቀችው አብረው ቁጭ ብለው እያወጉ ሳለ። ቀጥላም «እንዴት ያለ ደስ የሚል ስም ነው!» ስትል አሞካሸችው። ሰር ልዮኔል ድንዎልድ ከሚገኘው ቤቱ ውስጥ ቆንጆ ሚስትና ውብ የሆኑ ልጆች እንዳሉት መንገር እንደነበረበት አልመላለትም። ቪቫንም ማጣፊያው እስካጠራት ድረስ ይህንን አሳወቀችም።

«የደንዎልዱ ሰር ልዮኔል ራይዳል!» አለች ስሙን በድጋሜ በመጥራት። «እስከ ዛሬ ከሰማኋቸው ስሞች ሁሉ ከእንቲ ስም ይበልጥ የጣፈጠኝ ስም የለም» ስትል በድጋሚ አሞካሸችው። ከዚያም ከቪቫን ጋር ከተለያዩ በኋላ ሰር ልዮኔል ከአፖርተማው ገብቶ በእለቱ ያጋጠመውን ሁሉ ብቻውን ሆኖ ስማሰሳል ቸኩለ። ቢሆንም ከአፖርተማው እንደ ደረሰ በእለቱ ያጋጠመውን አያሰላሰለ ለሚስቱ የሚልከው ረጅም ደብዳቤ ጻፈ። ደብዳቤውን ጽፎ እንደ ጨረሰ የመንፈስ ደስታ እየተሰማው ተኛ። ሌሊቱንም በጥሩ እንቅልፍ አሳለፈ። የሊንዋ እመቤት ግን ወደ ቤትዋ ሂዳ ሌሊቱን በሙሉ ያለሰፈችው በእንቅልፍ ሳይሆን በትገቦት ነበር። የትገቦትዋ ይዘት የሚጣጥዋ ቢሆንም በውስጡ ግን የኃጥያት መገለጫ ነበር የሚያሰኝ ቅጥ

ያጣ ምሥጢር ነበረበት። ባልዋን አቅፋ ተኝታ የታገቸውና በአሳብ አያየች ያደረችው የሌላ ወንድ ገላ ነበር። ወንድ አቅፎ ሌላውን ወንድ ማለም!

ሴቶች በቀላሉ ራሳቸውን የማታለል ኃይል አሳቸው። ቢሆንም እንዲት ሴት የሰው ሚስት ሆና ሳለ በሌላ ወንድ ለመደሰትና ራስዋን አሳልፋ ለመስጠት መዘጋጀት ወይም ስለሌላ ወንድ ማሰብና መጨነቅ ማለት እንቆቅልሽ እንጂ የጤና አይደለም። ሰር ልዮኔልን በሕልሟ አየችው፡ ድምፁንም ሰማች። ማር ማር የሚል ሕልም ነበር ለእርስዋ። ከእንቅልፍዋ ስትነቃ በመኝታ ሰዓትዋም ስላልተሰያት እጅግ ደስ አላት። 'ያ ቀን እንድወድምበት የመጣ መጥፎ አጋጣሚ ነው ወይስ እንድደስትበት ፈጣሪ አስተካክሎ የቀየሰው መልካም አጋጣሚ ነውን' ስትል ደግማና ደጋግማ ራስዋን ጠየቀች። መልሱን ለማግኘት ግን ከአትሟ በላይ ሆነባት።

ምዕራፍ አሥራ ሰባት

ከተንገርረገገ የጽጌረዳ አበባ መሃል

የሊኑ መስፍን ከቆንጆዋና ከወጣትዋ ሚስታቸው ጋር ቁርስ ለመብላት ገበታ በቀረቡ ጊዜ ወትሮ አይተውት የማያውቁ አንጸባራቂ ገጽታ ከባለቤታቸው ፊት ላይ አዩ። ፊትዋ እንደ ማታ ጀምበር ፈክቷል። የዓይንዋ ብሌን ተጎልቶሎ ወጥቷል። ፊትዋ ከውስጥ በመነጪ ፈገግታ ተውቧል። ባልዋ ምክንያቱ ባይገባቸውም ውበትዋ በይበልጥ እንዲጎላ ያደረገው አንድ ነገር ለመኖሩ አልተጠራጠሩም። ቁርስ የቀረበው ከመናፈሻ ሥፍራ ስለነበር ተግራ ተቁኝ የጽጌረዳ አበባዎች ተንገርግገዋል። ግን እርስዋ እንደ ወትሮዋ ቀና ደፋ፣ ዞር ዞር እያለች አበባዎቹን አላየችም። እርስዋ ባአሳብ ታየው የነበረው ባለፈው ምሽት ያየችውና የተመለከተችው ማራኪ ፊት፣ ያማረና የሸነቀጠ ሰውነት ነበር።

«ቪቫን» አሉ ባልዋ፣ «ደስ ያለሽ ትመስያለሽ። ለመሆኑ በአሳብ የምታዪው ነገር አለ እንዴ?» ብለው ሲጠይቋት «አዎን» አለች በድፍረት። «ትናንትና ሂጀበት ከነበረው ግብግ ቦታ የነበረው ጨዋታ እጅግ ስላስደሰተኝ ያንን ነበር የማሰላስለው» አለቻቸው።

«የዳንስ ጨዋታ እንዴት እንደማትጠግቢና እንደማይሰለችሽ ይገርመኛል። እኔን ግን ይህን ያህልም አያነሳሳኝም» ሲሉ ስሜታቸውን

Scan by Easy Scanner

ሲገልጹላት «በእኔ እድሜ በነበሩበት ጊዜ እንኳን ሳያስደስቱት የቀረ አይመስለኝም» ስትል መለሰችላቸው። መስፍኑ አድሚያቸው መግፋቷን የሚያስታውሳቸው ነገር ሲሰሙ ይናደዱ ስለነበር ፊታቸው ከመትጸበቅ ተለዋወጠ።

«ለምንድነው የትናትናው ምሽት በጣም ያስደሰተሽ?» በማለት ትናት እያንገበገባቸው ሲጠይቅዋት «ጨዋታ የሚያውቁ ብዙ ሰዎች ስለነበሩ ነው» አለቻቸው። መስፍኑ ቀጥለው «እነርሱ እንማን ናቸውና?» ብለው ሲጠይቋት ትናቱ እንዳንገበገባቸው ሌላ ምስክር ሳያስፈልግ ፊታቸው መለከረ።

«ከግብጣው ቦታ እንማን እንደ ነበሩ ለማወቅ ስማቸውን ጋዜጣ ላይ ያዩታል። ከመጡት ሰዎች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት እኔ የማላውቃቸው ናቸው። የማውቃቸውን ስም ልጥራ ብልም ከፊሉን እንኳን ለማስታወስ አልችልም። ለመሆኑ ዛሬም ከእመቤት ቤሪ ግብጣ አይሄዱም?» ብላ ስትጠይቃቸው «አይመስለኝም፣ ግብጣው ከመናፈሻ ውስጥ ስለሆነ ሊሰለቻኝ ይችላል» ኢልዋት። «እንቺም እትሄጂም» የሚልዋት ስለመሰላት በድንጋጤ ቀና ብላ አየቻቸው።

«ምነው፣ ደስ ያላልዎት ይመስላሉ።»

«ከመቼ ወዲህ ነው ከግብጣ ቦታ አልሄድም ማለት መከፋት የሆነው? ከፈለግሽ አንቺ እንደ ትናንቱ ብቻሽን መሄድ ትቺያለሽ። እኔ ግን ይቅርታ አድርጊልኝና አልሄድም» ሲልዋት ልብዋ ተንፈስ ብሎ ደስታ ውስጥ ውስጡን እንክት አደረጋት።

ብቻዋን ልትሄድ! ነፃነት በገፍ! ያቺ ቀን የምታልፍ አልመሰላትም። ደቂቃው ሰዓት፣ ሰዓቱ ቀን፣ ቀኑ ዓመት ሆኑባት። በአምልኮትና በሚርት የምታምነዋ አልባሽዋ እመቤትዋ በአለቱ ምን እንደ ገጠማት አላወቀችም። አንድ ነገር እንደሆነ ግን ጠርጥራለች።

«በጣም ቆንጆ ሁኚ ለመታየት ስለምፈልግ ጥሩ አድርገሽ አሰማምሪኝ» ስትላት «እመቤቴ ከዚህ የቀለለ ምን ነገር አለ? እርስዎ እኔ የምሉትን ብቻ ይስሙ» ስትል መለሰችላት።

ሰማያዊ ቀለም ያለው የሐር ቀሚስና ከልብሱ ጋር የሚሄድ ባርኔጣ መረጠችላት። የሊንዋ ልዕልት ተኳኩላ ስትጨርስ ስአል እንጂ ሥጋ የለበሰች ሴት አትመስልም ነበር። ፊትዋ በደስታ ፈክቶ እንደ ጠዋት ፀሐይ አበራ፣ እንደ ፈንዲሻም ፈንድቶ ፍልቅልቅ አለ። መስፍንን ለመሰናበት እርሳቸው ወደ ነበሩበት ክፍል ሄደች። ሳንበሀ ብላ በእነብሮት እጅ ነሳቻቸው እንጂ ጉንጫቸውን ለመሳም አልተጠጋቻቸውም። ሰውዬው እንደዚያ አምሮባት ሲያዩ ሙስጣቸው ቅናት ቢያንገበግበውም የእርሳቸው በመሆንዋ ደስ አሳቸው።

«በጣም አምሮብሻል» ካሉ በኋላ «አብራሽ ብሄድ ማን ደስ ይለኝ ነበር» ሲልዋት አጢዋ ዱብ አለ። አብረዋት ከሄዱ ያ በአሳብ ያየችው ደስታ ሁሉ አፈር ድሜ ሊግዋ ነው። አብረዋት ከሄዱ ከሰር ሰራቸው እየሄደች ከባልዋ ጓደኞች ጋር ማውራት ይኖርባታል እንጂ እንደ ተመኘችውና እንደ ፈለገችው መዝናናት አትችልም። በሁለቱ መካከል ለተወሰነ ጊዜ ጸጥታ በሰፈነ ጊዜ እብደትዋ በመጠኑም ቢሆን መለስ ሰላለሳት «መደረግም ያለበት ይኸው ነው እንጂ እስከዚህም ከሌላ ወንድ ጋር ለማበድ ልቤ መሰቀል የለበትም» አለች ለራስዋ ቀሚስዋን እያስተካከለች።

«ቢሆንም ባልሄድ ይሻላል» በማለት መስፍኑ ጥቂት ቆየት ብለው ሲናገሩ «ለትንሽ አመለጥኩ» አለች አሁንም አርስ በራስዋ በትንጋር። «አብረውኝ ቢሄዱ ኖሮ ዛሬ ጉድ ሆኜ ነበር።»

ከቤትዋ ከወጣች ከአንድ ሰዓት በኋላ የተንገርገጣ የጽጌረዳ አበባ ከምላበትና ከሚያምረው የአትክልት ሥፍራ ውስጥ ከሰር ልዮኔል ጋር እያወራች ነበር። ሰር ልዮኔልን ለመናፈቅዋ መላ ግጽታዋ አሳማች። የፀሐይ ብርሃን ወለል ብሎ ቢወጣም ብዙ ስለማያቃጥል ጥላ ካለበት ሂዱ እያሰኝም። ሰር ልዮኔል ዞር ዞር እያለ ሲያይ ወንዶች ሁሉ ቀስ እያሉ ከቪቫን መራቃቸውን ተገንዘበ። ከመናፈሻው ውስጥ ወደ አንድ ጥግ በመሄዳቸውና ስዉም እየራቃቸው ስለሄደ ሁለቱ ብቻቸውን ቀሩ። ከተለያዩ አበባዎች የሚወጣው መዓዛ አካባቢውን አውዶታል።

«በመምጣትህ በጣም ነው ደስ ያለኝ» አለችው በጣም በሚጣፍጥ አንደበት። ዝግ ብላ ነው የምትናገረው። «በዚያ በኩል እድርገን ሄደን አውን ካለንበት ዞር እንበል እስቲ! ሉርድ ሴቭር ወደ እኛ እየመጣ ነው መለለኝ፣ ከእርሱ ጋር መጫወት ብዙም አይጥመኝም።»

ከነበሩበት ተነስተው የጽጌረዳ አበባ በብዛት ካለበት እስኪደርሱ እጅ ለእጅ ተያይዘው መንገዳቸውን ቀጠሉ። ጥቂት እንደ ተራመዱ የድንጋይ መቀመጫ ካለበት ደረሱ። መቀመጫው ሆን ተብሎ ያዘጋጁት ይመስል

ተግራ ተቀኝ በተንገርገባ አበባ የታጠረ ነው። ወደ ጓሳ፣ ወደ ግራና ወደ ቀኝ ፈት ቢያሁሩ የሚታየው የጽጌረዳ ባፍ የፈነዳ አበባና እምቡጥ ብቻ ነው። ቪቫን ከመንግሥተ-ሰማይ ውስጥ የገባች መሰላት።

«ይህ ቦታ የገጣሚው የመር ሰንሾችን አስታወሰኝ» በማለት ሰር ልዮኔል ሲናገር በዓትር በተሞላው ዓይንዋ ቀና ብላ እየችው። «ግጥም ከምታስማን በለራስህ ሕይወት እጂውተኝ» አለችው።

«ደስ የማይለኝ ርእስ» ካለ በኋላ ሰር ልዮኔል ከት ብሎ ሳቀ። «አንቺን ደስ ካሰኘሽ ግን...» ብሎ አሳቡን ሳይጨርስ «እኔ ግን እጅግ በጣም ደስ ይለኛል» ስትል ጣልታ ገባችበት። «ስለሚያስደስቡህ፣ ስለምታፈቅራቸውና ስለምትጠላቸው ነገሮች ሁሉ እጂውተኝ። ልብህ ውስጥ ለመጻጅና ሳፍታሪ ከናት ቦታ ካለም ለማወት እፈልጋለሁ። ታውታለህ፣ ግና ሳይህ ልቢ ከሁለት ትርትር ስላለብኝ 'ይህን ሰው ዓያኛ ማድረግ አለብኝ' ብዬ ስራሲ ታል ገባው። አደራሳቱ ግን ስህተት ሲሆን ይችላል።»

«ነው እንዴ!» ብሎ ቢናገርም አነጋገርዋ የሰር ልዮኔልን ስሜት በመነካቱ «ስለመልካሙ አላብሽና ምኞትሽ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ» አላት።

«እንደምታየው ከእሴ ጋር ለመተዋወቅና ለመጫወት የሚፈልግ ወንያ ቁጥር እጅግ ብዙ ሰለሆነ እሰከ ዛሬ ከብዙ ሰው ጋር ተዋውቂያለሁ። ነገር ግን አላዳጊዬ ሻለታ ከሞተ በኋላ ከተዋወቅኋቸውም ሆነ ከእሴ ጋር ለመተዋወቅ ከሚፈልጉ ሰዎች መካከል ግንም እውነተኛ ወዳጅ ሊሆን የሚችልና ልቢ የተማረከለት ሰው አላጋጠመኝም። ሁሉም የራሱን ጥቅም ፈላጊ ብቻ ነው።»

«ባለቢትሽ እውነተኛ ወዳጅሽ መሆን አለበት» ለማለት ፈልጎ ባልዋ የተሸመደመደ ሽማግሌ መሆናቸውን ስላስታወሰ አሳቡን መልሶ ዋጠው። «ምን ዓይነት የማይጣጣሙ ባልና ሚስት ናቸው ሲል ግን አሰላሰለ።

«ሁሉም ሰው በግሉ የብቸኝነት ስሜት የሚያጠቃው ይመስለኛል። የሚገርመው ግን የእኔ የብቸኝነት ስሜት የሚያገረሽው ብዙ ሰው ካለበት ስፍባ ነው። የልቢን ዘክገቢ የማጫውተው ሰው ቢያጋጥመኝ እያልኩ ዘወትር እመኝ ነበር። የእኔ ችልቱ ችግር ብቸኝነት ነው» ስትለው «'ያለያ ጋብቻ' ውጪት ነው» ብሎ በማሰላሰል ሰር ልዮኔል ለሴትዮዋ እጅግ በጣም አዘነላት። ሀዘኑን በዓይን ከማሳየት ሌላ ምንም ስላልተናገረ አርስዋ ንግግርዋን ተጠለች።

«ስለመልካም ጓደኛሞች ባነበብኩ ቁጥር 'እኔም መልካም ጓደኛ ያስፈልገኛል' እያልኩ እመኝ ነበር። እና አንተን ግና ሳይህ ያ የምፈልገው ጓደኛ መሰልከኝ። በውሰጤ አንድ ዓይነት ስሜትም ቀሰግኝ። ያ ስሜት መላ ሰውነቴን ወረረው። የሆነ ድምፅ ልቢን ሰንጥቆ ገብቶ 'ይህን ሰው ነው የፈለግሽውን' ብሎ የጠየቀኝም መሰለኝ። የምሰውን ሁሉ በትሰማ እንግዳ ነገር ሲሆንብህ ይችላል። እንግዳነቱ እንኳን ለአንተ፣ ለእኔም ሙምር ነው። አይገርምምን? እንዲያው ዝም ነው እንጂ ምን ይባላል»

«የተለየ ስበት ያላቸውና አርስ በአርስ የሚሳሳቡ ፍጡሮች እንዳሉ ይታመናል። ያ ደግሞ ድንገት የሚያጋጥም እንጂ ፈልገው የሚያገኙት አይደለም» ሲላት «ስለዚህ አንተንም በድንገት ነዋ ያገኘሁህ» ብላ ሰት ጠይቀው ቀና ብሎ በአድናቆት ተመለከታት። ሴትዮዋን የተዋወቃት ገና ትናንትና ቢሆንም አጅግ አድርጋ እንደ ወደደችው ገባው።

«ክትናንት በስቲያ የማያውቁት ፍጡር ዛሬ አሰክዚህ ሊያሳብድ ይችላል?» ብላ ስትጠይቀውም «መሆኑ ነዋ» ሲል መለሰላት። አውንም ፊትዋ ከወትሮው ይበልጥ እጅግ ፈክቶ እንደ ንጋት ኮከብ አበራ። ሰው እጅግ አድርጎ ሲደሰት ደስታው ፊቱ ላይ መታየቱ እውነት ነው።

«በጣም ነው ደስ ያለኝ» አለች በዝግታ። «እና ለእውነተኛ ወዳጅና አፍቃሪ ከልብሀ ውስጥ ጥቂት ሥፍራ ይኖራል?»

ለጥያቄዋ መልስ እንዲሆነው ነፃ ሰው አለመሆኑን ማለት ሚስትና ልጆች እንዳሉት ሊገልጽላት ብሎ ግና አፉን ለመክፈት እንደሞከረ የሆነ ነገር ምላሱን አንቆ ያዘበት። ስለዚህ ሊለው የፈለገውን አሳብ መልሶ ዋጠው። ግርማ ሞገስዋ፣ ውሃ የሚያደርግ እይታዋ፣ የድምፅዋ ልስላሴ፣ ጠቅላላ ቁንጅናዋና ሁናቴዋ ነበሩ አሳቡን የሰስበበት። ዳግም የሚስቱና የልጆቹ ጉዳይ ከምላሱ ጫፍ ሳይደርሱ ከሆዱ ውስጥ እንደ ተቀበሩ ቀሩ። የእርስዋ አፍዝ አደንግዝ ዓይን ሁሉንም ነገር ሽፍኖ ስላጪለመበትና አፉን ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰብ ምጥቀቱንም ጨምሮ ስለሰለበበት አጠገቡ ከቆመች ሴት አሳብ ሌላ ሁሉም ነገር ከህሊናው ተሰወረ። የህሊና መታወር ይሉሃል ይኼ ነው።

በመጨረሻ «ከልቢ ውስጥ ጥቂት ባዶ ቦታ ሊኖር ይችላል» ሲል እርስዋ የተናገረችውን ከደገመ በኋላ «ይህን ያህል ከመወደድ ይበልጥ ፈጣሪዬን ሌላ ምን እንዲስጠኝ አለምነዋለሁ» በማለት ተናገረ። ቪቫንም እጅግ

Scan by Easy Scanner

በጣም የጥሀ ሴት ስለነበረችና በብርቱ ስሜት ስለተሞጠች ከወደ ኋላ ሊመጣ የሚችለውን መጥፎ ነገር ሁሉ ለማየት ተሳናት።

«እውነተኛ ዓይኛና ወዳጅ በማግኘቴ እንዴት ነው ደስ ያለኝ» ብላ በመናገር ቪቫን በይበልጥ አሳበሳችው።

«ቪቫን» አላት በመቃከል፣ «እንዴት ብለሽ በአንድ ጊዜ እሰከዚህ ልታምኚኝና ልታቀርቢኝ እንደቻልሽ ብትገልጪልኝ በጣም ደስ ይለኛል፣ ማለቴ ከቻልሽና ፈቃድሽ ከሆነ» ሲላት ቶና ብላ አያየችው የሞቱ ፈገግታ በገፍ አስታቀፈችው።

«ቢሆንልኝማ አነግርህ ነበር። አስካሁን ከነግርኩህ በተጨማሪ ሲላ የማውቀው ነገር የልኝም። ነገሩ እኔንም ግራ አጋብቶኛል። ገና ሳይህ ከልቢ ውስጥ ይምፅ የሰማሁና ደወል የተደወለ ነው የመሰለኝ።»

ጨዋታቸው ቀጥሎ ከአትክልቱ ሥፍራ እየተዘዋወሩ ብዙ ተጫወቱ። ከጽጌረዳ አበባ መካከል ሲያልፉና የጽጌረዳ ሽክ ሲወጋቸው ግን ሁለቱም አልተሰማቸውም።»

ምዕራፍ አሥራ ስምንት

የወዳጅነት ጥንካሬ

ትንሽ ከተማ ውስጥ ወሬ በቀላሉ ይዛመታልና «የሊንዋ እመቤት ምን አገኘች?» ሲል የአካባቢው ሰው ሁሉ እርስ በእርሱ ተጠያየቀ። «በየእለቱ እያማረባት ነው እንዴ የምትሂደው? ትልቅ ለውጥ ነው የሚታይባት። ብዙ አትኩራም፣ ብዙም አትዘባነንም። ቢሆንም እንዲያው ብቻ እንደ መኩራራትም፣ እንደ መዘባነንም ያደርጋትና ወዲያው ደግሞ መለስ ትላለች» እያለ የአካባቢው ሰው ሁሉ ማውራቱን ቀጠለ።

ለማንኛውም በቪቫን ላይ የታየው ለውጥ እውነተኛ ነበር። ልብዋን የሞላው ፍቅር ግንባርዋ ላይ ጎልቶ ከመታየት አልፎ ተንፀባራቂነቱ ገሃድ ወጣ። ያጋጠማት መልካም እድል አመልዋን አለዘበው፣ ግርማ ሞገስዋን አሳደገው። ፍቅርዋ ገና መጀመሩ ቢሆንም እጅግ በጣም ጣፋጭ ሆኖ ነው ያገኘችው። ፍርሃት፣ ፍርሃት የሚላትና ፈራ ተባ የምትልበት ቀን አልደረሰም። ከፍቅርዋ መጣፈጥና ከደስታዋ ብዛት የተነሳ የምትሠራው ሥራ ኃጥያት ለመሆኑ ጨርሶ አልታያትም።

ኑሮን ኖርኩ የሚያሰኝ ተስፋ ድንገት ከቮች ሰላለላት ዘመትር ከእንት ልፍዋ ስትነታ የሚታያት ነገር ቢኖር ሰር ልዮኒልን መቼና የት ነው የሚገኘው የሚለ ሆነ። ከዚያ በፊት የዚያን ዓይነት ስሜት አልነበራትም። ጠዋት ከመኝታዋ ስትነሳ እንደ ወትሮው ማዛጋትዋ ቀርቶ ፊትዋን በፈገግታ ታጠሙበው ጀመር። ሰለእርሱ ማሰላሰሉ ብቻ ደስታ ይሰጣታል። ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ መጻራቱማ ሌላ ነገር ነው የሚያደርጋት። ሺህ ሰው ቢሰበሰብ ለማንም ደንታ ላይኖራት ሁለቱ በተገናኙ ቁጥር ዓይን ለዓይን እየተያዩ ከሰው ርቀው ብቻቸውን መጫወት ከመጠን በላይ ያረካቸዋል። ቱመናው፣ አነጋገሩ፣ አቋቋሙና ፈገግታው ልብዋን ሰለሚሰልበው የእርሱ ትዝታ፣ የእርሱን ዓይን ማየት እንደ ማር ይጣፍጣት ጀመር። አብረው በሚሆኑበት ጊዜ ጋሻ መከታዋ እንደሆነ ይሰማታል። እጅን ትከሻዋ ላይ ሲያሳርፍማ ዓለምን የጨበጠች ይመስላታል። እጅዋን ይዞ ከወዲያ ወዲህ ሲል ደግሞ ሲቃ ይሠአት የምትይዘውንና የምትጨብጠውን ታጣለች።

'ሴትዮዋ ምን ነካት?' ተብሎ ቢጠየቅ 'አያድርስ ነው ወዳጂ' ከማለት ሌላ መልስ ለመስጠት ያስቸግራል። ቪቫን ሰር ልዮኒልን ካገኘች ጀምሮ ሕይወት ጣመቻት። ቀደም ሲል መጠነኛ የሆነ ወይም ጨርሶ ሕይወት ስላልነበራት መንፈስዋ የወደቀ ነበር። አሁን ግን መንፈስዋ ተነሳስቷል፣ ስሜትዋ ነትቷል። አንቀላፍቶ የነበረው ልብዋ ሸፍቷል። ሆኖም አሁንም ቢሆን ሐቀኛ ምክር የሚለግሳት እውነተኛ ወዳጅ ብታገኝ ከእብደትዋ ልትመለስና ከጥፋት ልትድን ትችል ነበር። ሰው ስላልነበራት ያ አልሆነም። ቪቫን በአፈጣጠርዋ መልካም ሴት ስለነበረች ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባትና ለሰው አክብሮት ያላት ሴት ናት። በራስዋ ፈቃድ ከስሀተት ላይ የምትወድቅ ዓይነት ሴት አልነበረችም።

በማንኛውም የፍቅር ታሪክ መጨረሻው የተለያየ ቢሆንም ሲጀምሩት ፍቅር ሁሉ ይጣፍጣል። በቃላት ኃይል ለመግለጽ በሚያዳግት ዓይነት የእርስዋም ፍቅር ከእጅግመሩ እጅግ በጣም የጣፈጠ፣ በጣም የለዘበ፣ የላመና እጅግ በጣም የሚያጓጓ ነበር። አሁን ያጋጠማት ፍቅር ከሻለቃውና ከኖራ ፍቅር እጅግ የላቀና የመጠቀ ዓይነት ሆኖ ነው ያገኘችው።

«ሌላውን ሰው ምን እንደሚያስደስተው ደረስኩበት። ለካስ ሰዎች ደስ ብሎአቸው የሚኖሩት የሚወዱት ሰው ስላላቸው ነው። እኔም አሁን የምወደው ሰው ስላለኝ ደስ ብሎኝ ነው የምኖረው።» አያለች ዘወትር ራስዋን ታጽናናለች። ያም የእለት ተእለት ሕይወትዋና አሳብዋ ሆነ።

Scan by Easy Scanner

ባልዋን ሳይሆን ሌላ ወንድ ማፍቀርዋ አስነዋሪ መሆኑ አልታያትም። ሌላ ሰው ማፍቀርዋ ባልዋን ሊያስከፋ እንደሚችልም በውል አልተከሰተላትም። ከተሳሳተ ጎዳና እየገባሁ ነው የሚለው አመለካከትም ከአእምሮዋ ውስጥ አልገባም። 'ፍቅር እውር ነው' የሚባለው ለዚህ ሳይሆን ይቀራል! የታወሳት ነገር ቢኖር የባልዋ የማይጥም ጨዋታና ፍላጎት ተሸክማ ለረጅም ጊዜ መቀመጥዋ እንደ ውለታ የሚያስቆጥር ስለሆነ 'ደግ ሴት ነኝ' የሚለው አሳብ ብቻ ነበር።

ሁለቱ ፍቅረኞች፤ ከአሁኑ 'ፍቅረኞች' ብለን ልንጠራቸው የምንችል ከሆነ፣ እስካሁን በተገናኙ ቁጥር ስለጓደኝነት ወይም ስለወዳጅነት ያውሩ እንጂ ስለፍቅራቸው አንስተው አያውቁም። 'መቼ እንገናኝ' ብለውም ቀጠሮ አይሰጣጡም። በየጊዜው ግን ሁለቴም የሚገናኙበት ዘዴ ስለሚቀይሱ በየምሽቱ አብረው ናቸው። ከነአካቴው ሳያውቁትና ሳይገነዘቡት ቀስ በቀስ ከአጉል ወጥመድ ውስጥ ገቡ። በአንድ ምሽት ከአንድ ዝነኛ ከሆነ ቲያትር ቤት ይገናኛሉ። ቪቫን ከቲያትር ቤቱ የከንሰርት ሙዚቃ ለመስማት ብቻዋን ነበር የሄደችው። ባልዋ ቋሚ ብሎ ሙዚቃ መስማት ስለማይጥማቸው እርስዋ እጅግ አምሮባትና ንግሥት መስላ ነበር ብቻዋን ከቲያትር ቤቱ የሄደችውና ወንበር የያዘችው። ሰር ልዮኔል ደግሞ ከቲያትር ቤቱ መጥቶ ኖሮ በቀጥታ ከእርስዋ ቀጥሎ ወደ ነበረው ባዶ ወንበር ሄዶ ከአጠገብዋ ቁጭ አለ።

ስለፍቅር የሚያወሳው ሙዚቃ ፍዋ ብሎ ቀጠለ። ስለፍቅር ጽናት የተደረሰውና ስሜትን ክፉኛ የሚቀሰቅሰው ሙዚቃ ፍዋ ብሎ አዳራሹን ሲሞላው የእርስዋም ልብ በእንድ ዓይነት ስሜት ከአፍ እስከ ገደፍ ተሞልቶ በእሳብ ነጎደች። ሆኖም አካልዋ በአዲስ ሕይወት መሞላቱንና በአዲስ ስሜት መዋጡን ስትገነዘብ ነጉዶ ከነበረው አሳብዋ ተመለሰች። ልብዋ በደስታና በጭንቀት ስለተዋጠ ግራ ተጋባች። ከዚያች ቲያትር ቤት ውስጥ ነበር የሕይወት ታሪክዋን ለሰር ልዮኔል የዘከዘከችለት። ታሪክዋን በተመስጦየ አዳመጣት። የነገረችው ታሪክ 'የሚጣፍጥ ግን የሚያሳዝን ታሪክ ነው' የሚል ስሜት ፈጠረበት። ይህን ጊዜ «ቪቫን» አለ፤ «ገና ሳይሽ የአበሾች ደም እንዳለሽ ጠርጥሬአለሁ። መላ ሁናቴሽ ሁሉ ከእንግሊዛዊት ቤት ባህርይ የወጣ ነው። ግርማ ሞገስሽና ደም ግባትሽ ልብን ያሸፍታል።»

«እንግሊዛዊትና የእንግሊዛዊት ባህርይ ያላትን ሴት ብቻ ነው የምትወደው?» ብላ ስትጠይቀው ድምፅዋ የተሸማቀቀና በስሜት የተሳጸ እንዲሁም በትናት ነድዶ የሚጥት ዓይነት ስሜት የነበረው ለመሆኑ ያስታውት ነበር። እርሱም ከመሬት ተነስቶ ኩራት ኩራት ቢለውም ስሜቱ እንደ ተንካ ገጽታው ላይ ስለታየ ይህን ለመለየት ከባድ አልነበረም።

ኤሊኖር ከጊዜ በኋላ ትዝት ያልበላባት ጥሩ እንትልፍ ትቀኝ ጀመር። መንፈስዋ ተረጋጭቶ፣ በመጠኑም ቢሆን ዘጭንቀቶዋ በመላቀቅዋ ሰውነትዋ ተመለሰ። ጤናዋም እየተሻሻለ ሄደ። በዚህ ጊዜ ነበር ሲሪ ማሪ እረፍት ማድረግ የጀመረችው። ኤሊኖር ደንሙ ታሪክዋን ለሰው በመንገርዋና የሙንቀትዋ ተካፋይ በማግኘትዋ እየተከፈለላት ሄደ። ታሪክዋን ያሞየቻት ሴት እንደዘንችላትና ከእርስዋ ጋር መሆንዋን በተረዳች ጊዜ ሰላም አገኘች። ሰላም ስላገኝችም ነው ያለ ቅዝት ለመተኛት የቻለችው። ባልዋ ጥሎአት ከሱበለለ ጅምሮ ሌሊት ሌሊት ሳትቃዥ ያደረችበት ቀን በጣም ሙስን ነበር። ሲሪ ማሪም ኤሊኖር የልብዋን በማውጣትዋ ተደሰተች።

ሲሪ ማሪ ትሠራው የነበረውን ሥራ ሁለተኛዋ ሴር መሥራት ጀመረች። አዲስዋ ሴር ያንን የገረማውንና እጅግ የተዳከመውን የሲሪ ማሪ ፊት ባየች ጊዜ ኅሳረፍሽና ለውኑትሽን እረፍት በማድረግ እገናንብ ከሳገገሽው እንቺም በመረርሽኑ ትጠቂያለሽ። ሰምሳለ ሰሞኑን በመይጸ ሳትተኚ ሦስት ቀን አሳልፈሻል። ይህ ደኅሞ መሆን የለሰበት ነው' ስትል መከረቻት። «አሁን እኮ ኤሊኖር ስለተሸሳት ሁላችንም ለሙሶኝት እንችሳለን። ከአሁን በኋላ ብዙም እርጀታ አትሻም። እንደ በፊቱ ሌት ተቀን ማስታመም አያስፈልንትም። ያለሽን ጉልበት አሟጠሽ ለመጨረሽ የሚታይ ነው። ስለዚህ ከአሁን በኋላ 'ለራሴ አስባለሁ' ብለሽ ቃልሽን ከልለመሸኝ ለአለታትን ነግራ ከነበርሽበት እንዲመልሽ አደርጋለሁ። ይትሽን ምን ያህል እንደሚያስፈራ ባሞሽ፤ ባላያት ጊዜ ‹አሳዘኚኝ› ትትሽን መለሰችሳት እንደ ሙሳት ብላ። «ለማየት አሳመረልን ደንሞ ጥሩ ነው ብትልም ብቻሞን ስትሆን ፈትሞን በመስታወት አየቸዋለሁ።

«ያለ ቆንጆ ፊት ነው ከንዳችና ሴቶች ለማየት ይንኩሳት የነበረው ለእንድ ሙት ከሠንደች አሳ ተሰደቶ የማይሙቁና አንኳን ሳረምሰኝ ሽማሌዎቸም በዩት ሙጥር የተሰነመነሁለትና የድመሙሳት ፊት አሁን ተሳሳቁሎ የማየው ነው። ዛሬ እንዲህ ተሳሳቱሎ ቢያዩት ያስፈራል፣ እትቶረቡኝ አያለም ያሉ»ሳ ስትል አሳሳሰለች።

ሲሪ ማሪ ሠደ ነሱልዋ ስትሄድ ተደም ሲል ያየችሙ ግዜታዋን ዘዜያ ይበልጣ ለማየትና ለማሰሳሰል እድል ስላየነች ደስ አላት። ለምን እግዚአብሔር ምን ያህል እንደ ተጣት ግን ሊገባት አልቻለም። ቀድም ሲል ሌሎች ለሙቶ ከእርስዋ የነበሩ ሥራ ቢሙሩም ደስ ብሎአቸው እንደሚሰሩ ታዝባለች። ታዳያ ፈጣሪ ደህን ያህል እርስዋ ላደ ለምን ዘኋበነ እንድታርግ ነበር ወደ ከነአንዋ እንድትሄድ ምክር የተስጣት። ማሪ ግን አልሆነላትም። ከኤሊኖር አሳ የለማቻቸው ታላት እንኳን ሊደብተኞት ቀርቶ ሊደሰርቋትም አልቻሉም። «ቆንጆዋና ተመጀጅዋ ባለቪቱ ለዘላለም ተለይቼሽ ሙሄዴ ነውና ደህና ሁኚ። የሙሄደውም ወደ ዘሏለማው ንብ ወደ ሞት ይሆናል» በማለት ለየጎል የደብጽቢው መጀሞደሚያ ደደረገው አሳብ ሞንትሳልቫዋ ውስጥ አደተወዘለ አሰሸገራት።

«ወደ ዘሏለማ ጉሀና ወይ ሞት!» ከእርስዋ ጋር የሚያሳልፈሙን ሕይወት ያየው በዚህ ዓይነት እንደሆነ ከተገነዘበች ጊዜ ከልዮአል ጋር ብትቶይ ሕይወትዋ ተበሳ ደልነበረውና ወደ ዘሏለማው ሞት የሚያመራ ሕይወት ሊሆን ይችል እንደ ነበረ የገባት ያኩ ነው። ገፍቶታ ከፈተና ሙበዋ ብትዘሏምረው ኖሮ ከሚወጽት ሚስቱ አደለይም ነበር። የእርስዋ የሚያሳብድና ሰሜትን ተስቶሰ የሚያበገነው የመሊብ ፍላጎት ግፉቶቶት እንጂ ከልብ ወዶአት እንዳልነበረ ቪቫን ደውቶችው በዚያች ሰዓት ነው። ለዮአል ከእርስዋ ጋር ሲኖበልል አርስዋ ለእርሱ በነበራት ጽኑ ፍቅር ለንጂ እርሱ ከልብ አሳትሮአት እንደልነበረ በማወርወርዋ ሕይወትዋን ያበላሸችው በከንቱ እንደሆነ ኤሊኖር ከነባረቻት ታሪክ ተራዳች።

ቪቫን ተደም ሲል የሰማችው ታሪክ በእርስዋ ጥፋት የተከሰተ መሆኑን ባተገሞጥረ ሙንገድ ነው የተነገራት። ቢሆንም ግን ባልጠፋችው ጥፋት

ነው የተወቀሰችው። ኤሊኖር የነገረቻት ታሪክ ሙሉ ለሙሉ ባትከሽፍ እንዳልሆነ ተከራክራ ረዕዮን ነፃ ለማውጣት አልደፈረችም። ኤሊኖርም ብትሆን ሴትዮዋ ማን እንደሆነች ባታውቅ ነው እንጂ ብታውቅ ኖሮ ይህን ያህል አትጨክንባትም ነበር። በኤሊኖር እምነት ቪቫን አሳንሶ ያሰቸው ከባልዋ ጋር ነው።

ሰር ልዮኔል ሚስትና ልጆች እንዳሉት ባወቀ ጊዜ ጥላው አንዲ ሄደች ኤሊኖር ስለማታውቅ እውነታውን ለማየት አልቻለችም። ስለዚህ 'አንድ ቀን ኤሊኖር ከእውነታው ትደርስ ይሆን! እውነታውን ብታውቅስ እኔን ለማግኘትና ለማድነት ጥረት ታደርጋለች ወይስ ያኔም አጥላልታና ንቃ ትተወኛለች?' ብላ በማሰብና ኤሊኖር ያነሳቻትውን በማስታወስ አሳቦች ከቪቫን ጭንቅላት ውስጥ ተተራመሱ። ከዚህም በተጨማሪ 'እንዲህ ያለች ቆራጥና ብርቱ ሴት የት ትገኛለች! ኃይልዋ፣ የሰሚትነቷ ብርታት፣ ውበትዋና ግርማ ሞገስዋ! እንከን የሪታ-ታና ምንም ነገር ያልጎደላት የእመቤት እመቤት መባል የማያንሳት! ኃጥያትን እንደ ኃጥያት አይታና አመሳገባና በትክክልና ጎዳና ሳይ ለመጓዝ የምትጥር! ፍርድን ለፈጣሪ የምትተው! ነገርችን በነፋት ሳይሆን በጥና ግይን የምታይ ሴት፣ አይ ሴት' እያለች ቪቫን ሰለኤሊኖር ታሳትነትም ብዙ አውጠነጠነች።

«እና ይህ ነው እግዚአብሔር የጥሪኝ ሙሽራና ያጎናጸፈኝ መልካም ስም መጨረሻ! የሚያሳፍር ሕይወት፣ የሚያሳዛር ፍጻሜ፣ የሚያሳፍር መጨረሻ!» አለች ቪቫን ስለራስዋ ሕይወት ስታሰላስል። ቢሆንም ግን በዚያች ሰዓት የተመኘችውና ጸሎት ያደረሰችበት እንደ ጉዳይ ነበር። ይኸውም ምንም እንኳን በኃጥያት የተጨማለቀች ሴት ብትሆንም እምላክ የልብዋን አይቶ እንዲምራት አዘውትራ ፈጣሪን መማጠን። ኃጥያት የሠራ ሰው ለፈጸመው አሳፋሪ ተግባር ትጣት መቀበልና መሰቃየት እንዳለበት ስለምታምን 'ማንም ሰው በሠራው መጥፎ ተግባር ከተጸጸተ ምህረት ያገኛል' ስትል ለራስዋ ነገረች። ለመጥፎ ተግባር ማካካሻ እንዲሆንም ሊሉችን መርዳት ያስፈልጋል ብላ ስላሰነች ነው እንደ ኤሊኖር ያሉትን ለመርዳት ቆርጣ የተነሳሳችው። ስኃጥያትዋ ቢዛ ይሆንናል ብላ ስለገመተችም ነው ጉእግሥትን አገለላ ያደረገችውን ሁሉ ያደረገችው። ወደፊትም በደበልዋ በመሰቃየት የበለጠ በጎ ተግባር መሥራት እንደሚገባት ቆርጣ ተነሳሳች።

ሥጋዋደሙ ባልና ሚስትን ሰያይታለች። አባትና ልጅትን አረቆታል። ሥታ ቤትም አጥርሰለች። በዚያች ገርግ ሞገስዋ ከሚያስፈራና ቅርቀፍ ከሚሰበር የቁህ ሴት ልቦና ሥስጥ የጥላቻ አሳት ሜራለች። ስጸሀም ነው አርበቦን ለመመለስና ለማብረድ ጥረት ማደረግ እንደሰባት ስረዳ ቃል ገባችው። ስለዚህ ለይቅርታ ካዘጋጀቻት በኋላ ከዚያ ቤት ለመጀመሪ ጊዜ በፊትም ቢሆን የሰያየቸውን ቢተባብ መልሳ ማኮንት አገላለባት በጽኑ አመነች። ያለበለዚያ አምላክ እንደማይቅሬት ተገንዝባለች። ሆኖም ግን ያሰበችውን ሳትፈጽም ባልታሰበ ሰዓት ልዮኔል መሞቶ ሊያገኛት እንደሚችል ጠረጠረች። ይህ ግን ጨርሶ መሆን የሌለበት ጉዳይ ነው። ከዚያ ቤት ፈጥና ከሄደች ደግሞ ያሰበችውን ቀጠፈም ነው። ለማንሻውም ደብጸቢው ዘገፎቱ ይደርሰዋል በማል ተሰፋ ለጥቂት ቀናት መቆየቱን መረጠች። ሰውዬው ከመምጣቱ በፊት ግን ከዚያ ቤት መሄድ አለባት። ጓግም ተጥናቱው ገጽ ለገጽ ሙተያየት ያለባቸውም።

«በእነዚህ ሁለት ሰዎች ላይ እንደ ደረሰው ለጺያች ቅጽበታዊ ደስታ ተብሎ ሕይወት በከንቱ የባከነባት ጊዜ ይኖር ይሆን?» ብላ ቪቫን ራሰዋን መየቀች ከልዮኔል ጋር ያሳለፈችውን የሚጥም አጭር ጊዜ እያሰላሰለች። «ከልቡ ይወደኝ ወይም አይወደን እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አያሰጠንም። ግን እስ ምን ያጠራጥረኛል፣ ፍቅሩ ከልብ አልነበረም። የሚወደን ቢሆን ለሚበቱ በጻፈው ደብዳቤ 'ወደ ምትና ጨለማ ሕይወት መሄዴ ነው' ብሎ አይጽፍም ነበር። ስለዚህ ይህን የመሰለ ከባድ መስዋዕት ሰከፈልኩት በከንቱ ሲሆን የዚህ ዓይንቱ ታሪክ ለወሬ የማይመች ነው። ከእሁን በፊትም ተሰምቶ የሚታወቅ አይመስለኝም» አለች ለራስዋ ያችኩ በፊትም ተሰምቶ የሚታወቅ አይመስለኝም» አለች ለራስዋ ያችኩ ተውጣ።

የሆንውን መለወጥ ስለማይቻል ባለፈው ነገር መቆጨት ትርፉ ጨንራን መሳጥ ስለሆነ አንድ ሰው ቪቫን ከነበረችበት ሁናቴ ውስጥ ቢገፃ ለማድረግ የሚችሰው ነገረሰው ጥፋት ትምህርት ቀስሞ ለወደፊት ሕይወቱ የሚበጀውን እርምጃ መውሰድ ነው። ቪቫን የልዮኔልን ሚስትና ልጆች በማሰቃመም ከሞት አድናቸዋለች። ይህ ደግሞ የሚጠራጠሩት አይደለም። ስለዚህ ከአሁን በኋላ ማድረግ ያለባት ባልና ሚስት በቀረው የሕይወት ዘመናቸው ተደስተው እንዲኖሩ ማመቻቸትና ማገዝ ነው። ለጺህም የመጀመሪያ ተግባር ሊሆን የሚችለው ኤሊኖር ከባልዋ ጋር እንድትታረቅ ማገባባት ነው።

Scan by Easy Scanner

በሚቀጥለው ቀን ሲ/ር ማሪ የታመመች መሰለች። ሌላዋ ሴር ባዞኛ ጊዜ በህዘን ራስዋን ነቀነቀች። «እንቅልፍ አልመለደሽም እንዴ? የደነዘዝ ብዛት እንቅልፍ ሲያስወስድሽ እንኪን አልቻለም?» ሰትል ጠየቀችው። ሆኖም ግን ባገኘችው መጠነኛ እረፍት መንፈስዋ መርኩሀን ከገኘዋ ላኢ አየች። ቪቫን ጥሂት አሰበችና ጓደኞዋ ለጠየቀችው ጥያቄ መለሰችላት።

«አልተኛሁም፣ ግን እንቅልፍ ባይመስደኝም መንፈሴ ስላረፈ ነው መሰለኝ የመፀርታ ስሜት ይሰማኛል።»

ሲ/ር ማሪ ኤሊኖር ወደ ነበረችበት ሥፍራ ሄደች። የጠዋት ፀሐይ ውጥቶ ስለነበር ሥፍራው በጣም ደስ የሚል ትርዒት ነበረው። አእዋፋት እየተንጫጫ ነው። አበቦች ዴግሞ 'የወጣውን የፀሐይ ብርሃን ተሻጫ' የተባሉ ይመስል ሁሉም ፈክተዋል። ሴርዋ ኤሊኖር ከነበረችበት እንደ ደረሰች በላዮታ ተለዋወጡ።

«አሁንስ በቃሽ ቢለኝና በቶሉ ከሕመሜ ባገኝም ደስ ባለኝ። እንደምታዪው ፀሐይ ብርሃንዋን የፈንጠቀችውና ወፎች ዝማሬያቸውን የሚያሰሙት ለእኔ ብለው እንደሆነ ይሰማኛል» ስትል ኤሊኖር በምኳት ተናገረች። «ይገርምሻል፤ ባሬ ተሽሎኝ ነው ያደርኩት። የምነግርሽ ነገር ስላለኝ ለተወሰነ ጊዜ ከዚሁ ብትቆዪ» ስትላት ሲ/ር ማሪም በበኩልዋ የምትነግራት ነገር እንዳላት ገለጸችላት። ለኤሊኖር የምትነግራት ነገር እንዳላት ሰትገልጽላትም ፊትዋን ፈነ አድርጋ ነበር።

«እኔ ግኔ» አለች ሲ/ር ማሪ፤ «የማጫውትሽ ስለራሴ ጉዳይ ሳይሆን ስለንጹ ነው። ስላመንሽኝና በእኔ ስለተማመንሽ የልቤን ገልጨ ልነግርሽ ነው። እኛ ሴሮች ለእግዚአብሔር ያይርን ስለሆን ስለሌሎች ሕይወት መስክት መንፈሳዊ ኃላፊነት አለብን። የምናገለግለው ደግሞ ነፍሳቸውንም ሞምር በመሆኑ ለማዳን የምንሞክረው ሥጋቸውን ብቻ ሳይሆን መንፈሳቸውንም ሞምር ነው። በዚህም የተነሳ በሽተኞችን አክመን ጤናቸውን እንዲያገኙ በመርዳት ብቻ አንወሰንም፣ ስሜታችንንም በዚህ ብቻ አይረካም። እንቺም ብትሆኚ ሞንቀት እንዳለብሽና ስለአንድ ነገር በኃይል እንደምትሻ ከገጽሽ ለማየት ይቻላል። ስለዚህ ጥያቄ ብጠይቅሽና ለጥያቄውም መልስ ለመለጠት እንድትችዪ አኔው ራሴ ብረዳሽ» ስትላት «ጥያቄውን ልበማዋ እንግዲህ» ስትል ኤሊኖር በዝግታ ተናገረች።

«በመጠኑም ቢሆን ስሜትሽንና መንፈስሽን ሲነካ የሚችል ጥያቄ ስለሆነ እንዳትረበሺ ራስሽን ማበረታትና ስጥያቄውም መዘጋጀት እንዳለብሽ

ሥድሚያ ላስጠንቅቅሽ» ባለቻት ጊዜ «ግዴ የለም፣ ያስጎበጠሽን ነገሬን ለመስማት ልወሥው» አለቻት ሬሊኖር።

«ለመቼትሽ ሰር ልዮኔል ከቪቫንሽ ተመልሰ ቢመጣ 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ብለሽና ሙሀረት በማሙሬድ አጅብን በርግተሽ ትቂበደዋለሽ፣ ወያስ ትችሽን ታዞራበታለሽ?» ብላ ሰትጠይቃት ከጪለማ በኩሉ መልኩ ከዘቡበት ሥፍራ ወጥታ ሰፈነ። የኤሊኖር ፊት በድንገት ፍም መሰለ። ሥንጀቶ ሲደነግጡና ያልጠበቁት ነገር ሲጉጥግቸው የፌታቸው መቅሳት (ተለመጀ) ከመገረምም አልፉ ነገሩ አስደነገጣት። ይቪኔ ነበር ዶብጸቢ ከበልም መጸፍዋና ባልዋ በድንገት ከቤትዋ ሊመጣ እንደሚችል የታሰባት።

«ሰር ልዮኔል እኮ ባልተጠበቀና ባልታሰበ ሰዓት ሲመጣ ይችላል» ለቶ ቪቫን የፈገግታና የይቅርታ ፊት አያሳየቻት። «ከውሳኔ አሳብ ላይ ለመድረስ፣ 'ምናልባት የእኔ ምክር ይረዳት ይሆናል' ብዬ ሰላሰብኩ ነው አባቢን ሳነፍልሽ የፈለግሁት። እርሱ ከመጣ በኋላ ከወጪህ ወዲያ እያሉ ስለሳብ መዋለል ጥሩ ውጤት አያመጣም። ተዘጋጅተሽ ነው መጠበት ያለብሽ። ያለሽ ምርጫ ሁለት ነው። ይኸውም 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ብሎ ከእርሱ ጋር ተስማምቶ መኖር ወይም ዳግም ፊቱን አላይም ብሎ ለዘላለም አየተስታዩ መኖር» አለቻት ነገርዋን በማጥበቅ።

«እርሱስ 'ይቅርታ አድርጊልኝ' ብሎ ባይጠይቀኝስ» አለች ኤሊኖር። ነገሮዋን በመቀጠልም «ምንም እንኪን ብልሀና ቀና ልብ ያለው ሰው ቢሆንም ሲበዛ ኩሩ ነው። የቀረው ይቀራል እንጂ በቀላሉ እጅን የሚሰጥ ሰው አይደለም። ከዚህም በላይ እጅግ እንደጨከነብኝና በዚህም ላቢያ ብዙ መጎዳቱንና ቅሰሜ መሰበሩን ልቦናው ስለሚያውቅ 'ይቅርታ ታደርገልኛለች' ብሎ ሳያስብ ይችላል። ስለዚህ 'ይቅርታ አድርጊልኝ' ብሎ የሚጠይቀኝ አይመስለኝም። እነዳያውም ከአለቱው ወደ እኔ የመመለስ ምኞትና ፍላጎት አይኖረውም።»

«ወዳንቺ የመመለስ ምኞትና ፍላጎት እንደሚኖረው እርግጠኛ ነኝ» ለቶ ሲ/ር ማሪ ጣልቃ በመግባት። «በእርሱ ላይ የደረሰው ነገር ሥነ እንደሆነ አላወቅሽም። እንዴት ብሎ ከፈተና ውስጥ እንደገበም የምታውቂው ነገር የለም። ስለዚህ እርሱ የሚያስበውንና የሆነውን ላታውቂ 'ይህ ሊሆን አይችልም' ብለሽ ውሳኔ ባትስጪ ደስ ይለኛል።»

ይህን ጊዜ ከጣቶችሞ መትጠን የተነሳ ሊጠልቅ የተቃረበውን የጋሜ ቀለበትዋን እጅዋን ቀና በማድረግ ሳሳየቻት በኋላ «እባክሽን የጋሜ እስች ኤሊናር። «አልጣሽምም፣ እኔ እንደማስበው ለዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ነው ይቅርታ የማይገባው። ባለቤቱ የሠራው ሥራ ከይቅርታም በላይ ሰለሆነ ህሊናዬ የሚተበለው አደይለም።»

ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት

መደር የማይገኝለት ልመና

«እዚህ ላይም የተሳሳትሽ ይመስለኛል» አለች ሲ/ር ማሪ። «እነዚህ ሰው ያደረሰው ጥፋትና የፈጸመው በደል እጅግ ከባድ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ግን ጸጸቱንና ልመናውን አይተ ይምራዋል። ብትሆኚ ልብሽን አታደንድኚው። እርሱም ቢሆን ምን ያህል እንዲ ተሰቃየ ስለማታውቂ ስለማንሻውም ነገር አረጋገጠሽ ለመናገር አትችዪም ስትላት «ልቤን አደንድኜው አላውቅም» ስትል መለሰችላት።

«ባልሽ በሠራው ታጥያት ተጸጽቶና አዝኖ ቢመለስ ለእርሱም ቀላል ውሳኔ አይሆንም። ይህን ፈጽሞ ቢመለስም 'ይቅርታ አላደርግለትም' ሙ ያምትዪው? መላሳት የሰው ልጅ እጣ ፈንታ ሲሆን 'ይቅር ለእግዚአብሔር ብሉ ይቅርታን ማውረድ ግን መለኮታዊ ነው።»

«ግን እኮ ሲ/ር ማሪ፣ በእኔ ላይ የደረሰው በደል ከባድና ሊሽሙት የሚከብድ እንደሆነ አንቺም ታውቂዋለሽ። ከዚህም በላይ ባለቤቴ በሠራው ሥራ ለመጸጸቱ ምንም ዓይነት ፍንጭ አላየሁም። ይህን ያህል ጊዜ ሲቆይ ከእርሱ የሰማሁት ምንም ነገር የለም። በሠራው ሥራ የተጸጸተና ያዘነ መሆኑን ሊጠቁም የሚችል ደብዳቤ እንኳን ጽፎልኝ አያውቅም።»

«ምናልባት» በማለት ሲ/ር ማሪ ጣልቃ ገብታ «እንቺው ራስሽ እነዚ ልሽው በፈጸመው አሳፋሪ ተግባር አፍሮ ሊሆን ይችላል። የሠራው ሥራ ከባድ መሆኑን ስለሚያውቅ ምንጊዜም ቢሆን ይቅር አትለኝም' ብሎ ስላሰበ መድፈር አቅቶትም ይሆናል። በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል እስከ ዛፌ ደብዳቤ እንኳን ላይጽፍ የቀረው» ስትላት የኤሊኖር ፊት ትንሽ ፈገግ አለ።

«ለዚህ ይሆናል ብለሽ ትገምቻለሽ?» ብላ በመጓጓት ሴርዋን ስትመ ይቃት «እውና፣ ከዚህ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?» ስትል እርስዋም ጥያቄ

ለመቀጠት። «እሁን እንግዲህ ለዘብ ባለ አጻጻፍ ኑሐር ያለ ሌላ መልእክት ብትልኪለት ሮጠ መጥቶ ከመሥጊያኗ ስር ነው የሚደፋው። እሠግ ሥጥቶፉት ደብዳቤ ደርሶት ሲያነበው የልቧቹ ጥቅር ቱቀስቅስበትና ሰአንቺ ላይ ባደረሰው በደል ሳቢያ ያደረበት የህሊና ውቀላ አገርሽቶበትና ወቶ ከቤቱ ይመጣል አንበል። ታዲያ ምኑ አንቺ ምን ታደርጊያለሽ?»

«እኔ እንጂ፣ ነገሩ እየተመሳሰለ ከህሊናዬ ውስጥ በመገባት ያሰቀጣረኝ ሲሆንም እንዴት ብዬ እንደምተበለው አሁን ለመናገር ይከብደኛል። መከበድ ብጅ ላይሆን የምስጠው መልስም ምን መሆን እንዳለበት አላውቁሙም። ህሊናዬም ይሁን ልቤ ጉዳዩን እመዛገኖ መልስ ሲሰጥ ሁሉ በላልቻሶ ሙጉቱት ውስጥ ነው የጪመርሽኝ» ስትላት «እንዲያው ሰውቢሙ ህሊናሽ ምን የሚል ይመስልሻል?» በማለት ሴርዋ ሌላ ጥያቄ መቀቻች።

«ባለቤቴ በእኔ ላይ ያደረሰው በደል ብርቱ በመሆኑ ህሊናዬ ከጊህ ጋር 'ይቅር ለእግዚአብሔር መባባሱ ተገቢ አይሆንም' ሊለኝ ያው ሚናዬ ደግሞ እርሱም ቢሆን ደፍሮ 'ይቅር በይኝ' ብሎ የሚጠይቅ አይመስለኝም እያለ ይመክረኛል» ባለቻት ጊዜ «አሁንም ቢሆን ነገሩን አውጥተሽና አውርደሽ ብታስቢበትና ለነገሩ ጊዜ ብትሰጪው ምን ሚሆን ይመስልሻል?» ስትል ቪቫን በድጋሚ ጠየቀቻት።

«ባለቤቴ በቂ ምክንያት ሳይኖረው ከመሬት ተነስቶ እኔን እንደ ገፊ ደንጋይ ከሚጸዳ ላይ ጥሎኝ ና የሄደው። የሰው መሳሰቂያ ነው ያደረገኝ። የሱን አኮ ነው ከሴት ጋር የኩበለለው። ስለዚህ ባለቤቴ በድንገት ከቤቴ ሲመጣ እጅን ዘርግቼ ለመቀበል እጅግ በጣም ይከብደኛል። ህሊናዬም የሚቀበለው ነገር አይሆንም። ጥሎኝ በመኩብለሉ ለደረሰው ጥፋት ያናውን ገፈት ቀማስ መሆን ያለበት እርሱ ራሱ ነው።»

«እና አሁን የምትዪው ነገር ክልብሽ ነው? ልቦናሽም ይሽው ነው የሚፈቅደውን?» ብላ ሲ/ር ማሪ ስትጠይቃት ኤሊኖር ፈገግ በማለት እንደ መሳቅ አለች። ይህም የጥንት ፍቅርዋን ስላስታወሳት ፈገግታዋን በይበልጥ እንዲፈካ አደረገው።

«ክልብሽ» አለች ኤሊኖር ሴርዋ ቀደም ሲል የተናገረችውን ቃል በመድገም። «ልቤማ ደኅማ አማክረዬ በመሆኑ 'ተዪው፣ ከእንቺው ይቅር' ምሀረት በማውረድ በእምባ ተቀበይው፣ ህዘንሽ በእምባው ይታጠብና

Scan by Easy Scanner

ከእምነው ጋር አብሮ ይፍሰስ' እያለ ያስጥንረኛል፤ ከማስቸገር አልፎ ይመተውተኛል» ስትላት «እንግዲያውስ ሀሊናሽ የሚለውን ትተሽ ልብሽ የሚለውን ስሚ። ከሀሊናሽ ይበልጥ ልብሽ ትክክለኛውን እመስክነት የያዘ ስለሆነ እርሱን ብቻ አድምጪ» በማለት ቪቫን መከረቻት።

«ለመሆኑ የሆነ ተዓምር ተፈጥሮ አንቺ በእኔ ቦታ ብትሆኚ ይቅር ብለሽ ትታረቂዋለሽ?»

«እንዘትዘ» ብላ ስትመልስላት ዓለማዊ አነጋገር መሆኑ በታዘበቻት ጊዜ እንደ ማፈር አለች ሴርዋ። ከዚያም «አግቢአብሔር ስሚያውቀው ከልቤ ነው፤ እታረቅዋለሁ። በሕይወት ዘመኔ ከዚህ የበለጠ ነገር ደርሶብኝ 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ብዬ ትቼዋለሁ። አየሽ ኤሊኖር፣ በዓለም ላይ አንቺ ልታስቢላቸው የሚገቡ ሌሎች ብዙ ፍጡሮች አሉ። ከዚህም በላይ በዓለም ላይ ያለሽው ብቻሽን ብትሆኚ፣ ማለቴ ልጆችሽ ባይኖሩ፣ እንዲ ፈለግሽው ለመሆን ትችዪ ነበር። አሁን አንቺ ያለሽበት ሁናቴ ግን ከዚህ የተለየ ነው። ስለልጆችሽም ማሰብ ይኖርብሻል። ጥሩ ሰው ስለሆንሽ ሳስቀይምሽ አልፈልግምና አሁን ደፍሬ የልቤን ብናገር አትቀየሚኝም? ገለ ስትጠይቂት «እንዲት ብዬ! በአሁኑ ጊዜ በጭጋም ልብናዬ የማከብርሽ፣ የማቀርብሽና ያለሽኝ ወዳጅ አንቺ ብቻ ነሽ። ሳትፈሪ የልብሽን መናገር ትችያለሽ፣ እኔ ደግሞ አልቀየምሽም» አለቻት።

«እንግዲያውስ ቀደም ሲል እንዳጫወትኩሽ፣ ኤሊኖር ሁለት ምርጫ ነው ያለሽ። የቱን እንደምትመርጪ ማወቅ ያለብሽ ግን አንቺው ራስሽ ነሽ። ሀሊናሽ ውስጥ የሚብላላውን የበቀልና የቁጣ ሰሜትሽን አብርደሽ ከባልሽ ጋር መታረቅና የተደላደለ ሕይወት ለመኖር መወሰን ወይም ይቅርታ ማድረግ አይገባኝም በማለት ከባልሽ ጋር ተቆራርጠሽ ቀርተሽ የለቃይ ኑሮ መኖር ነው። ሁለተኛውን ከመረጥሽ ልጆችሽ ከእባት እንክብካቤና ጥበቃ ርቀው ያድጋሉ። ይህም በሕይወት ዘመንሽ በይበልጥ ያስቆይሻልና አስቢበት።

«አሁንም እኮ እየሆነ ያለው ይሽው ነው» አለች ኤሊኖር ጣልቃ ገብታ የከፋ ህዘን እየተሰማት።

«አሁንማ ልጆች ናቸው፤ አይደጉ ሲሄዱ ነው የአባታቸውን ድጋፍ ከእሁን በተለየ መልኩ የሚሹት። ለምሳሌ ጎርዶን ትምህርቱን መቀጠል ያለበት አገሩ ሲሆን እርሱን ይዘሽ ወደ አገርሽ ካልተመለሽ ይህ ሊሆን አይችልም። ብቻውን ወደ እንግሊዝ አገር ሲመለስ ደግሞ ሶምን ያህል ጊዜ ተለያይታችሁ አንደምትኖሩ እኔ አሳውቅዎታለሁ። አንቺ ብቻ አዕቢስቅ። ያለ ባለቤትሽ ልጆችሽን ያዘሽ ወደ አገርሽ ብትመለሺ፣ በአንቺ ላይ ሊደርስ የሚችለውንም አስተውይ። የሰው ወሬ፣ የጥንቱ ትዝታና የቢያ ይበልጥ ይህ ሁሉ ዘሚሆን 'ከእኔ ይቅር' ብሎ የየዘመ እፍ መኒታትና ዝነኛም ለመኖር መሞክር የሚሸል ይመስለኛል። ከዚህም በላይ ትወጂዋለሽ። እስካሁን እንዳየሁሽ በአፈጣጠርሽ ለሰው አላንም ጥቅም ብለሽ ከአሰብሽው መንገድ ርቀሽ የምትሂጂ ሩህሩህ ሴት ነሽ። ሌላም ማሰብ ያለብሽ ነገር አለ። እንበል አሁን ከሰር ልዮኤል ጋር አሌታረቅም ብለሽ ብትጪከኝ መብትሽ ይሁንና እምቢ እንዳልሽ ቅሪ። ግን ይህን መንገድ ብትመርጪ እርሱ ምን ሊሆን እንደሚችልም ጭሮ፣ ከባለ አዘቅት ውስጥ ገብቶ ጠቀመቅ ነው የሚጠርደው።»

የዋህዋና ጎርዋ ኤሊኖር «የለምን አይሆንም፣ ሊሆን የማይችል ነገር ነው» ስትላት «አይሆንምን ትተሽ ቢሆንስ ብሉ ማሰቡ ምን ይመስልሻል? ለአቶ ማስበል ተውጦና በሠራው ሥራ ተሸማምቅቆ፣ በሀዘን ብዛት ለሙታ አልቆና ስሚተ ሁሉ ተኩላሽቶ ወዲ አንቺ ቢመጣና አንቺ ፊት ብትነሺው፣ እኔ እንደሚመስለኝ፣ እስካሁን ካደረገው የተሳሳተ መንገድ ይበልጥ ከከፋ ሙሳኔ ላይ ሊደርስና ሀሊናን እጅግ ከሚሰቀጥጥ አደጋ ላይ ሊወድቅም ይችላል። አንቺ ደግሞ የዚህ ሀዘን ዜና በትሰሚ ከልብ ከማይወጣ ጸጸት ውስጥ አንደምትዘፈቂ የሚጠራጠሩት አይደለም።»

«ክፉ ነገር እንዲደርስበት እንኳን አልፈልግም። በፍኡም የማልመኘው ነገር ነው» አለች ኤሊኖር አሳቡ እየዘገነናት።

«አየሽ ኤሊኖር፣ አልታረቅም ብሎ ድርቅ በማለት የሚገኝ ጥቅም የለም። 'ሥብቀልኩት' በምትዪበት ጊዜ ምናልባት ልበናሽ ደስ ይለው ይሆናል። ግን ይህ ዋጋ የለውም። ከአላፊው በዚህ የተነሳ ራስሽን በይበልጥ ነው የምታሰቀይውና ልጆችሽንም የምትሳጂው። የምትጎጂው አንቺንና ልጆችሽን ብቻ አይደለም፣ ባለቤትሽንም ጭምር ይሆናል።»

«አሁን ደግሞ ሌላውን ግጭታ እንይ እስቲ። ለባለቤትሽ ይቅርታ አደረግሽልት እንበል። ይህን ካደረግሽ ሥጋ የለበስ ሁሉ በቀሳሉ ሊፈጽመው የማይችለውን መልካም ነገር ወራሽ ማለት ነው። ባለቤትሽ ደግሞ ይቅርታ እንዳደረግሽለት ሲገነዘብ ለእንቺ ያለው ሰሚትና አክብሮት ከቀድሞው ባመዘነ መልኩ 'ምን ዓይነት መሐሪና ይቅር

ባይ ልብ ነው ያላት' እያለ የሚያየደርግውን አጥቶ በአይናቶቹ ፈጠ
እንበል። ይህም ለእንቺ ያለው ከበሬታ አሳደገው፣ ያስከፋሽን ያህልም
አንቺን ለማስደሰት ጥረት እንዲያደርግ ስሜቱ ገፋፋው እንበል። 'ናትና
አገረሸ' ማለት ይሻው ነው። ይህም ማለት ሕያውነትን ለእንቺ አሳልፎ
በመስጠትና ያደረሰብሽን በደል በማካካስ የእርሱን ደስታ በእንቺ ደስታ
ለመጠ ብንል፤ ለእንቺ ብቻ መኖርን መረጠ ማለት ነው። ይህም ማለት
ቤታችሁ ውስጥ ሰላም ሰፈነ ማለት ሲሆን ቤታችሁ ውስጥ ሰላም ሰፍኖ
መንፈስ ቅዱስ ከቀረባችሁ ደግሞ ልቦናችሁ በዘላለማዊ ደስታ ተሞላ
ማለት ይሆናል። ስው ታዲያ ዘለቂታ ካለው ደስታ ሌላ ምን ይፈልጋል፣
ሞኝ ካልሆነ በቀር።

«ኤሊኖር እባክሽ ቱለመኚኝ። ከልቤ ልማጠንሽና እሺ በቂኝ። ከባልሽ
ጋር ታረቁ። ከታረቃችሁ ደስ ብሎአችሁ እንደምትኖሩ ይታየኛል።
ያ ደስታ ሊገኝ መይም የውሃ ሽታ ሆኖ ሊቀር የሚችለው ዛሬ አንቺ
በያዥወሰኚው ውሳኔ ባይ የተመሠረተ መሆኑን እወቂ። ተበድለሻል፣
ለዚህ ጥርጥር የለውም። ነገር ግን በይቅርታ በቀልን ረሰዱ ደስታ ሊገኝ
እንደሚችል አትርሺ።»

«ይቅርታ ለማድረግ የምችለው እኮ እርሱ ይቅርታ ሲጠይቀኝ ብቻ
ነው» ሰትሳት «ይህን አልጠራጠርም፣ ከቤቱ እንደ ተመለሰ ከመጫሚያሽ
ሰር ነው የሚወድቀው» ብላ እምነትዋን ገለጠችሳት።

«ግን ሲስተር፣ እርስዋን እኮ ጨርሰሽ ረሳሻት» ብላ ኤሊኖር
ስትመልስላት «ማን ናት እርስዋ ደግሞ» ስትል ሴርዋ ጠየቀቻት ቀና
ብላ እያየቻት።

«የሊንዋ እመቤት ናታ፣ ባለቤቴ ልጆቹንና እኔን የትም ጥሎ፤ እኖን
በእርስዋ ለውጦ ያበኮበለለችው ሴት ናታ፣ የእኔን ቦታ የወሰደችዋ ናታ
ቪቫንን የረሳሻት መሰለኝ» ብላ በመናገርዋ የቪቫን ፊት ተቀያየረ። ይህን
ጊዜ ኤሊኖር በጣም ተገረመች። ነገሩ ሊገባት አልቻለም።

«እኔ እንደሚመስለኝ» አለች ኤሊኖር በመቀጠል። «ይህቺ የሊንዋ
እመቤት የምትባለዋ ሴት ናት ዋናውን ቁልፍ የያዘችው እንጂ እኔ
እይደለሁም። ለዚህም በቅድሚያ መታየት ያለበት የእርስዋ ጉዳይ ነው።
ባለቤትዋ ሎርድ ሊን መሞታቸውን ነግሬሻለሁ? ባልዋ በመሞታቸው
ነፃ የወጣች ሴት ናት። እርግጠኛ ነኝ ልዮኔል ክእኔ ጋር በሕጋዊ ፍቺ

ሥላቱ እርሱም ነፃ ይሆናል። ያኔ ሁሉቱ ይጋባሉ። ብላ ኤሊኖር
ስታመሠጥት ቪቫን አሳቡ በጣም ስለዘገነናት መሬት መሬት እያየች
«እኔ እንዚህ በዚህ አሳምንም» አለች ሲዘር ማሬ።

እውነቱን ብትነግራትና ሁሉቱ አብረው ባለመሆናቸው በምንም
መንገድ ሊጋቡ እንደማይችሉ ብትገልጽሳት እጅግ ደስ ባላት። ግን
እምነቱን ለማሠጣት አቅም አጣች።

«እንዳንዴ የሕይወት እውነታን ለመቀበል ቢያስቸግርም የሆነውን
ከመቀበል ወደ ኋላ ማለት ግን ሞኝነት ነው። አየሽ ሲስተር ፣ ምናልባት
ተሰላችተውና ልቡ ወደ እኔ ተመልሶ ቢሆን ሌላው ቢቀር በደብዳቤ
ይቅርታ ይጠይቀኝ ነበር፣ አይመስልሽም፣ ዝምታው እሁንም ሴትዮዋን
እንደሚወድና እኔን እንደ ረሳኝ ነው የሚያሳየኝ።»

«ይህ ዓይነቱ አመለካከት ሎንቅሳትሽ የፈጠረው እንጂ እውነታው
ሌላ ሊሆን ይችላል» አለች ቪቫን እውነታው ምን እንደሆነ ልበናዋ
ለሚያሙቅ። «እንበል አሁን ባለቤትሽ ተመልሶ ቢመጣና ይቅርታ ቢጠ
ይቅሽ 'ይቅር ትይዋለሽ' ወይስ 'ዓይንህን ለአፈር' ብለሽ ትሸኚዋለሽ?
ይህን ብቻ መልሽልኝ» በማለት ሳታፋጥጣት «ምኑው ሲስተር፣ እርስዋን
ለምን ትረሻታለሽ?» ስትል በድጋሚ ጠየቀቻት።

«እርስዋን ተያት፣ ምንም አያግባትም። ነገሩ ያለው በእንቺና በእርሱ
መካከል ብቻ ነው» ባለቻት ጊዜ ኤሊኖር ግራ ተጋባች።

«እንዴት አያግባትም ትዪኛለሽ፡ የነገሩ መነሻና መጻረሻ ግን ሆነና
እስቲ እንቺ እንዴልሽው ይሁን እንበልና ነገሮች ሁሉ ይስተካከሉ። እኔ
እንኳን ይቅር ብለው ከእርስዋ ጋር ልገናኝ ዓይን ለዓይን ልንተያይ
አይሆንም፣ አይደረግም። የእርስዋን ሁኔታና ስለግኙነታቸው ሳሳውቅ
ምን ለማድረግ እችላለሁ፣ እስኩብሳይዋን ቢተውና ዳግም ላይገናኙና
ላያኋግራት ቢወስን ነገሩ የተለየ ይሆንና አንቺ ባልሽው አሳብ ለመስማማት
አይከብደኝ ይሆናል። አሁን ባለው ሁኔታ ግን በሁለታችን መካከል
አንቅፋት የምትሆነው እርስዋ ናት እንጂ ሌላ ነገር ያለ አይፈመስለኝም።
እርስዋው ናት፣ እርስዋ ናት፣ ይህቺ ደንቃራ» እያለች ስትናገር ሲ/ር
ማሪ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አለች። ቆይታ፣ ቆይታ ግን የሚሰማትን
ተናገረች።

Scan by Easy Scanner

«ኤሊኖር አየሽ፣ ስለጀረሰው ነገር የማሌ የሆነ አመለካከትና ግምት አለኝ። ያቺ የብብቱኞ ሌት ከባልሽ ጋር አብራ አይደለችም የሚል ግምት ነው ያለኝ። ግምት ብቻ ሳይሆን መለያየታቸውን እሌጠራጠርም። ባሳ ስትኖገር በተሰፋ የተሞላ ሰው ፊት ሠግግ እንደሚል ሁሉ የኤሊኖርም ፊት ከመጠን በላይ ወግግ አለ።

«እንዲሀ ብሎ ለመናገር ያስጀፈረሽ ምንድነው?» ስትል በንገት ጠየቀቻት። «ግምትሽና እምነትሽ የእኔ ቢሆንና ደፍሬ ከዚህ ዓይነቱ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ብችል እሮጣ በጣም ደስ ባለኝ ሕይወቴንም በዚያው አኪያ ባስተካክልሉ። አብረው የመኖራቸው ጉዳይ በታወሰኝ ቁጥር ያንገበግበኛል፣ እንደ አሳትም ያቃጥለኛል። ለባሌ የንበረኝ የፍትር ጸናት ብርቱ እንደ ነበረው ሁሉ ከእርሱ መለየቴና እርሱን የማጣቴ ጉጻደም እንዲሁ ብርቱ ስለሆነብኝ በተሳሳ የሚረባ ሆኖ አላገኘሁትም። በሊንቀ አመቤት ላይ ያለኝ ቅናትም እንዲሁ ብርቱ ስለሆነ ያንገበግበኛል።»

«ከልቡ የሚወዳት አይመስለንም» አለች ሲ/ር ማሪ። «የጻፈልሽን ደብዳቤ እንድምታሳዪኝ ታልሽን ሰጥተሽኝ ነበር። የሚወዷት ሲሆን እንደዚያ ያለና ተስፋ መቁረጥ የታከለበት ደብዳቤ ባልጸፈ ነበር። ስለደብዳቤው ይዘት የነገርሽኝ ትዝ ይለኛል፣ 'ወደ ፈጨለማው ሞት እያመራሁ ነው' ብሎ ነው የጻፈው። ወንዴሽ ከረቱርጥት ሌት ጋር ቢኾበልሉ እንዲህ ብለው አይጽፉም።»

«ታዲያ ካልወደዳት ለምን ብሎ ነው ይህለት የኩበለለው? እኔነ ለምን ጥሎኝ ጠፋ? ስለዚህ ከሴትዮዋ ጋር ፍቅር አልነበረውም ብሎ ማመኑ ይከብደኛል። ከዚህ ሌላ ምንም ነገር ብትዪኝ አምናለሁ፣ አሠነ የምትዪውን ለማመን ግን ያስቸገረኛል።»

«በአንድ አጋጣሚ ስላወቅኋቸው የሁለት ለዎች ታሪክ ሳጫውትሽ። ታሪኩን ስትሰሚ ምናልባት ይህ ነገር ሊሆን ይችላል ብለሽ አሠነ የያዝሽውን አመለካከት ትለውጪ ወይም እሠነ ከደረስሽበት ድምዳሜና ስለሰጠሽው ፍርድ አሳብሽን ትቀይሪ ይሆናል» አለቻት ሲ/ር ማሪ።

ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት

ያልተወደደች ሚስት ታሪክ

«እንዚህን ሰዎች በሚገባ አውቃቸዋለሁ» አለች ሲር ማሪ። «በቅድሚያ የቤትሮዋን ታሪክ፣ ሳውታሽ፣ ምክንያቱም እርስዎ ናት በጣም የሚታዘንላት። ሌት። ፍቅር የሚሉት ነገር አታውቅም። ሆኖም ግን ምናልባት በዓለም ላይ ካሉት ሴቶች ሁሉ ደስልዋ ከልብ ለማፍቀር የሚችል ስለሌሳት ብቸኛ ፍጡር ናት። እንድ ጨዋ የጨዋ ልጅ የሆነ ሰው ወንድም ስለሌሳት ብቸኛ ፍጡር ናት። እንድ ጨዋ የጨዋ ልጅ የሆነ ሰው አግዚናው በጉዲፈቻነት ተቀብሎ አንደ ራሱ ልጅ ስማሳደን አስጠጋት። የዚህ ሰው ሚስት ግን በእርስዋ ስለቀናችኞ ጠሳቻት። በዚህም የተነሳ ደሙቿ ልጅ ይሰጡ የሚሉት ነገር ሳታውቅ አደገች። ያ በጉዲፈቻነት የተቀበላት ደግ ሰው ግን በጣም ደመዳት ነበር። ከዚህ ሰው በሰተቀር ሌሳ ይህችን ልጅ የሚወድ ሰው አልነበረም። የሚያሳዝነው ግን ከዚያ ከልብ ከሚያፈቅራት ሰው ጋር ብዙም አብረው ሳይኖሩ በሙዴው በድንገት ሞተ። አሠነ አንግዲህ ይህቺ ልጅ ከዚያች ከምትጠሳትና ከምትቀናባት ሴት መዳፍ ስር ስለወደቀች አብራ ከመኖር በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበራትም። ይህቺ ልጅ ሲበሳ ቆንጆ ናት፣ ሰው ትመዳስች። ወንዶችን በቀሳሉ ሊያጠምድ የሚችል አስደናቂ ውበት ያሳት ለግሳጋ ወጣት ናት። ጊዜና ሁኔታ ቢፈቅድሳት ማንንም አግብታ የተከበረችና የተወደደች እመቤት ልትሆን የምትችል ልጅ ነበረች። ነገር ግን ጠማማ እድል ስለገጠማት መጠነኛ እንጂ የዘለቀ ትምህርት አልቀሰመችም። ኑሮዋም የተጋሳ አልነበረም። የሚገጥማት ነገር ሁሉ ጠማማ ሆኑ።

«ቢሆንም ተፈጥሮ ውበት ስለቸራትና ያያት ሁሉ ስለሚማረክሳት የወንዶችን ልብ በተሳሉ ለመስረቅ ቻለች። ዓይንዋ ያዘራል፣ ጉንጭዋ የደም ግምቦን ይመስላል። የቆዳዋ ልስላሴ፣ የዘንርዋ መንዠርገግ፣ የቁመናዋ መለሉነትና የመሳ አካልዋ ተመጣጥኖ መፈጠር ወንዶች በእርስዋ ላይ እንዲያፈጡ ውበትዋ ያስገድዳቸዋል። ሆኖም ግን ፈጣሪ ምንም ነገር ሳይቆጥብ የቸራት ዐጋና ውበት ደስታ ሊያስገኝሳት አልቻለም።

ውበትዋ እንደዚያ ሳማረበት ሰዓት፣ ጊዜ ሀብት የቸረው ዲታ ሽማግሌ ያያታል። የሽማግሌው ሀብት እጅግ የተትረፈረፈ ሊሆን የርስቱ፣ የጥሬ ንዝቡ፣ የቢቱና በአጠቃሳይ የንብረቱ መጠን እንዲያው ዝም የሚያስኝ

Scan by Easy Scanner

ባይኑት ነበር። ሰው ከዚያ የሞተ እንደሆነ የሴቲ ማሽላርቱ፣ በእንቁላ ያሸበ ቁሳቁሱና የቤቱ ኢቃ ባይነት እንኪን የሴቲ የወንድም ቀድብ ቦችሰና ሮሚማርነ ነው። ያህ ሀብታም ሽማሌ ቦትጻና ባይኒው እንደትነን በጠየቀት ጊዜ ነመጀመሪያ ጥያቄው አሮጌ አሳቅት። 'ለምን ገበጺ ነው ደህን የጠነዛ ሽማሌ የማነሙ?' ብላ ራሰዋን ጠየቀት። ጥያቄው ሩላ እንደ ሰድብ ነበር የቆጠሪችው።

«ውጣት ናት፣ ተፈጥሮ ሙበት ቢቸራት ምንም ነባር ያላስቀረባት ለሰነበር ሚንሻሙም ወንድ በእርስዋ ሙበት ሊማረክ እንደሚችል ልነኖቱ ያውቃል። ሆናም ሰውን የማፍቀር ልና ቢናራትም ያህን ሽማሌ ለማፍቀር ግን አልሆነላትም። ሀብት ሊኖረው ይችላል፣ ግን ከሀብቱ ሴላ ቢቶቹን ሊማርከለት የሚችል ኃይል አልነበረውም። 'ታዲያ የመጣትነት ትኩስ ኃይሌ የቀሀቀዘውን የሽማሌ ገላ ለማሞቅ ነው እርሱን የማገባው? ለምን ተነበሱ? ለገንዘቡ?' ስትል ራስዋን ከጠየቀች በኋላ «አይታሰብም» ከሚል ድምዳሜ ላይ ደረሰች። ነገሩ ግን ጉዳዩ ሀቢህ አሳቢም። ያቺ የምትጠላት ሴት ማለት ሺቫንን ያስጠጋው የዚያ ደግ ሰው ሚስት ለሙዱምን እንድታገባ አግባብታት፣ አባበለቻት፣ ከማባለልም አልፋ ጪቀቧቀቻት። ሴትዮዋ አፈ-ጮሌ ብጠ ስለነበረች የልጅትዋን ጪትባ አእምር ለማሰመን ጊዜ አልወለደባትም። የቱበፋ ዓለምን በሚያቦጪብው የአፈ-ጮሌዎች ቃላት ይለለጅት። ያቺ ምስኪን ደግሞ ብዙ ነገር ያላየች የዋህ ፍጡር በመሆንዋ ስለዚህ ዓለም የኑሮ ምሥጢር ብዙ አታውቅም። ሰው ያለ እውነተኛ ፍቅር ተደበቶ ሊኖር እንደማይችል ስለፍቅር ምነኑትና ፍቅር ከሕይወት ጋር ስላለው ቁርኝት ያላት እሰቱቀት እጅግ የመነመነና ስለሚያስከትለው ችግርም ያላት እውቀት ውስን ነው።

«ያቺ የምትጠላት ሴት ለተወለነ ጊዜ ለእርስዋ አሳቢና ተቆርቋሪ ሆነች። ለእርስዋ የምትጪነት በማስመሰል ትንክክባትለች፣ ፍቅር ታሳያታለች። ውበትዋንና ልጅነትዋን በገንዘብ ለመግዛት የጪለገው ሽማሌም ናላዋ እስኪሆር በገጸብረክት ብዛት አሸቄጠቄጣት። ስጠታውና የሴትዮዋ ውትወታ ያንን ሽማሌ አንድታገባው ስሚትዋ ይገፋፋት ጀመር። ትዳር መያዝ ማለት የሚያምር አዲስ ቱሚስ ገዝቶ ማጥለት መሰሳት እንጂ አውጥተውና አውርደውና ብዙ ተጪንቀውና ተጠበው የሚደርስብት ውሳኔ መሆኑን አላጤነችም። ልጅ በመሆንዋ ስለቢህ ጉዳይ የእሳብ ደሃ ነበረች። 'በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግሩ ነውና' አውነታኛና የበለስ መካሪም አልነበራትም። በዚህም ውሳኔዋ 'ባጨዛ ደውጣ' የሚል ስለነበር ለባልዋ

ሥታዛት ያህል ፍትር ሳይናራት፣ ሲት አጅ ችሩ ኑትደጀ ማግለት ረሥፉ ሥላፊነት ሥን እንደሆነ ሳታውቅ፣ ለመውደያና ለማኳሩር ያሰጠ ልብ የጨለገሙን ኑሳጎኝ ሥን ያህል ተሰፋ ሊቆርጥ እንደጣትል ኑተገሰ ያማገሌሙን ኢግተጉሙ። ያንን ሽማሌ ከመታገባ ቪህ ጊዜ ሥታ ቪህ ትኬ ሚትሰበር ይሻላት ነበር። ሥታ ዘቲቀበር ቢሆንስ ኩሜሩ ጋር ይመደነ አርስ ነበራት። ሥለች ይጊነሳ ጎልድትዋ የነገችበት መተመደ ያደጋ አድትዋን በአሳብ አየሸች ሰትል በመጨረሻ ኢሊናርን ጠየቀቻት።

«እሰን ታዞችኝ። እይ ምስኪን፣ ሰታሳዝን፣ ሰግለት ኩመለችጣት በጊነ «ለለልድትዋ ታሪክ ግለቲ ስለሙበትዋ፣ በሰጠባይዋና ሊላዎ ንር ከሰ ይዝርዝር ንገሪኝ» ሰትል ኢሊናር በመገፋት ጠየቀቻት።

«መንዶች ስለእርስየዋ ሲናገሩ 'ቁጊድናዋ በሕልም የሚታይ እንጂ በቆገ ርሚመለከቱት አያመስልም' ይሳሉ። ለእኔም ቢሆን መልከዋ ደሀ ይመሰል ለግለት ይቸግረኛል። ግርማ ሞገስዋ የንጉሥት ቢሆን እኔ ላውቃት ልነሽ ገራሽ ነው። ሰው በሣም ታምሩሰች። ስለመልከዋ ያልሽው፣ እርሱን ያ ወንድ ሁሉ እንደሚለው ከሆን ባእሳብ የሰልዋት እንጂ የእጣር ፍጡር አትመስልም። ብዙ ሙነዶች አጋጺሁ ለዓይናቸው ግረፊያ አንድትሆን ይመኝዋታል እንጂ በአካለቸው ለመገኳት እደደፍሩም። ሁሉም 'መጀም እሺ አትሰኝም' በሚል ሳራዎች ያልቋታል። 'ፕነብብን የዝ ሁሉንም ደገል' በሚል አምነት ነው ሽማሌው ብቻ የደረራት።

«ሰው ለመግሰት ወደ ባሪያ ገበያ እንደሚሄድ ገስሰብ ልጅትዋን ለመግዛትም ሽማሌው ወጣትዋ ወደ ነበረችበት ሄደ። በገንዘቡ ፕቱቶችም ወደ ለንደን ኩሁማ ይዞአት ነጎደ። ከዚያ ሰትደርስ በው ሁሉ እጅን ጀርንቶ ተቀበሳት። መግሰ፣ ሰላምታና ሽንገላ በዙ አሰታቀፍዋት። 'ያዚሀው ቃል ከልብ የመነጪ፣ የዚያ'ፍው ግን ከአንገት በላይ ነው' ብሎ ለመለየት የልጅነት አእምሮዋ አልፈቀደላትም። ይህን ለማወት የመጠቀ እውተትና የበሰለ አስተሳሰብዋን ይጠይቃል።

«በዚያን ጊዜ የልጅነት ሕይወትዋ ምን ይመስል እንደ ነበር በትክክል አውቀዋለሁ። እውነተኛ ደስታ የታለየው ሕይወት ሲሆን ልጅትዋ በኑርዋ እርካታ አልነበራትም። 'የዚህ ያጋጠመኝ ነገር መጪረሻ ምን ይሆን?' ብሎ ከመቄንት በስተቀር በጊዜው ሥንፈስዋን የሚያረክ ሆኖ አላገኘችውም። ቤትዋ ውስጥ ፍትር ሰላልነበረ ደስታ ራቃት። ባለቢትዋ ያያት ሁሉ እርስዋን እንዲያደንትና ሰው ሁሉ በእርሱ እንዲተና ነበር ፍላጎቱ።

Scan by Easy Scanner

«ሰውዬው በተፈጥሮው ክስታራ ይሁን እንጂ እስከዚህም የቀዘቀዘ ስሜት ያለው ሰው አይደለም። ሌላውን ማፍቀር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በመጠኑ ቢገባውም እንደ እርስዋ ግን ሁለመናው በፍቅር ጥማት የተሞላ አልነበረም። የሴትዮዋ ጋብቻ የፍላጎት ቢሆን ወይም ፍቅር የሚያስታቅፍ ባል ብታገባ ኖሮ ወይም ልጅ ብትወልድና እኩያዋን ብታገኝ ሕይወትዋ ጨርሶ የተለየ ይሆን ነበር። በዚያች ሰዓት የሕይወትዋ አጥር የተከበበው ከአሁን ታሁን ምን ይፈጠር ይሆን? ቀጥሎስ ምን ይከሰታል? በሚል ፍራቻ የተሞላ ነበር። ሆኖም የእለት ተለት ሕይወትዋ በጉጉት የተሞላ ነበር። ከመዝናኛ አዳራሽ የገባች እንደሆነ የሁሉም ዓይን ይከተላታል። ዓይንዋን ዞር ዞር ስታደርግ ቢቋንጅና የሚስተካከላት ስለማታገኝ ኩራት ከራት ይላታል። ሴት ናትና በዚህም እጅግ በጣም ስለምትረካ በውበትዋ ትመክለች። ቢሆንም ህብት ከተትረፈረፈበት ቤት ትግባ እንጂ የውስጥ ደስታ ስላልነበራት የአእምሮ ሰላም የላትም። ገንዘብ ሊገዛው የሚችል ነገር ሁሉ ብታገኝም ልብዋ አንድ ነገር በመፈለግ ዋተቱ—ፍቅር። ሰማፍቀርና ለመውደድ ብትፈልግም ፍላጎትዋን ለማርካት አልቻለችም።

«ያቺ እጅግ ያማረችና የደመቀች ሴትዬ ያቺ ለንደን ከተማ ውስጥ ከሚገኙት ታላላቅ መኳንንትና ወይዛዝርት መካከል የምትንፈላሰሰዋ ሴት፡ ያቺ በእንቁና በሴሳም በከበረ ድንጋይ የምታሸበርቅዋ ቆንጆ፣ ያቺ ምርጥ ዲዛይነር በከሸነው ምርጥ ልብስ የምትምነሸነሸና አንደ ዕሐይ የምታበራዋ ሴት ማታ ማታ ብቻዋን ስትሆን ብዙውን ጊዜ ከማልቀሰ በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበራትም።

«አንዲት ሴት ምንም ትሁን ምን፤ ሀብት ይኑራት ወይም መናጢ ድሃ ትሁን ያለ ፍቅር በደስታ ለመኖር ይከብዳታል። ፍቅር ለማንኛዋም ሴት ፍፁማዊ ሚሰሪያ ገመድ ስለሆነ ማንኛዋም ሴት በፍቅር ካልረከች ዘለቄታ ያለው ደስታ አይኖራትም» በትላት ኤሊኖር «እንዲት ያበፈራል» በማለት ተናገረች። ይህን ያለችው በቁጭትና በሀዘኔታ ስለነበር ሲ/ር ማሪን ፈገግ አሰኛት።

«በዚያ በልጅነት አድሜዋ በፍቅር የምትወዲውን ለው ለማግኘት ልብዋ ተንጠልዋሎ ሳለ የዚህ ዓይነት እድል ሲገጣጣት አታሳዝንም? አየሽ ኤሊኖር፣ እኔ አንቺን አስካወቅሁሽ ድረስ እንደዚያች ሴት ምርጫ እጥቶ የተሰቃየ ሰው በዚህ ምድር ላይ የለም ነበር ያልኩት። ይህቺ ሴት፣ ያም ጋብቻ ሆነና ችዳር ተብዬው ከያዘች በኋላ ያላሰበቸውና

ያለጠበቀችው ነገር ደረሰባት። አንድ ቀን ለንደን ከተማ ውስጥ ከሚገኙት ሾፐኖ ናቸው ከሚባሉት ቤቶች አንዱ ወደ ሆነው ቤት ትሄጻለች። ለዚያ ቤት ውስጥ ሕይወትዋን የሚለውጥና የወደፊት እጣ ፈንታዋ የሚወሰንበት ያጋጥማታል» ስትላት «እሺ ንገሪኝ እስቲ፣ ምን ተፈጠረ ልትደን ነው ይገሙ?» ስትል ኤሊኖር ጠየቀች። ቪቫንም ታሪክዋን ቀጠለች።

«ዚያን እለት ነበር ከዚያ ከነበረው ሰው ሁሉ የተለየና ለመልኩ ወደር የሌለው ውንድ ያየችው። የለውጌው ማግር ነበር ልብዋን ከሁለት አመታብዋ የነበረውንና የምትቀርበውን ወንድ ተግጠነችው። ከዚያ ሰው ጋር እንዲያስተዋውቃት ሉተናገረች በኋላ ‘የለም ኤሊኖር፣ ወደ ዝርዝሩ ባልገባ ይሻላል፣ የሆነው ነገር ሰማም አሳዛኝ ስለሆነ መላእክት እንኳን ታሪኩን ቢሰሙ ማዘናቸው አይቀርም’ ብላ ብትናገርም ታሪክዋን ቀጠለች።

«ያቺ ብቸኛና ፍቅር የጠማት ሴት ተሰምቶ በማይታወቅና የፍቅሩ ግለት ለብን በሚያቀልጥ ዓይነት የፍቅር ጽናት ተያዘች። ሰውዬውን ወደደችው፣ አፈቀረችው፣ የእርሰዋ ብቻ እንዲሆን ተመኘችው። በዚያች ሰዓት አውነተኛ ፍቅር ማለት ምን እንደሆነ አውቃ ትምህርት ቀሰመችበት። ተጠራቅሞ የቆየው የፍቅርዋ ጭማት ውልቅ ብሎ ለመውጣት ጊዜ አልወሰደበትም።

«የተራበ ሰው በልቶ የሚጠግብ ለለማይመስለው ከመጎለፍሰፍ አልፎ እግበስባሽ እንደሚሆን ሁሉ እርስዋም የፍቅር ረሃብተኛ ስለነበረች ያላየችው መነሰፍሰፍ ከሥሃብተኛው ብዙም የራቀ አልነበረም። ልብዋ የተመኘውን ለማመመው ያግኝችውን ከመጨበጥ ወደ ኋላ አላለችም።

«አስታውሺ ኤሊኖር፣ ይህቺ ሴት ውስጥ ውስጡን ደስታ እንክት ሲያደርጋት የፍቅር ዋዜማ እንደሆነ አልገባትም። ቢሆንም ውብ ነገር ሆኖ ነው ያገኘችው። ከዚያ በፊት በሕይወት ዘመንዋ ያላጋጠማት አዲሱ ስሜትዋ ክቡርና መለኮታዊ መሆኑን ስላመነች ከመቀበል አልፋ ተቀበለችው። ነገር ግን ሊቋቋሙት የማይቻልና ልብን የሚከዳ ስሜት ሆኖ ስላገኘው ልብዋ ተሰበበ። እሁን የሥትኖርበት ዓለም በድንገት የተለመጠ ሌላ ዓለም መሰላት እንጂ ወትሮ የምታውቀው ዓለም አልመስልሽ አላት። የእለት ተእለት ሕይወትዋም እንዲሁ ከመቅጽበት ተለወጠ። ልብዋ፣ አስብዋና ዋላጎትዋ ሁሉ በአንድነት ተጠቃልሎ ከአዲሱ ፍቅረኛዋ ቤት ገቢ። ዓለም ግለት ይህ ሰው ብቻ እንደሆነ ዓይነት ስሜት ተሰማት።

Scan by Easy Scanner

«ስለሰውዬው እንኳን ከመናገር ትንሽ ቆጠብ ማለቱ ሳይሻል አይቀርም። ብቻ ታሪኩን ለመደበቅ ሳይሆን እንደ እርስዋ ስለእርሱ ስለማላውቅ ገዢነር ሁኔታውን ለመግለጽ ይከብደኛል። ሆኖም ግን እርሱም በበኩሉ እንዳይነቃበትና በማም እንዳትረባት እሠታለሁ። በድርበቡ ቢሆንም ሳይወዳት አልቀረም። ከዚያ ሁሉ መኪንንትና ትላልቅ ሰዎች መካከል እርሱን በመምረጥዋ ኩራት ኩራት ሳይለውም የቀረ አይመስለኝም። ነገር ግን» አለች ሲር ማሪ የሀዘን ስሜት እያተስማቷ፤ «ከልብ የወደዳት ስለማይመስለኝ እንደ እርስዋ በፍቅር ወጥመድ መያዙን እጠራጠራለሁ። ስሜት አስገድዶት ተከትሎአት ሄዶ ይሆናል እንጂ እንደ እርስዋ በፍቅር ገመድ ተተብትቦ መሳተኑን አላውቅም። በመጨረሻ የሆነውንም በለማላውቅ እርግጠኛ ሆኜ ለመናገር ቢከብደኝም በውዐትዋና ባሳየችው የፍቅር ስሜት ተበሰበ ተማረከላት እንጂ ከልቡ እንዳልወደዳት ለመናገር እችላለሁ። ሲገናኙ ምን ይመሩ እንደ ነበር አላውቅም እንጂ በቀን በቀን መገናኘታቸው እርግጥ ቢሆን የፍቅርዋ ጽናትና ብርታት ከሰውዬው እንድትለይ ስላልፈቀደላት እንጂ ላይ ተጠምጥማ አለቅህም እንዳለችውም እውነት ነው። ይህን በማይረባዋ ፈጣሪ ብቻ ነው ትክክለኛ ፍርድ ሊሰጣት የሚችለው። የማመዝበን ኃይል ስላልነበራት የሰሜት ተገዥ ሆነች። ከዚህ በሀተት ውስጥ የገባችውም ወድዳ ሳይሆን በግዴታ እንደሆነ አመነችበት።

«የእርስዋ ፍቅር አንዳንድ ሴቶች እንደሚያደርጉትና በኋላ መውጫ ቀዳዳ እንደሚያጡለት በቀልድ መልክ ሦስጀመረ የፍቅር ግንኙነት አልነበረም። ገና ከመጀመሪያው ብርቱ የሆነ የመማረክ ስሜትዋ ሀሊናዋን ያሳወረው። ወደ ዓፋት ያሚያመራ ጎዳና ጠመዝመዝና በአሰቦ ያጌጠ ሲሆን እርስዋ በቅድሚያ ያየችው አበባውን ነው። ከአበባው በር አሜከሳ እንዳለ አልተገነዘበችም።

«ሁለቱ ሰዎች ከሥን ዓይነት ስህተት ውስጥ እንደ ተዘፈቁ ያወቁት ወደ በስተ መጨረሻ ነው። ሰውዬው ከእንቅልፉ የነቃው መጨረሻ ላይ በመሆኑም ከገደል አፋፍ ላይ መቆማቸውን የነገራት ያኒ ነው። በዚያን ጊዜ እንኳን እርግጠኛ ነኝ ፍቅር አልያዘውም። ለሰሜቱ ማርከሊያ ብቻ እንድትሆን ነው የፈለጋት። የታወረውና ያልተገደበው ፍቅር የእርስዋ ብቻ ነበር። እርስዋ ከልብ በመነጨ የፍቅር ስሜት አምርራ ስትወደው እርሱ እንዴ እርስዋ በፍቅር ባለመከነፉ ተለያዩ። ከዚያም እርሱ መጸጸቱ ከተማ ተመለሰ። እርስዋ ግን ያሲ እርሱ ለመኖር ትችል እንደሆነ የተጉላትን ሁሉ አደረገች። ለተወሰኑ ቀናት እንደ ምንም ብሳ ቻለችው።

ቀን እያለፉ ሲሄድ ያቺ የተከፋች ምስኪን ሴት ያለ እርሱ ሕይወትዋን መግፋት እንደማትችል አመቀች። በመካከሉ ሽማግሌው ባልዋ እንዳንድ ቆንጮ በማየታቸው ሐቀኛነትዋን ተጠራጠሩ። ስለመደደችው ሰው ወሬ ተነስቶ በእርሱ ምክንያት ባልና ሚስት ተጣሉ። ሲጣሉ ቤቱን ጥለለት ወጣች። ከቤትዋ ከወጣች በኋላ ለፍቅረኛዋ ደብዳቤ በመጻፍ በእስቸኳይ ወደ እርስዋ እንዲመጣ ተማጠነቸው። መማጠን ብቻ ሳይሆን አጥብቃ ለመነችው። በፍጥነት መጥቶ ዓይኑን ካላየች ሕይወትዋን የምታጠፋ መሆኑን ገልጻ ነው ደብዳቤ የጻፈችለት። እሱም ፍቅር ያስተማራትና ይህን ሥሜድረጉ የበደላት መሆኑን ልበናው ስለሚያውቅ ከነበረችበት መጣ።

«ጸግም ከተገናኙ በኋላ ሁለተኛ ጥሎአት አልሄደም። ምናልባት ልቡ ውስጥ ትልቅ ትግል መካሄዱን አምናለሁ። እጅግ በጣም ስለምትወደው በፍቅርዋ ጽናት ተማርኮ አሳቡ ስለተከፈለበትና ወጥመድ ውስጥ ስለገባ ምንም ሊያደርግ አልቻለም። በእርግጥም ውድ ልጅ ቆንጆና በስሜት የተዋጠች ሴት አለቅህም ብሳ ከሰውነቱ ላይ ስትጠመጠም ከእርስዋ ለመለየት ይከብደዋል። አምላክ ካልረዳው ከመዳፍዋ በር መውደፋ አይቀሬ ነው። በዚህም ሰው ላይ የደረሰው ደኽው ስለሆነ አገራቸውን፣ ቤቶቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ጥለው ወደ ውጭ አገር ለመሄድ ዝንጅት አደረጉ። የሚያዝነው ደግሞ የፈጣሪን ቁጣ ተሸክመው ነው አንዱ ለሌሳው ቢል ውጭ አገር ሂዶ ለመኖር የተነሳሱት። አገር ጥሎውና ርቀው ለመሄድ የወሰኑት ያለፈውን ሕይወታቸው የሚያስታውሳቸውን ነገር ከሚሄዱበት አገር እንዳሚኖር ስለገመቱና ስላመኑ ነው።

«ያን ጊዜ እንኳን ቢሆን» አለች ሲር ማሪ «ያን ጊዜ እንኳን ቢሆን ሳቅፎ ሊሰማት ልቡ ውስጥ ፍቅር አልነበረም። ታሪኩን ስለማውቅ አሁንም ቢሆን አረጋግጬ ለመናገር እችላለሁ። እርስዋ ግን በፍቅር ስለታወረች ይህን ማየትና መገንዘብ አልቻለችም። ከሰውዬው ፍቅር ሌላ ምንም ነገር ቢሆን ጭንቅላትዋ ውስጥ ዘልቆ ሊገባ አልቻለም። ለአሞር ጊዜ ቢሆንም ለደስታዋ ወሰን አልነበረውም፣ ለአሞር ጊዜ ብቻ! ነገሩን ባሰብኩት ቁጥር ለዚያች ምስኪን ሴት አልቅሺ፣ አልቅሺ ይለኛል። ከዚያም አልር !ከልብሽ አዜኒላት› እያለ ሀሊናዬ ይውተውተኛል።››

ይህን እንዳልች እውነትም ከዚያች ቆንጆ ፊትና ውብ ዓይኖች የእምባ ዘለላዎች ኩስል ብለው እንደ ጎርፍ ፈስሱ፣ ተንጠባጥበውም የለበሰችውን ልብስ አራሱ። ይህን ጊዜ «አይ ምስኪን!» አለች ኤሊኖር። ምስኪን ብሱ

መናገር ይቀናታል። «ታሪኩ አሳዛኝ ነው፤ ግን የኃጥያት መጨረሻው ሁሌም ሀዘን ነው» ስትል «የፍቅር መጨረሻም ሀዘን ነው» አለች ሲ/ር ማሪ። «ከፈጣሪ ፍቅር ሌላ» በማለት ራስዋን አረመች።

«አይ፣ የሁሉም ምድራዊ ፍቅርም ቢሆን መጨረሻው ሀዘን ነው ብሎ ለመደምደም ይከብዳል» ስትል ኤሊኖር ጣልቃ በመግባት ጮክ ብላ ተናገረች። «እርግጥ ነው ሴቶች ወንዶችን ሲያፈቅሩ መጨረሻው ሀዘን ሲሆን ይችላል። ለምሳሌ እናት ለልጆችዋ ያላትን ፍቅር ተመልከቺ። ከዚህ ዓይነቱ ፍቅር ሀዘን አላይበትም። ሲስተር ለምን ይሆን ልጅትዋ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ተደስታ የኖረችውን ምክንያቱን ብታሰረጂኝ ደስ ይለኛል።»

ምዕራፍ ሃምሳ አራት

ቃልዋን ሰጠቻት

«አሁን የማወራልሽ» አለች ሲ/ር ማሪ ቀጠለችና፤ «ፍቅረኞቹ ወደ ማይታወቅ ግን ተስፋ ወደ ተጣለበት አገር ነበር ለመሄድ ያሰቡት። ወደ እዚያም በመሄድዋ ያቺ ምስኪን ከህሊና ወቀሳ የምትርቅና በሠራችው ሥራ የማትጸጸት መስሎአት ነበር። ለማንኛውም ግታውኑ ጨረቃ ወለል ብላ ወጥታ ሳለ ጉዞአቸውን ለመጀመር ተነሱ። በመርከብ ለመሳፈር ወደ ባህር ዳርቻ ሄዱና ከዚያ ቁጭ ብለው ጨዋታ ጀመሩ። እንዲያው ያቺ ረዳተ-ቢስ ምስኪን፤» ካለች በኋላ ቢቫን አሁንም ማልቀስዋን ቀጠለች።

«ኤሊኖር እምባ በአምባ በመሆኔ አትሰልቺኝ፣ ልጅትዋ በጣም ስለምታሳዝነኝ ነው። የእርስዋ ጉዳይ በተነሳና ትዝ ባለኝ ቁጥር የማደርገውን ያሳጣኛል። ለጥቂት ሰዓቶች ደስታ ተብሎ የተሰዋ ሕይወት ይዘገንነኛል፤ ያሳዝነኛል። ያቺ ምስኪን የጨረቃ ብርሃን ከውሃ ላይ አርፎ መብለጭለጩን አያየች ታዋራዋለች፣ ጉንጩን ትስማለች። እርሱ ግን ሳይታሰብ በድንገት ጸጥ ይልባታል። ከባድ የሆነ ሀዘንም ከፊቱ ላይ ይነበባል። ስለምን እንደሚያስብ ሰትጠይቀው ሳያስብና ሳያሰተውል ይመልስላታል። ምን ብሎ መልስ የሰጣት ይመስልሻል?

«ስለልጆቼና ስለባለቤቱ!»

«ጨረቃ ብርሃንዋን መስጠት ቀጥላ ከጨረቃዋ የሚፈነጥቀው ብርሃን ከመርከቡ ተንፀባራቂ አካል ላይ በማረፉ ለመርከቢቱ የተለየ ድምቀት ሰጥቷል። በተለይ ደግሞ በማዕበል የሚርገበገበው የባህር ውሃ ከነብርሃኑ

ከመርከቡ ጋር ሲጋጭ ማየቱ የተለየ ደስታ ያስታቅፋታል። ወዲያው ደግሞ ማዕበሉ አይሎ ውሃው በይበልጥ ስለተተራመሰ ያንን የተፈጥሮ ውበት አያደነቁች ሳለ ነበር አሳዛኙን ዜና የሰማችው። ስተወሰነ ጊዜ ቃል ለትተነፍስ ዝም አለች። በጦር እንደ ተወጋ ሰው ከተቀመጠችበት ድንጋይ ሆና ቀረች። እነዚያ ቃላት ልብዋን ከሁለት ነው የሰነጠቁት። ቆይታ ቆይታ «ምኔን ነው ያልከው?» ብላ ጠየቀችው። ያ ቅጥ ያጣው ፍቅርዋና የወይፊት ተስፋዋ ሁሉ በአንድ ጊዜ ጭልምልም ብሎ አፈር ድሜ ሲግጥ በአሳብ አየችው።

«ሚስቴና ልጆቼ» ሲል ደገመላት። ከዚያ በኋላማ ሲትቦዋ በይበልጥ ድንጋይ ሆነች። ትዳር አለው ብላ ያላሰበችውና ያላለመችው ነገር ስለሆነ አለመሞትዋም የሚደነቅ ነው። የምትይዘውና የምትጨብጠውን አጥታ ከው ብላ ቀረች።

«እንዴት ይገርማል» ስትል ኤሊኖር ተናገረች። «ትዳር ያለው ሰው ለመሆኑ ቀደም ሲል ማወቅ ነበረባት። አንድ ወንድ ትዳር ያለው ከሆነ ሰለእርሱ ትዳር መያዝ ማንኛውም ሰው ያውቃል።»

«አታውቅም ነበር» አለች ሲ/ር ማሪ። «ትዳር እንዳለው ጨርሶ አልጠረጠራትም። ይህ ሰው ለንደን ከተማ ውስጥ ዘወትር ይታይ የነበረው ብቻውን ነው። የትም ሲገናኙ ባስቤቱን ይዞ አልመጣም። ሌላው ነገር ደግሞ የትዳር ጓደኛው እስከዚህም የታወቀች ሴት አልነበረችም።»

«ክፉ ሰው ቢሆን ነው ይህን የደበቃት» ብላ ኤሊኖር አሳብዋን ስትሰነዝር «አንዳንድ ጊዜ እኮ ሰዎች በሚገባ ካላጤኑት እዳ ውስጥ ሲገቡ መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል አያገናዝቡም» በትል ሲ/ር ማሪ ግልቃ ገባች። «አዋቂና ጎበዝ ሰው እንደ ነበር ስምቻለሁ። ምናልባትም በዚያን ጊዜ የፈጸመው ስህተት የመጀመሪያው ሊሆን ይችላል። ግን ለዚህ ስህተት የከፈለው እዳ በጣም ከባድ ነው የሚመስለኝ። መርከቡ ጉዞውን ለመቀጠል ሲዘጋጅ መለያየት እንዳለባቸው ነገረችው። 'ከሁለት ያጣ' ይሉሻል ይኼ ነው። መለያየት ብቻ ሳይሆን ዳግም መገናኘት እንደሌለባቸውም ገለጸችለት። እኔ እንደማውቀውና እርስዋም እንደ ተናገረችው፣ ሰውዬው የሌላ ሰው ንብረት መሆኑን ስትገነዘብ እንደ አሳት ነው ያቃጠላትና ያንገበገባት። በእርስዋ እምነት ሰውዬው ከእርስዋ ሌላ የሚወዳት ሴት በዓለም ላይ አልነበረችም፤ አሁን ግን አለች። በመጀመሪያ እንደ ማበድም እንደ መሳትም አደረጋት። ብሽቀቱ እጅግ በጣም እንጨባረራት። ሰውዬው

ሁናቴዋን ሲያይ «ይህን ያህል ማልቀስ እኮ የለብሽም፣ የገደልኩሽ ያህል ነው የተሰማኝ» አላት።

«የሠራኸው ሥራ ከዚያም የከፋ ነው» ስትል መለሰችለት። «ባጣዋ ነው የጨከንክብኝ። ወደድኩህ፣ አፈቀርኩህ፣ አሁንም እወድሃለሁ። ገና ከመጀመሪያው አሁን የነገርከኝን ባውቅ ኖሮ የሌላ ሴት ባል አልሰርቅም፣ አቅመ-ደካማ ከሆኑ ልጆችም አባታቸውን የመቀማት ኃይል አይኖረኝም ነበር። የዚያን ዓይነት ባህርይ ያላት እቡይ ሴት አይደለሁም። አባት ልጆቹን ማፍቀርና መንከባከብ ሲገባው እኔ ልነጥቃቸው፣ የዚህ ዓይነቱ ጭካኔ አልተፈጠረብኝም። በሕይወት ዘመኔ ሁሉ የምወደው ነገር ቢኖር እውነትን ይዞ መጓዝ ነው። በለሳብ የሳልኩህ እንጂ በውን በአካል ያገኘሁህ አይመስለኝም ነበር። ከወንዶች ሁሉ አንተ ብቻ ነህ ልቤን ሰውረህ በፍቅር ያሳበድከኝ። ነገር ግን አሁን ያወጣኸውን ምሥጢር ቀደም ብዬ ባውቅው እስከዚህ በፍቅርህ አልጠመድም፣ ስለአንተም ደንታ አይኖረኝም ነበር። የሌላ ሴት ባልና የልጆች አባት መሆንህን ነግረኸኝ ቢሆን ገና ከጅምሩ አልጠጋህም ነበር» ብላ ስለልጅትዋ ታሪክ ነግራት ቀጠል አድርጋም «ልጅትዋ አታሳዝንሽም?» ስትል ኤሊኖርን ጠየቀቻት። «ሕይወትዋን በሙሉ አሳልፋ የሰጠችው ለዚያ ቅጽበታዊ ደስታ ነው።»

«በጣም ነው የምታሳዝነው» በማለት ኤሊኖር መለሰችላት። «የህዘኔታዬ መጠን ይኼ ነው ልልሽ አልችልም። በርግጥም ምስኪን ሴት ናት።»

«ካሳዘንኸሽ ስለልጅትዋ አስተዛዝኜ ሰናገር ሦን ማለቱ እንደሆነ ገብቶሻል ማለት ነው። ይኸውልሽ የምስኪን ምስኪን ማለት እርስዋ ናት» አለች ሊሪ ማሪ። «ብዙ ሰዎች በእርስዋ ላይ ይፈርዳሉ። ሆኑም ቀረም የልጅትዋ ታሪክ የሚያበቃው ከፍቅረኛዋ ጋር ለዘላለም ስትለያይ ሲሆን ስውዬው ስትለየው 'እፎይ ተገላገልኩ' ይበል ወይም ይናደድ የሚታወቅ ነገር የለም። እርስዋ ግን ከውሳኔዋ ነስንስ አላለችም።

«ከደረሱበት ደርሰው በመጨረሻ መለያየት፡ ጠቃሚታ ስለሌለው አብረው እንዲቆዩ ሰውዬው ብዙ ለመናት፣ ተማጸናት። ከዚያ በኋላ ወደ ባልዋ ተመልሳ ለመሄድ እንደማትችልም አስረዳት። እርሱም ቢሆን ወደ ቤቱ ለመመለስ እንደማይችል ነገራት። እርስዋ ግን አሳብዋን ለመቀየር አልፈለገችም። ከነአካቴው ስለምንም ነገር መነጋገር ስላልፈለገች ከነበሩበት ጥላው ሄደች። አየሽ ኤሊኖር፣ ልጅትዋ በለራስዋ ስትናገር እንዳለችው ክፉ ሴት በመሆንዋ ባልናጎን ጥሳ ነው ያሄደችው። ነገር ግን ክፉና እቡይ ሴት ብትሆንም እስከዚህ ጨከና የሌላ ሴት ባል መቅማት አልፈለገችም፣ በተለይም የልጆች አባት።»

«ምናልባት እኮ በአንድ ወቅት ጨዋና የተከበረች ሴት ልትሆን ትችላለች» በማለት ኤሊኖር ስትናገር «አዎን ጨዋ ነበረች፣ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ እንደ ሰማሁት ልጅትዋ ወደ ቤትዋ አልተመለሰችም። ባለመመለስዋም ሰው ሁሉ የገመተው ከፍቅረኛዋ ጋር እንደሆነች ነው። ግን ሥጂንችሽ ነገር፣ እንኳን እርስዋ ፍቅረኛዋም ወደ ቤቱ አልተመለሰም። እርስዋ ከዚያ በኋላ የት እንደ ሄደች፣ እርሱም የት እንደ ደረሰ እንቆቅልሽ ሆኖ ነው የቀረው። ሰዎች ግን 'አብረው ናቸው' እያሉ ያወራሉ።»

«ማራ የሚያጋባ ታሪክ ነው» አለች ኤሊኖር አሳብ እንደ ገባው ሰው ዝግ ብላ።

«እውን ልክ ነሽ፣ ነገሩ ሁሉ ግራ የሚያጋባ ነው። ከሰማኋቸው አሳዛኝና እውነተኛ ታሪኮች ሁሉ የዚያች ሴት ሕይወት በዚያ ቅጽበታዊ ደስታ የተነሳ እንደ መበላሸቱ ያህል የሚያሳዝነኝ ታሪክ የለም» ስትላት «ልክ ነው ያሳዝናል» አለች ኤሊኖርም። «ቤትዋን ጥላ ከመሄድ በስተቀር ሌላ የሠራችው ኃጥያት የለም። ለምን ይሆን ወደ ቤትዋ ያልተመለሰችው?»

«ለምን እንዳልተመለሰች ግልጽ ነው። ባልዋን ጨርሶ አትወዳቸውም። በኋላ ደግሞ ሙሉ ልብዋን ለዚህኛው ወንድ ነው የሰጠችው። ልብዋ በዚህኛው ወንድ ተሰርቆ ሳለ እንዴት ብላ ወደ ማትወደው ሰው ትመለስ ስለዚህ የት እንደ ሄደች አይታወቅ እንጂ አገር ጥላ መሄድዋ እሙን ነው። ወደ ባልዋም ይሁን ወደ ሥጋዊ ዓለም እንዳልተመለሰች እርግጠኛ ነኝ።»

«ሞታ ይሆናላ» አለች ኤሊኖር ሀዘን እየተሰማት።

«ይኸላታል፤ ከዚያ የተሻለ ምን ምርጫ አላት ብለሽ» ስትል ሊሪ ማሪ ሀዘን እየተሰማት ተናገረች። «የሕይወት ጣዕም አጥታ ከምትኖር መሞቱ ነው የሚበጃት» ስትላትም «ሰውዬውስ ምን ሆኖ ይሆን?» ስትል ኤሊኖር ጠየቀች ከአጭር ጊዜ ዝምታ በኋላ።

«እኔ እንጃ! ኩተለያዩ በኋላ ስለእርሱ የሰማሁት ነገር የለም። ደፍሮ ወደ ቤቱ ለመመለስ እንዳልቻለ ግን አውቃለሁ። ምናልባትም ሚስቱን ፈርቶ ይሆናል። 'ከቤቴ ብመለስ ይቅርታ አታደርግልኝም' ብሎ ተጠራጥሮም ሊሆን ይችላል» ባለቻት ጊዜ «ነገር ግን» አለች ኤሊኖር፣ «እኔ

እንደሚመስለኝ ምንም እንኳን ሰውዬው ደካማና ቂል መስሎ ቢታይም ጥፋቱ በይበልጥ የሴትዮዋ ነው» በማለት በሴትዮዋ ፈረዱች።

«ቀደም ሲል እንደ ነገርኩሽ ከልብ ሰለመነጨው ፍቅርዋ የምጠራጠረው አይደለም። በጣም ትወደው ነበር። ለማንኛውም የህሊቱ ሰዎች ሕይወት ብልጭ ካለ በኋላ ድርግም ብሎ ነው የጠፋው። ስለእንድ ነገር አሳብሽን ስጪኝ እስቲ። አንቺ የዚያ ሰው ሚስት ብትሆኚና ወጂ ቤቱ ተመልሶ ቢመጣ 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ብለሽ ትታረቂው ነበር? እንዴት ብሎ ከወጥመዱ ውስጥ እንደ ገባ በማመዛዘን ማሰቡ ነው። ይህ ሰው በፍቅር ተደልሎና በውዳሴ ከንቱ ተታልሎ ነው ከዚህ ወጥመድ ውስጥ የገባው። ለንደን ከተማ ውስጥ የታወቀች ቆንጆ ሴት አፈቀረችው። ከአርስዋ ሸሽቶ ርቆ ሊሄድ ቀርቶ ከመጻፍዋ ሰር ሊያመልጥ አልቻለም። ቶሎ ድረሰልኝ ብላ ጠርታው አገር ጥለው እንዲከበልሉ አጥብቃ ለመነችው። የዚህ ዓይነቱን ፈተና ሊቋቋም የሚችለው የትኛው ወንድ ነው? አንቺ የዚያ ሰው ሚስት ብትሆኚ የነገሩን አመጣጥ በማመዛዘን ይቅር ትይዋለሽ ወይስ አትይውም ኤሊኖር?» ብላ ስትጠይቃት ኤሊኖር ግራ ተጋብታ ፈዝዛ ቀረች። ቆይታ ቆይታ እምባዋ ግጥም አለ።

«አዎን» አለች ሬጋ ብላ እምባ እየተናነቃት። «ሚስቱ ብሆን 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ብዬ እታረቀዋለሁ።»

«ያልሽውን በማለትሽ ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ» ካለች በኋላ ሲር ማሪ አምርራ አለቀሰች። ትንሽ ቆየችና «በዚያች ምስኪን ሴት ላይ ፍርድ ስጪ ብትባይስ ትጨክኚባታለሽ? ወይስ እርስዋንም ትምሪያታለሽ» ብላ ስትጠይቃት «እንዲህ ያለውን አያምጣ» አለች ኤሊኖር። «በሂዚው በሥራችው ሥራ ተጸጽታ ተመልሳለች። ቢሆንም ነገሩን ጠለቅ ብለው ሳይሆን ላይ ላዩን ሲያዩት ከባድ ኃጥያት ነው የፈጸመችው።»

«ይህን እውነተኛ ታሪክ ለምን ብዬ እንደ ነገርኩሽ ገብቶሽ የለ? ታሪካቸውን ያጫወትኩሽና የፍርድ ውሳኔ ያስተላለፍሽባቸው ሁለት ሰዎች ኃጥያት በባለቤትሽና በአንቺ መካከል ከደረሰው ጋር ሲነጻጸር የእናንተ ያንሳል እንጂ በምንም ዓይነት መሰፈርት ሊበልጥ አይችልም» ብዬ አስባለሁ።

«የነገርሽኝ ዓይነት ሌላ አሳዛኝ ታሪክ ይኖራል ብዬ አልገምትም» በማለት ኤሊኖር ስትመልስላት ሲ/ር ማሪ ደንግጣ ቀና ብላ በማተኩር

አየቻት። ግን ኤሊኖር የጥርጣሬ መልክ አሳሳየችም። ፊትዋ ላይም ለውጥ አልታየም። የነገረቻት ታሪክ የራስዋ ስመሆኑ ጨርሶ አልገባትም።

«ባለቤቴን የቀማችኝ ሴት በአርግጥ ደፋርና ባለጌ ስመሆንዋ የሚያጠያይቅ አይደለም። በነገርሽኝ ታሪክ ውስዋ ከተጠቀሰችዋ አሳዛኝና ምስኪን ሴት ጋር የማትነጻጸር ክፉ ሰው ስለሆነች ጨርሶ የተለየች ናት።»

«እንዴት ልታውቂ ቻልሽ ልጂ? እርስዋም ብትሆን እስ ከዚህ የከፋ ታሪክ ሊኖራት ይችላል። ማን ያውቃል እንበል የእርስዋም ታሪክ ከዚህችዋ ሴት ታሪክ የከፋ ቢሆን ይቅር ትያታለሽ?» ብላ ስትጠይቃት አሁንም ከፊትዋ ላይ የርህራሄ ስሜት አልታየም። እንዲያውም ከአካቴው የበቀል ስሜት ያደረባት ይመስል ፊትዋ ቱቲዋወጠ።

«ጭካኔ የተሞላባት ሴት በመሆንዋ ማድረግ የሌለባትን ድርጊት ነው የፈጸመችው» አለች ኤሊኖር በዝግታ። «የሊንዋ እመቤት ቪቫን ባለቤቴ ትጻር ያለው ሰው መሆኑን ማወቅ ነበረባት።»

«ላታውቅም ትችላለች» ስትሳት «ካሳወቀች በይበልጥ መወቀስ ያለበት ባለቤቴ ነው» በማለት ኤሊኖር መለሰችላት። «ትጻር ያለው ሰው ስመሆኑ ከደበታት እርሱ ላይ ነው ኃጥያቱ የሚበዛውና ጥፋቱም የሚሆነው።»

«አንድ ነገር ንገሪኝ አቦቲ» ስትል ሲ/ር ማሪ አጥብቃ ያዘቻት። «የሊንዋ እመቤት ቪቫን በዚህ ዓይነት መታለልዋን ብትደርሺበት ይቅርታ ታደርጊላታለሽ?» ስትል በመከሳተር ጠየቀቻት። በዚህ ጊዜ ኤሊኖር ሳታመላክል «አምን ይቅር እላታለሁ» ብላ መለሰችላት።

«ፈጣሪ ሁሉንም ነገር ያመቻቻል» ስትል ሲ/ር ማሪ ተናገሪች። «አሁን እንግዲህ ወደ ጀመርነው ጨዋታ እንመለስ። ባለቤትሽ ወደ ቤቱ ቢመለስ እርሱንም ይቅር ትዪው የለ? ልብሽ ፍህሩህ..» ብላ ስትጀምር ኤሊኖር ጣልቃ በመግባት «ልቤማ ከመቁሰል አልፎ ተሰባብሮአል» አለቻት። «ልቤ ተሳልሟል፣ ተሸራርፎአል» አለች ቀጠለችና። «ቢላሳተና ቢሰባበርም ግን አልሞተም፣ ሕይወት አለው። ሕይወት ስሳለውም ይንቀሳቀሳል። በሕይወት ከተንቀሳቀሰ ደግሞ 'ፍቅረኛዩን ስጡኝ' አደለ መወትወቱ አልቀረም። አሁንም ጥሌን የክበለለውን ወንድ አምጪ አደለ ይጠይቀኛል።»

«ካሳሰበው ፈተና ውስጥ ገብቶና በሰው ተመርቶ የሄደ ሰው ብትዪ ይሻላል» ስትል ሲ/ር ማሪ ጮክ ብላ ተናገረች። «ሰማሽ ኤሊኖር ያሁኑን

ብቻ አይደለም ማየት ያለብሽ። የወደፊቱንም ለማየት ሞክሪ። አሁኒ ሌላም ነገር ልጠይቅሽና መልሱን ንገሪኝ። ለመሞት እያጣጣርሽ ነው እንበል። በዚያች ሰዓት አልጋ ላይ ተኝተሽ 'ሁለም ነገር ገደል ይግባ በዓለም ላይ ያለ ሁሉ እንደ ፈለገው ይሁን፤ በአፍ ጢሙ ይደፋ፤ እኔ ብቻ ሰሞት መንግሥተ-ሰማይ ልግባ' ማለት ትጂያለሽ?» ብላ ሰቅጠ ይቃት «እይ እሱንስ አልልም፤ ከባለቤቱ ጋር 'ይቅር ለእግዚአብሔር ብንባባል' ብዬ ማለቤና አሳቤን መግለጼ አይቀርም» ስትል መለሰችላት።

«ታዲያ መጪረሻው ሰዓት ላይ ማለቴ ከሞት አፋፍ ላይ ሁነሽ ይህን የምትዪ ከሆነ ከአሁኑ መታረቁ ምን ይገዳል?» ብላ ስትጠይቃት ዝም ዝም ተባባሉ። ከአጭር ጊዜ ዝምታ በኋላ ግን ኤሊኖር ከሲ/ር ማሪ አንገት ላይ ተጠመጠመች።

«ሲ/ር ማሪ» ብላ ስምዋን ጠርታ «ባለቤቴ ይቅርታ ሊጠይቀኝ ከመጣ ይቅርታ አደርግለታለሁ፤ ልቤ ቂም ሳይቋጥር እቀበለዋለሁ» በማለት ኤሊኖር ስትመልስላት ቪቫን ምኞትዋ ሰለተሳካላት በጣም ደስ አላት።

ምዕራፍ ሃምሳ አምስት

ከማድያ የከፋ

ሰር ልዮኔል ራይጸል ከቪቫን ጋር ከተሊያየ በኋላ ተደስቶ የሚኖር ሰው አልነበረም። ኑሮውን የሚገፋው በቁሞትና ራሱን በመበደል ሲሆን የየእለት ሕይወቱን የሚመራው የህፍረት ማቅ ለብሶ ነበር፤ ያም ኑሮ ከተባለ። ጠዋት ማታ ራሱን ስለሚገስጽ በሕይወት ሰመቆየት የነበረው ጉጉት እሰከዚህም ሆነ። አንዳንዴ የሠራው ሥራ ትክ ሲለው 'አሁን እንደ እኔ በሕይወቱ የቀለደና ኑሮውን በገዛ እጁ ያበላሸ ሰው በዓለም ላይ ይገኝ ይሆን?' እያለ ራሱን ይጠይቃል።

ሁለቱ በተለያዩበት እለት ቪቫን ትነግረው የነበረው ነገር እውነት ለመሆኑ እንኳን ሰይጥ ለማወቅ አልተቻለውም። 'ሁለተኛ አንገናኝም' ስትለው ቀልድ እንጂ እውነት አልመሰለውም ነበር። ነገሩ እውነት ሆኖ ሲመጣ ግን በጣም ነው የተገረመው። መገረም ብቻ ሳይሆን ክው ብሎ ነው የደነገጠው። ለረጅም ጊዜ «ዳግም እንገናኛለን» የሚል ተስፋ ነበረው። በተሰፋ ብቻ ሳይወሰን ያምንበትም ነበር።

ቪቫን ከአጠገቡ ከሄደች በኋላ ከባሀሩ ጻርቻ ከአሸዋው ላይ ለረጅም ሰዓት ከወጪያ ወዲህ እያለ ተጎቀራጠጠ። እንደ ተለያዩ ርቃ እስከትሄድ ድረስ በዓይኑ ተከተላት። ልክ ከዓይኑ ስትሰወር ባህሩ በሚሰበል ተናውጠ ሰለነበር ከዚያ ሙስጥ የገባችም መሰለው። እየጮኽ ወደ ነበረችበት ሮጠ ግን አላገኛትም። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ዓይንዋን አላየም።

ሰር ልዮኔል ከዚያ በኋላ እጅግ በጣም ነው ግራ የገባው። ግራ ስለተጋባም የሚያደርገውን ያላጣዋል። ራሱን በአሳብ ባህር አሰምጦ ከነበረበት ብዙ ከቆየ በኋላ ሌላ ምርጫ ስላልነበረው ወደ ዎሪስ ከተማ ለመሄድ ከመርከብ ሙስጥ ገባ። ቀደም ሲል ከባህሩ ጻርቻ የሄደው በሌላ ባቡር ሲሆን በዚያን ሰዓት ቪቫን አብራው ነበረች። አሁን ግን ብቻውን ስለነበር ባዶ የመሆንና የቀፎነት ስሜት ተሰማው። በቡጢ እንደ ተመታ ሰው ነገሩ ሁሉ ዞረበት። ግን ነገሩ ሁሉ ቢምታታበትም ሰውር ሃሊናው ከሞንቶቱና ከሀሊና ወቀሳው 'የአሁኑ ይሻላል' የሚል መልእክት በቋሞት አሰማው።

ሰውዬው በተፈጥሮው ከሺና ክሩ ሰው ስላልነበረ በሴት ጮሌ ምሳሰ ተገፋፍቶ ወደቢሀ ኃጥያት የገባ ለመሆኑ ደጋግሞ ለራሱ ነገረ። ነገሩን አውጥቶና አውርዶ ሲያስላስለው መጂጫ ያጣለታል። እንዲት ብሉ ከእንደዚያ ያለ ስህተት ውስጥ ሊዘፈቅ እንደ ቻስ ማወቅ ተሳነው። መርከቡ ወደነበረበት የባህር ጻርቻ ሲያመራ እርስዋ ወደሄደችበት አቅጣጫ ለመሄድም ፈለገ። ከዚያ ቦታ በጨለማ ብቻዋን እስከ መጪረሻው ትቶ መሂዱ የጭካኔ ሥራ መሰለው። ሆኖም ግን እንዳይከተላትና ጻግም እንዳይፈልጋት አስጠንቅቃዋለች። ስለዚህ ከዚያ በኋላ እርስዋን መፈለጉ ሞኝ እንደሌለው ተገነዘበ። ቢያገኛት እንኳን ፊት ልትነሳው እንደምትችልም ጠረጠረ።

ከለንደን አብረውት የመጡ ሁለት መንገደኞች አፈጠጡበት። ለንደን ውስጥ ባቡር ላይ ከተሳፈሩ ጀምሮ ዓይናቸውን ስባው የነበረችው ቆንጆ ሴት አሁን ከእርሱ ጋር የለችም። እርሰ በእርስ በመጠቃቀስ ስለቆንጆዋ ሴት ሁለቱ ወንዶች ሲነጋገሩ ለማቸው። የሚያወጧቸው ነገር ባይኖርም ለማወቅ ያህል ብቻ ጉዳዩ ብዙ እወያያቸው። ያቺ ገና ሊያይዋት ልብ የምትሰርቀዋ ቆንጆ ሴት ቀደም ሲል ከሰውዬው ጋር ተጣብቃ ነበር ያይዋት። «ታዲያ አሁን ዮት ነባች? ማንን አምኖ ነው ያቺን የመሰለች ቆንጆ ብቻዋን የለተቃትና ከዓይኑ ያራቃት? ሰውዬው የብቸኝነት ለሚት

የተሰማው ይመስላል፤ ሰውነቱም ተቀያይሮአል። ነገሩን ሲያጢኑት ገረ ያታባል። ሰውዬው እንዴት ባንድ ጊዜ እስከዚህ ሊለወጥ ቻለ? ፈተ ገርጥቶአል፤ የሮንቀት ምልክት ፊቱ ላይ በግልጽ ይነበባል፤ የከፍው ሰው ለመሆኑ ጥርጥር የለውም» እያሉም ከማያገባቸው ውስጥ በመግባት ብቁ ፈተፈቱ፤ ሰውዬውንም በመሬ ብዙ ቦጫጨቁት።

ከሁለቱ ሰዎች እንደኛው ደፋር ብጤ በለነበር «ጌታውን ብቻውን ነው እንዴ የሚጓዙት?» ብሎ ጠየቀው። ነገር ግን የሰር ልዮኔል የተከሳተረ ፊት፣ የንቀት አመለካከትና ግልምጫ ጠያቂው ሌላ ጥያቄ ለመጠየቅ አድል አልሰጠውም። ጥልቅ ባዩ በመሸማቀቅ ፊቱን አዞረ።

ደፋሩ ሰው ልክ ነበር፣ ሰውዬው ብቻውን ነው የሚጓዘው። ከአስበበት በቅሎ እንዲደርስ ይገፋፋው የነበረው ኃይል አሁን አብሮት የለም። በውሸት ብርሃን ስለነበር የተመራው ተከትሎት የመጣው ፍጡር ተሰውሮበታል። 'ብቻውን ኖት?' የሚለው ሐረግ ግን በጣም ከነከነው። ባቡሩ ወደፊት እየገሰገሰ ሲጓዝ ወደ ሷላ መለስ ብሎ የደረሰበትንና ጥሎት የመጣውን ሕይወት ማሰላሰል አልፈለገም። በፈጸመው ድርጊት የደረሰበትን ጸጸትና ጭንቀት ከህሊናው መንጭቆ ለማውጣት ነበር ፍላጎቱ። ሆኖም ህሊናነ በቀላሉ ማዘዝ ስለማይቻል ዓይኑን ሲጨፍን እንኳን የዚያች ቀንጆ ሴት ፊት ድቅን ይልበታል።

በደስታ የተፍለቀለቀው ፊትዋና ደም የዞረበት ክንፈርዋ በአሳብ ያያቸዋል። ያ ደስታዋ ደግሞ የመጀመሪያዋና የመጨረሻዋ እንደሆነ ልቦናው ያውቃል። እንቅልፍ ወስዶት እንደ ባኔነ ሰው እሱም በዚያች ቅጽበት ከአሳቡ ባንኖ የነቃ መሰለው። ያፈጠጠ ዓይኑን ጨፈነው። አሁንም ያቺ ጥላው የሄደችው ቆንጆ ሴት በዓይነ-ህሊናው ታየችው። ስሜቱን መቆጣጠር ስላቃተው አምርሮ አለቀሰ። እምባው ክጉንጮቹ ላይ እንደ ጎርፍ ፈለሱ። ምኑው ባሳየኋት ሲል ሰውነቱን አሳቀቀ። የሆነው ሁሉ እንዳልሆነ ቢሆንና ሴትዮዋን እንዳልተገናኛት ለማድረግ ቢቻል የነበረውን ሀብት ሁሉ ቢሰጥ ቅር እንደማይለው ለራሱ ነገረ።

«የት ነው ያለችው? ከባህር ውስጥ ገብታ ሰጥማለች? ፖሪስ ከተማ ውስጥ ከሚገኙት ሆቴሎች መካከል ከአንደኛው ውስጥ ገብታ ቁም ብላለች? ወደ እንግሊዝ አገር ተመለሰች? ከዚያስ ተመልሳ ምን እየሠራች ነው? ምንስ እየሆነች ነው? ከባልዋ ቤት ተመልሳለች? ካልተመለሰች ታዲያ የት ነው ያለችው?»

ከባቡሩ ውስጥ ቁጭ ብሎ የሐዲዱን ኪሳታና የሞተሩን ጫጫታ ሲሰማ የጠየቃቸው ጥያቄዎች ነበሩ። ቀጥሎም «ምነው ችዕግሥቴን ቢሰጣትና ረጋ ብላ ነገሮችን በማመዛዘን እኔ ያልኳትን ብትሰማ ምነው ጥቂት ቆይታና ምክሬን ሰምታ እንድ የሆነ ነገር በደርገላትብ እኔ እንጻልኳት ቢሆን እኮ ሁሉም ነገር ደህና ይሆን ነበር» ሲል ከአሳቡ ጋር ግብግብ ገጠመ።

ስለቆንጆዋ ሴት ያውጠነጥነው የነበረው አሳብ ሽዝም እጅግ ብርቱ ሆኖ ቢከብደውም ወርውሮ ሊጥለው ግን አልቻለም። በተፈጸመው ስህተት እየተንገበገበ ፖሪስ ከተማ ከሚገኘው ባቡር ጣቢያ ደረሰ። ያኔም ቢሆን ህሊናውን አስጨንቆ የያዘው አሳብ 'የት ገባችኮ?' የሚለው ጥያቄ ነበር። አብረው የሚመጡ መስሎት ከናስ እንዲያዝሳቸው አሰቀድሞ ካዘዘበት ሆቴል ከመሄድ በስተቀር ሌላ አማራጭ ሰላልመጣለት ወደዚያው ሄደ።

«ጌቶች ብቻውን ነው እንዴ የመጡት? ከሌት ጓደኛዬ ጋር ነው የምመጣው ያሉ መሰሉን ነበር» ብሎ አስተናጋጁ ሲጠይቀው «እምን ብዬ ነበር፤ አርስዋ ዘግይታ ነው የምትመጣው» ሊል ቾኩሉ መሰለለት።

«በርከት ያሉ የእሜቴ ሻንጣዎች ቀደም ብለው ደርሰዋል» ካለ በኋላ «ሻንጣዎቹ ምን እናድርጋቸው?» ብሎ አስተናጋጁ ጥያቄ ቢጠይቀው «ያሻንጣዎቹ ባለቤት አስከ መጣች ድረስ ከእቃ ማስቀመጫ ክፍሰችሁ ውስጥ ማቀየት ነዋ» ብሎ መለሰለት።

ልዮኔል ቀደም ብሎ እንደ ወጠነው ከሆቴል ቤቱ ቀየ። አሁንም ቢሆን 'ምናልባት አሳብዋን ለውጣ ትመጣለች' የሚል አሳብ አልተለየውም። አርስዋ ግን አሳብዋን በሳልቀየረች የተመኘው ነገር መና ሆኖ ቢቀርም አስከ ተወሰነ ቀን ድረስ ከዚያው መቆየቱን መረጠ። ከዚያም ሆኖ ነው ለሊኑ መስፍንና ከበርቴ ደብዳቤ የጻፈላቸው። ከደብዳቤው ውስጥ ግን ያቺ ወጣት ቆንጆ ሚስታቸው ጥላው እንደ ሄደች አልገለጸላቸውም። ለዘላለም መለያየታቸውን ከበርቴው እንዲያውቁ አልፈለገም። ደብዳቤው ከጻፈላቸው ሥፍራ ለአንድ አሥር ቀን ያህል በለሚቆይ ከፈለጉት ከዚያ ሊያገኙት እንደሚችሉ ግን ነግሮአቸዋል። ሚስትን የሚያህል ንብረት ቀምቶ ከፈለጉኝ ብሎ ነገር እንኳን አይገባም። አርሳቸውም ቀላል ሰው ሰላልነበሩ ለጻፈላቸው ደብዳቤ መልስ አልሰጡትም፣ የቪሻንም ወሬ እስከ መጨረሻው አልተሰማም።

ከሆቴል ቤቱ የነበሩ ሠራተኞች «ይህ አንግሊዛዊ ምን ነካውን በጣም ነው የሚያዝነውና የሚተክዘው» እያሉ ይገረማሉ። ብዙ ገንዘብ የጠፋበትም መሰላቸው። ልዮኔል በስልክ ክፍል ባስያዘበት ጊዜ መልእክቱን የተቀበሰው የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ ሲሆን ስለሴትዮዋ ሊያነሳበት አልፈለገም። ቀናት እያለፉ ቢሄዱ ሰር ልዮኔል የአርባ ቀን እድሉ ምን እንደሆነ እየገባው ሄደ። ሎርድ ሊን ለደብዳቤው መልስ አልሰጡትም፣ ቪቫንም እንደ ተለየችው ቀረች፣ እርሱም ብቻውን ከነበረበት ቀረ። በዚህም ሎርድ ሊን እርሱን ለመከሰስ እንዳላቀዱ ጠረጠረ። እንዲሁም ቪቫን ወደ እርሱ እንደማትመጣ በትክክል አወቀ። በእርሱ እንዝህላልነትና ሞኝነት የሦስት ሰዎች ሕይወት መበላሸቱንም ተገነዘበ።

አሁን ምን ያድርግ? ከነበረበት መቆየቱ ጥቅም እንደማይሰጥ ስላወቀ ወደ ቤቱ ልመለስ የሚል አሳብ ሲመጣበት አሳቡ ስለዘገነነው ሐሞቱ ፈሰሰ። ስለዚህ እግሮቹ እንደመሩት የትም ይድረስ እንጂ ወደ ቤቱ ላለመለስ ወሰነ። ኤሊኖርን ከጭንቅላቱ ውስጥ ባስገባና የሠራው ሥራ በታወሰው ቁጥር ወደ እርስዋ የመመለሱ ጉዳይ እንደማይታሰብ አመነበት። ባለቤቱ ሰለሁሉም ነገር አውቃለች። በጻፈላት ደብዳቤ ስለሠራው ታጥያት ግልጥልጥ አድርጎ ነው የገለጸላት። አሁን በድጋሚ የፈለገውን ያህል የተለያዩ አሳቦችን ጨማምሮ ደብዳቤ ቢጽፍላት፣ ቢምል ቢገዘት አሳብዋን ልትቀይር እንደማትችል ልቦናው ያውቃል። ቀደም ሲል ለምን ብሉ እንደዚያ የከረረ ደብዳቤ፣ በተለይም እኅቢያን ለመደምደሚያ የተጠቀመባቸው ቃላት አክሎ መጻፉ አሁን አንገበገበው። «አብራኝ የከበለችው የሊንዊ አመቤት ቆንጆዋ ቪቫን ናት» ብሎ ያካተተው ወረፋቱ ነገር እንደ እሳት አቃጠለው።

«ያን አስቀያሚ ደብዳቤ ባልጽፍ ኖሮ» ሲል በጣም ተቆጨ። ደብዳቤውን በመጻፉም እጅግ አድርጎ ራሱን ገሰጸ። ያ ባይሆን ኖሮ አሁንም ቢሆን ወደ ቤቱ ተመልሶ ኤሊኖር ሚስቱን ይቅር፫ ጠይቆ ይታረቁ ነበር። ያ የከረረ ደብዳቤ ግን መንገዱን ሁሉ ዘጋበት። ከዚያ አስቀያሚ ደብዳቤ በኋላ 'ይቅር፫ አድርጊልኝ' ብሎ ኤሊኖርን መጠየቁ አሳፈረው። እርሱ ራሱ የጠላውንና የኃቀፈውን ያህል እርስዋም ሥራውን በይበልጥ ስትኑቅፍና እርሱን ስትጠላ በአሳብ ታየው። ጉዳዩ ይህ ከሆነ ልዮኔል አሁን ወዴት ነው የሚሄደው? ስለእርስዋስ ምን ሊያደርግ ይችላል? በአንድ ቀን ለሁተት ሕይወቱ ለዘላለም ተበላሸ።

ካቦቻ ቦታ እየተንቀሳቀሰሉ እድሚን መግፋት የሚቻል ነውን? ለአንድ ቀን ለሁተትስ የእድሜ ልክ ካሣ መክፈል አግባብ ይሆናል? በእድሜ ልክ የመንከራተት ሕይወት ሊቀጣው አምላክ መወሰኑስ ትክክል ነው? ከዚህ ጭንቀት ለመላቀቅ ምን መደረግ አለበት?' እነዚህ ሁሉ በየእለቱ ቀኑን በሙሉ በማንኛውም ሰዓት፣ በማንኛውም ሥፍራ የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ሲሆኑ ለሁሉም መልስ አሳጥኖላቸውም።

ከሆቴሉ ሳሎን እንደ ተቀመጠ ባጋጣሚ ከግብፅ አገር ከመጣ ሰው ጋር ይገናኛል። ይህ ሰው አሁንም ተመልሶ የሚሄደው ወደዚያው አገር ነበር። ስለአገሩ አስደናቂ ታሪክ ብዙ ስላወጋው ሰር ልዮኔል 'ወደዚያ አገር ብሄድስ' የሚል ሰሜት አደረበት። ሩቅ አገር በመሆኑ ከዚያ ሲመድረስ ጊዜ ስለሚወስድ በመካከሉ አሳቡን ሰብስቦ ኩተሻ ውሳኔ ላይ ሊደርስ እንደሚችል ገመተ።

የመንገደኛው በም ሚሲ ኒኮል ይባላል። ይህ ሰው ወደፊት ታዋቂ ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ እስከዚህም የታወቀ ሰው አልነበረም። ሰውዬው አሌክሳንደሪያ ወደሚባል ከተማ እንደሚሄድና ከዚያም ለተወሰነ ጊዜ እንደሚቆይ ለሰር ልዮኔል ገለጻለት። ቀጥሎም «አሁን ካሰበት ማጠናቀቅ ያለብዎት አጣዳፊ ሥራ ከሌለብዎት ለምን አብረን አንሄድም?» ብሎ ሰር ልዮኔልን ጠየቀው። ሰር ልዮኔልም «ከዚህ የምወራው ሥራ እንኳን የለኝም» ሲል መለሰለት። «እንጂያውም 'ከዚህ ቀጥዬ የት ነው የምሄደው' እያልኩ ሳስብ ስለነበር አብረን ብንሄድ ደስ ይለኛል። እውነቱን ንገረን ካልከኝ ደግሞ ከዚህ ሥፍራ ብዙ ከቆየሁ የማብድ ይመስለኛል።»

«እንዲህ ብለው መናገርዎ እደባባይ ለማውጣት የማይፈልጉት የተደበቀ ምሥጢር አለ ማለት ነው» ባለው ጊዜ «ይህን መክዱ ራስን ማታለል ይሆናል» ሲል ሰር ልዮኔል መልሰለት የትክዜ ምልክት እየታየበት።

«ነገሩ ይህ ከሆነ አብረን እንሂድ። ህዘንን ለመርሳትና ሸክምን ለማቃለል ከበድ ያለና እድካሚ ሥራ ከመሥራት የተሻለ ዘዴ ስለሌለ አብረን እንሂድና የሆነ ከባድ ሥራ እኔ ከዚያ አፈልጋለሁ። አንድ ችግር አንዳለ ቀደም ብዬ ጠርጥሬአለሁ። እንደ እርስዎ ያለ መልክ-መልካምና ህብታም ሰው ያለ ምክንያት ከባድ ጭንቀት ውስጥ አይገባም። ሰው እንዳልገደሉ ግን ተበፋ አደርጋለሁ። ለመሆኑ በእጅዎ ሰው ጠፍቷል?» ሲል ኒኮል ጠየቀው።

Scan by Easy Scanner

«የለምፕ ይህን እንኳን አሳደረግሁም» አለ ሰር ልዮኔል። «ነገር ግን የሠራሁት ሥራ ከዚህም የከፋ ላይሆን ይቀር ብለህ» ብሎ ሲናገር «ከሰው መግደል የባሰ» ሲል ኒኮል ጮክ ብሎ ተናገረ። «እንግዲያውማ ከበድ ያለ ነገር መሆን አለበት» ሲለው «በጣም ከባድ ነው» አለ ሰር ልዮኔል በመከፋት። «እጅግ በጣም የከበደና የሚያስከፋ ተግባር ነው የፈጸምኩት» ብሎ ሲናገር «እንግዲያውስ የሴት ጣጣ መሆን አለበት» ሲል ኒኮል ጣልቃ ገባ።

«የሴትስ ቢሉህ የእንዲት ሴት መሰለህ፣ የሁለት ሴት ጣጣ ነው» ብሎ ሲናገር «የሁለት፣ ይህማ ነገሩን በይበልጥ ከባድ ያደርገዋል» አለ ኒኮል።

«ከዚህ ጨዋታ በፊላ ሁለቱ ሰዎች ለሁለት ዓመት ሙሉ አብረው ሲቆዩ የጉዳዩ ምንነት ዊሊ አንስቶበት አያውቅም። ዓደኛው በሴት ምክንያት ከከፋ ችግር ውስጥ መውደቁን በለተረዳ ጉዳዩን በማራገብ ዳግም ሊያሰቃየው አልፈለገም። ወዳጅ ይሉሃል ይኼ ነው። አንዳንዱማ ወዳጁ ከባህር ላይ ለመውደቅ ሲንገዳገድ እንደ መዳገፍ አንዲሰምጥ መጅ አስሮ ነው የሚለቀው።

እነዚህ ሁለት ሴቶች የሰሙዬው ሚስቶች ይሁኑ እህቶች ወይም እናቶች እስከ መጨረሻው አላወቀም። ሰሙዬው ከችግር ላይ መውደቁን እንጂ በማን ወይም በምን ምክንያት እያለ ነገር መጎንጎን አልፈለገም። የእርሱ ፍላጎት ዓደኛው ችግሩንና ጭንቀቱን የሚረሳበት መንገድ መሻት ነበር። ለተወሰነ ጊዜ አሌክሳንደሪያ ውስጥ አብረው ቆዩ። ከዚያም የናይልን ወንዝ ተከትለው ወደ ቆላ ብንወርድ የሚል አሳብ ሰር ልዮኔል በቀረበ ጊዜ «አብረን ወደዚያ ብንሄድ ደስ ባይልህ አይቀርም» ሲል ዓደኛው አሳቡን ደገፈለት። እንዲያውም ከነአካቴው በቶሉ እንዲሄዱ ዊሲ ሰር ልዮኔልን አግባባው።

«መሳ ጭንቀቅሳትህ በአዳዲስ አሳብ መዋጡን ተገንዝቤአለሁ። ከዚያ አሳብ የሚከፍሉ ብዙ ነገሮች ስላሉ እሱን የሚያስጨንቅህን አሳብ ያስረሳሃል። ዓለምም አንተ ከምታስበው በላይ ትሰፋልሃለች፣ ትልቅነትዋንም ትገነዘባለህ። ከአሁን ጀምሮ የልብ ወዳጆችና ዓደኛሞች አንድንሆን ብጠይቅህ አንተ በዚህ ትስማማለህ?» ብሎ ሲጠይቀው «እስማማለሁ» ሲል መለሰለት። በዚህ ዓይነት ለመወዳጀት የፈጸሙት ቃለ-መሐላ ሳይጣስ ለረጅም ጊዜ ቆየ።

ምዕራፍ ሃምሳ ስድስት

የጓደኛ ቃል

ሁለቱ ዓደኛሞች የናይልን ወንዝ ተከትለው ሲወርዱ ብዙ አስደናቂ ነገሮችን አዩ። አይታው በሕልም የሚያዩት እንጂ እውን ሆኖ በአካል የሚመለከቱት ነገር ሆኖ አላገኙትም። ባለፉበት ሁሉ የሚታየው ውበት እጅግ ማራኪ ስለነበር ዓይኔን ላንሳ አያሰኝም። በዚህ ጉዞ ነበር የመደፈት ሕይወቱ ተስፋ ያለው ሊሆን እንደሚችል ሰር ልዮኔል የተገነዘበው። ሰውዬው እስከዚህም ነገር የሚያጠብቅ ሰው ስላልነበረ በሳለፈው ሕይወቱ ብዙም የሚጨነቅ ሰው አልነበረም። ነገርን እንደ አመጣጡ ሲቀበል ዘወትር የሚያየው የራሱን ሕይወት እንጂ በሰው ነገር ግብቶ ነገር አይፈተፍትም። ስለሰውም ብዙ አይጨነቅም። የተፈጥሮን ውበት ለማድነቅ የሚያደበት ዓይን እጅግ በጣም ውስን ነው። 'ይህ ነገር ከዚህ ጉዳይ ጋር ለምን ተጣመረ? ያኛው ጉዳይ ለምንድነው እንዲህ ሆኖ የተፈጠረው? ወይም ይህቺ ዓለም እንዴት ሙሳ ናት እያለ ብዙም አይፈላሰፍም።

ሰር ልዮኔል የናይልን ወንዝ ተከትሎ ሲሄድ ነው ቀደም ሲል ያሳየውን ማየት፣ ያላጤነውን ማጤን የጀመረው። በዚህ ዓይነት ነበር ቀድሞ ከለመደው ሕይወት ወጣ ብሎ ከአዲስ ሕይወት ውስጥ የገባው። የጓደኛው ነገርን አርቆ የማየት ችሎታ የጸበረና የበሰለ መሆኑን የተገነዘበውም በዚህ ጊዜ ሲሆን ይህም ለሰር ልዮኔል ባህርይ መለወጥ አስተዋጽዖ አድርጓል። ሰር ልዮኔልም ለውጡን በተገነዘበ ጊዜ በሰዎች መካከል ሊኖር የሚችለውን ልዩነትና እንዱ ሌላውን ለመለወጥ ያለውን አቅም ማድነቅ ጀመረ። ለንደን ኩተማ ሆኖ ከጓደኞቹ ጋር በተግናኙ ቁጥር ያወጡት የነበረው በተወሰኑ አርእስተ-ጉዳዮች ላይ ብቻ በማተኮር ነበር። ይኽውም ስለሴቶች ቁንጅና፣ ስለሰው ህብትና ንብረት መጠንፐ በቁማር ጨዋታ አንዱ ግለሰብ ምን ያህል ገንዘብ አገኘ፣ ሌላው ስንት ተበሳ፣ አልፎ አልፎም ስለታሪክ ያወራሉ እንጂ ስለሳይንስ ጥበብም ሆነ ስለፍልስፍና ተጫውተው አያውቁም። ስለፖለቲካና ስለሥኑ ጽሑፍ የሚነጋገሩበት ጊዜ ደግሞ እጅግ ውስን ነበር።

አዲሱ ዓደኛው ቅን ነው፣ ደፋር ነው፣ የማያውቀው ነገር ዳግሞ የለም። ስለዚህ ዮሀንስ ዓደኞቹና የዚህ ሰው ልዩነት የአልማዝና የብር ያህል ሆነበት። የአዲሱ ዓደኛው ነፍስ የጠራች ስለሆነች ተንኮል ከሀሊፍው ውስጥ

Scan by Easy Scanner

ገብቶ እያውቅም። በአፈጣጠር ጨዋ የጨዋ ልጅና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት በመሆኑ ከሰው ነገር ውስጥ ጥልቅ አይልም። ፍላጎቱና ምኞቱ ሰለሥነፍጥረት መመራመር ነው እንጂ ትርኪ ምርኪ ስለሆኑ ነገሮች ማውራት አይወድም። የሴት ወሬ ከተነሳማ ፊቱን ያዞራል። እስከዚያን ጊዜ ድረስ ሴት አፍቅሮ ወይም ይህቺን ሴት የትዳር ጓደኛዬ ባደረግኋት ብሎ ተመኝቶ አያውቅም። ሴትን አፍቅሮ ከትዳር ወጥመድ ውስጥ መግባት ለእርሱ ርካሽ አርምጃ ነው። በንት ሥራ ሞልቶ እያለ ሰዎች ከእንዲህ ያለ ወጥመድ ውስጥ ገብተው ሲዋኙ ባስተዋለ ቁጥር እጅግ ይገረማል። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም በዓለማችን ውስጥ የሚገኙና ድንቅ የሚያሰኙ የተፈጥሮ ውበትና አስገራሚ ነገሮች ሁሉ ከእርሱ ጆሮና ዓይን ያላመለጡት።

የፈጣሪን ምሥጢር ከትላልቅ ነገሮች ብቻ ሳይሆን ከጥቃቅን ነገሮችም ውስጥ ፈልፍሎ የማውጣትና የማየት ችሎታ አለው። እንደ አረም ከቀጠነች ሳር፣ ከባህር ዳር ከምትታይ አነስተኛ የወፍ ጎጆና ከትንሽዋ የነፍሳ ቅጠል የእግዚአብሔርን ጥበብ የማየት ስጦታ ስላለው ተፈጥሮን በጣም ያደንቃል። ስለዚህ አእምሮው በአስገራሚ ነገሮች እውቀት የተሞላ ነበር ለማለት ይቻላል። ለምሳሌ በንባብ ሰለእከሻቻቸው አስገራሚ ታሪክን ጨዋታ የጀመረ እንደሆነ እፍ ያስከፍታል። ጥሩ መጽሐፍ ይዞ ከማንበብ ወይም ጥሩ ሰባኪ ከማድመጥ እርሱን መስማቱ ይመረጣል። ሲናገር ብዙ ጊዜ «ከተፈጥሮ ሥራ ወደ እግዚአብሔር ጥበብ» ይላል። ከዚህ ሰው ጋር ውስ ማደር ማለት ትምህርት ቤት እንደ መማሪት ያህል ነው። እና ሰር ልዮኔል በዚህ አጋጣሚ በጣም በመጠቀሙ የዚያች ታላቅ አገር አስገራሚ ታሪክ ከህ እስከ ፕ ሰለተነገረው ብዙ አዳዲስ ነገሮችን አወቀ። ከጓደኛው ጨዋታ በተዓጽኛ ያንን ታላቅ ወንዝ በአንክሮ ተመለከተው። ያ ወንዝ ምሥጢር የተሞላበት ወንዝ ሲሆን ያ ወንዝ ብዙ የፍቅር ጨዋታ ያየ ወንዝ መሆኑን ተረዳ። ያ ወንዝ የተፈጥሮን ጥበብ የሚያደንቁበት ወንዝ ሲሆን ሰር ልዮኔልም ወንዙን እጅግ እደነቀው።

የነገሥታት መቃብር የሆነውን ፒራሚድን፣ አስፈንክስንና ለመቢታቸው ወደር የሌላቸው ሴሎች ሞንታዊ ሐውልቶችን ጎበኘ። እያንዳንዱ ሞንታዊ ቅርስን እንዲሁም የናይል ወንዝን በጥልቀት ሰላየ ጉብኝቱ ከሰር ልዮኔል አእምሮ ውስጥ አንድ ዓይነት ስሜት ቀረጸበት። ግብፃውያን በጊዜያቸው ምን ያህል ሰልጥነው እንደ ነበረም አወቀ። በዘመኑ የሰው ልጅ ጥበብ ምን ያህል ተራቅቆ እንደ ነበርም ተገነዘበ። በዚህም ወደፊት የሰው

ልጅ ጥበብ ከምን ደረጃ ላይ ሊደርስ እንደሚችል አሰተዋለ። የእነዚህን ሥልጣኔዎች ቅርስ ማማር ከራሱ ሕይወት ጋር ሊያነጻጽር ስሜት ተሰማው። እርሱ ይጪንት የነበረው የግል ሕይወቱን ለማሳደግና ዝናን ለማትረፍ፣ እንዲሁም ሴትን አማርጦ የፈለጋትን ማግኘት ሲሆን ይህም ከንቱ ምኞት እንደሆነ ሰራሱ ነገረ።

ጊዜያዊ የሆነ ደስታን ለማግኘት ሲባል ብቻ የሚደረገው መሯሯጥ የሚያበገነው ጥቅም ኢምንት እንደሆነና በሴት ፍቅር መጠመድም እንዲህ ዋጋቢስ እንደሆነ አመነበት። አሁን የሚያየው ነገር ሁሉ ወደፊት የሰው ልጅ የሚያደንቀውና ለወደፊት ትውልድም የሚተርፍና የሚኩራራበት መሆን እንዳበት ለራሱ ነገረ። የወደፊት የሥራ ሕልሙ ይህ እንዲሆን ቢመኝም ባለፈው ጊዜ የሠራው ሥራ ጸአት ግን ሲሰቀው አልቻለም። የጭንቀቱ መጠን በማየሉ የደረሰበትን ለመርሳት እንደ ፈረስ ጉግስ፣ አደንና እሳ ማጥመድ ያሉ የአሰፖርት ዓይነቶችን አዘወተረ። 'ሥራ ስለሚበዛብኝ ለጭንቀት ቦታ የለኝም' ስለሚባል እርሱነቱን በሥራ ቀበረ።

'ፈጣሪ በጥበቡና በችሮታው ቀድሶ የለጠኝ ቆንጆ ሚስቴ እንዴት ሆና ይሆን? አሁን የት ነው ያለችው? ምን እየሠራች ነው? እንድጠብቃቸው ኃላፊነት ተሰጥቶኝ ሳለ ጥዬአቸው የኩበለልኩት ልጆቼስ እንዴት ይሆኑ? እኔስ ወደፊት ምንድነው የምሆነው?' ዘወትር ሀሊናውን ወጥረው ያስጨንቁት የነበሩት ጥያቄዎች የመላሰሉት ነበሩ።

ቤተሰቡን በሚንከባከብበትና በሚጠብቅበት በዓት የቤት ሠራተኞች እንኳን ሰሙን በክፉ አያነሱም ነበር። እንደዚያ የተከበረ ሰው ነው አሁን እንደዚህ የተዋረደው። ይህን ሲያውጠነጥን ነው 'ምነው ከልጅነቴ ጀምሮ ከዚህ የተሻለ የኑሮ ልምድ ቢኖረኝ ኖሮ!' ሲል ሕይወቱን ወደ ኋላ ተመልሶ ቃኘው። 'ሳይደግስ አይጣላም' ነውና በዚህ ጊዜ ነበር ዓደኛው ዊሊ ኒኮል በጣም እየቀረበውና እየወደደው የሄደው።

ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ሰር ልዮኔል የሆነ ለውጥ ያሳያል። ያ ተስፋ የመቁረጥና የመበሳጨት ስሜት፣ ያ የመማረርና በሕይወት የመቆየት ጥላቻ ቀስ በቀስ ወደ ተስፋ፣ የደረሰውን ወደ መቀበልና መቻል በመለወጣቸው ሰር ልዮኔል በመጠኑም ቢሆን ደስ እያለው ሄደ። በእለፈ ውድቀት ተብክኩቱ ዘወትር ከማልቀስ ብዙዎች ያልደረሱበትን አልሞና ያንን ለመፈጸም መጣጣር ይሻላል የሚል እምነት ስላደረበትም የአመለካከት ለውጥ አሳየ። ሰዎች ሊያደንቁትና ሊኩራሩበት የሚያስችል ሥራ

ሠርቶ ሰምን ማደስ አስፈላጊ እንደሆነም አመነ። ይህም የእለት ተእለት ሕይወቱን እንዲለውጥ ረዳው። ዊሊም ከተፈጥሮ ውበትና ከሰዎች ጓዳኝነት ድንቅ ሥራ ጋር አስተዋወቀው። ያንንም ውበት እንዲያይ ዓይኑ እንጂ ያለፈውን በማንሳት አልነቀፈውም። አንዳንድ ለየት ያሉ የግል እምነቱንም አልጫነበትም። 'ከሰው ልጅ ሥራ ወደ እግዚአብሔር ጥበብ እያለ የፈጣሪን ሥራ ዘወትር አዳነቀለት።

ሁለቱ ሰዎች ረዘም ላለ ጊዜ አብረው ሲቆዩ ወዳጅነታቸው ሰር ሰድዶ ልብ ለልብ የሚገናኙና የሚከባበሩ ወዳጆች ሆኑ። ሳይሰለቻቹ ለረጅም ሰዓት ከአንድ ቦታ ቁጭ ብለው ያወጋሉ። ይጫወታሉ እንጂ አይጨቃጨቁም። ይወያያሉ እንጂ አይነቃቀፉም። የዚህ ዓይነቱ ግኑኝነት ደካማውን ልብ ወደ ብርቱው አእምሮ እየሳበ ስለሚመጸደው ሰር ልዮኔልም በዚሁ ተጠቅሞ ወደ አዲስ የሕይወት ፈር አመራ። ሁለቱ ጓደኛሞች ከተመሰነ ጊዜ በኋላ ወደ ካይሮ ተመለሱ። ከተመለሱም በኋላ ዊሊ ካይሮ ውስጥ ለመቆየት አቅድ አወጣ። ሰር ልዮኔል ግን ከከተማው ርቆ ለመሄድ ፈለገ።

ሰር ልዮኔል ከዚያ ርቆ ለመሄድ የፈለገበትን ምክንያት ዊሊ ለማወቅ ፈልጎ «ለምንድነው ከዚህ ለመቆየት ያልፈለግከው? አሁን የምትሠራውን ሥራ አልወደድከውም?» ብሎ ሲጠይቀው ሰር ልዮኔል «አልወደድኩትም፣ ዋናው ምክንያት ግን እርሱ አይደለም። በአካባቢው ብዙ እንግሊዛውያን ስላሉ ከእነርሱ ጋር ለመገናኘት ስላልፈለግሁ ነው» አለው።

«ያ የተጠናወተህ በሽታ አሁንም አልለቀህም ማለት ነው» ሲለው «አልለቀቀኝም፣ በቅሎም የሚለቀኝ አይመስለኝም። 'ያደቆነ ሰይጣን ላያቀስ መቼ ይለቅና'» ብሎ ከመለሰለት በኋላ «ካይሮ ከተማ ውስጥ ብዙ ባንቆይ ደስ ይለኛል» አለው በመግጠን መልክ።

«ደስ ካላለህማ ብዙ አንቆይም፣ አንተን ብቻ አይከፋህ» ብሎ ሊመልሰለት ሰር ልዮኔል ጓደኛውን በጣም አዳነቀው። ያን እለት ማታ ከሰገነት ላይ ቁጭ ብለው ቢራ እየጠጡ ለረጅም ሰዓት ብዙ አወጉ። በጨዋታቸው መካከል ግን ዊሊ ጓደኛውን ትኩር ብሎ ተመለከተው። ከዚያም «ልዮኔል» አለው በስሙ በመጥራት። «በጓደኝነትና በመፈቃቀር አብረን ስንኖር ሁለት ዓመት ሞላን እኮ። አብረን ቢቆየንባቸው ጊዜ አስቸጋሪ የሆኑ መጥፎ አጋጣሚዎችን አብረን ተጋፍጠናል፣ አብረን በልተናል፣ አብረን ጠጥተናል፣ አብረን ክፉንና ደጉን ተመልክተናል፣

ከሳችንን አንድ በማድረግ ኑረናል። ስለዚህ እውነተኛ ጓደኛሞች ነን ለማለት ይቻላል። በዚህ የምንተማመን ከሆነ እስካሁን ሰዓት ድረስ ሆዴ ውስጥ የሚብላላውን ጥያቄ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ» ሲለው «የምን ጥያቄ?» ብሎ ሰር ልዮኔል የመልስ ጥያቄ ጠየቀው።

«አስቴ እስከ ዛሬ ሆድህ ውስጥ ቋጥረህ ያስቀመጥከውን ያለፈው ሕይወትህ ታሪክ ምሥጢር ንገረኝ። ለሚለት የፈለግሁት ለምሳሌ እኔ ለጎጃንድ ነገር በመመሪመር ከአገር አገር ስዞር ነው ሕይወቴን የምዟው። ሚስት የለኝ፣ ትዳር አልያዝኩ። ልጅ የለኝ፣ ጎጆ አልቀለስኩ። በዚህ ኑሮዬ በአየር ላይ ነው። በዚህም ቅር አልሰኝም። የአንተ ሕይወት ግን ስእኔ የተሰየ ነው የሚመስለኝ። ግና ከጅምሩ እንደ እኔ ከቦታ ቦታ በመዞር ሕይወትህን ለማሰልፍ የተፈጠርክ ሰው አትመስለኝም። ምናልባትም ትዳር መስርተህና ጎጆ ቀልሰህ ለመኖር የምትፈልግ ይመስለኛል፣ ተሳሳትኩ?» ብሎ ሲጠይቀው «አልተሳሳትክም» ሲል ሀዘን እየተሰማው መለሰለት።

«እንግዲያውማ ከቦታ ቦታ እያሉ ሕይወትን መግፋት ለእንተ የሚሆን አይመስለኝም። አብረን በቆየንባቸው ዘመን ጠባይህን እንዳጠናሁት ምን ሊያበደስትህ እንደሚችል ገምቻለሁ። ቢሆንም የልብህን ምሥጢር አውጣና ንገረኝ ብዬ አላስጨንቅህም። ነገር ግን ብታምነኝና የምልህን ብትሰማኝ ለእንተ የሚበጅ ይመስለኛል።»

«ለመተማመኑማ አምንሃለሁ፤ ይህን አትጠራጠር፣ ምሥጢሬንም ላካፍልህ ዝግጁ ነኝ። ነገር ግን ታሪኬ አሳፋሪ እንጂ የምኩራራበት አለመሆኑን በቅድሚያ እንድታውቀው አፈልጋለሁ።»

«በዚህ ዓለም ሲኖር የተሰሳተ ጎዳና ተከትሎ የሄደ የመጀመሪያውና ብቸኛ ሰው ስላልሆንክ አትጨነቅበት። ማነው የማይሳሳትና የሚያሳፍር ሥራ ያልሠራ፣ የማይሠራ፣ ብልጭታ ወደ ሰማይ እንደሚዘል ሁሉ ማንኛውም ሰው ይሳሳታል» በማለት ጓደኛው ዊሊ ሲያጽናናው «የእኔ ግን የተሰየ ነው» ሲል ሰር ልዮኔል በትካዜ መለሰለት። «የፈሪ ሥራ ነው የሠራሁት። እርግጥ ነው ማንም ሰው ሊሳሳት ይችላል። ሆኖም የፈሪ ሥራ የሠራ ሰው ማንም 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ብሎ ሊያልፈው አይችልም» አለው።

«ምነው ልዮኔል፣ አብረን በቆየንባቸው ዘመን ከብድ ነገር ውስጥ ገብተን በጀብደኝነት አብረን ተጋፍጠናል። ታሪታውስ እንደሆነ እንዳንዶቹ አስከ

ሞት ሊያደርሱ የሚችሉ ነበሩ። አጋይቶ ሊያቃጥል ከሚችል እሳትና አረፋ አስደፍቆ ሊያሰምጥ ከሚችል ማዕበል ፊት አብረን በመቆም ተጋፍጠናቸዋል። የሚበላ ጠፍቶ አብረን ጦማችንን አድረናል። ጠፍቶ አጥንት ከሚሰብር ብርድ የሳሳ ልብስ ለብሰን አብረን አድረናል። የአውሬነት ባህርይ የተጠናወታቸው ሰዎች ሰይፍና ረሃብ ካቃጠላቸው አራዊት ጥርስና ውጊያ አምልጠናል። ይህ ሁሉ ሲሆን አንድም ቀን የፈሪነት ባህርይ አሳየሁህም። አሁን ደግሞ 'የፈሪ ሥራ ሠራህ ትለኛለህ። ይህ ታዲያ እንዴት ሊሆን ይችላል?» ብሎ ዊሊ ቢጠይቀው ሰር ልዮኔል እንገቱን ከቆሙ ነቃነቀ።

«የእኔ ፍርሃት እኮ የተለየ ነው» በማለት ተናግሮ «ፍርሃቴ የሞራል እንጂ የአካል አይደለም። የቆንጆ ሴት ውትወታ፣ የቆንጆ ሴት ማባበያ መቋቋም የተሳነኝ ፍጡር ስሆን ወደ በደልኳቸው ሰዎች ተመልሼ ለመጨረስ ድፍረትና አቅም ያጣሁ ሞኝ ሰው ነኝ። ወዳጄ፣ የሕይወት ታሪኬን ልንገርህና አንተ ልትፈርድብኝና ልትታዘበኝ ትችላለህ» አለው።

«ለማህ ልዮኔል ያልከው ነገር ሁሉ ምንም ዓይነት ለውጥ አያመጣም። በሕይወቴ ዘመን ያሳፈሩኝ ሰዎች ቢኖሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው። አንተ ምናልባት ከእነዚያ ሰዎች መካከል አንዱ ልትሆን ትችላለህ። ሆኖም ለእኔ ማፍቀር ማለት ዘላለማዊ እንጂ ጊዜያዊ አይደለም። እምነቴ ይህ በመሆኑ የፈለግከው ታሪክ ብትነገረኝ በእኔ ላይ ለውጥ አያመጣም። እኔ ሳውቅህ እውነተኛ፣ ጎበዝ፣ ታማኝ፣ ደፋርና ኩሩ ሰው ነህ። ወደፊትም ከዚህ የተለየ ሰው ነበር ብዬ አላሴን አለውጣለሁ የሚል እምነት የለኝም። ስለዚህ ላትፈራ እውነተኛው ታሪክህን ንገረኝ።»

ሰር ልዮኔል ለተወሰኑ ደቂቃዎች ዝም አለ። ዊሊ ኒኮል የሚከራከሩትና የሚመካከሩት ጓደኛው ስለነበር ያለፈውን የጎደፈ ታሪኩን ለመናገር ስለከበደው በውስጡ ይካሄድ የነበረው ትግል ቀላል አልነበረም። ዊሊ እንደዚያ ቀድሶ ባሞገሰው ጊዜ ሰር ልዮኔል ውስጥ ውስጡን ደስ አለው። ሆኖም ግን አውነተኛ ታሪኩን ካወጣ ምናልባት የሚወደው ጓደኛው ቅር ሊሰኝ እንደሚችል ጠረጠረ። ስለእርሱ የነበረው ከፍተኛ አደናቆት ሊከሽፍ እንደሚችልም ገመተ። ቀሳል ውሳኔ ሰጣልንበረም ፍርድ ቤት ቀርቦ ላደረሰው ጉዳት የሚጠየቅ መሰለው። ይህን ጊዜ ነበር ፊቱ ላይ የሀዘንና የጭንቀት ምልክት የታየው። ጓደኛው ያንን ቢገነዘብም ግልታ ገብቶ ነገር ማደፍረስ ስላልፈለገ በትእግስት አለፈው። ቢሆንም «እንዴት

ያለ ጥሩ ሰው ነው» ሲል ዊሊ አሰላሰለ። «ጨዋ የጨዋ ልጅና ጠባየ-ሸጋ ፍጡር ስለሆነ ከተሳሳተ ዓለም ለመግባት ሲያመራ ዝም ማለቱ ትክክል እንዳልሆነም አመነ። 'ይህን ጊዜ በወቅቱ ከአንድ ከማይረባ ነገር ውስጥ ገብቶ ይሆናል የወደፊት ሕይወቱን ያበላሸው። ምናልባትም ከእዚህ ግባ በማይባልና በተረገመ ፍቅር ተለክፎ ከዚህ ደርሶ ሊሆን ይችላል። የስንቱ ጨዋነት ያልራቃቸው ሰዎች በፍቅር ሰበብ ፊር እየለቀቀ ሕይወታቸው ተበላሽቶ የለ!' ሲል አሰበ። 'አንድ ሰው ምርምር አካሂዶ ምርምሩ ለይሳካለት ቢቀርና ቢያብድ ይገባኛል። በሕይወት ዘመኔ ሙሉ ሰሙሉ ልቡ ያረፈበት ነገር ቢከሽፍበት አበደ ቢሉኝ ነገሩ ሊገባኝና ሳዝን አችላለሁ። በሌት ምክንያት ሰው አበደ ቢሉኝ ግን ጊዜው ያለፈበት ጉዳይ ነው ብዬ የማልፈው ይመስለኛል' ሲልም አሰላሰለ። ሰር ልዮኔል ቆይቶ ቆይቶ መልስ ሰጠው።

«ታሪኬን አውጥቼ ለመናገር ዓመት ወሰደብኝ አይደል» ካለ በኋላ ሲኛራ አውጥቶ ሲያቀጣጠል «ግድ የለም መጠበቅ እችላለሁ» አለ ኒኮል ሲመልስለት። «የሚያስቸኩለን ነገር ስለሌለ ልትነገረኝ የፈለግከውን ዛሬውኑ መናገር የለብህም። ከፈለግህም በሌላ ቀን ልናደርገው እንችላለን» ሲለው «የለም» አለ ሰር ልዮኔል፤ «የሚሆን ከሆነ አሁኑኑ ነው መሆን ያለበት። የገባህበት ፈተና ጽናትና የግል ድክመቴን በማመዛዘን የኃጥ ያቴ መጠን ምን ያህል እንደሆነ አንተ ግምቱን ብትነግረኝ ደስ ይለኛል። እኔ እንደሆነ ጥልቁቹንና ምጥቁቱን ለማየት ከተሳነኝ ቆይቷል።»

«ተፈጥሮን እንጂ የሰዎችን ሕይወት አለማጥናቴ እውነት ነው። ሆኖም ስለአንድ ነገር አፈን ሞልቼ ለመናገር እችላለሁ። ከብዙ ሰዎች ጋር ተዋውቄአለሁ፣ ከእነርሱም ጋር አሳብ ተለዋውጫለሁ። ታዲያ እስከ ዛሬ በሕይወት ዘመኔ ያልተሳሳተና ኃጥያት ያልሠራ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም። እና አንተ አሁን ከሰው ሁሉ የተለየህ ይመስል 'ኃጥያተኛ ነኝ' ብለህ መጪኔቅህ ሊገባኝ አይችልም።»

«እኔ ከሌሎች ሰዎች ሁሉ ይበልጥ ለለተሸሸልኩና እኩይ የሆነ ሥራ ስለሠራሁ ነዋ ከሌሎች የምለየው» አለ ሰር ልዮኔል ሃፍረት እየተሰማው።

«ለምንድነው ፈጥነህ እጅህን የምትሰጠው? አንተ የሠራኸው ሥራ ሌሎች ሰዎች ከሠሩት ሥራ ሁሉ የከፋ ነው ያለው ማነው?» ብሎ ከጠየቀው በኋላ «ከምትነግረኝ ታሪክ በፊት ለማወቅ የምፈልገው አንድ ሌላ ነገር አለ። ይኸውም እኔ በምሰጠው አስተያየትና ፍርድ የምትረካ

Scan by Easy Scanner

መሆን አለመሆነህን በቅድሚያ አረጋግጥልኝ። እኔም አንተን ለማስደሰት ስል ላልተጥፍ የሚሰማኝን ሁሉ በትክክል ከመናገር ወደ ኋላ የማልል መሆኔን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ» ሲለው ሰር ልዮኔል «እኔም የምፈልገው ይኸው ነው» አለው።

«እኔም በበኩሌ ይህን ለመፈጸም ቃል እገባልሃለሁ» ሲል ጓደኛው ዊሊ እውነትነት በተሞላበት አንደበት መለሰለት። «ለደረሰብህ ችግር ማቃለያ የሚሆን አሳብ ልበጥህ እሞክራለሁ። ነገር ግን አሳቤን አክብረህ የምትቀበለው ለመሆኑ ቃልህን ስጠኝ። በዚህም ትስማማለህ?»

«የሚበጀኝን ምክር ይሰጠኛል ብዬ ስለማምን ባልኸው አስማማሁ» አለ ሰር ልዮኔል። «ስለዚህ ለአንተ ይበጃል ብለህ የመከርከኝን ከመቀበል ወደ ኋላ አልልም። ለዚህ ደግሞ ቃሌን አሰጥሃለሁ።»

ምዕራፍ ሃምሳ ሰባት

«የሠራሁት ሥራ ከይቅርታ በላይ ነው»

ታሪኩ ቀጥሎ ሰር ልዮኔል ታሪኩን መናገር ሲጀምር ተስያት ስለነበር ፀሐዩ በጣም ያቃጥላል። ከታሪኩ መጨረሻ ሲደርስ ግን ፀሐይ ብርሃን የመስጠት ተግባርዋን ፈጽማ ተመሳሳይ ተግባርዋን እንድታከናውን ለጨረቃ ካስተላለፈች ቆይታለች። ሆኖም ታሪኩ ረጅም በዓት ቢወስድም ኒኮል ጣልቃ በመግባት ጥያቄ አልጠየቀም፣ አስተያየትም አልሰጠም። ሰር ልዮኔል ያንን አሳዛኝ ታሪኩን አንድም ሳያስቀር በመዘርገፉ ቅልቅ፣ እጅግ በጣም ቅልቅ አፎይታን አገኘ። ያ እንደ ከባድ ድንጋይ ተጭኖት የነበረውን አሳብ ከራሱ ላይ በማውረዱ ሸክሟ እንደ ተራገፈላት አጋሰስ ስውነቱ ተንፈስ አለ። እየፈራ የሚወረውራቸው ቃላት ከአፉ በወጡ ቁጥር እንደዚያ ክብዶት የነበረው ልቡ ወደ ባዶነት ተቀይሮ የኩበት ያህል ስለቀለለው ወደ ቀፎነት የተለወጠ መሰለው።

«የልቤን ገልጬ መናገሬ ጥሩ ነው። ጓደኛዬ ያለውን ይበል እንጂ እኔ እንደሆነ ሰውነቱ ሁሉ እየቀለለኝ ነው የሄደው» አለ ሰር ልዮኔል በልቡ የኒኮል ፍርድ ምን ሊሆን እንደሚችል እየተጠባበቀ። ዊሊ በአሳብ ተውጦ ከጓደኛው ላይ በማፍጠጥ ከነበረበት አልተነቃነቀም። የሰማው ታሪክ እጅግ አስተከዘው። ያን የመሰለ ታሪክ ይነግረኛል ብሎ የጠበቀው አልነበረም። ከዚያ በፊትም ያን የመሰለ ታሪክ ሰምቶ አያውቅም።

«የሚያስፈራው ታሪኬን ግልጥልጥ አድርጌ ነው የነገርኩህ። አሁን አንባዲህ የተሰማህን ስሜት ሁሉ በተራህ ፍርጥርጥ አድርገህ ንገረኝ። ታዝበሽኝም ከሆነ ልስማው» በማለት ሰር ልዮኔል አሳቡን ጠየቀው።

«እነግርሃለሁ» አለ ጓደኛውም፣ «በመጀመሪያ ደረጃ አንተም እንዳልከው ታሪኩ ትንሽ ግር የሚያሰኝ ነው። ከአሁን ቀደም ከሰማኋቸው የፍቅር ታሪኮች ሁሉ የተለየ ሆኖ ነው ያገኘሁት። የነገርከኝ ታሪክ ከመጽሐፍ ብነበው 'ታሪኩ የተነገረላቸው ገጸ-ባህሪያት ሥራ የሚያረካ አይደለም' አለ ነበር። ለምሳሌ አሁን አንተ ያሳየኸው ገጸ-ባህርይ 'ድክመት አይሉት ደግሞ' ነው የሆነብኝ። ወይ ገና ከመጀመሪያው ፈተናውን ለመቋቋም ለሞከርክም፣ ወይ ደግሞ የተሳሳተውን መንገድ ይዘህ አልገሩህበትም። ምስኪንዋ ቪቫንም እንዲሁ። እርስዋም ገና ሲጀመር በፍቅርህ ባልተሟረከች፣ ወይ ደግሞ ነገሩ ከዚያ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ እስከ መጨረሻው ዘልቀህበት ጥሩ ነበር። ስለዚህ በሁለታችሁም በኩል ድክመት ይታያል። ሆኖም ቀረም በስተመጨረሻው እርስዋ ያላየቸው ጉንካሬ ከማስገረሙም በላይ የሚገባ አይደለም። ባልዋን ጥላ ከአንተ ጋር ለመኩብለል ስትፈቅድ ከሚሰትህና ከልጆችህ ኑዮታ ለመውሰድ አለመፍቀድዋ ግራ የሚያጋባ ነው» ባለው ጊዜ ሰር ልዮኔል ፈጥኖ «ስለእኔስ ምን ታስባለህ? ምንም ነገር ሳትደብቅ እውነቱን ንገረኝ» ሲል ጠየቀው።

«አንተማ» አለ ሳይፈራ፤ «አንተማ የውራኸው ሥራ የእምነት ሳይሆን የስሜት ውጤት ነው። ለሁለቱም ሴቶች ታማኝ አልነበርክም። ለምትወዳት ሚስትህም ሆነ ለወደደችህ ቆንጆ ሴት እውነተኛ ሁነህ አልተገኘህም። ሥራህ የሚነቀፍ እንጂ የሚወደስ ሆኖ አላገኘሁትም። የቪቫን ውሳኔ ግን በመጠኑም ቢሆን የሚከብድና የሚደነቅ ነው» ባለው ጊዜ «የፈሪ ሥራ ነዋ የሠራሁት!» ሲል ሰር ልዮኔል ተናገረ።

«እምነ፣ ሥራህ የፈሪ ነው። የዚያ ፍራቻና ድክመት ውጤት ነው የሦስት ሰዎች ሕይወት እንዲበላሽ ያደረገው» አለው።

ሰር ልዮኔል እውነቱን እንዲነግረው ጓደኛውን ጠየቀ፣ የጠየቀውንም አገኘ። ሆኖም እውነታው ሰር ልዮኔልን ክፉኛ ስለመታው ከጸጸት ባህር ውስጥ ዘፈቀው። ቢሆንም ግን ከእውነተኛ ወዳጅ የሚጠበቀው ይኸው እንደሆነ አልሳተውም።

Scan by Easy Scanner

«የልብ ወዳጄ በመሆንህ ትጠላኛለህ ብዬ አላምንም። ስለዚህ በእኔ ላይ የምትሰጠው ብያኔ ይኸው ነውን? ያ ከሆነ ደግሞ አንተ ወዳጄ ይህን ካልክ ሌሎች ሰዎችማ ከዚህ ይበልጥ እንደሚፈርዱብኝ አልጠራጠርም። ታዲያ ይህን የመሰለ የፈሪ ሥራ ሠርቼ ዳግም ላልፈራና ላልሸማቀቅ ከወንዶች ፊት ቆሜ ለመሄድ የምችል ይመስልሃል?» ብሉ ሲጠይቀው «አዎና» ሲል መለሰለት በድፍረት። «ትችላለህ፤ አሁንም እውነቱን ላልደብቅና ላልቀጥፍ ስለጠየቅከው ጥያቄ የመለስኝን መልስ ልበጥህ። መቼም የፈጸምከው ተግባር ስህተት መሆኑን ማንም የሚክደው አይደለም። በሠራኸው ሥራ የሦስት ሰዎች ሕይወት መበላሸቱን አንተም ታውቀዋለህ። ስለዚህ ላያስፈልግ የተፈጸመ አሰነዋሪ ድርጊት አንደሆነ ልደብቅህ አልችልም። ወንዶች ለሴት ሲሉ የሚያሳዩትና ሴቶችም ለከንቱ ውዳሴ ብለው የሚፈጽሙትና ድክመት የሚታይበት ተግባር ነው። የሁለት ራሰ-ወዳድ የሆኑ ሰዎች ስሜት የተንጸባረቀበት ተግባር እንደሆነ ይታያል። ባለቤትህ ኢሊኖር ግን የሴቶች ቁንጮ ሁና ነው ያየኋት። ንጹህና መንፈስ ቅዱስ የቀረበት ታማኝ ሴት ሆና ነው የታዋቅኝ፤ አሁን አንተ በነገርከኝ ማለቴ ነው» ሲለው «ያልከው ሁሉ የሚያንሳት እንጂ የሚበዛባት አይደለም» አለ ሰር ልዮኔል እምባ እየተናነቀው።

«ግዙፍ አካልን በጥላ ነው የለወጥከው» ብሎ ኒኮል ሲናገር «አሁንም ልክ ነህ» ሲል ሰር ልዮኔል መለሰለት። ሆኖም ግን ይህን የመሰለ መልስ ቢሰጠውም ከልቦናው አንዱ ክፍል አሁንም ቪቫንን እንደ ተመኘ ነበር። እንደዚያ ያፈቀረችው ምስኪንዋ ቪቫን ለመጨረሻ ጥላው ብትሄድም ሊረሳት አልቻለም፤ አልፈለገምም። በእርስዋ ላይም ክፉ ነገር እንዲነገር ስውር ሀሊናው አልፈቀደም። ከነበረችበት የከበር ሥፍራ በእርሱ ፍቅር ምክንያት መውረድዋን ልቦናው ስለሚያውቅ ሰር ልዮኔል የጸጸት ሰሜት ተሰማው።

«ልቤ» አለ ዊሊ፤ «ልቤ ሁሣም ያዘነው ለኤሊኖር ነው። የመኖር አጋጣሚ ሽክም ያረፈው እርስዋ ላይ ስለሆነ ሌሎች በሠሩት ስህተት ክባድ ሽክም ከቆንጆዋና ከየዋህዋ ሴት ላይ ማረፉ ያሳዝነኛል። ይህ ደግሞ ለመርሳትና ለመቀበል የሚያስቸግር ጉዳይ ስለሆነ የጭካኔ ተግባር ውጤት እንደሆነ አድርጋ ልትቆጥረው ትችላለች። ያቺ በፍቅር ያበደችውና ብትኖዋ ቆንጆ ሴትም ታሳዝነኛለች። የእርስዋም ታሪክ በጣም አሳዛኝ ነው። አንተ ግን ወዳጄ ነህ ብዬ አልደልልህም፤

ለሞከሻሽህም፤ ተሳስተሃል። በዚህና በዚህ ምክንያት ነው የተሳሳትከው እያልኩ ራሴን በማሞኘትም አላዝንልህም። በእምነት ሳይሆን በስሜት ተመርተህ በእሳት በመጫወትህ የሆነው ነገር ሆነ። ስለዚህ ለእደረሰከው በደልና ለፈጸምከው ታጥያት ደስታህን መስዋዕት ማድረግ ይኖርብሃል። እፃህን እስከ ሕይወትህ መጨረሻ መክፈል ከአንተ የሚጠበቅ ነው» ብሎ ኒኮል ሲናገር «ይህ መሆን ያለበት ጉዳይ እንደሆነ አውቃለሁ» ሲል ሰር ልዮኔል በትካዜ መለሰለት።

«ማድረግ ያለብህ አንድ ነገር ብቻ እንደሆነ ይሰማኛል።»

«ምንድነው እሱ?»

«አሁን ያለህበት ሁኔታ በአፋጣኝ መለወጥ አለበት። በምህም መታደስ ይኖርበታል። ይህ እንዲሆን ማንኛውንም ነገር ከመፈጸም ወደ ኋላ ማለት የለብህም። እኔ ያሰብኩትን መፈጸም ቀላል ስለሚይሆን ራስን ማዋረድንና ዝቅ ማድረግን፣ እንዲሁም ምንተ-እፍረት መዋጥን ይጠይቃል። ይህን ከፈጸምክ አሁን ያለውን ሁኔታ ለማሻሻል ችችላለህ። ደግሞም መሻሻልና መለወጥ ያለበት አሳፋሪ ድርጊት ነው። ለመሆኑ ቪቫን ምን የሆነች ይመስልሃል?» ብሎ ሊጠይቀው «ጨርሶ አላውቅም» አለ ሰር ልዮኔል።

«በጣም የሚያስጨንቀኝ የእርስዋ ጉዳይ ነው። ታሪክህን እየሰማሁ ሳለ 'የሊንዋ አመቤት ምን ሆና ይሆን?' እያልኩ ብዙ አሰብኩ፤ አሳቡም አስጨነቀኝ። ልረሳት ሞክሬ ነበር፣ ግን አልቻልኩም። 'ሊን' በማለት ስምዋን ከጠራ በኋላ 'ይህን ስም ስለማ አንድ የማውቀው ነገር አንዳለ ስውር ሀሊናዬ ይነግረኛል። በቅርቡ አንድ ስለሊን ቤተሰብ የሰማሁት ወይም ያነበብኩት ነገር አንዳለ ይሰማኛል» ሲል ዊሊ ተናገረ። ጓደኛው ይህን ሲናገር ሰር ልዮኔል በጉጉት ቀና ብሎ አየው።

«የሰማኸው ወይም ያነበብከው ነገር ካለ ለማስታወስ ሞክር እስቲ?» ሲል ሰር ልዮኔል ጠየቀው። ዊሊም ጥቂት አሰበና «አሁን አስታወስኩ፤ ስለዚህ ጉዳይ የሰማሁት ከአንድ ሆቴል ቤት ውስጥ ሁኜ ነው። የሆቴሉ ባለቤት እንግሊዛዊ ናቸው። በየሄድኩበት ጋዜጣ ማንበብ ስለምወድ ከዚያ ሆቴል ቤት ውስጥ ነው ስለሎርድ ሊን ቤተሰብ ያነበብኩት። ጋዜጣው ላይ ያነበብኩት ስለሎርድ ሊን መሞት እንደሆነ ትዝ ይለኛል» ብሎ አሳቡን ሳያጠቃልል «ቪቫን ወደ ሎርድ ሊን ቤት ተመልሳ ሄዳ ይሆን?» ሲል ሰር ልዮኔል ጣልቃ ይገባል።

Scan by Easy Scanner

«የለም አልተመለሰችም፤ ምክንያቱም እዚያው ጋዜጣ ላይ ስለእርስዋ ወጥቶ መቅረትም ተጽፎአል። ከቤትዋ ከወጣች ጀምሮ ወሬዋ እንዳሉትስ ነው ጋዜጣው ያተተው።»

«እና ሎርድ ሊን ሞተዋላ» ካለ በኋላ ሰር ልዮኔል «ሳደረስኩባቸው በደል ይቅር ብለውኝ እንደ ሞቱ ተሰፋ አደርጋለሁ» ሲል ተናገረ።

«እንደሚመስለኝ ከሴትዮዋ ጋር አብረው በቆዩበት ጊዜ ደስ ብሎአቸው አልኖሩም» አለ ዊሊ።

«ስውዬው በትንሹም በትልቁ የሚቆጡ ቆፍጣና ሽማግሌ ሲሆኑ በእድሜም ከሺቫን በአርባ ዓመት ገደማ ይበልጣሉ። እርስዋ ደግሞ ከእርሳቸው የተለየች ፍጡር ስለነበረች በእርሳቸው ምክንያት ብዙ ተሰቃይታለች። አቤት መልከዋ! አቤት ቁንጅናዋ! አቤት ሰው ስትወድ!»

«ከዚህ የተሻለ እድል ቢገጥማት ጥሩ ነበር» ብሎ ዊሊ ሲናገር «ያ ነበር ትክክለኛውና ተገቢው ፍርድ። ታዲያ ምን ይሆናል፤ ያ እድል አልገጠማትም» አለ ሰር ልዮኔል። «ግን እኮ አሁን ነፃ ሆነች ማለት ነው። ሌላ የተሻለ ባል ማግባት ትችላለች» ብሎ ቢናገርም እንደዚያ ትወደውና ታፈቅረው የነበረችዋ ሴት አሁን ሌላ ወንድ አፍቅራና ወድዳ እንዲሁም እርሱን ተንከባክባ ለመኖር ትችል ይሆን ሲል አሰበ።

«እኔ እንደሚመስለኝ» አለ ዊሊ፤ «ስለሌላ ወንድ የተዛባ ሳይሆን ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖራት የማድረግ ኃላፊነት አለብህ። ብቻ ያ ደግሞ አሁን ሳይሆን ቀደም ሲል መደረግ የነበረበት ጉዳይ ነው።»

«ታዲያ አሁን ያ እንዲሆን ምን ማድረግ አለብኝ? እንዴትስ ላደርገው እችላለሁ? ሌሎች ሰዎችስ ከእኔ ምን ይጠብቃሉ?» ሲል ሰር ልዮኔል ጮክ በማለት ጠየቀው።

«ከቦታ ቦታ እየዞሩ ከመኖር ለምን የዚህች እድለቢስዋ ሴት እውነተኛና ትክክለኛ ባጭታ ምን እንደሆነ እድል ባገኘህ ቁጥር ለው እንዲያውቅ አታደርግም? ወዲያው እንደ ተለያያችሁ ወደ እንግሊዝ አገር ተመልሰህ ለሎርድ ሊን ደብዳቤ በጻፍክ ኖሮ ጥሩ ነበር። አንተ እንኳን በትደፍር በዉው በኩል ንጽህናዋንና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባት ሚዛናዊ ሴት መሆንዋን ማሳወቅ ነበረብህ። ለው ሁሉ የሚደሰበው አሁንም ከእንተ ጋር እንደሆነች ነው። ትክክለኛ ነገር ነው ብላ ባመነችበት ጉዳይ የተነሳ ከአንተ መለየትዋን ባስማሳወቅህ ጥሩተኛ ነህ ብዬ ብፈርድብህ አትቀየመኝም።»

«አልፈርድብህም፤ ያልከው ነገር ትክክል ነው። መለያየታችንን ማሳወቅ ነበረብኝ። እስከ ዛሬ ይህ አሳብ ጨርሶ ከህሊናዬ ውስጥ አልገባም።»

«እኔ በአንተ ቦታ ብሆን» አለ ጓደኛው ቀጠለና፤ «ትክክለኛ ግንዛቤና ፍርድ አደባባይ እስካልወጣ ድረስ እንቅልፍ አይወስደኝም ነበር። ገበህ፤ አሁን ስለተጨዋወትነው ጉዳይ ማለቴ ነው። የሎርድ ሊን መሞት ጥሩ አጋጣሚ ሊሆን ይችላል። የሚሆንልህ ከሆነ ስለሎርድ ሊን መሞት የተጻፈውን ከጋዜጣ ላይ ብነበብክ ጊዜ እመቤት ሊን ወደ እንግሊዝ አገር አለመመለስዋን ማወቅህን፣ አንተ የእንግሊዝን አገር ለቅቀህ ከወጣህበት ቀን ጀምሮ መለያየታችሁን፣ እንዲሁም ከዚያን ጊዜ ወዲህ አለመግናኘታችሁን ገልጸህ ለመጻፍ አጋጣሚው ጥሩ እድል ይሰጥሃል።»

«አሁን በእውነት፣ አንተ በእኔ ቦታ ብትሆን ይሀን ታደርግ ነበር?» ሲል ሰር ልዮኔል አጥብቆ ሲጠይቀው «በሚገባ፣ ይህን ከማድረግ የሚያግደኝ ነገር አይኖርም ነበር። እንዲያውም ጊዜ ሳለጠፋ ወዲያውኑ ነበር መልእክቴን የማስተላልፈው» ብሎ ዊሊ መለሰለት። ይህን ጊዜ «ቀደም ብዬ ባስብበት ኖሮ እንዴት ጥሩ ነበር» አለ ሰር ልዮኔል ሊናገር።

«ይሻል ነበር፤ ነገር ግን አሁንም ቢሆን ጊዜው አልመሸም። እስከዚህም ተስፋ ከሚያስቆርጥበት ደረጃም አልደረሰም። የምትጽፍላቸው ሰዎች ደግሞ 'ዜናውን የሰማው አሁን ነው' ብለው ሊገምቱ ስለሚችሉ 'ደብዳቤውን አሁን በመጨረሻ የጻፈው በዚህ የተነሳ ነው' ብለው ያስባሉ።»

«ታዲያ አሁን ደብዳቤ መጻፉ ምን ይፈይዳል? ጥቅሙስ ምን ላይ ሊሆን ነው?» ሲል ሰር ልዮኔል ሲጠይቀው «ጥቅምማ አለው። ዛሬም ጊዜ ውስጥ ዜናው በመላ እንግሊዝ አገር ይሠራጫል። ወሬው ሲሰማ ጋዜጠኞች ስለጉዳዩ በብዛት ይጽፋሉ። እንግሊዝ አገር ደግሞ ታውቀዋለህ፤ በጋዜጣ የሚጸፍም ሆነ ባሬድዮ የሚነገር ዜና በእጭር ጊዜ ውስጥ አገር ሁሉ ይሰማዋል። ድፃ አይል ህብታም፣ ሁሉም ጋዜጣ ያነባል። ዜናው በዚህ ዓይነት ከሁሉም ዘንድ ይደርሳል። በሁለት ሳምንት ጊዜ የእንተና የሊንዋ እመቤት ጉዳይ ከለው ሁሉ ጆሮ ገብቶ እውነታው ሳይዛባ በትክክል ይታወቃል» ሲል መለሰለት።

«ዛሬውኑ ከመተኛቴ በፊት ደብዳቤውን ጽፌ አድራለሁ። በቅጥቃጭ ለጋዜጣ አዘጋጆች እንዲደርስ አድርጊ ነው የምልከው። በዚህ ዓይነት መልኩ አስቤው አላውቅም። አይ ምስኪን ቪኻንዝ ገና ከመጀመሪያው ይህን አስቤ ቢሆን ኖሮ ቀደም ብዬ አደርገው ነበር።»

«ሌላም የምለጥህ ምክር አለኝ» አለ ዊሊ። «ምናልባት ይህኛውን አሳቤ ሰትሰማ ተግባር ላይ ለማዋል የማይቻል መስሎ ሊታይህ ይችል ይሆናል። ግን ብልህ ሰው ስለሆንክ እንደ ምንም ብለህ ባድፍረት ልትፈጽመው እንደምትችል ይለማኛል። ምንም ነገር ቢሆን እንዳይቅና እንደ ወሰዱት ስለሆነ ተግባር ላይ ለማዋል የማይቻል ነገር የለምና እወቅበት። አሁኑኑ ወደ ቤትህ መመለስ አለብህ። ይህ ደግሞ ዛሬ ነገ የሚሉት ነገር አይደለም። ሳታወላውል ወደ ቤትህ ተመልሰህ ባለቤትህን ይቅርታ ጠይቃት።»

ሰር ልዮኔል የመጨረሻዎቹን ቃላት በሰማ ጊዜ ኢጅግ ደንገጠ፣ ልቡም በኃይል ይመታ ጀመር። «ወደ ቤትህ ተመለስ!» ሲል በማቃሰት ተናገረ። «ይህን ለመፈጸም አቅሙም ሆነ ጉልበቱ የለኝም።»

«ይኼ የአንተ አመለካከትና አስተሳሰብ ሲሆን እኔ ደግሞ የማልቀበለው ነው፤ ጨርሶ አይዋጠኝም። ከቤትህ መመለስ አለብህ፣ ደግሞም ትሄዳታለህ። አንተ ከፈለግህ፣ ወደ ቤትህ ከመመለስ የሚያግድህ ነገር የለም።»

«አስከ ዛሬ ከቤቴ የመመለሱ ጉዳይ የሚቻል ነው የሚል ተርጣሬ ከህሊናዬ ውስጥ ገብቶ አያውቅም» ሲል አጉረመረመ።

«ከገዛ ቤቱ ኮብልሎ መጥፋት አሳፋሪ ተግባር ስለሆነ ማንም የሚቀበለውና የሚደግፈው ነገር አይደለም። 'ወደ ቤቴ አልመለስም' ብሎ መወሰን ደግሞ የጥፋት ጥፋት ነው። ባጭሩ 'ከቤቴ የመመለሱ ጉዳይ የሚቻለኝ አይደለም' ነው የምትለው። ለምንድነው የማይቻልህ?» ብሎ ሲጠይቀው የሰር ልዮኔል አምባ ዱብ ዱብ አለ። እስከዚያች ሰዓት ድረስ ጨዋታ ሲጫወቱ አምባ አውጥቶ ያለቀሰበት ጊዜ አልነበረም፤ አሁን ግን አደረገው።

«አስከ ዛሬ የመሰልኝ» አለ ሰር ልዮኔል ሲመልስ፣ «የሠራሁት ሥራ ከይቅርታም በላይ ስለሆነ 'ባለቤቴ ትምረኛለች' የሚል ተስፋ ከህሊናዬ ውስጥ ገብቶ አያውቅም።»

«ሊሆን ይችላል። ግን እስካሁን ባሚወትከኝ ባለቤትህ እስከዚህ ዉህኝ ለው አይደለችም። ፍሀሩህ ልብ ስላሳት ይቅር እንደምትልህ እርግጠኛ ነኝ። ለመሆኑ ለምንድነው መጥፎውን ተግባር ከሚገባው በላይ የምታደርገው? አንዳንድ ጊዜ እኮ ሰዎች በአላብ በፈጠሩት ጉዳይ ራሳቸውን ከመጠን በላይ እንደሚያበቃዩ ታውቅ የለ?»

«ግን እኮ» አለ ሰር ልዮኔል በተስፋበረ ድምፅ፣ «ይቅርታ የሚገባኝ ሰው አይደለሁም። አንተ የምትሰው ነገር ደግሞ የሚገባኝ አልሆነም» ብሎ ሲናገር «ፍርዱን ለእርስዋና ለፈጣሪ ብትተወው ይሻላል» አለው።

«በእንድ ወቅት ከቤቴ ወደ መመለሱ አዘንብዬ ነበር» ብሎ ሰር ልዮኔል ሲናገር አሳቡን ሳይጨርስ ጎደኛው የቀኝ እጁን እፈፍ አድርጎ ይዞ «ወደ ቤትህ ተመለስ» በማለት ጣልቃ ገባበት። «ማንኛውም ሰው ሲሆን ሲሳሳት ይችላል። ግን ሁሉም ሰው በሠራው ሥራ ሳቢያ የሚመጣውን መዘዝ በዘዴ መያዝና መቀበል አይችልም። ሳደረስከው ጥፋትና ሰፈጸምከው በደል ቤዛ የምትሆንበት ጊዜ አሁን ነው። ሴላው ቢቀር የበደልከውን ለመካስ ስለምትችል ወደ ቤትህ ተመልሰህ የሚበትህን ቀሪ ሕይወት አድስ። ቀሪ ሕይወትዋ ደስታ እንዲኖናጸፍ መጣና መጥፎ አሳብ አደሆንም። አሁን ካለችበት የብስጭትና የበቀቀን ኑሮ ውስጥ ሰዘላለም ከመተው ሕይወትዋን ለመለወዋ መሞከር እጅግ የተሻለ መንገድ ይመስለኛል።»

«ምስኪንዋ ኤሊኖር» አለ ሰር ልዮኔል በማቃሰት። «አሁን ያልከውን አውነት ነው ዊሊ። በሕይወት ዘመኔ የፈጸምኩት በደል ወደ ጓላ መለስ ብዬ ሳየው እኔነቴን እስክ መጥሳት አደርሳለሁ። ኤሊኖርን በጣም ነው የበደልኳት። እኔው ራሴ የዚህ ዓይነቱን ሥራ ለመሥራቴ ማመን ያቅተኛል። ያም ሆነ ይህ የአንተን ምክር መቀበሉ ሳይሻል አይቀርም መለለኝ። ወደ ቤቴ ተመልሼ ሄጀ እድሴን ልሞክር።»

«ደግሞም ይህን ምክር ስለማስህ በራሴ ላይ በመፍረድ እንደሆነ አትዘንጋ» አለ ዊሊ ኂኩል። «አንተ ከእኔ ስትርቅና ወደ አገርህ ስትሄድ የልብ ወዳጀን እንደማጣ እወቀው። ቢሆንም ለአንተ የሚሻለው ይኸው ነው። ለእኔ ግን አብሬን ብንቆይ ነበር የሚሻለኝ።»

ከዚያ በኋላ ብዙም አልተነጋገሩም። ያን አለት ሚታ ሰር ልዮኔል እጽፋለሁ ያለውን ደብዳቤ ጸፌ። በሚቀጥለው ቀን ወደ ቤቱ ለመሄድ ጉዞውን ቀጠለ።

Scan by Easy Scanner

ምዕራፍ ሃምሳ ስምንት

መልካም ዜና

ሰር ልዮኔል ቸኩሎ ወደ ቤቱ ቢገበግሰም የጻፈው ደብዳቤ ቀድሞት ይደርሳል። እንዳጋጣሚ ሆኖ መንገድ እንዳለ ስለታመመ የኑሀውን ጊዜ አራዘመበት። የበሽታው መንስዔ ጸጸት፣ የህሊና ወቀሳና ጭንቀት እንደሆነ ታወቀ። ከቤቱ በቶሎ ለመድረስ እጅግ ጓጉቶ ስለነበር ተገቢውን ጥንቃቄና ዝግጅት ሳያደርግ ነበር ጉዞውን የጀመረው። በገዛ ሳይ እንዳለ እንቅልፍ ለመተኛትም ሆነ እህል ለመቅመስ የነበረው ፍላጎት እጅግ በጣም ተመናመነበት። በዚህ ጊዜ ደግሞ ደጋግሞ ያስበውና ያሰላሰለው የነበረው ከቤቱ ለመድረስ የሚቀረው ጊዜና ሰዓት ነበር። ቀደም ሲል ህሊናውን ምን እንዳጨለመበት ሊገባው አልቻለም። ከዚህም ሌላ የቪቫንን ንጽህናና እውነተኛነት ማሳወቅ እንደሚገባ እንዴት ብሎ እንዳላሰበበት በጣም ይገርመዋል፤ በዚህም በእርሱነቱ እጅግ ይማረራል። ለማንኛውም በተቻለው ሁሉ ጉዞውን አቀላጥፎ ለመቁጠል ብርቱ ጥረት አደረገ። ቢሆንም 'የቸከለ አፍሶ ለቀመ' እንዲሉ ችክላውና ጭንቅቁ ማን ጉዳት አደረሰበት እንጂ አልጠቀመውም። ስለታመመ የአሰበው ጉዳይ በቶሎ ሊሆንለት አልቻለም። በሽታው ግን ለክፉ የሚሰጥ አልነበረም።

«መሄድ አለብኝ፣ የሞት የሽረት ያህል ነው ጉዳዬ። ከአገሬ ከእንግሊዝ አገር በቶሎ መድረስ አለብኝ» አለው መንገድ ላይ እንዳለ ላከመው ሐኪም። ሐኪሙም ሲመልስለት «ጉዞህን የምትቀጥለው በሕይወትህ ላይ ፈርደህ እንደሆነ እወቀው። በመቸኮልህ የምታተርፈው ነገር አይኖርም። እኔ የምልህን ሳትሰማ ልሂድ ብለህ ከተነሳህ እንዳሰብከው አገርህ በሕይወት አትገባም» ሲል ሐኪሙ እጅግ ከስተር ባለ አነጋገር አስጠነቀቀው። ስለዚህ ሰር ልዮኔል ከገባበት ሆስፒታል አርፎ ከመተኛት በስተቀር ሌላ አማራጭ ስላልነበረው ሰተወሰነ ጊዜ ከጉዞው ተስተጓጉለ። በዚህም አገሩ ለመድረስ ካሰበበት ቀን ብዙ ዘገየ። የፍቅረኛቹ ግኡኝነት ዜና ግን እርሱ እንግሊዝ አገር ከመግባቱ በፊት ደረሰ።

ስለቪቫን ንጽህናና በዚያች ሰዓት አብረው እንዳልሆኑ በመግለጽ የጻፈው ደብዳቤ የሟቹ የሎርድ ሊንን ጉዳይ ለሚከታተሉ ጠበቆች ነበር የላከው። በደብዳቤው ስለሎርድ ሊን መሞት በጋዜጣ ማየቱን፣ ቪቫን ከእርሱ ተለይታ መሄድዋንና ከሦስት ዓመት በፊት ለአጭር ጊዜ

ተገናኝተው ከተለያዩ በኋላ የት እንዳለች እንደማያውቅና ያቀረበው አለብ ደግሞ እውነት ለመሆኑ አጥርቶ ነበር የጻፈው። ሰዎች ዜናውን በመጀመሪያ ሲሰሙ በጣም ተገረሙ፣ ማመንም አቃታቸው። ለቪቫን በማሰብም ሰዎች ስለባሕርይዋና ስለትክክለኛነትዋ እንዲያውቁና ምን ያህል የተሳዳች ሴት እንደሆነች እንዲገነዘቡ አጠንክሮ ነበር የጻፈው። የሎርድ ሊን መብት ጠባቂ መሥሪያ ቤት ይህን በሰማ ጊዜ በጣም ትገርሞና ተደንቆ «ሽማግሌው ይህን ሰምተው በሞቱ!» ሲል ዋናው ጸሳፊ ተመኘ። «እውነት ነው፤ ዜናውን ሰምተው ቢሞቱ ለእርሳቸው ትልቅ ነገር ነበር» ብሎ ሲናገር የዋናው ጸሳፊ ልጅ የአባቱን ፈለግ ተከትሎ «የደረሰባቸው ከባድ ሀዘን ከስማቸው መጥፋት ጋር ተዳምሮ ብዙ አሰቃያቸው። ስለዚህ የደብዳቤው ግልባጭ ለቤተሰቡ መላክ አለብን» ሲል አሳብ ስለሰጠ እርሱ በተሰነዘረው አሳብም ስለተስማሙ የደብዳቤውን ግልባጭ ለቤተሰቡ ተላከ።

«የሰውዬው ባለቤት ለወንድ መልክና ቁመና ብላ ሀብቷን፣ ምቾትዋንና መልካም ስምዋን በቀላሉ ሸጠች። ያ ያሳዝናል። ከሰውዬው ጋር አብራ ክብልላ ብዙም ሳትቆይ ያንን ሰው ደግሞ ጥላ ሄደች። ይህ ደግሞ እጅግ ያሳዝናል። 'ምን ዓይነት ለጆሮ የከበደ ታሪክ ነው' ሲሉ አባትና ልጅ ብዙ ተጫወቱ። ጨዋታቸውንም በመቀጠል «ለምን ይሆን ቤትዮዋ ይህን አሳፋሪ ድርጊት የፈጸመችው?» ብሎ ልጁ ሲጠይቅ «እግዚአብሔር ይወቅ እንጂ እኔ ምን አውቃለሁ» ሲሉ አባት መለሱለት። «የአገሩ ሰው ሁሉ እንዳስበሙና እንደገመቱው ሁለቱ ወዳጆች አብረው የከበለሉት በፍቅር ምክንያት አልነበረም ማለት ነዋ!» በማለትም አሳባቸውን አጠቃለሉ።

የዜናውን ግልባጭ ጋዜጠኞች ስላገኙት ዜናው በየጋዜጣው ታትሞ ወጣ። «ቪቫን በመልክዋና በሣርማ ሞገስዋ በጣም የታወቀች ሴት ነበረች፣ አሁን ግን የት እንዳለች አይታወቅም» ብሰው ስለጻፉም የመጥፋትዋ ጉዳይ ብዙውን ሰው ግራ አጋባ። 'ወንድ አፍቅራ ክበለለች' ተብሎ የተወራው ወሬ ውሸት መሆኑ ሲሰማ ብው ሁሉ 'ምንድነው ነገሩ' ሲል ብዙ ተወያየበት። ሰር ልዮኔል በዚህ ሳያቆም የሠራው ሥራ ትክክል አለመሆኑንና ቪቫን ከእርሱ ጋር እንዳልሆነች በግክል ለግሉ ጠበቃ ሌላ ደብዳቤ ጽፎአል። በእንግሊዞች ባህል መሠረት በቂ ህብት ያለው እያንዳንዱ ቤተሰብ መብቱን የሚያስከብርለት የግል ጠበቃ ስላለው ነበር ለጠበቃው የተለየ ደብዳቤ የጻፈው።

Scan by Easy Scanner

«ቀደም ብዬ ባስተውል ኖሮ ሰው ሁሉ የተሳሳተ ወሬ ሲነካ መልስ አስጥቤት ነበር እንጂ ዝም አልልም ነበር» አለ ሰር ልዮኔል ያን ደብዳቤ ሲጽፍ። «በዚያን ጊዜ ጉዳዬን አደባባይ ለማውጣት አልፈለኩም እንጂ የእንግሊዝን አገር ለቅቀን አብረን ወደ ፈረንሳይ መኸብለላችን እውነት ነው። ቢሆንም በእለቱ ወደ ሚታ ካሌይ ከሚባል ወደብ ስንደርስ ተለያየን፣ ከዚያም ወዲህ አልተገናኘንም። ስለዚህ አሁን ዓለም ይህን ምሥጢር እንዲያውቅ ስለምፈልግ የዚህ ደብዳቤ መንፈስ በጋዜጣ እንዲወጣ አድርግ» ሲል የግል ጠበቃውን አዘዘው እንጂ ደብዳቤውን የጻፈው ቁጥኩሱ ስለነበር አሁን እርሱ ወደ ቤቱ ለመመለስ መንገድ ላይ እንደሆነ አልገለጸለትም።

ደብዳቤውን ለጠበቃው ለሚ/ር ኖርተን የጻፈው ከግብፅ አገር ላይወጣ ስለነበር ደብዳቤው ከየት እንደ መጣ በአድራሻው ታውቀ። ጠበቃው ደብዳቤው ደርሶት ሲያነበው ሰር ልዮኔል የሚለው ነገር ትክክል ለመሆኑ እልተጠራጠረም። ነገር ግን 'ይህን ደብዳቤ ከሦስት ዓመት በፊት ቢጽፈው ይሻል ነበር' ሲል ለራሱ ነገረ። ጠበቃው ወዲያው ሌላ ደብዳቤ ጽፎና ባለጉዳዩ የጻፈውን ደብዳቤ ግልባጭ አያይዞ ለመሬት ከበርቴው ለኤሊኖር አባት ላከላቸው። ሽማግሌው ደብዳቤው ሲደርሰቸው እንዴት ብሎ ሰውነታቸው እንደ ተለዋወጠና እንዴት እንደሆኑ ለመጻፍ ከመሞከር ይልቅ አንባቢ በአሳብ ቢያየው ይሻላል ብዬ ትቼዋለሁ።

«ኤሊኖር እንደታመመች አውቃለሁ» አለ ጠበቃው ደብዳቤውን ሲጽፍ። «በሕመምዋ ላይ ይኼ ሲጨመር ሊገዳት ይችላል ብዬ ስለገመትኩ የደብዳቤውን ግልባጭ ወደ እርስዎ አልላኩም። ቢያስፈልግ እርስዎ ቀስ ብለው ያስረድዋት። ሰር ልዮኔል በጻፈው ደብዳቤ የተካተቱ አሳቦች ግን የምጠራጠራቸው ስላልሆኑ እንዳለ መቀበል ነው። ቪቫንና ሰር ልዮኔል አብረው እንዳልሆኑ እኔም ጠርጥሬ ነበር። ለዚህም የተጨበጠ ምክንያት አለኝ። ሆኖም ግን ካሌይ ወደብ ላይ ለመለያየት አብሮ መከብለላቸው በእጅጉ ግራ የሚያጋባ ከባድ ምሥጢር ያለው ይመስላል። ምሥጢሩን ለማውጣት የሚችለው ደግሞ ራሱ ሰር ልዮኔል ብቻ ነው።»

የመሬት ከበርቴው ደብዳቤውን ባነበቡ ጊዜ የተዘበራረቀ ስሜት ተሰማቸው። «ሰር ልዮኔል ያቺን ቆንጆ ከሞቀ ቤትዋ አስኮብልሎ መውሰዱ እርግጥ ነው፣ ምክንያቱም 'ቆንጆዋና ኃጥያተኛዋ ቪቫንን ይዤ ነው የኮበለልኩት' ብሏል። ይህ ከሆነ ደግሞ የተደበቀ ምሥጢር ያለው አይመስልም። አብራው ካልሄደች እንደዚያ ብሎ አይጽፍም ነበር።»

በሠራው ሥራ ስለተቀየመ ዜናውን እንደሰሙ ያልተሳደቡት በድብ አልነበረም። አሁን ደግሞ 'ወዲያው ነው የተለያዩነው' ይላል በማለት ብዙ ቆዘሙ። የሽማግሌ አእምሮአቸው መልሱን ሲሰጥ ስላልቻለ ዘመትር አስቸጋሪ ነገር ቢገጥማቸው እንደሚያደርጉት ባለቤታቸውን ለማማከር እርሳቸው ወደ ነበሩበት አቀኑ። ባለቤታቸው ልጃቸውንና የልጅ ልጃቸውን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ሴትት ልዊስ ከሚባል ሥፍራ ነበር የሚገኙት። ከዚያ እንደ ደረሱ ባለቤታቸው ሚስስ ጎርዶን ደብዳቤውን አነቡት።

«የተጻፈው ነገር እውነት እንደሆነ ተሰፋ አደርጋለሁ። የተባለው ነገር እውነት ከሆነ በኤሊኖር ሕይወት ላይ ታላቅ ለውጥ ያመጣል። ሰውዬው ተመልሶ ቢመጣና ወዳጅነታቸውና ፍቅራቸው እንደገና ተቀስቅሶ ሰር ቢሰድ፣ ብዙም የሚደንቅ ነገር አይሆንም» ሲልዋቸው «ታጂያ ሴትዮዋ የት ነው ያለችው? ምን ሆና ይሆን? የወደፊት ዓላማዋስ ምንድነው?» በማለት የመሬት ከበርቴው ባለቤታቸውን ጠየቁ።

«ያ የእኛ ጉዳይ አይደለም» አሉ ሚሰስ ጎርዶን። «እኛ ማሰብ ያለብን ስለኤሊኖር ነው። አሁኑኑ ቡቶሎ ሂድና ደብዳቤውን አሳያት፣ ትውቀው። ሐኪሞች ከሚሰጥዋት መድኃኒት ይበልጥ ይህ ደብዳቤ ጤናዋን በቶሎ ይመልሰላታል።»

በዚህ ጊዜ ደህና አድርገው እንዳስለጠኑት አሽከር ሚ/ር ጎርዶን የሚስታቸውን ትእዛዝ ተቀብለው በቀጥታ ወደ ልጃቸው ሄዱ። ባለቤታቸው በሰጓዘሩት አሳብ ተደሰተዋል። ማንኛውም ወንድ ሌሳውን ወንድ ለማንበረከክና ለመቅጣት እንደሚጓጓ ሁሉ እርስቶቹም ሰር ልዮኔልን ለመቅጣት ከፉኛ ቋመጡ። ልጃቸው ከነበረችበት ቪላ ሲደርሱ ኤሌኖር በመጠኑም ቢሆን ተሽልዋት ነው ያገኙዋት። ልጅዋ ግን ብዙም አልተሻለውም። ሲ/ር ማሪ ነበረች ይህን የነገረቻቸው። የሲስተርዋ ሬት ጠቂቋር በሽተኛ መስላ ሲያይዋት እጅግ አዘኑላት።

«ሲስትር» አሉ የኤሊኖር አባት፣ «ልጅን ለማየት ፈልጌአለሁ። መልካም ዜና ነው ይዤላት የመጣሁት።»

«ጥሩ ነዋ፣ እርስዋ ሰትደሰት እኔንም ደስ ይለኛል» አለች ምሥጢሩ ምን ይሆን በማለት ልብዋ አይሰላሰለ። 'ስለሰር ልዮኔል ሲሆን ይቻላል' ብሚል ልብዋ ጠርጥሯል። «ኤሊኖር በማም ተሽሉአታል፤ መልካሙ ዜና ደግሞ በበለጠ እንደሚያሽላት አልጠራጠርም» አለቻቸው ቀጠለችና።

Scan by Easy Scanner

ሸማሌው ዓይን ዓይንዋን እያዩ «ጉዳዩን አንቺም የምታውቂው ይመስለኛል» ሲልዋት በጥፊ እንደ ተመታ ሰው ክው አለች። ልብዋ በኃይል ይመታ ጀመር።

«ስለኤሊኖር ታሪክ ማለትዎ ከሆነ አውቀዋለሁ፣ ነግራኛለች» አለች ሲ/ር ማሪ ስትፈራ ስትቸር።

«ጥሩ ምክር እንደ ሰጠሻትና አሁንም እንደምትሰጫት አተማመንብሻለሁ» አሉ የመሬት ከበርቴው በስሰለሰ እንደበት።

«ቀደም ሲል እኔ የሰጠኋት ምክር» አለች ሲ/ር ማሪ፣ «ድንገት ባለቤትዋ ወደ ቤቱ ቢመለስ ሳታወላውል ይቅርታ እንዲታደርግለትና የሚሻለው መንገድ ይኸው እንደሆነ ነው» ስትላቸው ወገግ ብሎ የነበረው ፊታቸው ትንሽ በመቀየሙ እንዳ መጥቆር አደረገው።

«ይህን ነው በውል የነገርሻት?» ሲሉ ጠየቅዋት።

«እምን፣ ብያታለሁ። ደህንነትዋን ለማየት የሚፈልግ ማንኛውም በስሜት ያልተዋጠ ሰው ይህን ነው ማለት ያለበት» ስትል መለሰችላቸው። ይህን ጊዜ ያለማመንታት «ደፋር ነሽ» ሲልዋት «እርስዎ ልጅዎን ቢጣሙ ይወዳሉ። ማንም ከእርስዎ ይበልጥ ልጁን ያፈቀረ የለም። ስለዚህ ለደስታዋ አንቅፋት አይሁኑ። አበቦች ያለ ውሃና የጸሐይ ብርሃን ለማደግና ለማበብ እንደማይችሉ ሁሉ እርስዋም ያለ ባልዋ ተደስታ ለመኖር አትችልም። ባልዋ ተመልሰ ከመጣ እርስዎ ጣልቃ አይግቡ። ይቅርታ ታድርግለትና ከእርሱ ጋር ተደስታ ትኑር» ስትል ነገርዋን አክርራ ነገረቻቸው።

«እሺ አንቺ እንዳልሽው ይሁን፣ ጣልቃ ገብቼ አልበጠብጥም» ሉ ኮፍጣናው የመሬት ከበርቴ። «እውነትሽን ነው፣ እኔ ጣልቃ ከገባሁ አርስዋን ማለቃየትና በእርስዋ ላይ የሞት ብያኔ ማሳለፍ ይሆናል። ግን ፈቃዱና ምርጫው የእኔ ብቻ ቢሆን ሳላመነታ እገድለው ነበር። ሆነም ቀረ ምርጫ ስለሌለኝ የግድ ስሜቴን መዋጥና መቆጣጠር ይኖርብኛል።»

«ልክ ኖት፣ ስሜትን መዋጥ ነው የሚጠቅመው» አለች ሲ/ር ማሪ ሀዘን እየተሰማት።

«ሽጉጤን አቀባብዬ ግምባሩን ላቡ ባቆሰለውና የሚተናነቀኝ ስሜቴ ቢወጣልኝ 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ሰማለትና ከእርሱ ጋር ለመታረቅ

ይቀለኝ ነበር። ብቻ አንቺም እንዳልሽው ቢቀር ይሻላል። እመኚኝ ሲስተር፣ እርሱ ይምጣ እንጂ እኔ ቃሌን አላጥፍም። አሁን ጨዋታው ይብቃንና ልጁ ካለችበት ገብቼ ያቦብኩትን ልንገራት። የምነግራት ዜና ሕሊምኞ ከሚሰጥዋት ክኒን ይበልጥ ከበሽታዋ ሊያድናት እንደሚችል ባለቤቴ ነግራኛለች።»

«ስለባልዋ ነው መልካሙ ዜና?» ስትል ሲ/ር ማሪ በማመንታት ስትጠይቃቸው «አዎን፣ ስለባልዋ ነው። ብቻ ስለእርሱ የሚነገር ነገር ሁሉ መልካም ዜና ከተባለ ይሁን፣ እንደ መልካም ዜና እንቁጠረው። እኔ ግን መልካም ዜና አልለውም» ሲሉ መለሱላት። የሲስተርዋ ልብ በድን ጋጠ ሊፈርጥ መድረሱን ግን ከፊትዋ ላይ ለማየት አልቻሉም። ፊትዋ ከመቅጽበት አሻቦ መሰለ።

«ተመልሶ ሊመጣ ነው?» ስትል በመንቀጥቀጥ ጠየቀቻቸው።

«የለም፣ አይመጣም» አሉ የመሬት ከበርቴው። «የዚህ ዓይነቱ ዜና እንኳን የመጣ የለም፤ እስካሁን የተሰማው ዜና እንደ ሥራው የጨለመ ነው። ምን ዜናው ብቻ ህሊናውም የጠቁረ ነው እንጂ። አሁን ያለው ግብፅ አገር ነው» ካሉ በኋላ ልጃቸው ከነበረችበት ክፍል ገቡ።

ከክፍልዋ ውስጥ ገብተው ሲያይዋት እውነትም የመሸሽል ለውጥ እንዳላት ተገነዘቡ። ደብዳቢውን አሳይዋት። ደብዳቢውን ካነበበች በኋላ ምን እንደ ተባባሉ አይታወቅም። ብቻ ሽማግሌው ከክፍልዋ ሲወጡ እምባ በእምባ ሆነው ነው የወጡት። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ኤሊኖር ሲ/ር ማሪን አስጠራቻት። ሲ/ር ማሪ ስትገባ ከዚያ በፊት አይታው የማታውቅ እርካታና ፈገግታ ከኤሊኖር ፊት ላይ ተመለከተች።

«ሲ/ር ማሪ ነዪና ሳሚኝ» አለቻት ጮክ ብላ። «ዘወትር ታጽናኚኝ ስለነበር የሰማሁትን አስደሳች ዜና በቅድሚያ ለአንቺ ነው መንገር ያለብኝ። ይኸውልሽ መልካም ዜና ነው የሰማሁት። እስከ ዛሬ ባለቤቴ ከሲንዋ እመቢት ከሺቫን ጋር ነው ያለው ብለን እናምን ነበር። እውነታው ምን እንደሆነና ባለቤቴ ምን ይመራ እንደ ነበር ታውቂያለሽ? ሁሉንም እነግርሻለሁ።»

Scan by Easy Scanner

ምዕራፍ ሃምሳ ዘጠኝ

ትልቁ ደብዳቤ

ከሚር ኖርተን ቢሮ በራፍ መኪና መጥቶ ይቆማል። ጊዜው የቢጋ ወራት ስለነበር የቀኑ ብርሃን ወለል ነው ያለው። አንድ መልኩመልካም ወንድ እጅግ በጣም ቸኩሎ ከመኪናው ወረደ። ከኾነላው ብዛት የቀነሳ እቃውን ለማውረድ ሲታገል ሊረዳው ጠጋ ካለ ሰው ጋር ተጋጨ።

«ሚር ኖርተንን በአስቸኳይ እፈልገዋለሁ» በማለት ጮክ ብሎ ሊጣራ «ክቢሮአቸው ናቸው» የሚል መልስ ተሰጠው። 'እኔ በአስቸኳይ የምፈልገው ሚር ኖርተንን ሲሆን እነርሱ ግን ከፊቴ እየተደነቀሩ ይተረማመሳሉ' ሲል አሰበ። ሰውዬው የሚር ኖርተን ቢሮ የት እንደሆነ ያውቅ ስለነበር በቀጥታ ወደ ቢሮአቸው አመራ። ሚር ኖርተን ሰውዬውን ሲያዩ የሚናገሩት ጠፍቶአቸው ዝም አሉ።

«ምነው እያውቁኝም እንዲ?» ሲል አፈጠጠባቸው።

«እሪ የለም» ብለው ከመለሱለት በኋላ አፍጥጠው ሲያዩት «እንዴት አያውቁኝም፣ እኔ እኮ ሰር ልዮኔል ራይዳል ነኝ» አላቸው። በዚህ ጊዜ ሚር ኖርተን ከመቅጽበት ከመቀመጫቸው ተስፈንጥረው ብድግ አሉ።

«ሰር ልዮኔል ነህ? እንዴት ሊሆን ይችላል? የፈጣሪ ያለህ ምነው ተሰዋወትክብኝሳ! በሚገባ ነው እንጂ የማውቅህ። ጢምህ ተንዠርግጎ ፊትህ ተሰዋውጠና ከመጠን በላይ ክስተህ ሳይህ ጨርሶ የማውቀው ሰር ልዮኔል አልመሰልከኝም፣ በጣም ተለዋውጠሃል። በድንገት ሳይህ ሌላ ሰው ነው የመሰልከኝ። የሚገርም እኮ ነው፤ በጣም ተቀይረሃል። አሁንማ ሰር ልዮኔል መሆንክን ካወቅሁ 'እንኳን ደህና መጣህ' ልበልህ እንጂ» ቢሉም በሚታቸው ግን ወዲያው ቀዝቀዝ አሉ። ያ መዋር ሥራው ትዝ ስላላቸው ወደ ኋላ አፈገፈጉ። ሰር ልዮኔልም ለውጣቸውን አዮ።

«ሚስተር ኖርተን፣ አስደንግጥክዎት አይደል፤ ቢሆንም ስለፈጣሪ ብለው ፊት አይንሱኝ። በእኳል በመገናኘታችንም አይክፋዎት» ሲሳቸው «እሪ የለም፣ ጨርሶ አልከፋኝም። እንዲህ ባትል ግን ይሻላል መሰለኝ» ሲሉ መልሰውለት ስሜታቸውን ለመቆጣጠርና አይታቸውን ለማሻሻል ታገሉ። ከዚያም «ሳይታሰብ በድንገት ላይህና ግን እንደሆንክ ሳውቅ ትንሽ እንደ መደንገጥም፣ እንደ መውናበድም አድርጎኝ ስለሆነ አትቀየመኝ» አሉት።

«አይፈረድብዎትም፣ ሳይታሰብ በድንገት ነው የመጣሁበት። ለውነቱ እንደ ተለዋወጠ እኔም አውቂዋለሁ» አላቸው ሰር ልዮኔል በመረጋጋት።

«አሁንም እኮ ግብፅ አገር ያለህ ነበር የመሰለኝ» ሲሉት «እንዲያውም ከዚያ ከተነሳሁ በኋላ ጥቂት አሞኝ ነው እንጂ ከአስር ቀን በፊት ከዚህ እደርስ ነበር» ሲል ዣዮ ላይ እንዳለ ስለደረሰበት ችግር ነገራቸው።

«ታዲያ አሁንስ እንዴት ነህ፣ ተሻለህ? ለማንኛውም እንኳንም ለአገርህ አበቃህ፣ እንኳን ደህና መጣህ» በማለት ነገሩን ለማረሳሳት ሞከሩ እንጂ አሁንም ቢሆን የቃላቸው አወጣጥና የድምጻቸው ቃና የተናገሩት ነገር ከልባቸው እንዳልሆነ ሳያስጣቸው አልቀረም።

ሰር ልዮኔል ደክሞት ስለነበር ወንበር ጎብ አድርጎ ቁጭ አለ። ቁጭ እንዳለም «እቦቲ አንዱንም ነገር ሳይደብቁ ስለሁሉም ነገር ያጫውቱኝ» ሲል ጠየቃቸው በመጓጓት። «ከዚህ አገር ድምጼ ከጠፋ ጀምሮ የሆነውን ሁሉ አንዱንም ሳያስቀሩ ይንገሩኝ። በቅድሚያ ግን ስለባለቤቴ ቢያጫውቱኝ በጣም ደስ ይለኛል። ኤሊኖር አሁን ዮት ነው ያለችው?» ብሎ ሲጠይቃቸው «ኤሊኖር ልጆችዋን ይዛ ከአባትዋና ከእንጀራ እናትዋ ጋር ደቡብ ፈረንሳይ ውስጥ ነው ያለችው» ሲሉ ሚር ኖርተን ገለጹለት። ቀጥለውም የሚያውቁትን ሁሉ ነገሩት። ዓለም ስለእርሱ ምን ብሎ ያወራ እንደ ነበርም አስረዱት። ሳይፈሩ ሁሉንም በነገሩት ጊዜ ያ የበረሃ ፀሐይ ያቃጠለው ፊቱ በትካዜና በሀዘን ብዛት ባይበልጥ ጠቁሯል። ሽማግሌው ጠበቃ ለማለት የፈለጉትን ሁሉ ተናግረው እንደ ጨረሱ እጃቸውን ወደ ሰር ልዮኔል ዘረጉና ተጨባበጡ።

«እግዚአብሔር ይስዮልኝ፣ አሁን የተናገሩት ሁሉ ከእውነተኛ ሰው የሚጠበቅ ትክክለኛ አመልካከት ነው። የሠራሁት ሥራ ትክክል ስላልሆነ የሚገባኝን ነው የነገሩኝ። የሞኝ ሥራ ነው የሠራሁት። ነገር ግን ሥራዬ የሞኝ ቢሆንም በሠራሁት ሥራ ከልብ መጸጸቴን ይወቁልኝ። ሚር ኖርተን» እለ ቀጠለና የሽማግሌውን ፊት እያየ፣ «ስለቪቫንም የሚያውቁት ነገር ካለ ቢነግሩኝ። ይህን ሲያጫውቱኝ እኔ ደግሞ በመካከላችን ምን እንደ ተፈጠረ አንዱንም ሳልደብቅ እነግሮታለሁ። የት እንዳለች የሚያውቅ ሰው ካለም እርሱንም ቢጠቁሙኝና ቪቫንን ባኒጋግራት ደስ ይለኛል። ላገኛት አፈልጋለሁ። ይህም ብዙ አስቤ የቆረጥኩበት ሌላው ጉዳይ ነው» ቢላቸውም ለጊዜው የእርስዋን ነገር በዚያው አቁሞ የሆነውን ታሪክ አንድ በአንድ እርሱ ሲነግራቸው ጠበቃው እጅግ ትገረሙ።

Scan by Easy Scanner

«የሚገርም ነው» አሉ ሚ/ር ኖርተን። «እስከ ዛሬ የሴቶች ባህርይ ምን እንደሆነ ለማወቅ ብዙ ብሞክርም ምሥጢራቸው ሊገባኝ አልቻለም፣ ወደፊትም የሚገባኝ አይመስለኝም። ስለዚህ ቪቫን ከአንተ ጋር መለየትዋ ለምን ይሆን ወይም ምን ማድረግዋ ነው በማለት ጊዜዬን ላጠፋና ራሴን ለማስጨነቅ አልፈልግም። በእኔ አመለካከት ይህን ማድረግዋ ምንም ዓይነት ትርጉም ያለው አይመስለኝም። ለማንኛውም አሁን ማድረግ ስለምንችለውና ምን ማድረግ ስላለብን ጉዳይ ብንነጋገር ነው የሚሻለው። እንደ ገባኝ፣ ቪቫን የት እንዳለች አውቀህ ልታገኛት ትፈልጋለህ። ስለዚህ እቅማችን በፊቀደ ሁሉ እርስዋን ማፈላለግ አለብን ማለት ነው። እሳብህ ይኸው ነው፣ አይደል?»

«ይኸው ነው፣ እርስዎ ብዙ ነገር ያዩና በሕይወት ዘመንዎም ብዙ ነገር ያሳለፉ ሰው ኖት። እና ምን የሆነች፣ የትስ የገባች ይመስሉታል?»

«ይህን ለማወቅ ያስቸግራል። ተራ ሴት ብትሆን እንኳን የመላምት ግምት ለመውሰድ በተቻለ። የእርስዋ ጉዳይ ግን ትንሽ ለየት ያለ ነው። አንዳንድ ሴቶች የዚህ ዓይነቱ አጋጣሚ ሲደርስባቸው ሳያወላውሉ ራሳቸውን ያጠፋሉ። በሕይወት እየኖሩ ከመጨነቅ መሞትን ይመርጣሉ። እንዳንዶቹም ከአንዲህ ያለ ፈተና ውስጥ ሲገቡ በቀጥታ ወደ ባሎቻቸው ይመለሳሉ የሚል አምነት ነው ያለኝ። እርስዋ ግን እንደሚገባኝ ከብርዋን የማታስደፍር ቆራጥ ሴት ናት። የሠራችው ሥራና የወሰደችው ቆራጥ እርምጃም ሲታይ ከብዙ ሴቶች የሚጠበቅ ስላልሆነ ከሌሎች የተለየች ሴት ናት። ጨዋነት የተሞላበትም ድርጊት ነው የፈጸመችው» ሲሉት «ምን ዓይነት ሴት እንደሆነች ይገባዎታል?» ብሎ ጠየቃቸው።

«እርሱን ለጊዜው እናቆየውና አሁን ምን ለማድረግ እንደምትፈልግ ብንነጋገር ይሻላል» ሲሉ የጨዋታቸውን መስመር ለመቀየር ሞከሩ።

«በትክክል እንኳን አላውቀውም። እዚሁ ለጉዶን ለጥቂት ቀናት አቆያለሁ የሚል እቅድ ነው ያለኝ። በዚያ መሃል ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ለመወሰን እችላሁ» በማለት ሰር ልዮኔል መለሰላቸው።

«ወደ ባለቤቴ እመለሳለሁ ከሚል ድምዳሜ እንደምትደርስ ተስፋ አደርጋለሁ። በሕይወቴ ብዙ የተከራ ሰዎችን አይቻለሁ፣ የእርስዋ ግን እጅግ በጣም የተለየ ነው። በጣም አዝናለች፣ በጣምም ተከፍታለች።»

«ይህን ባያነሱብኝ እመርጣለሁ» ሲል ሳይታወቀው ጮኸባቸው። ከዚያም አንገቱን ከእጆቹ ስር ወሽቆ ዝም አለቀሰ። «አሁን ያሉትን ስለማ መንፈሴ ሁሉ ይረበሻል» አለ ከንፈሮቹ በኃይል እየተንቀጠቀጡ። «ሚ/ር ኖርተን፣ ለዛሬ ከዚሁ ሳይ ብናቆም ይሻላል፣ በቱሉ እመለሳለሁ። ከዚህ ይበልጥ ስለጀመርነው ጉዳይ ለመነጋገር አቅሙም ሆነ ብርታቱ የለኝም» ብሎ ለመውጣት መንገድ ሊጀምር «ማታ አብሬን እራት እንብላ» ሲሉ ቃበዙት እጅግ በጣም ሀዘን እየተሰማቸው።

«እግዜር ይስጥልኝ፣ ስለግብዣዎ ክልብ አመሰግናለሁ። ከሰው ጋር ተቀላቅሎና ሀብረተሰብ ውስጥ ገብቶ ለመዝናናት የመንፈስ እርካታ ያስፈልጋል። እኔ ደግሞ ያ እርካታ አሁን የለኝም። ግብዣው ከዚህ ትንሽ ጠንከር ስል ቢሆን ይሻለኛል። ሰንደንን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ግን አጠይቆታለሁ።»

ሆኖም ግን በመካከሉ ብዙ ያልተጠበቀ ነገር ሆነ። ሰር ልዮኔል ወደ አረፈበት ሆቴል ቢመለስ ለንደን ከታማን ማየቱ አስጠላው። ከተማው ያለፈውን ትዝታ እየቀሰቀሰ አሰጨነቀው። ወደ ምዕራብ ክፍለ-ከተማ አቅጣጫ፣ በተለይም ከቪቫን ጋር አብረው ወደ ሄዱበት አካባቢ መሄድ እጅግ ዘገነነው። ከአረፈበት ሆቴል ገብቶ ቁጭ አለ። በሚቀጥለው ቀን በጠዋት ተነስቶ ገንዘብ ካስቀመጠበት ባንክ ሄዶ የባንክ ሠራተኞችን ለማነጋገር ወሰነ። ስዴት ሳይ በነበረበት ጊዜ ያጠፋው ገንዘብ በጣም ጥቂት ስለሆነ አሁን ብዙ ገንዘብ ሲኖረው እንደሚችል ገመተ። ከባንኩ ሲደርስ ከዚያ የነበሩ ሰዎች ወዲያው አወቁት። የመቀየም መልክ ሳያሳዩ በፈገግታ ተቀብለው አስተናገዱት። የረጅም ጊዜ ደምበኛቸው በመሆኑ 'የግል ሕይወቱን እንደ ፈለገው የመምራት መብት አለው' በሚል ይመስላል ሁሉም ሠራተኛ እጅን ዘርግቶ ነው የተቀበለው። ከባንኩ ባለቤት ከሚስተር ብራውን ቢሮ ተጠርቶ ገባ። ከለውጌው ጋር የሞቀ ሰላምታ ተለዋወጡ። ከባለቤቱና ከዋናው ሥራ አስኪያጅ ቢሮ ለመግባት የሚፈቀድላቸው ለዎች ቁጥር እጅግ ውስን ነው። እንርሱም በጣም የታወቁ ወይም ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ከባንኩ መስዋ ያስቀመጡ መሆን አለባቸው።

«በዛሬው ቀን መምጣትህ እንዴት ያለ አጋጣሚ እንደሆነ ልነግርህ አልችልም። በቅርብ ክባለቤትህ ከአሲኖር ደብዳቤ ደርሰን ስንመለከተው ወደ አንተ የሚላክ እንዲሁም ለእኛ ከተላከው ደብዳቤ ውስጥ ሌላ

Scan by Easy Scanner

የታሸገ ደብዳቤ አገኘን። ለእኛ የተጻፈው ደብዳቤ ደግሞ ከየትም ብሰን በአስቸኳይ ደብዳቤውን ለአንተ እንድንከልህ የሚጠይቅ ሲሆን ከደብዳቤው ፖስታ ላይ 'አስቸኳይ' ተብሎ ተጽፎበታል። እኛ 'ደብዳቤው በቶሎ እንዲደርስህ እንዴት አድርገን ብንልክለት ይሻላል' እያልን ስንጨነቅ አንተ ዳግሞ ከዚሁ ከቢሮአችን ድረስ ከተፍ አልክልን። 'እንዴት ያለ አጋጣሚ ነው' ያሰኘኝ ይኼ ነው።»

«ደብዳቤውን ቢሰጡኝ» ብሎ ሲጠይቅ በዝግታና በእርጋታ ለመናገር ቢሞክርም ጭንቀት፣ ፍርሃትና ድንጋጤ ከፊቱ ላይ መታየቱ አልቀረም። ቁና ቁና እየተነፈሰና ከንፈሮቹ እየተንቀጠቀጡ ደብዳቤውን ተቀበለ።

«መልእክቱ መጥፎ እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ» አሉ ሚ/ር ብራውን ትህትና በተሞላበት አንደበት። ከዚያም «ምናልባት ደብዳቤውን ብቻህን ለማንበብ ከፈለግክ እኔ ልውጣልህ» ብለው ከቢሮአቸው ወጡ። ሰር ልዮኔል ጊዜ ሳይወስድ እጁ እየተንቀጠቀጠ ፖስታውን ከፈተው። ደብዳቤውን ገና ሲያየው እጅግ ይጓጓትና ያፈቅራት የነበረችው የባለቤቱ የእጅ ጽሑፍ መሆኑን ወዲያው ለየው። «ምን ተፈጥሮ ይሆን?» ሲል ራሱን ጠየቀ። የሚወደው ልጁ በጠና ታሞ 'አባቴን በቶሎ አምጡልኝ' እያለ መዋተቱን ከደብዳቤው ተረዳ።

ልጁ በጠና ታሞ 'ያባቴ ያለህ' ሲል የትኛው አባት ነው 'ጆሮ ዳባ ልበስ' ብሎ የሚቀር! ምን ዓይነት ፈሪና ጨካኝ ሰው ቢሆንስ ነው በልጁ ላይ የሚጨክን! ይህ ሰው የሚያሳዝን ወንጀለኛ ቢሆን እንኳን ይህን ያደርጋል! ይህ እንግዲህ ከሰር ልዮኔል ጭንቅላት ውስጥ ይመላለስ የነበረው አሳብ ነው።

ሕፃን ልጅ አደጋ ላይ ነው። እርሱን አምጡልኝ ሊያለ ይጮሃል። ታዲያ የልጁን ዓይን እንዴት አድርጎ ነው የሚያየውን? የሚሰቱንስ? የልጁን መልክ አሰላለለ። ያ እምቡጥ ገላው፣ እነዚያ ከአሁን ተአሁን ተሰበሩ የሚያሰኙ ለስላሳ ጣቶቹ፣ የልጅነት ግርማውና እንደ ጠዋት ፀሐይ የሚፈካው ፊቱ፣ ሌላም ሌላም ነገር ሁሉ ከፊቱ ላይ ድቅን አለ። ልጁ እየሮጠ መጥቶ ከእንገቱ ላይ ሲጠመጠም በአሳብ በታየው ጊዜ መላ ሰውነቱ ከሚገባው በላይ ተቅበጠበጠ። ልጁ ሕፃን ሆኖ ግንባሩን፣ ጉንጩን፣ አንገቱንና እጆቹን ይስም እንደ ነበረው ሁሉ አሁንም ያንኑ መድገሙ ስለማይቀር ፍጠህ ወደ ቤትህ ሂድ አሰኘው። ታዲያ ከክብሩም በላይ ሀፍረቱን፣ የሰውነት መሸማቀቁን እንዴት ሊያደርጋቸው ነው!

ይህ የእግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን የሰውንም ሕግ ጭምር የጣሰው ግለሰብ ሰውነቱን መቆጣጠር ተሰኖት እንደ መዝለፍለፍ ብሎ ከመሬት ላይ ወደቀ። እምባው አልቆም ስላለው የሚያምረውን ሰጋጃ በእምባው አራሰው። ከዚያ በፊት አድርጎት የማያውቀውን ከባድ ለቅሶ አለቀሰ። ይህ ሰው በሌሎች ፍጡሮች ላይ የመከራ ዝናብ አዝንቦአል፤ ራሱንም ከፉኛ አሰቃይቷል። አሁን ግን ከማንኛውም ጊዜ የበለጠ፤ የከፋ ነገር ነው የገጠመው። ልጁ ሞቶም ሊሆን ይችላል። ምናልባት ትናንት 'አባቴን አምጡልኝ' አለ እንጂ ዛሬ እኮ በሕይወት የለ ይሆናል። ያ ነው ልቡን ከሁለት ሰንጥቆና ከመሪር ሀዘን ላይ ጥሎ አምርሮ እንዲያለቅስ ያደረገው። ከአሰር ደቂቃ በኋላ ሚ/ር ብራውን ሰለተመለሱ ደብዳቤው የያዘው መልእክት እጅግ አሳዛኝና አስከፊ ዜና እንደሆነ ነገራቸው።

«ልጄ በጠና ስለታመመ አሁኑኑ ነው ወደዚያ የምሄደው። የሴ ንት ልዊስ ከተማ መንገድ በየት አቅጣጫ ነው?» ብሎ ሲጠይቃቸው የመንገዱን አቅጣጫ ነገሩት። በየት በኩል አድርጎ ቢሄድ በቶሎ ሊደርስ እንደሚችልም አስረዱት።

«ልጅህ ተሽሎት እንደምታገኘው ተስፋ አደርጋለሁ» ብለውት የፌቱን ሁኔታ ማጤን ጀመሩ። ከዚያም ለማጽናናት ይመስላል «ነገሩ ያሳዝናል፤ ግን ልጆች እኮ ዘጠኝ ሕይወት ነው ያላቸው» አሉት። ሰር ልዮኔል ጥርሱን እንደማጋጪትና ከንፈሩን እንደ መንከስ ብሎ «ልጄ አንድ ነገር ቢሆን ሕይወቴ ከዚህ በበለጠ የተበላሸና የተዘበራረቀ ይሆናል» አለ።

የእንግሊዝን ባህር አቋርጦ ለመሻገር ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ ወሰደበት። በመንገድ ላይ እያለ ያስበውና ይጨነቅበት የነበረው ጉዳይ ከበፊቱ የተለየ ሆነ። የአሁን ጭንቀቱ 'ልጄ ይሞታል ወይስ ይድናል' የሚል ስለነበር ጉዞው እጅግ የሚያስከፋ ሆኖ ነው ያገኘው። ከአነስተኛዋ ከሴንት ልዊስ ከተማ ደረሰ። ከተማዋን ባየ ጊዜ ባለቤቱ እንዴት ብላ ከዚያች ጭር ካለች አነስተኛ ከተማ ለመኖር መወሰንዋ ግራ አጋባው። ቢሆንም ባለቤቱና ልጆቹ ከየት አካባቢ እንደሚገኙ ለማወቅ ሰዎችን ማጠያየቅ ነበረበት። የሚኖሩበት ቤት በምልክት ሲያጠያይቅ ከተማው ውስጥ የወረርሽኝ በሽታ መግባቱን ነገሩት። ይህም በይበልጥ የሚይዘውንና የሚጨብጠውን አሳጥቶ ብዙ አስጨነቀው። እንደ እድል ሆኖ በድንገት ቤተሰቡ የት እንዳለ የሚያውቅ ሰው አጋጠመው። ባለቤቱና ልጆቹ ለጥቂት ከሞት መትረፋቸውንና በሕይወት ሊያገኛቸው የቻለውም

Scan by Easy Scanner

በሴሮች ታላቅ ጥረትና መስዋዕትነት መሆኑንና ያሉበት ቤት አደራሽ የት እንደሆነ ነገሩት። ከተማው ውስጥ ከሚገኝ ትልቅ ሆቴል ቤት ሄዱ ከፍል ተከራዩ። ከሆቴል ቤቱ ባለቤት ጋር በመሻረክ ስለቤተሰቡ ሁኔታ አንዳንድ አሳቦችን ቃረመ።

ሕይወት ባጋጣሚ የተሞላች ስለሆነች አሁንም ባጋጣሚ የሆቴሉ ባለቤት ቤተሰቡን ያውቅ ስለነበር የባለቤቱ አባትና የእንጀራ እናት ከከተማው ውስጥ መኖራቸውን ገለጹለት። ሴት ልጁ ከኢያትዋ ጋር እንደሆነች፣ ባለቤቱ ኤሊኖርና ወንዱ ልጁ ራቅ ካለ ቦታ ትልቅ ቪላ ቤት መከራየታቸውንና ሁለቱም ታምመው አልጋ ላይ መሆናቸውን አስረዱት። ስለዚህ 'ወደ ቪላው ቤት በቅድሚያ መሄድ አለብኝ' ሲል ወሰነ። 'የባለቤቴን አባት ግን ቀየት ብሎ ማነጋገሩ ይሻላል፤ ከእርሳቸው ጋር መነጋገሩ ቀላል አይሆንም' ሲል ለሆቴሉ ባለቤት ነገራቸው። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በቆራጥ መንፈስ በቀጥታ ባለቤቱና ልጁ ወደሚገኙበት ቪላ ቤት ሄደ።

ምዕራፍ ስልሳ

«መጣህ፣ ምስጋና ለፈጣሪ»

ሰር ልዮኔል ሚስቱና ልጁ ወደሚገኙበት ቪላ ቤት እያመራ ሳለ ልጁ ሳይሞት በሕይወት ሊያገኘው በመቻሉ ፈጣሪውን ከልብ አመሰገነ። ልጁ እጅግ በጣም ታሞ እንደ ነበርና አሁን ግን ከሞት ማምለጡ ተነገረው። ኤሊኖር ሚስቱን ለማግኘት ካለችበት እንደሚገባ ባለታወሰ ጊዜ ፍርሃት ፍርሃት አለው። እንዴት ብሎ ዓይንዋን እንደሚያይና እርስዋም እንዴት ብላ እንደምትቀበለው ሲያሰላስል እጅግ ጨነቀው። ታክርፈዋለች ወይስ ታናግረዋለች፤ ብታናግረውስ ምን ልትለው ይሆን? እርሱስ ምን ሊላት ነው?

ያቺ ቅጽበት እንዴት ብላ እንደምታልፍ በአሳብ ለማየት ስላልቻለ ሁኔታው እጅግ አበጨነቀው፣ አስፈራው። የፈራው የእርስዋን ግለጼ ወይም ስድብ አልነበረም። የፈራው 'ከቤትዋ ታስወጣኝ ይሆን ወይስ ይቅርታ ታደርግልኛለች' የሚለው አሳብ ነበር። ኤሊኖር ጨዋና ለሌሎች የምታዝን ሩህሩህ ሴት እንደሆነች ያውቃል። ቢሆንም ግን የሠራው

ሥራ ደካኛ የተሞላበት ስለነበር ልቡ ተጨነቀ። ታዲያ ማንኛውም ሰው በሠራው ሥራ ካፈረና ከተጸጸተ መጥፎ ሰው አለመሆንን ስለሚያመላክት ያንን ይህናነት ታይ ይሆን እያለ አሰላሰለ። የዚህን ዓይነት አመለካከት ከያዘች ነገሩ እንደሚቀል ገመተ።

ሰር ልዮኔል ዴፋርና ብርቱ ፍጡር በመሆኑ ቀደም ሲል ፍርሃት የሚሉትን ነገር የማያውቅ ሰው ነበር። የሚሆነው ይሆናል የሚል እምነት ያለው ሰው ስለሆነ ሞት እንኳን ጥርሱን አግጥጦ ቢመጣበትና ምንም ነገር ለማድረግ ቢሳነው ሞትን በፀጋና በጥሞና የሚቀበል ዓይነት ሰው ነው። ሆኖም ያ ሚስቱና ልጁ የነበሩበትን ትልቅ ቪላ ቤት ባየ ጊዜ ከሞት ይበልጥ ፈራው። ወደ ቤቱ የሚያስገባ ደረጃ መውጣት ሲጀምር ግራ ተጋባ፣ ፍርሃት ፍርሃት አለው፣ መላ ሰውነቱ ራደ። እደናቅፎት ሊወድቅ ሲል የደረጃውን ጠርዝ ስለያዘ ከመውደቅ ዳነ። ወደ በሩ ተጠግቶና ደወል ደውሎ ባለቤቱ እንዳለች ጠየቀ። በሩ ቢከፈትለትም በየት በኩል አድርጎ እንደሚሄድ ስሳላወቀ ግር አለው። ከቤቱ በራፍ እንደ ቆመ በዓይኑ ሲያማትር ቅርጹና መልኩ የሚያውቀው የሚመስል ጠና ያለ ሰው እርሱ ወዳ ነበረበት አቅጣጫ ሲመጣ በሩቁ ተመለከተ።

«ሠራተኛዬ ቤኔት ነው» በማለት ሳይታወቀው ጮክ ብሎ ተናገሮ «ተመስገን፣ ስለሁሉም ነገር እርሱ ይትገረኖል» ሲል ራሱን አጽናና። ሰውዬው እየቀረበ ሲመጣ በእጁ ከረጢት መሳይ ነገር መያዙን አስተዋለ። ከረጢቱ ክፍት ስለነበር በውስጡ የተለያዩ የመድኃኒት ብልቃጦች መሆናቸውን ሲመለከት እጅግ አዘነ። ቤኔት በእድሜ የገፋ ሰው ስለነበር ሀጉሩ ሽብድል። ሰር ልዮኔል ከቤቱ ሸፍቶ ሲሄድ የቤኔት ፀጉር እስከዚህም አልሸበተም ነበር። አሁን ግን ጨርሶ ነጭ ሆኖአል። ፊቱ ሳይ የሀዘን ስሜት በጉልህ ይነበባል። ሰር ልዮኔል ወደ ቤት መግባቱን ትቶ ቤኔት ወደ ነበረበት አቅጣጫ ሄደ። ቤኔት አቀርቅሮ ይራመድ ስለነበር የጣንት ጌታውም ፊት በተንዠረገገ ጢም ስለተሸፈነ አልለየውም።

'ደህና አደርክ' ብሎ ሰር ልዮኔል የእግዚአብሔር ሰላምታ ሲያቀርብለት 'ደህና አደሩ ጌታዬ' ብሎ መለሰ እንጂ ቀና ብሎ ስላላየው አሁንም አልለየውም። ሰር ልዮኔል የጥንት አሽከሩ እንዳላወቀው በተገነዘበ ጊዜ ትኩር ብሎ እያየ «ቤኔት» ሲል በስሙ ጠራው። «ረሳኸኝ እንዴ? እስቲ ቀና ብለህ እየኝ። ሰዉን ሁሉ ልትረሳ ትችላለህ፤ እኔን ግን ልትረሳ አትችልም» ሲለው ሽማግሌው ደንግፀ ወደ ኋላ ዝለት አለ።

Scan by Easy Scanner

«የፈጣሪ ያለህ! ሰር ልዮኔል እርስዎ ኖት? በሕይወት ተመልሰው ጸግም የማይዎት አልመሰለኝም ነበር። መጡ፤ የሚገርም ነው። ለአምላክ ምን ይሳነዋል፤ አሁን እንግዲህ ጎርዶንም በቶሉ ይድናል ማለት ኣከ ነው!» ሲል ሳይታወቀው ቤኔት ብዙ ተናገረ።

«በጣም አሞታል እንዴ?» ሲል ሰር ልዮኔል ጠየቀው።

«ጌታዬ እርስዎ አላዩም፣ አልሰሙም እንጂ ልጅዎ እጅግ ናፍቆዎት ስለነበር 'አባቴን አምጡ' እያለ ያሰማው የበረው ጩኸት ከበሽታው ጋር ተጸምሮ እንኳን ሰው ድንጋይን ያስለቅስ ነበር። ያንን ፍላጎቱ ማንም ሊያሟላለትም ሆነ ሊያስጥለው ስላልቻለ ልጁ ብዙ ተሰቃየ። እናቱ እንኳን ብዙ ብትሞክርም ዝም ልታሰኘው ስላልቻለች እርስዎም ብዙ ተሰቃየች።»

«ቤኔት» አለ ሰር ልዮኔል፤ «እስቲ ከዚህ ዞር ብለን ጥቂት እናውጋ። ልጄንና ባለቤቴን እንዴት ብዬ እንደማያቸውና እንደምቀርባቸው መመከከሩ አይከፋም። ያለፈው ስህተቴን መድገም አልፈልግም፣ የቂል ሥራ ነው የሠራሁት» ሲለውና ትልቁ ሰውዬ አሳዳሪ ጌታው እንደዚያ ራሱን ዝቅ አድርጎ ሲናገር የቤኔት ዓይኖች እምባ አቀረሩ።

«ና እንሂድ» አለ ሰር ልዮኔል፤ «ድምፃችን ከማይሰማበት እንሂድና የምታውቀውን ማለቴ የተባለውን ሁሉ ትነግረኛለህ» ብሎት ጌታና አሽከር ተያይዘው ሄዱ።

'በሌላ ጊዜ ሽማግሌው ከተሳከበት በቶሉ ይመለስ ነበር፤ ዛሬ ምን ነካው' ብላ ሲ/ር ማሪ ልታስብ እንደምትችል ቤኔት ጠረጠረ። ቢሆንም ምክንያቱን እርስዋ ራስዋ ትገምት እንጂ እውነታውን ማንም ሊነግራት እንደማይችል ሰራው ነገረ። ቤኔት የሆነውን ለሰር ልዮኔል ለመንገር በዓይነ-ህሊናው ወደ ኋላ ቢመመለስ የሆነውን ለማስታወስ ብዙ ታገለ። የታረከ መነሻ ከአትክልት ሥፍራ ቁጭ እንዳለች ጌታው ለመጨረሻ ጊዜ የጻፈላትን ደብዳቤ አምጥቶ ሲሰጣት እንዴት እንደሆነች አስታወሰ። ኤሊኖር ደብዳቤውን ካነበበች በኋላ እንዴት ብላ እንደ ተለወጠች ትዝ ስላለው ያንን ሁናቴዋ ለሰር ልዮኔል ነገረው። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ያጠፋው ስለሲስተር ማሪ ያየውን ሁሉ በመናገር ነበር። ሆኖም ሰር ልዮኔል ስለሲስተርዋ የሰማው ታሪክ ብዙም አላስደሰተውም። እርሱ ለመስማት የፈለገው ስለሚስቱና ስለልጁ ነበር። ስለዚህ አሁንም፣ አሁንም

መልሶና መላልሶ የጠየቀው ስለሁለቱ ብቻ ነው። በተለይ ስለልጁና ስለሚበቱ ሕመም አጥብቆ ነበር የጠየቀው።

«እንዳያትና እንዳነጋግራት የሚፈቅዱልኝ ይመስልሃል?» ሲል ሰር ልዮኔል በጉጉት ቤኔትን ሲጠይቀው «የሚቻል አይመስለኝም» የሚል ነበር የሰጠው መልስ።

«ኤሊኖር አሁንም ቢሆን በሽታው ጨርሶ አልለቀቃትም፤ በጣም ነው የከሳችውና የተጎዳችው። ሰውነትዋ አልቆ በጣም ገርጥታለች። በድንገት የሚገኝ ደስታ ሰውን ይገድል አይገድል እንደሆነ እኔ ብዙ አላውቅም። ለማንኛውም እርስዎ ትንሽ ቢታገሱ የሚሻል ይመስለኛል። ውሳኔው የእርስዎ ሳይሆን የሐኪሙ ቢሆን ይመረጣል።»

«ሌላው ቢቀር» አለ ሰር ልዮኔል ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ፤ «ሌላው ቢቀር ልጄን በቶሉ ማየት አለብኝ።»

«እርሱን ማየቱ እንኳን የሚቻል ይመስለኛል። ደህና ስለሆነ ሐኪሙም ይፈቅዳል። እንዲያውም ጎርዶን እርሰዎን ሲያይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው ከአልጋው የሚነሳውና በሽታውም በቶሉ የሚለቀው» ብሎ ቤኔት ሲናገር «አሁን ከልጁ ጋር ያለው ማነው?» ሲል ሰር ልዮኔል ጠየቀው።

«ተራ በተራ የሚጠብቁትና የሚያስታምሙት ሴሮች ናቸው። ዛሬ ጠዋት ከከተማ የሚመጣ ነገር እንዳለ ለመጠየቅ ጎርዶን ከተኛበት ክፍል ስገባ 'ቤኔት ስትመለስ አባቴን ይዘህ እንድትመጣ' ብሎ ነበር ያዘዘኝ። አጋጣሚው የሚደንቅ ነው። ይገርሞዎታል፤ ጎርዶን ከተኛበት ክፍል በገባሁ ቁጥር ይህን ጥያቄ ሳይጠይቀኝ ቀርቶ አያውቅም። ታዲያ እኔ እርስዎን ከየት ብዬ ልፈልግዎት? እንዴትስ ብዬ ላግኝዎት? 'ምኑው እኔ በሞትኩና እርሳቸው በተመለሱ ብዬ የተመኘሁበት ጊዜ ብዙ ነው። ሆነም ቀረም ዛሬ ጠዋት ልጁ ከተኛበት ክፍል ስገባ የነበረችው ተረኛ ሴር ሲ/ር ማሪ ነበረች። አሁንም አብረው ሳይሆኑ አይቀርም ብዬ እገምታለሁ።»

«ቤኔት፣ ልጄን ለማየት እርሱ ከተኛበት ክፍል ውስጥ አሁኑኑ ብገባ ሴርዋ ቅር የምትሰኝ ይመስልሃል?» ብሎ ሰር ልዮኔል ሲጠይቀው «ቅር አይላትም፣ እንዲያውም በጣም ነው ደስ የሚላት። እርስዋ የተለየች ሴት ስለሆነች ልጁን ለማዳን ያላደረገችው ጥረት የለም።»

Scan by Easy Scanner

ነገር ግን ሰር ልዮኔል ስለእርስዋ ሳይሆን የተጨነቀው ልጁን በቶሌ ስለሚያይበት መንገድ ነበር። ከጉጉቱና ከሞንቀቱ ብዛት ሳቢያ ልቡ ቶሌ ቶሌ ይመታ ጀመር።

«የሆነው ይሁን፣ አሁኑኑ አብረን እንሂድና ልጄን ልየው» ቢል ሰር ልዮኔል ነገሩን በማከረር ጠየቀው ቤኔትን። አሁን ባጫወትከኝ የእኔ መምጣት ልጄን የሚጎዳው አይመስለኝም። ኤሲኖር ግን እኔን ስታይ ምናልባት ስሜትዋ ታውከ ጉዳት ሊደርስባት ይችላል። ለማንኛውም በል ተነስ አሁኑኑ ልጄ ወዳለበት እንሂድና ልየው። የመሄጃውን አቅጣጫ አንተ ምራኝ።»

ቤኔት የሰር ልዮኔልን የከረረ ጥያቄ ሲገንዘብ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ፤ ጌታውም ያንን በተገነዘበ ጊዜ «ምነው ፈራህ እንዴ? ብሎ ሲጠይቀው «የለም አልፈራሁም፤ ብቻ እኔ እኮ....የእርስው መምጣት የሞተ ሰው እንደ ተነሳ ዓይነት ነው የቆጠርኩት» ብሎ ቤኔት ሲናገር «እኔ እኮ ታዲያ አገሬን ጥዬ ከጠፋሁ ሦስት ዓመት ብቻ ነው» አለው ጣልቃ በመግባት።

«ሦስት ዓመት ብቻ!» አለ ቤኔት የጌታውን ቃል በመድገም። «ለእኛ ግን ሰላሳ ዓመት ነው የመሰለን። ጌታዬ እኛ የጠበቅኖት ለሦስት ሳይሆን ለሰላሳ ዓመት ነው» አለ የመከፋት ስሜት ፊቱ ላይ እየታየ።

«እሲቲ እውነቱን ንገረኝ፣ ሰር ልዮኔል አንድ ቀን ከቤቱ ይመለሳል ብለህ አስበህ ታውቃለህ?» ብሎ ሲጠይቀው «አምንት፣ ስለዚህ ጉዳይ አንድም ቀን ተጠራጥሬ አላውቅም። ፈጣሪ ሲታረቀን 'አንድ ቀን ጌታችን ከቤታቸው ይመለሳሉ' እያልኩ ዘወትር እናገር ነበር» አለው።

«ኤሲ.....ኤሲኖርም ተመልሶ ይመጣል ብላ ታስብና ትናገር ነበር?» ብሎ ሲጠይቀው «እርስዋ እንኳን ይህን አላስችም። እርስው ወደ ቤትዎ የሚመለሱ አይመስላትም ነበር። በዚህ ዓለም ውስጥ ዳግም እንደምትገናኙ እምነትዋ አልነበረም።»

ምዕራፍ ስልሳ አንድ

ዳግም መፋጠጥ

ልጅ እንቅልፍ ወስዶታል። ከታመመ ጀምሮ እንደዚያን እለት የወለደው ዓይነት እንቅልፍ ወስዶት አያውቅም። ተኝቶ በማደሩ ሲ/ር ማሪ በጣም ደስ አላት። ጥሩ እንቅልፍ ስለተኛም የልጁ ፊት ከወትሮው በተለየ መልኩ ፈካ ብሎአል። ዓይኑን ጨፍኖ ነው የተኛው። ሲ/ር ማሪ ከአጠገቡ ቁጭ ብላ ዓይን ዓየኑን ስታይ 'አሁንስ ከመሞት ድኖአል፣ አያሰጋውም' የሚል ስሜት አደረባት። በዚህም የመንፈስ እርካታ አገኘች። ከእንቅልፍፉ ሲነቃ እህል ቢቀምስ ከዚያ ይበልጥ ደህና ሆኖ እንደሚታይና እናቱ ደግሞ ተሸሎት ስታየው ደስታዋ እጥፍ ሊሆን እንደሚችል አሰላሰለች። ለማንኛውም ከእንቅልፉ ቀስቅሶ የሚበላውን ከመስጠት እንቅልፉን ቢጨርስ ይሻላል ብላ ወሰነች። ይህ በዚህ እንዳለ እጅግ በጣም ዝቅ ባለ ድምፅ የሚናገር ሰው በአካባቢው እንዳለ አወቀች። ወደ አርስዋ የሚመጣ የሰው እግር ኩቴም ሰማች። በዚህ ጊዜ ከማንኛውም ጥቃት ልትከላከልለት የምትችል ይመስል ወደ ልጁ ጠጋ ብላ አጎነበሰች። ድምፅ የሚያሰማው ሰው ዝም እንዲል ስለተነገረው ይሰማ የነበረው የእግር ኩቴና ድምፅ ጸጥ አለ። ሆኖም ግን ከበሩ አጠገብ ሰው እንዳለ ሲ/ር ማሪ ጠረጠሩች። ነገር ግን ብዙም ጉዳዩ ስላላስጨነቃት ያለ መርበትበት አሳለፈችው።

የሚሰጅ ድምፅ እንዳገና ተሰማ፤ በሩም ተከፈተ። ምናልባትም ሠራተኛዋ ትሆናለች ብላ ሰላሰበች ሲ/ር ማሪ ቀናም አላለች። የጣባው ሌላ ሰው ቢሆን ያናግረኝ ነበር ስትልም ገመተች። ቢሆንም 'ማነው የገባው?' በሚል ቀና ብላ አየች። የማየው ነገር በሕልም ነው ወይስ በውን ስትል ራስዋን ጠየቀች። እጅግ በጣም ዞረባት። ሰውነትዋ ተንቀጠቀጠ። ልብዋም በኃይል መታ። ፊትዋ በላብ ተጠመቀ። ዓይንዋ ማየቱን አቁሞ ሁሉም ነገር የጨለመ መሰላት። ከጭንቀትዋና ከድንጋጤዋ ብዛት የተነሳ ለመሮህ እንኳን አልቻለችም። መላ ሰውነትዋና ስሜትዋ ሁሉ ሽባ እንደሆነ ነገር ተሰማት። ድምፅ-የለሹ ሰው ወደ እርስዋ ስለተጠጋ ፣ጣው ከበዳት። እጅግ ከመቅረቡ የተነሳ ልብስዋን ነካው። የአንድ የተጨነቀ ወንድ ድምፅ ለመናገር ከራሱ ጋር ሚብንብ እንደ ገጠመ ታወቃት። አሁንም በይበልጥ ተጠጋት።

Scan by Easy Scanner

«እንቅልፍ ከወሰደው አትቀስቅሸው» ካሰ በጓላ «ፊቱን ባየው ግን ደሰ ይለኛል» ሲል ተናገረ።

«የፈጣሪ ያለህ፣ ድምፅም የእርሱ ነው» አለች ለራስዋ። በዚያች በዓት ታስበውና ታስላስለው የነበረው ሰው ድምፅ እንደሆነ አልተጠራጠረችም። ያ ሰው ዳግሞ አሁን በአካል ከአጠገብዋ ቆሞአል። ፈራችው፣ ሆኖም ግን ናፍቃዋለች። የፈራችውና የናፈቀችው ሰው መጥቷል። መምጣት ብቻ አይደለም፣ ከአጠገብዋ ቆሞአል። እርግጥ ነው በጣም ደንግጣለች፣ ፈርታለች፣ የምትይዘውንና የምትጨብጠውን አጥታለች። የምትሞትም መስሳት። ከመጠን ያለፈ ድንጋጤ ሰው ሲገድል ቢችልም እርስዋ ግን አልሞተችም። በዚያች ሰዓት ከፈጣሪ ሌላ የምትቀርበው ሰላልነበራት ፈጣሪዋን ተማጠነች።

«አቤቱ እምላኬ ሆይ፣ ከዚህ ጉድ የምወጣበትን ብርታት ስጠኝ። እስከ ዛሬ ከሆዴ ውስጥ አምቄ ያስቀመጥኩትን ምሥጢር አውጥተህ አታጋልጠኝ። እጅግ ሰለደነገጥኩ ልቤ ቀጥ ብሳ ልሞት ሰሰምችል ከዚህ ሰውረኝ። ብርታቱንና ትእግስቱን አንተ ለግሰኝ። ኃጥያተኛ ሴት ነኝ፣ ቢሆንም አታጋልጠኝ። እምኑቴ በአንተ ሳይ ነው።»

ከልብዋ የጸለየችው ጸሎት ሲሆን ይህም ጸሎት በጣም ነው የረዳት። ፍቅሩ ደም ሥርዋ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ በመፍነክነክ የወደደችውና ነፍስዋ እስኪጠፋ ያፈቀረችው ወንድ በድንገት መጥቶ ከአጠገብዋ ቆሞአል። ገና ስሙ ሲጠራ የተርበተበተችለትና እንደ ጣዖት ያመለከችው ወንድ ነው አሁን ከአጠገብዋ የቆመው። በመጨረሻም ልብዋ የደም እምባ እያዘነበ በጠፍ ጨረቃ የተለየችውና የዚያ ልብ-አትልጥ ወንድ ድምፅ ነው የሰማችው። በሕይወት ዘመንዋ የወደደችው ወንድ ቢኖር እርሱን ብቻ ነው። አብረው እያሉ ሲሰግት ከንፈሮችዋ ደንዝዘዋል፣ ሲያቅፋት ሰውነትዋ ታቅረክርኪል፣ ሲነካካት መላ ሰውነትዋ እሳት ውስጥ እንደ ተጣደ ብረት ግሎአል። ሆኖም ግን ይህ ሰው ከአጠገብዋ ሲቆምም የሰማይ ምጥቀቱንና የምድር ስፋቱን ያህል ተራርቀዋል፣ ሳይገናኙ ተለያይተዋል። ምን ዓይነት አሳዛኝ ታሪክ!

ቀስ ብላ የልጁን እጅ ለቀቀች። ከእንቅልፉ እንዳይነቃ በሚል እንቁላል ከእጅ አምልጦ ቢወድቅ ፍርክስክሱ እንዳይወጣ የሚጠነቀቁለትን ያህል ተጠነቀቀችለት። በትንፋሽዋ እንኳን ልጁ የሚቀሰቀስ ስለመሰሳት ትንፋሽዋን ዋጥ አደረገችው። ነፍስ እንዳይገባው ሲባል የተጋሬይውን ጨርቅ በዝግታና በጥበብ አነሳችው። የራስዋንም ፊት ከልሱ የነበረውን ጥቁር ጨርቅ ገልጣ ከዚያ ከነበረችበት ሥፍራ ዞር አለች። ከክፍሉ ውስጥ አንድ ዓይነት ድምፅ ተሰማ።

ሰውዬውን ቀና ብሳ አየችው። አዎን አልተሳሳተችም፣ እርሱ ራሱ ነው። እርሱም በበኩሉ አተኩሮ አሳያትም። የሚገርም ነው፣ አሁንም ተስፋ ያልቆረጠውና ያልተገራው ልብዋ ከልቡ፣ ፊትዋ ከፊቱ፣ ጡትዋ ከደረቱ፣ ከዳሬርዋ ከከንፈሩ ቢሳተም ደስታውን አትችለውም። ሴሳው ቢቀር ብድግ ብሳ ሄዳና እጁን ሞምቅ አድርጋ ብትይዘው ምንኛ ደስ ባሳትና ስውነትዋ በተፍነከነከ። ያ ስሜት፣ ያ ምኞትና ፍሳሳት የእውነተኛ ፍቅር ምልክቶች ሲሆኑ በድርጊት እንጂ በቃሳት ኃይል ለመግለጽ ስለማይቻል እንዲያው ዝም ብሎ ማለፉ ይሻላል። ዘወትር የምታጠልቀውና ፊትዋን የምትሸፍንበት ስስ ጨርቅ ተመልሶ ወርዶ ፊትዋን እንደገና በመጠኑም ቢሆን ሸፈነው። እርሰዋም ከነበረችበት ወደ ጓላ አፈገፈገች። አሁንም ቢሆን እርሱ በቅጡ አሳያትም። ዓይኑን ከልጁ ሳይ ስለተከለ እርስዋን ከልብ አላጤናትም።

ወደ መሬት እንዳቀረቀረ «እግዜር ይስጥልኝ» ሲል ሲ/ር ማሪን አመሰገናት አሽከሩ ቤኔት የነገረው ልፋትዋን በማስታወስ። እርስዋ ቦታዋን ለቅቃ ዞር በማለትዋ እርስዋ የለቀቀችውን ቦታ ልርሱ ወሰደ። ልጁ ከተኛበት አልጋ አጠገብ ሄዶ ተንበረከከ። የአልጋውን ጠርዝ ስለነካው አልጋው ተንቃነቀ። ከአልጋው ንቅናቄ ሌላ ስሜቱን ለመቆጣጠር የሚታገል ሰው ሲያቃስት ሰማች። ሰር ልዮኔል ማልቀሱ እንደሆነ ገባት። ልታጽናናው ብትፈልግም አልሆነላትም። ብታደርገው ግን እጅግ በጣም ደስ ይሳት ነበር።

ከሰውዬው አጠገብ ቆማ ያሳለፈችው ጊዜ ቅጽበታዊ ይሁን፣ ብዙ በኮንዶች ወይም ደቂቃዎች ይሰፉ ጨርሶ አልታወቃትም። ሰውነትዋ ግን ይንቀጠጣል። ፊትዋ እንደ ተሸፈነ ነው። ሰር ልዮኔል ተንበርክከ ሲንፈቀፈቅ እጅትዋ እጨበጨቡ። በዚህ ጊዜ ሰር ልዮኔል ከተንበረከከበት ተነሳ። ያጋጣሚ ነገር ሆኖ ልክ በዚያች ቅጽበት ጎርዶን ዓይኑን ገለጠ።

ሲ/ር ማሪ ያቺን ሰዓት እስከ እስቱ-ሞትዋ አልረሳቸውም። የልጅነት ዓይን በኃይል ተከፍቶ ሳለ የሚያየውን ነገር ምንነት ለማወቅ ሰለሚጓጓ አመለካከቱ የተለየ ይሆናል። ጎርዶን አባቱን ዝም ብሎ አየው፣ ማየት ብቻ ሳይሆን አፈጠጠበት። በመጀመሪያ ከእንቅልፉ በሚገባ ሰላልነቃ

ወይም የሚያየው ነገር እውን ስላልመሰለው ሊሆን ይችላል፣ ግራ ተጋባ። ከአጠገቡ የቆመው ሰው ማን እንደሆነ ባወቀ ጊዜ ግን በደስታ ፈነደቀ። የደስታው ብዛት ስላስለቀሰው እምባውን እያዘራ ከተኛበት ብድግ ብሎ «ይህ አባቴ ነው፣» ሲል በመጮህ ጠየቀ። ቀጥሎም «የእኔው አባት ነው የመጣው» አለ። ከዚያም ብድግ ብሎ ተነስቶ ከአባቱ አንገት ላይ ተጠመጠመ። ቀጥሎም አንገቱን ከአባቱ ደረት ላይ አሳረፈ።

«አባዬ፣ አባዬ፣ ሳመኝ አባዬ። ስለመጣህ በጣም ነው ደስ ያለኝ። እንቶ ከመጣህ እማዬም ደህና ትሆናለች። እና ሁላችንም እንደገና ደስ ብሎን እንኖራለን። የመጣኸው አባዬ አብረኸኝ ለመኖር ነው፣ አይደል? ሁለተኛ ደግሞ አትሄድም?» ብሎ ሲጠይቀው «የለም ጎርዶን፣ ሁለተኛስ ትቼህ አልሄድም» ሲል መለሰለት። አባትዮው ሙስጥ ሙሰጣ ጎን ምን ያህል ይሰቃይ እንደ ነበር ከድምፁ ቢታወቅም ልጁ ግን ሰይቶ አልደረሰበትም።

በዚያች ሰዓት ከልጆቹ፣ ከሚሰሙና ከሞቀ ቤቱ የነጠለችውን ሴት እየረገመ ይሆን ወይስ ምን ነበር የሚያስበው? ብሎ ለመጠየቅ ይቻላል። ከአጠገቡ መቆምዋን ቢያውቅስ በጥሞና ያናግራታል? ወይስ 'ይህ ሁሉ የደረሰው በአንቺ ምክንያት ነው፤ አንቺ ከተመቻቸ ሕይወቴ ውስጥ ጣልቃ ባትገቢ ኖሮ ደስታ በገፍ ከሚታፈስበት ቤቴ ውስጥ ህዘን አይተካም ነበር። አንቺ ነሽ ለዚህ ሁሉ ጥፋት ገዳፋ የሆንሽው» እያለ ይገስጻታል?» ብሎ መጠየቅም ይቻላል። ነገር ግን በእርግጥ እንነጋገር ከተባለ ለጥያቄዎቹ መልስ ሊሰጥ የሚችለው ሰር ልዮኔል ራሱ ብቻ ነው?

ሰር ልዮኔል ልጁን እቅፍ አድርጎ ይዞ እምርሮ ሲያለቅስ ሲ/ር ማሪ ነቅነቅ እንኪን አሳለችም። አባትዮ ያስደስተዋል ያለውን ሁሉ ለልጁ በመንገር አባበለው። በአንድ እጁ ቀስ እያለ እጅጉና ፊቱን አሻሸለት። በዚህ መሃል ልጁ ቀና ብሎ ሲያይ ሲ/ር ማሪን በተመለከተ ጊዜ «ሲስተር፣ ሲስተር፣ ሲ/ር ማሪ አባቴ እኮ መጣ። ይህ እኮ አባቴ ነው» ሲል በመጮህ ተናገረ። እርስዋ ግን እንደ ሐውልት ድምፅ ሳታሰማ ከነበረችበት ደርቃ ቀረች እንጂ መልስ አልሰጠችውም።

ሰር ልዮኔል በስሱ ፊቱን አዙሮ በታላቅ አክብሮት አንገቱን ወደ መሬት በማሳንበስ እጅ ነሳት። ሆኖም ግን አሁንም ቢሆን ዓይኑ ያረፈው ከልጁ ላይ ነበር። ሲ/ር ማሪ ፊትዋን በስስ ጥቁር ጨርቅ

ስለሸፈነችው በጉልህ ሊያያት አልቻለም። ሴርዋ ለእርሱ ሚስቱንና ልጁን በመንከባከብ የረዳቻቸው የእግዜር ሰው እንጂ ከዚህ የተለየ ግንኙነት ያላት ሴት አይደለችም። ያቺ ከአጠገቡ የቆመችውና ፊትዋን በጥቁር ጨርቅ የሸፈነችው ሴር የተለየ ቁላጎትና የተለየ ስሜት ልትሰጠው የምትችል ሴት ለመሆን እንደምትችል ጨርሶ አልጠረጠረም።

«ሲ/ር ማሪ ለምን ብለሽ ነው ራቅ ያልሽው፣ ጠጋ በዪ እንጂ» ሲል ልጁ ድምፁን በማጉላት ጠራት። «ከአሁን በኋላ መድኃኒት የሚባል ነገር አልፈልግም። አሁን አባቴ ስለተመለሰልኝ ቶሎ እድናለሁ። አባቴ ስለመጣልኝ ድሮ አደርገው እንደ ነበረው ከወዲያ ወዲህ እያልኩ ለለምፂወት ደህና እሆናለሁ» ብሎ ቢናገርም የልጁ ፊት በመጠኑም ቢሆን ተለወጠ። አባትዮ ሰውነቱን ሲነካው ትንሽ ያተኩሰው መሰለው። አባቱን ያቀፈበት እጁም እንደ መንቀጥቀጥ አለ። ሰር ልዮኔል ደነገጠ።

«ጎርዶንዬ» አለ አባቱ፣ «ዝም ብትል ይሻላል፣ ብዙ ከተናገርክ ይደክምሃል። ዝም ካላልክና ካላረፍክ የእኔ መምጣት ይጎዳሃል እንጂ አይጠቅምህም» ሲል አባበለው። ከዚያም ወደ ሴርዋ ዞር ብሎ «ሲስተር» በማለት ተጣርቶ «ልጄን ሳላስጨንቅው አልቀረሁም መሰለኝ። ስለዚህ ትንሽ ለቀቅ ባደርገው ነው የሚሻለው?» ብሎ ሲጠይቃት ሲ/ር ማሪ ወደፊት ተራምዳ ተጠጋችው። አሁንም ፊቱን ወደ እርስዋ ስላዞረና ሕሊናው ሁሉ በልጁ ሕመም ላይ በለተኩሪ እርስዋን ያረሳት መሰሳት። እርሱ ግን ፊቱን ወደ እርስዋ ባያዞርም እርስዋን ማናገሩን ቀጠለ።

«ከልጄ ጋር ከተለያየን ትንሽ ሰንበት ብሎአል» አላት ከማን ጋር እንደሚነጋገር ባለማጤን። «ከደስታ ብዛት ከክቱ ነገር ላይ እንዳይወድቅብኝ አሰጋለሁ» ሲሳት በአጠገቡ አልፋ ወደ ልጁ ጠጋ አለች። ሆኖም ግን በአጠገቡ ስታልፍ ባጠለቀችው ካባ ሰውነቱን ነካችው። በተከላተፈና ለመስማት በሚያስቸገር ዝቅተኛ ድምፅ ይቅርታ ጠየቀችው። ድምፅዋን አጉልታ ለመናገር አልደፈረችም። ይህን ብታደርግ የገዛ ድምፅዋ ጉድዋን እንደሚያወጣ ታውቃለች። ልጁን ከአባቱ እጅ አላቅቃ ጋደም እንዲል ትራሱን እመቻችታ አስተኛችው።

«እርጋታና ጥንቃቄ የተሞላበት አያያዝ» ብሎ ሰር ልዮኔል ሲናገር እጅዋን ከልጁ ግንባር ላይ አሳረፈች። ዳግም እንዳይናገር «እሽሽ፣ ዝም በል» በትል ገስጸችው አሁንም በዝቅተኛ ድምፅ።

Scan by Easy Scanner

«ሲ/ር ማሪ» ሲል ልጹ እንደገና ጠራት። «በመጪረሻ አባቴ አከ መጣ፣ ይኼ እኮ አባቴ ነው። ደግሞም ሁለተኛ ጥሎኝ አይሄድም። በመምጣቱ ደስ እንዳለሽ ንገሪው።»

ሰር ልዮኔል እንደ ማፈር አለ። የልጹን እጅ እንደገና ይዞ «ግድ የለም፣ አሁን አረፍ በል እንጂ ከሲስተር ጋር አሁን ባይሆን ወደፊት በቅሙ ስንተዋወቅ አሁን ያልከውን ትነግረኛለች» አለው። ሰር ልዮኔል አሁንም ቢሆን የሴርዋን ፊት ቀና ብሎ አላየም።

«ሲ/ር ማሪ እኮ የምትመጣ አልመሰላትም ነበር» አለ ልጹ የመጓጓት ስሜት እየታየበት። «አየሽ ሲስተር አሁን ግን አባቴ መጣ፣ አባባ ትልቁና ሚ/ር ቤኔት ወደ ሩቅ አገር ሄደህ እንደ ነበር ነግረውኛል። 'አገሩ እጅግ በጣም ሩቅ በስሆነ ምናልባት አይመለስ ይሆናል' አያሉም አስፈራርተውኝ ነበር» ሲለው «ግብፅ ወደሚባል አገር ሄጂ ነበር» በማለት መለሰለት። ልጹ ከአግር ጥፍር እስከ ራስ ፀጉር ተመለከተው።

«ግብፅ ማለት ሙሴ ከውሃ ውስጥ ሊስጥምበት የነበረው አገር ነው፣ አይደል?» ሲል ልጹ ይህን ታሪክ በማወቁ በመኩራራት ተናገረ። «ስለሙሴ ታሪክ አማዬ ነግራናለች። ቅርጫት ውስጥ አስቀምጠው ወንዝ ውስጥ ነው የጣሉት። ከዚያም አንዲት ጎበዝ ልዕልት አገኘችው። ፎቶአቸውን አይቻለሁ።» ልጹ ይህን ሲናገር ሰር ልዮኔል እጁን እንደ ያዘው ነበር።

«አሁን ዝም በልና ትኛ፣ ታሪኩን በኋላ ትነግረናለህ» ካለ በኋላ አሁንም ልጹን እያየ «ሲስተር ልጹ አርፎ እንዲተኛ ምን ብናደርግ ይሻላል?» ብሎ ሲጠይቃት መልስ ስላልሰጠችው 'ለምን? ደግሞስ ለምንድነው ለዚህን ያህል ጊዜ ፊትዋን አዙራ የምትቆመው? ፊትዋንስ ለምን ሸፈነችው? ሰው ይህን ያህል አፋራም ይሆናል እንዴ?'» ሲል ራሱን ጠየቀ። ነገር ግን ሴሮች ጠንቃቃ፣ አፋራምና ሰው አክባሪ እንደሆኑ ጠንቅቆ ያውቃል። ቢሆንም የቪችኛዋ ሴር ትንሽ የበዛ ቢመስለውም ልጹን ስላጸነችለት እርስዋን ከአባሀርይዋ ተቀብሎ ማክበር እንደሚገባው አመነ። ስለዚህ ልታናግረውና ዓይኑን ለማየት ካልፈለገች 'ዝም ከማለት ሌላ እርስዋን መወትወት አያስፈልግም' ሲል ራሱን መከረ። ይህን እያሰላሰለ አሁንም አሳቡ ወደ ልጹ ለለተመለሰ የሴርዋ ከዚያ መኖር ረሳ። በመካከሉ ጥቂት ጊዜ አለፈ።

«ሲስተር» ሲል ልጹ እንደገና ተጣርቶ «እየመሸ እኮ ነው፣ የት ነው ያለሽው?» ብሎ ሲጠይቃት ብድግ አድርጋ አቀፈችው። በዚህም

የደስታው ብዛት ትኩሳቱን ከፍ እንዳደረገው ተገነዘበች። ራቅ ብሎ የተቀመጠውን ጠርሙስ በሌባ ጣትዋ ስታመላክተው ሰር ልዮኔል ፍላጎትዋ ምን እንደሆነ ገባው።

«ውሃ ነው የፈለግሽው፣ አይደል?» ብሎ ጠየቃትና ቢብርሙቁ ቀድቶ ሰጣት። ልጹ ውሃውን ሲጠጣ ትንሽ ተንፈስ ያለ መሰለ። ትንሽ ነቃ ስላለም የሴርዋን ፊት ሸፍኖ የነበረውን ሻሽ ገለጠው። በዚህ ጊዜ የሃፍረት ድምፅ ባታሰማ ኖሮ አሁንም ቢሆን ሰር ልዮኔል ባላወቃት። ድምጽዋን ሲሰማ ከመቅጽበት ፊቱን ወደ እርስዋ አዞረ። አተኩሮ ተመለከታት። ፊትዋ ነፍስዋ ከሥጋዋ የተለየች ሴት እንጂ በሕይወት ያለች ሴት ፊት አልመሰል አለው። ፊትዋ ነጥቷል፣ ገርጥቷል።

ያ የፈራችው ቀን፣ ያ የፈራችው ስዓት ደረሰ። ደመና ቅርጽ እያወጣና እየሰላ ሲሄድ ዓይኖችን እርሱን አልፎ ለማየት እንደሚችል ሁሉ ከጊዜ ብዛት የተረሳ ፊት መልሰው ሲያዩት ያለፈን ትዝታ እንደሚቀሰቅስ ሁሉ፣ በሕይወት የኖረ ወዳጅ ሞት እውን በሆነ ጊዜ እንደ ሾህ እንደሚወጋ ሁሉ ለእርስዋ የነበረው ጥልቅ ትዝታና በእርስዋ የቀነሳ የደረሰበት የሕይወት ፈተና እንዳለ ከፊቱ ላይ ድቅን ብሎ እንደ ጦር ወጋው። አሁን በድንገት የዚያኙ የቆንጆዋን ቪቫን ፊት ነው የሚያየው። ለጥቂት ለከንድ ይሁን ወይም ለጥቂት ደቂቃዎች እንደሆን ላይታወቀው ሰውነቱ በድንጋጤ ደንዝዞ ስለፈዘዘ አፍ አውጥቶ ቃላት ለመሰንዘር አልተቻለውም።

ሁለቱም ተፋጠጡ እንጂ አልተናገሩም፣ ሰላምታ አልተለዋወጡም። ነገሩ ሁሉ ዝምፕ ዝም ብቻ ስለሆነ የሚናገር ጠፋ። መናገር ቁርጥ ከቆሙበት ለዓመል ያህል እንኳን አልተንቃነቁም። ሁለቱም ከመቃብር የተነሱ ነው የመሰላቸው። ሁለቱም በየፈፈናቸው በእሳብ ሰመጡ። ሁለቱም መጨረሻው ያላማረውንና አሳዛኝ ታሪካቸውን ስላስላለሱ የት እንዳሉ እንኳን አልታወቃቸውም። ለምን ያህል ጊዜ እንደተፋጠጡ ላይታወቃቸው በመጨረሻ ሰር ልዮኔል ከንፈሮቹ እየተንቀጠቀጡ ተናገረ።

«ቪቫን በሕይወት አለሽ? ያንቲ አለህ! በእውነት አንቺ ቪቫን ነሽ?» ብሎ ሲጠይቃት ለመናገር ብትችል በመለሰችለት ነበር። የመናገር አቅም ስላልነበራት ድምፅዋ እንደ ተዘጋ ቀረ። ነገር ግን በሌባ ጣትዋ አቅም ስላልነበራት ድምፅዋ እንደ ተዘጋ ቀረ። ነገር ግን በሌባ ጣትዋ ጎርዶንን አሳይታው ከክፍሉ ወጥታ ሄደች። ሰር ልዮኔል ከነበረበት

Scan by Easy Scanner

ደርቆ ቀረ። ለድንጋጤው ወሰን አልነበረውም። የሆነው ሁሉ እጅግ በጣም አስገረመው። ገጽታው ላይ የመከፋት እንጂ የመደሰትም ሆነ የእርካታ ስሜት ጨርሶ አልታየም።

ምዕራፍ ስልሳ ሁለት

«ከፈተና ውስጥ በጨመርኩሽ ጊዜ አብጂ ነበር»

ልክ በዚያቹ ሰዓት ሲ/ር ማሪን የምትተካዋ ሌላዋ ሴር ሁለቱ ከነበሩበት ክፍል ገባች። እድሜው በስሱ ጠና ያለ የሚመስልና ቁመናው እጅግ ያማረ፤ ግን ፊቱ የጠቆረ ወንድ ከሲ/ር ማሪ ጋር ቆሞ ስታይ ደነገጠች።

«አባቴ፣ አባቴ ነው» ሲል ጎርዶን እንደ ቀድሞው ጮክ ብሎ ሲናገር አባቱ ፈገግ ማለት ነበረበት። ነገር ግን በድንጋጤ የገረጣው ፊቱና የተጣበቁ የመሰሉ ከንፈሮቹ ነቅነቅ እንኳን አላሉም። ስለዚህ ብዙ ቆይቶ ነው የተናገረው። መናገር ሲጀምርም የራሱን ድምፅ በለማ ጊዜ ሌራሱም ቢሆን አስፈራው። እንደ ምንም ብሎ ወደ አዲሰዋ ሴር እየተመለከተ «ሰር ልዮኔል ራይዳል እባላለሁ» አላት።

«አባቴ ነው» ሲል ልጁ በድጋሚ ተናገረ። «የእኔ ማለቴ የእኔ የብቻዬ አባት እኮ ነው» በማለት ትንሹ ጎርዶን ለማስረዳት ሞከረ።

«ከሲስተሮቹ አንደኛው አንቺ ነሽ?» ብሎ ሰር ልዮኔል ሲጠይቃት «አዎን ልክ ኖት፣ ሁለተኛዋ ሴር ማለት እኔ ነኝ» ስትል ችህትና በተሞላበት እንደበት መለለችለት።

«አንቺ ከመምጣትሽ በፊት ልጄን ትጠብቅ የነበረችው ሌላዋ ሴር ስም ማነው?» ብሎ ሲጠይቃት «ስምዋማ ሲ/ር ማሪ ይባላል» ስትል መለሰችለት። በዚህም የራስዋን ስም ይዛ ለመቆየት እንዳልፈለገች አወቀ።

«ብድንገት በመምጣቴ ልጄን በደስታ ብዛት ሳላስጨንቀው አልቀረሁም። ለተወለነ ጊዜ እኔ ብለየውና እርሱ ቢያርፍ ይሻላል። አንቺ ግን ከአጠገቡ ቁጭ ብለሽ አጫውቺው። እኔ ደግሞ ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ከዚህ ልውጣና እርሱ ይተኛ። 'ጎርዶንዬ' አለ ወደ ልጁ ዞሮ፣ 'ድምፅ ሳታሰማ ብታርፍ ይሻላል። አሁን ተኛና ከእንቅልፍህ ስትነቃ ተመልሼ አብሬን እንሆናለን። ያኔ በይበልጥ እንጫወታለን» አለው።

«እንግዲያውስ አባዬ ሳመኝና ሂድ። ከዚያ በኋላ እኔ ምንም አልናገርም። ጸጥ ብዬ ነው የምተኛው» አለ ልጁ ለአባቱ ቃሉን ሲሰጥ። ከዚያም በደከመ እጁ አጥብቆ ሲጨብጠውና ምጥጥ አድርጎ ሲስመው የአባቱ እምባ ከልጁ ከርን ላይ እርግፍ እርግፍ አለ።

«ቶሎ እመለሳለሁ፣ ከእንቅልፍህ ስትነቃ ከአጠገብህ ቁጭ ብዬ ታገኘኛለህ» ሲለው 'ቶሎ የተኛሁ እንደሆነ በቶሎ ነቅቼ አባቴን አየዋለሁ' በሚል እምነት ይመስላል፤ ልጁ ለመተኛት ዓይኑን ጨፈነ። ከመተኛቱ በፊት ግን 'አባቴ እኮ መጣ' በማለት ሰነርሰዋ ለመንገር ፈልጎ 'አልናገርም' ብሎ ለአባቱ የገባውን ቃል ስላስታወሰ ከመናገር ተቆጠበ። ሰር ልዮኔል ወደ ሴርዋና ልጁ እያተመለከተ ከክፍሉ ወጥቶ ሄደ።

ቪቫንን አግኝቶ የልቡን መግለጽ እንዳለበት ሰር ልዮኔል ቢወስንም የሆነው ነገር ሁሉ እርሱ ሞቶ ሌላ ዓለም ውስጥ ይሁን ወይም እንቅልፍ ወስዶት ቢሕልሙ ያየው ነገር ይሁን ለመለየት ቸገረው። ነገር ስለሆረበት የት እንዳለ እንኳን በትክክል ለማወቅ ተሳነው። ጨርሶ ያልጠበቅነው ነገር ሲደርስ ግራ እንደሚገባን ሁሉ እርሱም ግራ ተጋባ። አሁን ያለበት ቤትና የቆመበት ሥፍራ ለእርሱ እንግዳ ስለነበሩ ከቤት ውስጥ ሆኖ ከቤት ውስጥ አልነበረም። ከነበረበት ክፍል ለጥቂት ደቂቃዎች በመግረም ግድግዳ ተደግፎ ቆመ።

ባለቤቱ በጠና ስለታመመች ከቤቱ መመለሱን በድንገት ብትሰማ ለሕይወትዋ ጥሩ አንደማይሆን ያውቃል። የት ልሂድ? ምን ልሥራ? ቪቫንን የት ላግኘት? እያለ ራሱን ቢጠይቅም መልስ ግን ሊያገኝላቸው አልቻለም። በመስኩት አሻግሮ ሲያይ በሩቁ የሚታይ ጋራ ተመለከተ። የተለያዩ የአበባ ዘሮችም ከሚዳው ላይ በስፈው መታቀፊያቸውን ተገነዘበ። ቪቫንን ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ሁና ነው ያገኛት። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ማነው ይህን ያጠናቀረው? ፈጣሪ ወይስ ሰው? ወይስ ያጋጣሚ ነገር ነው? ወይስ ያያት ሴር መስሉት ነው እንጂ ቪቫን አይደለችም? ቪቫን ከሆነች አሁን የት ነው ያለችው? ከዚህ ጭንቀት፣ ከዚህ መውናበድ ማነው የሚገላግለው? ቪቫን ወዴት እንደ ሄደች ሠራተኞችን ጠርቶ ሊመጠየቅ ይችላል፤ ግን አልደፈረም። የቪቫን ምኞት ምን እንደሆነ ዳግሞ አያውቅም። ከዚያ ቤት ውስጥ የቪቫንን ማንነት የሚያውቅ ሰው እንደሌለ አልተጠራጠረም። ለማንኛውም የእርስዋን አሳብ ማግኘት

Scan by Easy Scanner

ጠቃሚ እንደሆነ ስለተገነዘበ ምንም ነገር ከመወለኑ በፊት ቪቫን የምትለውን መስማት እንደሚያስፈልግ አመነበት።

«ቪቫን ከእዚህ አካባቢ አለሽ?» ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተጣራ። ድምፁን ከፍ አድርጎ የተጣራው መልሰ አገኛለሁ በሚል ግምት ነበር። በዚያች ቅጽበት ስለእርስዋ ብቻ ነበር የሚያስበው፣ የእርስዋ አሳብ ብቻ ነው መላ ጭንቅላቱን የያዘው። ከሚሰቱ ጋር ናት ወይስ ከልጇ? ብቻዋን ናት? ግን የት? የትም ትሁን የት በቾሉ እንዲያገኟት ፈለገ። ወደ ሚሰቱ የተመለሰው ህዘኑን ሊገልጽላትና ስለፈጣሪ ብላ ምህረትዋን እንድታወርድለት ለመለመን፣ ለመማጠን ነበር። ነገር ግን ከቢቱ ሲመጣ ጨርሶ ያለጠበቀው ነገር ሆነ። ማንን አገኘ? አብዳ ያሳበደችው ሴት—ቪቫን። ይህም በአጋጣሚ የፈጸመው ስህተትና ታጥያት እጅግ ብርቱ እንደሆነ በይበልጥ አጉልቶ አሳየው። የሠራው ሥራ ህሊና ሲታወር የተፈጸመ ድርጊት እንደሆነ ቆልሞ ብሎ ታየው።

በዓይኑ ሊያማትር ገረበብ ያለ በር በፍቁ ተመለከተ። ወደዚያ ሄዶ ቀስ ብሎ አንኳኩቶ በፍን በቀስታ ከፈተው። ለካስ ወደ ውጭ የሚያስወጣ በር እንጂ ከፍል አይደለም። በበሩ በኩል ወደ ውጭ ወጣ። የሚያማምሩ አበቦችንና የዛፍ ተክሎችን በአካባቢው በብዛት አንዳሉ አጤነ። ከአበቦቹና ከዛፎቹ መካከል ጥቁር ልብስ የለበሰች ሴት በሩቁ ስላየ ቪቫን ሊመሆንዋ አልተጠራጠረም። ሮጠ ሄዶ ከሴትዮዋ አጠገብ ቆመ። ሴትዮዋ ከአንድ ትልቅ ዛፍ ስር ተንበርክካ ታለቅሳለች። አምርራ ለማልቀስዋ ከፊትዋ ላይ የሚታየው አምባ ይመስክራል። ስትንሰቀሰቅ በመስማቱ የሚያደርገውን አጥቶ ለጥቂት ለከንዶች ዝም ብሎ ከአጠገብዋ እንደ ቆመ ቀረ። ራሱን ጥቂች ካበረታታ በኋላ ግን ወደ እርስዋ ጠጋ አለ፣ ሰውነትዋን ግን አልነካም። ለማናገርም አልደፈረም።

ቪቫን የለው ኩቴና ድምፅ በሰማች ጊዜ ቀና አለች። ይኼኔ ነበር አምርራ ማልቀስዋን ያረጋገጠው። እምባዋ በጉንጮችዋ አጀርጦ ወርዶ እንገትዋ አካባቢ ያለው ልብስዋን አርሶታል። የፊትዋማ ነገር አይወራ፣ በእምባ ብዛት ተጨማልቆአል።

«ቪቫን» ሲል በደከመ ድምፅ ጠራት። ከአጭር ጊዜ ዝምታ በኋላ ቀና ብላ ሳታየው እንዲጨብጣት እንድ እጅዋን ዘርግታ «ተወኝ እባክህ» አለችው እንዳቀረቀረች። «ባታናግረኝ ይሻላል። እንበል አታውቀኝም አሉ። ከዚህ እንገናኛለን ብዬ ያላሰብኩትና ያለሰምኩት ነው። እኔ ግን

ከዚህ ሥፍራ በቶሎ እጠፋለሁ» ካለች በኋላ በሚንከራተት ዓይን ቀና ብላ በማተኮር አየችው። ያ ግርማ ሞገስዋ፣ የሚያስፈራ ሆኖም የሚማርክ አይታዋ፣ እነዚያ የሚያባብሉ ትላልቅ ዓይኖችዋ ብዙ ነገር አስታወሱት።

«ቪቫን» አለ ስምዋን በድጋሚ በመጥራት። «ላንነጋገር ባትሄጂ ይሻላል። ይህቺን የመጨረሻ እድል አትንፈጊኝ። የልቤን ሳልገልጽልሽና የሆዴን ሳልተነፍስ ከሄድሽ የልቤ ቁስል ለረጅም ጊዜ አይሽርም። ለአጭር ጊዜ ቢሆን እንኳን እንነጋገር። ጨርቄን ጥዬ ላብድ ብዙም የቀረኝ አይመስለኝም። በዓይኔ አያየሁሽ አንቺ በእርግጥ ቪቫን መሆንሽን እንኳን መለየት እያቃተኝ ነው። ድንገት ከዓይኔ የምትሰወሪም ይመስለኛል። ርኩስ መንፈስ የተጠናወተኝም ይመስለኛልና እስቲ ዝግ ብለሽ አናግሪኝ።»

«ምን ብዬ ላነግርህ? እስቲ አሁን ምን ለማለት እችላለሁ?» ስትል ለመስማት በሚያስቸግር ዝቅተኛ ድምፅ ጠየቀቸው። «ምን ዓይነት ቃላት ናቸው በእኔና በአንተ መካከል መነገር ያለባቸው—የፍቅር ወይስ የጥላቻ? ዳግም መገናኘታችን እጅግ በጣም አሳዛኝ ነው። አሁንም ቢሆን አልተገናኘንም፣ አልተያየንም አሉ። ርሳኝ፣ እረሳሃለሁ። ሌላም ምርጫ የለንም። የእኔና የአንተ ግኙኝነት ሀሊና ሲታወር እንደ ተፈጸመ ድርጊት ቆጥረነው የሆነው ሁሉ አንዱንም ሳናስቀር እንርሳው።»

ሰር ልዮኔል ለቪቫን የነበረው ፍቅር ብዙም አላገረሸበትም። ነገር ግን በእርስዋ በኩል አሁንም ቢሆን ምን ያህል እንደምትወድደው አልተጠራጠረም። አመለካከትዋና የዓይንዋ መንከራተት የፍቅርዋን ጥናት በግልጽ አሳየው። እንዲያውም ከነአካቴው ከድሮው ይበልጥ አሁን ነበር የፍቅርዋን ብርቱነትና ጽናት በጉልህ ለማየት የቻለው። ታዲያ ከመቆዘምና ዓይን ዓይንዋን ከማየት በስተቀር ሌላ ምንም ሊያደርግለት አለመቻሉን ተገነዘበ። ስለዚህ «ምን ዓይነት ፍቅር ነው» ሲል ራሱን ጠይቆ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ሰላለገኘ በይበልጥ ግራ ተጋባ።

ይህቺ ቆንጆ ሴት ለእርሱ ስትል ምን ያላደረገችው ነገር አለ እርሱን ለማግኘት ብላ ባልዋን ጥላ ከቤትዋ ወጣች። እርሱን አገኛለሁ በሚል ሀብትዋን፣ ክብርዋንና ሰምዋን ሸጠች። ከሁሉም ይበልጥ ያ ምቹ ኑሮዋን ትታ ተከተለችው፣ ፍቅርዋንም ሰገፍ አስታቀፈችው። አሁን ግን ያ ቆንጆ ፊትዋ የሀፍረት ማቅ ተከናንቦ ወደ መሬት አቀረቀረ። ልብዋ ቆሰለ፣ አንጀትዋ ተከማትሮ አረረ። ውስጣዊ ስሜትዋ ይኸ ሆኖ ሳለ

'ርሳኝ፤ ልርሳህ' ነው ያለችው። በዚህ ጊዜ ነበር ሰር ልዮኤል 'ወዳፊት እንገናኛለን ወይስ አሁን ከሄደች ዳግም አንተያይም' ሲል ያሰበው።

ሰውዬው ባለቤቱ ኤሊኖር ወደምትባችበት አገር እርስዋን ፍለጋ መጣ። ታዲያ ከዚያ ማንን ቀድሞ አገኘ—ነፍሰዋ እስኪጠፋ የወደዳችው ሴት፣ ቪቫን። እንዴት ሆኖ—መንኩሳ። ምን ዓይነት አጋጣሚ— እስካሮኛና ቅጥ ያጣ መጥፎ አጋጣሚ ይሉሃል ይኼ ነው። ከዚህ ይበልጥም አቅደቢስ የሆነ አጋጣሚ ሊኖር አይችልም። ምን ዓይነትዋስ እድለቢስ ሴት ናት!

«የልም ግድየለሽም፣ ጥቂት አጫውቺኝ። ለመሆኑ ምን ዓይነት ታይል ነው ከዚህ ያመጣሽ? የልጆቼንና የባለቤቴን ሕይወት ለማዳን እኩ ነው የመጣሽው፣ ለማመን የሚቸግር ምን ዓይነት ተአምር ነው? እንደ ገበያ ድንጋይ ጥላኝ የሄደች ሴት መልአክ ሁና ካለሁበት የመጣች ነው የመሰለኝ። ለመሆኑ እንዴት ብለሽ ነው ከዚህ ለመምጣት የቻልሽው? ምን እግር ጣለሽ? ከቢተሰቢስ ጋር እንዴት ብላችሁ ነው የተገናኛችሁት? ከተለያየን በኋላ ወደ ቤትሽ አልተመለስሽም? ከባለቤትሽና ከጓደኞቻችን ጋር አልተገናኘሽም? እስቲ አጫውቺኝ፣ ሁሉንም በዝርዝር ንገሪኝ?»

አሁንም እንደ ልማድዋ ቀና ብላ አየችው። እርስዋ እርሱን በታይ እርሱ ታዲያ ለው ሳይሆን መልአክ የሚያይ ነው የመሰለው። ቢሆንም ያ ከፊትዋ ላይ የሚነበበው ተስፋ የመቁረጥና ያ የፍቅር ረሃብተኛ የሆነው ተንከራታች ዓይንዋን ነው እንዳለ ከነነፍሱ ያየው።

«ንገሪኝ ካልከኝ ልነግርህ እችላለሁ። ግን ምን ያደርግልሃል? ምን ዓይነትስ ጥቅም አለው?» አለች ዝግ ብላ። ለተወሰነ ጊዜ በመካከላቸው ፀጥታ ሰፈነ። ሁለቱም ለመቀጠል አልቻሉም። ከአጭር ጊዜ ዝምታ በኋላ ግን ቪቫን ንግግርዋን ቀጠለች።

«ጻግም በለግንገናኝ ብነግርህ አይከፋኝም። የእኔ ሕይወት እንደሆነ አብቅቶለታል። ገና ድሮ ሞቼ ተቀብሬ ቢሆን ጥሩ ነበር። ምርጫ ቢኖረኝ ደግሞ ያንን ነበር ሳላወላውል የምመርጠው፣ ግን አልሆነም። ቢሆንም እኩ ሳልሞት መሞቴን ረሳሁት መሰለኝ። አንተ ምናልባት አሁን ከእኔ ላይ የሚታይህ ከፋቴን ብቻ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን እንድታየው የምፈልገው የፈጸምኩትን ኃጥያት ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ነፍን ቢሆን ደስ ይሰኛል። ምናልባትም ያቺ ደግዋ እናቴና ጠር ሜጳ የቀረው ጀግናው አባቴ ፈጣሪዬን ለምነውልኝ ሳይሆን አይቀርም በውሰጤ

ክፉት ብቻ ሳይሆን ደግነትም ያስታቀፈኝ። ያ አዛኝና ደጉ ነፍ ሳይሆን አይቀርም ለአንተ ያሰኝን ፍቅር አምቆና ደብቆ ከሆነ በታ የወሸቀብኝ።

«በዓለም ፊት 'ይህስ ከይቅርታ በላይ ነው' የሚያሰኝ ኃጥያት ውርቼ ይሆናል። ሆኖም ግን ምን ጊዜም ቢሆን ሁሉንም ነገር በትክክል የሚያይ ፈጣሪ እንዳለ ተጠራጥሬ አላውቅም። ገና ሳይህ በፍቅርህ በመጠለፌ ነው ቤቴን ጥዬ የወጣሁት። ያ ሥራዬ የአብይት አንጂ የጠነሰ ሰው ሥራ አልነበረም። ያ ያበደው ስሜቴ ትንሽ በረድ ሲልለት ልብ ገዛሁ። ገና ሳይህ ግን ህሊናዬ ሙሉ ለሙሉ ሳይታወር አልቀረም ለማለት እችላለሁ። ስሜት አሸነፈኝ።

«ለዚያ ለሠራሁት ኃጥያትና በሰዎች ላይ ላደረስኩት በደል ሕይወቴን መስዋዕት በማድረግና እዳዬን እየከፈልኩ መኖርን፣ እንዲሁም በየአለቱ ንስሐ በመግባት ፈጣሪዬን መማጠን ይሻላል ብዬ ወሰንኩ። ለዚህም ነው የመነኮስኩት። እናም ከዚህ ዓለም ተድላና ደስታ ይበልጥ ድህነትን፣ ከሚያሳብድ የወንድ ፍቅር ይበልጥ ችግሮኞች መርዳትን መረጥኩ። ይህም ከፈጣሪ ጋር ይበልጥ ሊያቀራርበኝ እንደሚችል አመንኩበት። ከአንተ ጋር ሳብድ የራቅሁትን አምላክ በምንኩስና ልቀርበው እንደምችልም አመቅሁ። በዚህ ጊዜ ነበር ሕይወታቸውን ለሌሎች መስዋዕት ስለሚያደርጉ 'ሴሮች' የሰማሁት። በቀጥታ እነርሱ ወደሚገኙበት ሄጀ እኔም ከእነርሱ አንደኛዋ ሆንኩ። ታሪኬ ይሽሙ ስለሆነ ቢቢቃኝ ይሻላል» ስትለው «ታዲያ ከዚህ እንዴት ልትመጪ ቻልሽ?» ሲል ሰር ልዮኤል ጠየቃት።

«እሱማ የፈጣሪ ተዓምር ነው። የታመሙትን ለመርዳት አለቀቼ ላኩኝ። የመጣሁበት ቤት የአንተ ቤተሰቦች ያሉበት ቤት ሆኖ ተገኘ—ሚስትህና ልጆችህ! ያም የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ነው። የሠራሁት ኃጥያት ምን ያህል ከባድ እንደ ነበርም የተረዳሁት በዚህ ጊዜ ነው።»

«ከአንቺ ኃጥያት የእኔ ኃጥያት ይከፋል። ገና ከጅምሩ ማንኑቴን ብገልጽልሽ ኖሮ እስከዚህ ግጻፋ አልሆንብሽም ነበር። ታዲያ አንቺም አትቅረጂብኝ። አብዶ የሚያሳብድ ፍቅርሽ ህሊናዬን ሰውሮ እኔንም አሳብዶኝ። ለማንኛውም በእኔ በኩልም ህሊናዬ ታውሮ የፈጸምኩት በደል ስለሆነ ያንን ለመመለስ አይቻልም። ለአንባቢና ታሪካችንን ለሰማ ሁሉ ስለሆነ ያንን ለመመለስ አይቻልም። ለአንባቢና ታሪካችንን ለሰማ ሁሉ ትምህርት ሊሰጥ እንደሚችል ግን አልጠራጠርም።»

Scan by Easy Scanner

ምዕራፍ ስልሳ ሦስት

ለስእሉ ስም መስጠት

«አየህ» አለች ሲ/ር ማሪ ቀጠለችና። «አየህ» ብላ ስትናገር ግን ከህሊናው ውስጥ እስከ ዘላለም ያልጠፋው ገጽታዋ ላይ የታየው ብርሃን ነበር። «አየህ ልዮኔል፣ ያደረግሁትን ያደረግሁት ለክፋት ብዬ እንዳልሆነ አምላኬ ያውቀዋል። አምላክ በጥበቡ ነው ከመጨረሻው ጥፋት ያዳነኝ። እና አሁንም ቢሆን ቶሎ ብለን መለያየት አለብን። ዳግምም በዚህ ምድር ላይ አንገናኝም። ሆኖም ግን አሁን ብንለያይም ከምጽዓት በኋላ እንገናኛለን» ብላ ከእንገትዋ ላይ የተንጠለጠለውን መስቀል ቀና አድርጋ ላመችው። መስቀሉን ለመላም ፊትዋን ባቀናች ጊዜ ያየው ገጽታ የመላክ እንጂ የሰው አልመሰለውም።

«ለአጭር ጊዜ ግን ከዚሁ መቆየት አለብኝ» አለች፣ «የጀመርኩትን ሥራ መጨረስ ይኖርብኛል። ከአንተ የሚጠበቀው ዳግም ምሥጢራችንን መጠበቅ ይሆናል። አሁኑኑ ተነስቼ ከዚህ ብጠፋ የፊሪ ያስመሰልብኛል። የሊንዋ እመቤት ቪቫን እንደ ሞተች ቁጠራት። ያ ከንቱ ውበትዋ፣ ያ የሚያላብድ ፍቅርዋና የተበላሸው ሕይወትዋ አብሮ እንዳ ተቀብረ አድርገህ ውሰደው። ይህ እንዳለ ሆኖ ሲ/ር ማሪ በሕይወት ስላለች የጀመረችውን ሥራ እንድትቀጥል ፍቀድላት። ቢሆንም 'የሊንዋ እመቤት ቪቫን ከአሁን ለዓት ጀምሮ ሞታለችና በሕይወት የለችም' ብለህ ለህሊናህ ንገረው። ከአጠገብህ ያለችው ሲ/ር ማሪ ናትና እርስዋን ግን አትርሳት። የእኔ የሲ/ር ማሪ ትዝታ አካልህ ውስጥ ይቀረጽና የዚያ ትዝታ ዳግም ታጥያት ከመሥራት ይከላከልልህ። ደግሞም እኔን ዘወትር ለአንተ ደህንነት እንደምትጸልይ መነኩሲት አስታውሰኝ። ምነው ልዮኔል ዓይኖችህ እምባ አቀረሩሳ» ስትለው «ለሊንዋ እመቤት ከልብ አዝነው ይሆናሳ» አላት ልቡ በሀዘን እየቆሰለ። «ዓይኖቼ እምባ ያቀረሩት እንደ ሲ/ር ማሪ ስለማስታውሳት መነኩሲትና ልቤ ውስጥ ተቀርጸ ስለምትቀር አፍቃሪ ሴት ብለው ይሆናሳ» አላት ቀጠለና።

«ከአሁን በኋላ ይህን ዓይነት ጨዋታ ብናቆም ይሻላል» አለች ሲ/ር ማሪ በመከሳተር። «ከመሄዴ በፊት የመጣሁበትን ሥራ ማጠናቀቅ አለብኝ። ከባለቤትህ ጋር እንድትገናኙ እኔ ቀደም ብዬ ሳግኖትና ሳዘጋጃት» ባለችው ጊዜ «ይህንንም ማድረግ አለብሽ?» ሲል በመሪረ ሀዘን ጠየቃት።

«ቪቫን የአሁኑስ ይበዛል። እሰከዚህ መሄድ ያለብሽ አይመስለኝም። ይህን እንኳን ከአንቺ የምጠብቀው ጉዳይ አይደለምና ለመሸከም ይከብደኛል።»

«ምነው የነገርኩህን ቶሎ ብለህ ረሳህሳ» አለችው ረጋ ባለመንፈስ። «ቪቫን እኮ በሕይወት የለችም፣ ሞታለች። የሞተችውም ኃጥያትዋን፣ ፍቅርዋንና ስሜትዋን እንደታቀፈች ነው። ከአሁን ጀምሮ ስምዋ ዳግም አይነሳም። ለወደፊቱም እኔ ለአንተ ሲ/ር ማሪ ነኝ።»

ሳይወድ በግድ ለእርሱ ሳይታወቀው አካልዋን ለመንካት እጁን ዘረጋ። እጁን እንደ ዘረጋም «ሲስተር ማሪ፣ ይህንንም ታደርጊያለሽ?» ብሎ በድጋሚ ሲጠይቃት ተልእኮዋ እንደ ተሳካና ሕይወትዋን በብቃት መስዋዕት እንዳደረገች ተሰማት።

«ኤሊኖር በጣም ነበር ያመማት። አሁንም ቢሆን ድናለች ብሎ ለመደምደም አይቻልም። ቢሆንም ከበፊቱ በጣም ነው የተሻላት። ድንገት ብቅ ብትልባት አደገኛ ሊሆን ይችላል፣ በጣምም ነው የምትደነግጠው። መደንገጥ ደግሞ ለታመመ ሰው ደግ አይደለም። በሕይወትዋ ላይ ያልተጠበቀ ነገር ሊያስከትል ይችላል። አየህ ልዮኔል፣ ባለቤትህ የተባረከች ቅዱስ ሴት ናት። እርስዋ መልአክ እንጂ ሰው አይደለችም። ንጹህ ሴት በመሆንዋ የምትወደድ፣ የምትናፈቅና የምትከበር ሴት ስለሆነች አከብራት። ደግሞም አንተ ከምታውቀው በላይ ትወድሃለች። እንድም ነገር ሳትደብቅ ታሪክዋን ሁሉ ነግራኛለች። አልጋ ላይ ከዋለች ወዲህ ብዙ ነገር ተጨዋውተናል። ማን እንደሆንኩ ግን ምንም አልጠረጠረችም። ሩህሩህ ልብ ስላላት ለሰው አዛኝ ናት። እኔንም እንደ ሲ/ር ማሪ በጣም ነው የምትወደኝ። ስለዚህ መቼም ቢሆን ሰለእኔ ማንነት ሚወቅ የለባትም። እንደ ሲ/ር ማሪ ብቻ ትወቀኝ። እንደ ሲ/ር ማሪ ትወደደኝ።»

«ስላደረግሽው ነገር ሁሉ ከልብ አመሰግንሻለሁ። ልጆቼንና ባለቤቱን በንጹህ ልብ ተንከባከበሽ በሕይወት ስላቆየሽልኝና ስላዳንሽልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው። ፈጣሪ እንጂ እኔ ዋጋሽን ልከፍል አይቻለኝም» ሲላት «እኔ ምስጋና አልፈልግም። በጎ ሥራዬ ነው የመንፈስ እርካታ ያሰጠኝ። አሁንም ለመልካም ዓለማ መዋሸት ስለምፈልግ ያንተ እርዳታ ያስፈልገኛል። ከዚህ ብዙም ሳልቆይ መሄድ ይኖርብኛል። በድንገት ተነስቼ ከምጠፋ ለአጭር ጊዜ ከዚሁ ከቆየሁ በኋላ በአስቸኳይ ወደ ገዳም እንድመለስ የተጠራሁ አስመስዬ ሰመሄድ ነው የምፈልገው። ለዚህም ነው

Scan by Easy Scanner

ያንተን እርዳታ እፈልጋለሁ ያልኩት። ሌላ ሴር የእኔን ቦታ ሊመውሰድ በቅያሬ እንደምትመጣ ገልጬ ነው ለመሄድ የምፈልገው። አሳቢንና ዓላማዬን ለማሳካት እንድችል ትረዳኛለህ?»

«ምን ገዶኝ!» ብሎ ሲመልስላት አሁንም ሳይታወቀው እምባ ከጉንጩ ላይ ሲፈስ ታየ። ቀጥሎም «ወደ ፖሪስ ነው የምትሂጂው?» ሲል እምባ እየተናነቀው ጠየቃት።

«ከማውቃቸው ሰዎች ጋር ልገናኝበት ወደማልችልበት አገር ነው የምሄደው። አለቆቻችን ወደ ቻይና ሲስተሮች እንዲሄዱ ይፈልጋሉ። የሃይማኖታችን በዚያ አገር መስፋፋት አጥብቀው ነው የሚመኙት። እኔ ደግሞ ወደ ቻይና እንድሳክ የምፈልግ መሆኔን ገልጬላቸዋለሁ።»

«ወደ ቻይና!» ሲል እርስዋ ያለችውን ደገመ። «ይህም ማለት ተከብረሽ ወደኖርሽበት አገር ተመልሰሽ የመምጣቱ እድል የመኑመነ ይሆናል ማለት እኮ ነው» ብሎ ሲናገር «አልመለስም፣ ለመመለስም አልፈልግም። ከዚያ ብዙ ሥራ ይኖራል። ያንን ሥራ ለመሥራት የሚፈልጉ ብዙም ፈቃደኞችና ወዶ ዘማቾች ሴሮች አልተገኙም። እኔ ግን ከወዶ-ዘማቾች አንደኛዋ ለመሆን ነው የወሰንኩት።»

«እና እኔ፣ ከዚህ ሁሉ መከራ፣ ስቃይና ፈተና ውስጥ የዘፈቅኩሽ ሰውዬ ዳግም እንዳይሽ እድል አይኖረኝም ማለት ነዋ! ሁለተኛ ዓይን ለዓይን እንተያይም ማለት ነው?» ብሎ ሲጠይቃት «በፍጹም፣ በዚህ ዓለም ውስጥ ዳግም አንገናኝም። ከእግዚአብሔር ፊት ቆመን ስንገናኝ ፍርሃት፣ ፍርሃት እንዲለን አያስፈልግም። ደግሞም እኮ በዚህ ዓለምም ቢሆን በአሳብ እንገናኛለን። ሴሳው የምነግርህ ነገር ቢኖር ደርባባዋ ባለቤትህንና ጨዋ ልጆችህን ባስታወስኪቸው ቁጥር ደስ እንደሚለኝ ነው። ከእንተ ጋር እንደገና ተገናኝተው ደስ ብሎአቸው ሲኖሩም በአሳብ ማየቱ ታላቅ ደስታ እንደሚሰጠኝ አትጠራጠር። ይህም መሆን ያለበት ጉዳይ ነው፤ አይመስልህም?» ብላ ስትጠይቀው «የእምላክ ፈቃድ ከታከለበት ይሆናል» ሲል ዓይን ዓይንዋን እያየ መለሰላት።

«ከዚህ መሄድ አለብኝ፣ ደህና ሁን። በቅድሚያ ግን ኤሊኖርን ማነጋገር ይኖርብኛል። እንተን ለማነጋገር ዝግጁ ስትሆን ሰው አልክብሃለሁ። ያኔ አንተ ትመጣለህ እየደል?» «እመጣለሁ» ሲል ተቻኩሎ መለሰላት።

«ደህና ሁን» አለች ሲ/ር ማሪ። «ሰማይ ቤት እንደምንገናኝ ተስፋ በማድረግ ለአሁኑ በዚሁ ይብቃንና እንለያይ። ሆኖም ግን ለመጪረሻ ጊዜ ፊትህን ትኩር ብዬ ልየው። ድምፅህንም ለመጪረሻ ጊዜ በጥሞና ልስማው። ዳግም መለያየት፣ ዳግም ህዘን ከሌለበት መንግሥተ-ሰማይ እንደማይህና ድምፅህንም እንደምሰማ ተስፋ አደርጋለሁ። ያኔ የአካል ፍቅርህን በመንፈሳዊ ፍቅር እለውጠዋለሁ። ያለማመንታት ከልብ የወደድኩህ ፍቅረኛዬ ዳግም ስለይህ እጅግ ይከብደኛል፤ ግን ምርጫ የለኝም። ደህና ሁንልኝ።»

ከመሄድዋ በፊት አተኩራ ስትመለከተው «ደህና ሁኚልኝ» አላት እርሱም እርስዋ ያለችውን በመድገም። «ደህና ሁኚልኝ» አላት በድጋሚ። ከዚያም እጅዋን ለመሳም ጎንበስ ባለ ጊዜ ዓይኖቹ በእምባ ስለተሞሉና በትክክል ለማየት ስላልቻሉ እጆችዋ የት እንዳሉ እንኳን መለየት ተሳነው። እርስዋ ግን በእጆችዋ ፈንታ ከደረትዋ ላይ ተንጠልጥሉ የነበረውን መስቀል ወደ ከንፈሮቹ አስጠጋችለት። እርሱም መስቀሉን ምጥጥ አድርጎ ሳመው። በዚሁ ተለያዩ። ከዚያ በኋላም ዳግም አልተገናኙም። ሰማይ ቤት ተገናኝተው እንደሆነ ግን ከፈጣሪ በስተቀር የሚያውቅ የለም።

የፍቅረኛዋ ሚስት ወደ ነበረችበት ክፍል አመራች። እርሱም በዓይኑ ተከተላት። ከዓይኑ እስከ ተሰወረችም ፊቴን አላዞረም። ከዓይኑ ስትሰወር በአፍ ጢሙ ተደፍቶ እምርር አለቀሰ። ሰው በጸጸት ተሰቃየ ቢባል ከእርሱም በላይ የተሰቃየና ልቡ የቆሰለበት ሰው ነበር ለማለት አይቻልም።

ሲስተር ማሪ ኤሊኖር ከነበረችበት ክፍል ገባች። ኤሊኖር በጉጉት ትጠብቃት ስለነበር እጅዋን ዘርግታ ተቀበለቻት። ሲ/ር ማሪ ኤሊኖርን ስትመለከታት በርትታና ተሸሉአት ነው ያገኘቻት። መልክዋም በጣም ተመልሷል። በፍቅር ተሳሳሙ።

«እንዶ ጽጌረዳ የሚያምረው መልክሽ እየተመለሰ ነው። ተነሽና ልብስሽን ልበሺ» ከማለት ሌላ ሲ/ር ማሪ ነገር ለማብዛት አልፈለጉችም። በማግሽ ሰዓት ውስጥ ኤሊኖር ተነስታ ፊትዋን ታጥባና ልብስዋን ለብሳ ጨረሰች። ከዚያም ከሶፋው ላይ ጋደም አለች። ለምን ብላ ሲ/ር ማሪ ሌላ ሰው ሳይደርስባት ልብስዋን እንዳስበስቻትና ፀጉርዋን እንዳበጠ ረችላት አልገባትም። ለምን ብላ የጽጌረዳ እምቡጥ ከልብስዋ ላይ እንደ ሰካችላትም ግልጽ አልሆነላትም።

Scan by Easy Scanner

«እንዲህ አድርገሽ የምታለማምሪኝ ሐኪሙ ሰለሚመጡ ነው?» ስትል ኤሊኖር ሲ/ር ማሪን ጠየቀቻት። «ምን አሰፋሽ፣ እርሳቸው እንዲሆነ ነገር እያስተውሉም» ብላ 'ለምን ይሆን እጅግ በጣም የምወደውንና የሚያምርብኝን ልብስ የመረጠችልኝ' ስትል ኤሊኖር በልብዋ አሰላሰለች እንጂ ሲ/ር ማሪን በጣም ስለምታከብራት ያለቻትን ሁሉ ከመፈጸም ወደ ኋላ አላለችም። ከዚያም የሲ/ር ማሪን ፊት እያየች ፈገግ አለች።

«ምነው ዛሬ በጣም አሰማመርሽኝሳ» ስትል ኤሊኖር ሲ/ር ማሪን ጠየቀቻት። «እንዲህ እንደ ዛሬ ካማረብኝና ቆንጆ ሁኜ ከታየሁ ሬጅም ጊዜ አልፎአል» ብላ ስትናገር ሲ/ር ማሪ ጣልቃ ገባችና «ሁሌም እኮ ቆንጆ ነሽ» አለቻት። በዚህ ጊዜ ኤሊኖር አሁንም ፈገግ አለች የእንባት በላይ ንግግር እንዳልሆነ በመረዳት። ኤሊኖር ጨዋታዋን በመቀጠል «ሲያኩራርዋትና ሲያደንቋት ደስ የማይላት ሴት እንደሌለች አውቃለሁ» አለቻት ትህትና በተሞላበት አንደበት።

«ልክ ነሽ፣ ብቻ ይህን ያልኩት አንቺን ለማኩራራትና ለማሞካሸት ሳይሆን እውነቱን ለማውጣት ነው። ቢሆንም አምረሽ እንድትታዪ የፈለግሁት ያለ ምክንያት አይደለም። ለማንኛውም እንዴት እንዳማረብሽ ልነግርሽ አልችልም። ቆይ እስቲ መጋረጃውን ዝቅ ሳድርገው መሰለኝ። የአበባ ማስቀመጫውም ባዶውን መቀመጥ የለበትም» ብላ ሲ/ር ማሪ ስትናገር ኤሊኖር አንደገና ሳቅ አለች።

«ደስ ነው ያለኝ፣ እውነትም እንዲህ ካማረብኝ ቆይቷል፣ በራሴ ተኩራራሁ። እንደ ስእል ነው የሳልሽኝ» አለች በመስታወት ራስዋን እያየች። «ለስእሉ ስም እንስጠው መሰለኝ፣ ታዲያ ምን እንበለው? ለምን 'ከቁጥር የማይገባ ጊዜ' ብለን አንለይመውም?»

«የለም ከዚህ የተሻለ ስም ነው መስጠት ያለብን» አለች ሲ/ር ማሪ። «እስቲ ስም እንፈልግ፣ ምን እንበለው፡» ካለች በኋላ ሲ/ር ማሪ ወደ ኤሊኖር ተጠግታ ከእጠገብዋ ተንበረከከች። ኤሊኖርም የሲ/ር ማሪን እጅ እንቃ ይዝ መንፈስ ቅዱስ የቀረበውን ሰውነት በማተኩር ተመለከተችው። እነዚያ ሁለት ሴቶች ለመጨረሻ ጊዜ ዓይን ለዓይን ተፋጠጡ። ሆኖም ግን አብረው ሁነው እያለ ተራራቁ። አምን ለመጨረሻ ጊዜ! ነገር ግን ሁለቱም በአሳብ ሰጥመው ተራራቁ ቢባልም የአንድዋ ልብ ከሌላዋ፣ የአንድዋ ነፍስ ከሌላዪቱ ነፍስ ውስጥ የተዋሃዱ መሰሉ።

ምዕራፍ ስልሳ አራት

እንደገና ተጣመሩ

ለጥቂት ደቂቃዎች ሰፍኖ የነበረው ዝምታ በኤሊኖር ልቅሶ ታወከ። ከፊት ለፊትዋ ሁና አንገብሳ ታያት የነበረችውን ቆንጆ ሴት ፊት ሳይ አፈጠጠች።

«ሲስተር ማሪ ምንድነው ነገሩ?» ብላ ጠየቀቻት። «ፊትሽ ተቀያየረብኝሳ! ሰውነትሽም ይንቀጠቀጣል፣ ምን ነካሽ? ምን አገኘሽ? ለማያውቅሽ ሰው ከሙታን ተለይተሽ የመጣሽ ነው የምትመስዪው።»

«እርሱ እንኳን ሊሆን አይችልም» ብላ ሲ/ር ማሪ መናገር ስትጀምር ኤሊኖር አቋረጠቻት።

«ምነው የድምፅሽም ለዛ ተለዋወጠብኝሳ! ምን ሆንሽ? ምን አዲስ ነገር ተገኘ? ያዘንሽም ትመስያለሽ። አዲስና የሆነ እንግዳ ነገር እንደገጠመሽ ያስታውቃል። ቢሆንም ምን እንደሆነ ለማወቅ ከብዶኛል። ሲ/ር ማሪ ምነው ባታሰጨንቀኝ፣ ጌዳዩ የእኔ ነው ወይስ ያንቺ?»

«የእኔ አይደለም፣ ስለእናንተ አስቢ ነው» ስትሳት «ጎርዶን አመመው እንዴ? ልጁ ሕመሙ ጠናበት?» በማለት በመርህ ጠየቀቻት።

«የለም፣ የለም እርሱ ተሽሎታል። ጎርዶን ከአሁን በኋላ አያስጋውም። ጠዋት አይቼው ደህና ነው ያደረው፣ ተሽሎታል። እንዲያውም በቅርቡ ወደ አገሩ ወደ እንግሊዝ አገር ተመልሶ ሄዶ ከዚያ ከሚያምር ግቢያችሁ ውስጥ እየሮጠ ሊቦርቅና ሲጫወት ይታየኛል። ሲያድግ እንዴት ያለ ብርቱ ወጣት እንደሚሆን የሚጠራጠሩት አይደለም። ሆኖም ግን ያሰፈው ሲቃዩን የሚረሳ አይመስለኝም፣ እኔንም እንዲሁ እንደ ማይረሳኝ ተሰፋ አደርጋለሁ።»

«ማንኛችንስ ብንሆን እንዴት ብለን እንረሳሻለን!» ስትል ኤሊኖር መለሰችላት። «አንቺ እኮ የሕይወታችን አንድ ክፋይ ሁነሻል። አንቺን በማግኘታችን ዘወትር ፈጣሪያችንን እናመሰግነዋለን።»

«አንቺም ትወጅኛለሽ ማለት ነዋ!» ብላ ኤሊኖርን ስትጠይቃት «በሚገባ ነዋ!» በማለት መለሰችላት።

«እንግዲያውማ ከዚህ ርቄ ሰሄድ እንዳስታውሰው የምፈልገው ነገር ስላለ የዚያ ማረጋገጫ እንድትሰጪኝ አፈልጋለሁ። ይኸውም እስከ ዛሬ የሠራሁት ሥራ ጠቀሜታ ኖሮት ከልብሽ ውስጥ ገብቶ ከሆነ ያ ለእኔ ትልቅ ማበረጃ ይሆነኛል፤ ትልቅ እርካታም ይሰጠኛል። ለመሆኑ ዋሩ አበታማሚ ነኝ ወይስ 'እንደ ነገሩ' የሚሉት ዓይነት? እውነቱን ንገሪኝ።»

ሲ/ር ማሪ ይህን ጥያቄ ስትጠይቃት ድምፅዋ 'እስቲ መንፈሴን አረጋጉልኝ' የሚል ቃናና ቅላፄ ነበረው። ዓይንዋ በጣም ስሰተንከራተተ የኤሊኖር አንጀት ተላወሰ።

«ልገልጸው ከምችለው በላይ ነው» አለች ኤሊኖር በዝግታ። «ምን ያህል እንደምንወድሽ፣ ምን ያህል እንደምናከብርሽ፣ ምን ያህል ከልጆቻችን ውስጥ እንዳ ገባሽና ባለውለታችን እንደሆንሽ ለመናገር ቃሳት ያጥረኛል ከማለት ሌላ የምለው ነገር የለኝም። ውለታሽን በትክክል ለመግለጽም በጣም ይከብደኛል። እሰከ ዛሬ በሕይወት ዘመኔ እንዳንቺ የወደድኳት ሌላ ሴት አላውቅም። እንቺን የምትበልጥ ሴትም በምድር ላይ አለች ብዬ አላምንም።»

«ደስ ነው ያለኝ» ካለች በኋላ ተረጋግታ በማጎንበስ የኤሊኖርን የገረጣ ጉንጭ ሳመች። «ከልብሽ እንደምታከብሪኝና እንደምትወጂኝ በመስማቴ በጣም ነው ደስ ያለኝ።»

«ለዚህማ ምንም ጥርጥር የለኝም፣ ሁሳችንም በጣም ነው የምንወድሽ። ደግሞም በተለይ ለእኔ ባለውለታዬ ነሽ። ለዚህም እጅግ አድርጌ ሳመሰግንሽ እፈልጋለሁ። አንቺ ባትደርሽልኝ ኖሮ እርግጥ ነኝ ልጄ ዛሬ በሕይወት የለም። የእኔም ጉዳይ ቢሆን ያው ነበር የሚሆነው። ሁለታችንም ሙታን ተቀብረን ነበር።»

«እንግዲያውስ አንድ ዘወትር ከአንጀቴ የማይወጣና የሚያብሰለስለኝ ነገር ልጠይቅሽና ሳትደብቂ እውነቱን ንገሪኝ።»

«ውይ፣ አንቺ ጠይቂሺኝ ነው፣ ምን ቆርጦኝ። ግድ የለም፣ አሳብሽን ልስማውና እውነቱን ነው የምነግርሽ።»

«ምናልባት ከጊዜ በኋላ ስለእኔ አንድ ደስ የማይል ነገር ብትሰሚ አሁን ያልሽውን ቃል የምታጥፊ ይመስልሻል? 'ባለፈው ሕይወቴ ስላደረስኩት በደል ወይም እንበል ስለሠራሁት መጥፎ ድርጊት ብትሰማ ለእኔ ያላት ፍቅር ትለውጥ ይሆን? ለምንስ ይህቺን ሴት አከበርኳት፣ ወደድኳት ብላ ትጸጸት ይሆን?' አያልኩ ብዙ አስባለሁ።»

«የለም» አለች ኤሊኖር ሳታመላውል። «ምን ዓይነት ሴት እንደሆንሽ ስለተረዳሁ ምንም ዓይነት ወሬ ስላንቺ ብሰማ አሳቢን አልቀይርም።»

«አሁን በይበልጥ ነው ደስ ያሰኝ» አለች ሲ/ር ማሪ። «ዛሬ ጠዋት አንቺም እንደ ጠረጠርሽው የሆነ ለውጥ አላይቻለሁ። ነገሩ ምን እንደሆነ ከመግለጹ በፊት ግምባሬን ብትስሚና በድጋሚ እወድሻለሁ ብትዪኝ ደስ ይልኛል» ስትላት ኤሊኖር ሲ/ር ማሪን ሳብ አድርጋ ሳመቻት፣ የሞቀ ረገግታም አሳየቻት። «እመድሻለሁ» ስትልም ፍቅርዋን አረጋገጠችላት። ሲ/ር ማሪ ለአጭር ጊዜ ዝም አሰች። ከዚያም ሰዛው በጣፈጠ አንደበት ተናገረች።

«አየሽ ኤሊኖር፣ ዛሬ ልክ አርቲስት እንደ ሳለው ስእል አስክትመስጪ ድረስ ነው ያሰማመርኩሽ። ለምን እንደሆነ ጠርጥረሻል?»

«ሕኪሙን ወይም አባቴን ለማስደሰት ነው የመሰለኝ» ካለች በኋላ «እርግጠኛ ነኝ እንዲህ ሆኜ ቢያየኝ አባቴ በጣም ደስ ይለዋል» ብላ ስትናገር «ዛሬ ታዲያ እርሳቸው ይመጣሉ እንዴ? እኔ በማውቀው እርሳቸው ዘሬ አይመጡም። ምናልባት ከመሽ በኋላ ሊመጡ ይችሳሉ። ያሰማመርኩሽ ግን ሌላ የተለየ ሰው ለማስደሰት ነው» አለቻት። ከቃላቱ ይበልጥ አኳኋገርዋ ነበር የኤሊኖርን ልብ የሰለበውና ያፈዘዘው።

ሲ/ር ማሪ በመቀጠል «እኔ እንጃ ብቻ» አለች በማመንታት። «ምን ያህል እንደ በረታሽ የምታውቂው ራስሽ ነሽ። አንድ አስደሳች ወይም አሳዛኝ ዜና ብነግርሽ በሕመም የተሳሳቄለው ሳንሽ የሚችለው ይመስለኛል። ከዚያ በፊት ግን ሌላ ጥያቄ ልጠይቅሽና እውነቱን ንገሪኝ?»

«እሺ ጠይቂኛ» አለች ኤሊኖር ልብዋ እየመታ።

«አሁን በቅድሚያ የምትልጊውን ንገሪኝ፣ ማለቴ 'ምን ብታገኚ ልቦናሽ ደስ ይለዋል?' ተብለሽ ብትጠየቂ ምን ብለሽ ትመልሻለሽ? ኤሊኖርዬ፣ ሳትደብቂ እውነቱን ንገሪኝ?»

«እውነቱን ልንገርሽ» አለች ኤሊኖር በእሳብ እንደ ተዋጠች። «ብቻ ሊሆን አይችልም» ብላ ተናገረች።

«ምኑ ነው ሊሆን የማይችለው?» ስትል ጠየቀቻት። ይህን ጊዜ «የባሌን ፊት እንደገና ማየት» አለቻት።

«ቢሆንስ ምን ትያለሽ?» ስትል ሲ/ር ማሪ ስትጠይቃት «ህህ..» ብላ ኢሊኖር በድንገት አቃሰተች። ፊትዋም ተለዋወጠ። ሰውነትዋ የተንቀጠ ቀጠም በለመሰላት ሲ/ር ማሪ በጣም ደነገጠች። ንግግራቸው የኢሊኖርን ሕይወት እንደ ቀጠፈው ገመተች። ኢሊኖር የሲ/ር ማሪን እጅ አጥብቃ ይዛ «አሁን አንቺ በተራሽ እውነቱን ንገሪኝ» ስትል ኢሊኖር ተናገረች። «ለማወቅ ቸኩያለሁ። ባለቤቴ መጣ እንዴ? ማለቴ ባለቤቴ የት እንዳለ የሰማሽው ነገር አለ?»

«ሰምቻለሁና ሁሉንም እነግርሻለሁ። አንቺ ብቻ ሬጋ በይ። ጥሩ ዜና ነው ይገፍልሽ የመጣሁት። ታዲያ አንቺ መንፈስሽን ካሳረጋጋሽው ልነግርሽ አልችልም። አንቺ ብቻ ተረጋጊና መንፈሰሽን አጠናክሪው። ፍርሃቱንና የሰውነት መንቀጥቀጡን ጉዳይ ወደ ጎን በዪው። አለበለዚያ ሳያስፈልግ ራስሽን ትጎጂያለሽ። በዚህ ከተስማማሽ ስለባልሽ የሰማሁትን ሁሉ እንድ በአንድ እነግርሻለሁ።»

«አላውቅም» አለች ኢሊኖር ሲቃ እየተናነቃት። እምባዋ በጉንጮችዋ አጀርጦ ይንጠባጠብ ጀመር። «የሆነው ይሁን፣ አንቺ ብቻ ስለባሌ የሰማሽውን ንገሪኝ።»

«እንዲህማ ከሆንሽ አልነግርሽም። ሰማሽ ኤሊኖር፣ መከራና ስቃይ ተፈራርቀውብሻል። ያንን መከራ ያንን ስቃይ ለመቋቋም ሲል ሰውነትሽ ብዙ በመታገሉ ዛሬ መላ አካልሽ ደክሞአል። አሁን ደግሞ የምሥራቹን ቶሎ ብዬ ብነግርሽ የላላው ጎንሽ ሽክሙን አይችለውም። ስለዚህ ሰውነትሽን አበረታችው እንጂ ይበልጥ አታድክሚው። እንዲያውም አሁን የሚሻለው ጋደም ብትዪ ነው። ስለዚህ ጋደም በይ። ባለቤትሽ በጣም ደህና ነው። በሕይወት ነው ያለው፣ ሰውነቱም ደህና ነው። ስለጎርዶን መታመምም ሰምቷል። ልጁንም ለማየት ወደዚህ እየመጣ ነው።»

«'እየመጣ ነው' ነው ያልሽው?» ስትል ኤሊኖር በደከመ ድምፅ ጠየቀቻት። «ከዚህ ካለንበት ሥፍራ ነው የሚመጣው? እውነትሽን ነው?»

«አምን፣ የሚመጣውም አንቺን ለማግኘትና በጣም የተጸጸተ መሆኑን ለመግለጽና እጅግ አድርጎ እንደተላላተ ሊነግርሽ እንደሆነ ሰምቻለሁ።

ያነጋሩን ፍሬ አሳብ ከእርሱው ብትሰሚው ነው የሚሻለው። ብቻ ሀሊናው ታውሮ የሠራው ኃጥያትና የፈጸመው ወንጀል አንቺ እንደምታስቢው ላይሆን ይችላል።»

ኤሊኖር ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ሲ/ር ማሪ እንዴት ብላ ስለባልዋ ያን ያህል ልታውቅ እንደቻለች ማሰላሰልዋን ቀጠለች። ብድግ ብላ ሲ/ር ማሪን በማቀፍ ልቅሶዋን ለቀቀችው። «እባክሽን ሲስተር ብዙ አታስጨንቂኝ። እውነተኛውን ዜና ንገሪኝ» ብላ ስትጠይቃት እምባዋ በጉንጮችዋ አጀርጦ መፍሰሱን ቀጠለ። ያ እምባ ደግሞ ጭንቀትዋንና ድንጋጤዋን ይዞ ሰለወረደ መንፈሰዋ በመጠኑም ቢሆን ተበረታታ፤ ተረጋጋ።

«ከዚህ ይበልጥ የምታውቂው ነገር ስላለ አሁኑኑ ብትነግሪኝ ይሻላል።»

«አምንሽ፣ ከዚህ ይበልጥ አውቃለሁ። ባልሽ ዛሬ ይመጣል» ስትል የምሥራቹን ነገረቻት። «የአንቺን ፊት ለማየት እጅግ በጣም ጓጉቷል። ሆኖም ግን ውሳኔው የአንቺ ነው። ከተረጋጋሽና እርሱን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆንሽ መጥቶ ያነጋግርሻል። 'የለም አሁን አላነጋግረውም' ካልሽ ካለበት ይቆያል። ይህ ያንቺ ምርጫ ነው። ነገር ግን አሁን አላናግረውም ብለሽ ከመሰንሽ እርሱን እጅግ በጣም እንደሚያስከፋውና እንደሚያሳዝነው እርግጠኛ ነኝ።»

እውነትም 'ዜናው ኤሊኖርን ገድሏታል' ለማለት ይቻላል። ሲ/ር ማሪ ቆሎ ብላ ሂዳ የሚጠጣ ነገር አመጣችላት። ያመጣቻላትን ስትጠጣ የኤሊኖር ኑፍስ መለሰ አለ። በመጀመሪያ ግን «ምንም ነገር አልቀምስም» ብላ አሰቸግራ ነበር።

«አሁን እውነተኛውን ታሪክ ልነግርሽ እችላለሁ» አለች ሲ/ር ማሪ። «መልካም ዜና እንጂ የሚያስከፋ አይደለም። ዛሬውኑ ከባለቤትሽ ጋር ብትገናኙ ደስ አይልሽም?»

«ዛሬውኑ» አለች ኤሊኖር በማጋነን ሲ/ር ማሪ ያለችውን በመድገምና ዓይንዋ ጣራ ጣራውን እያየ። «ዛሬውኑ አልሽ ሲ/ር ማሪ? የምትዪው ነገር እውነት ሊሆን ይችላል?» ብላ ስትጠይቃት «እውነት ነው» ስትል መለሰችላት። «አሁን እንኳን መንፈስሽ የተረጋጋ ይመስላል፣ ልክ ነኝ?»

«ልክ ነሽ፣ የሰውነቴ መንቀጥቀጥና የመንፈሴ መረበሽ በመጠኑም ቢሆን እርጋታ ያገኘ ይመስለኛል። ኧሬ እንዲያውም የለም፣ እውነትሽን ነው

Scan by Easy Scanner

በጣም ተረጋግቻለሁ። በመጀመሪያ የባለቤቴ መምጣት ጉዳይ ስታነሺብኝ ሞቼና ከመንግሥተ-ሰማይ በር ቆሜ ለዎች በሩን ከፍተው 'ነይ ግቢ' የሚሉኝ፣ እንዲሁም ከአንቺ ጋር ሳወጋ በድኔን የማወራ ነበር የመሰለኝ።»

ኤሊኖር ይህን ስትናገር የሲ/ር ማሪ ፊት እየገረጣ ሄደ። እርስዋም በበኩልዋ የሕይወትዋና የተልዕኮዋ ፍጻሜ የተቃረበ እንደሆነ አወቀች።

«ከዚህ ሌላ እንድ የምነግርሽ ነገር ስላለ ራስሽን አዘጋጂ» ባለቻት ጊዜ «ከዚህ ሌላ ደግሞ ምን ተገኘ?» ስትል ኤሊኖር ጣልቃ ገባች።

«ለታላቁ ዜና እንዳዘጋጅሽና ዜናው እንደ መርዶ እንዳያስደነግጥሽ ተነግሮኝ ነው የመጣሁት» ስትላት ኤሊኖር መልስ ከመስጠት ዝምታን መረጠች። ከእለታው ላይ ስትጋደም ፊትዋ እንደ ጠዋት ፀሐይ በራ።

«ሲስተር» አለች ኤሊኖር። «ባለቤቴ ከዚሁ አካባቢ ነው ያለውን? ልክ ነኝ፣ አይደል?»

«አዎን፣ ከዚሁ ነው ያለው። ከእንቺ ጋር ለመገናኘት መልካም ፈቃድሽን እየጠበቀ ነው። ይግባ ካልሽ፣ አሁኑኑ ሰው ልኬ አስጠራዋለሁ። ነስሐ ለሚገባ ሁሉ እግዚአብሔር እጁን ይዘረጋል። 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ብትዪ አምላክም ደስ ይለዋል። ስሚትሽን ውጠሽ ቶሎ መጥቶ እንዲያናግርሽ ፍቀጂለት» ካለቻት በኋላ ሲ/ር ማሪ የኤሊኖርን እጅ ጥርቅም አድርጋ ያዘች።

«የሚበቃውን ያህል ተሰቃይቷል፣ በጸጸት አለንጋም ራሱን በሚገባ ገርፎአል። ነገር ግን የተሰቃየው መሰቃየት ስለነበረበት ነው። አሁን ግን ቢበቃው ይሻላል። ለበቀል መንፈስሽን ለማነሳሳት አትሞክሪ። ይህ ደግሞ አምላክ የሚወድደው ነገር ስላልሆነ ፈጣሪን አታስቀይሚ። 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ብለሽ ባልሽን ለመቀበል ከቻልሽ ወደፊት የደስታ ኑሮ ይጠብቅሻል። ያለፈው የስቃይ ኑሮሽ ዳግም ማብቃት አለበት። ታዲያ ኤሊኖር ምን ትያለሽ? ነገሩን ከዚሁ ላይ ብናቆመው ይሻላል። 'ባሌን እንደ ጥንቱ እፈቅረዋለሁ' ብለሽ ቃልሽን በጪኝ። ይህን ብቻ ነው ተምበርክኬ ለመጪረሻ ጊዜ ከልቢ የምለምንሽ። ኤሊኖር አታሳፍሪኝ፣ ስለፍቅራችን ብለሽ ቃል ግቢልኝ?»

ሲስተር ማሪ ስለኤሊኖርና ስለባልዋ ያሳየቸው አዲስ ስሜት ኤሊኖርን በይበልጥ ግራ አጋባት። ሲ/ር ማሪ ቀጠለች። «ስትገናኙ ሳሚው እንጂ አትገለፊው። ይህን እንደምታደርጊ ተሰሩ አደርጋለሁ። ውደጂው እንጂ አታበላጪው። ባልሽ ነውና አክብሪው እንጂ አታዋርጂው። እንዲደሰት ጣሪ እንጂ አታስከፊው። አሁንም ልስምንሽና ለዚህም ቃልሽን ስጪኝ።»

«በጣም ስለማከብርሽ ያልሽውን ሁሉ ለመፈጸም ቃል እገባልሻለሁ» ስትል ኤሊኖር በመለሰችላት ጊዜ ሲ/ር ማሪ ከመቅጽበት ተወርውራ ሳመቻት። ቢሆንም ያ እርስዋ የላመችው ከንፈር ማን ሊስመው እንደ ተዘጋጀ አስታወሰች። በዚህም የእርስዋ ምድራዊ ሕይወት ማክተሙን አወቀች። ኤሊኖርን ለመሳም ተንበርክካ ስለነበር ከተንበረከከችበት ተነስታ ደወል ደወለች።

«ኤሊኖር ሰር ልዮኔልን ለማነጋገር ዝግጁ መሆንዋን ንገረውና ይምጣ» በማለት የደወል ድምፅ ሰምቶ የገባውን አሽከር አዘዘችው። አሽከሩ በሩን ዘግቶ ወጣ። ያ ቅጽበት ለሲ/ር ማሪ ቀላል ጊዜ አልነበርም። ሆኖም ወደ ኤሊኖር ተጠግታ «እኔ አሁን እሄዳለሁ። ደግሞም ብቻችሁን ብትነጋገሩ ይሻላል» አለቻት።

ከዚያ በኋላ ቃል ሳትናገር ቪቫን ከክፍሉ ወጥታ ሄደች። ቀላል መለያየት አልነበረም። ከሞት የከፋ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። በሩን ከመዝጋትዋ በፊት ግን ኤሊኖርን ለመጪረሻ ጊዜ አፍጥጣ አየቻት። ከዚያ በኋላ በአካል አልተገናኙም። በኮሪዶሩ አድርጋ ልታልፍ ስትል ሰር ልዮኔል ሚስቱ ከነበረችበት ክፍል ገባ። ከዚያች ክፍል ውስጥ ምን እንደ ተነገረም ሆነ ምን እንደ ተባለ ከእግዚአብሄርና ከሁለቱ ፍቅሪኖች በቀር ያወቀ ወይም ያየ የለም። ምን እንደ ተባባሉም ከማንም ጆሮ አልገባም። ወደ ማታ ጀምበር ልትጠልቅ ስትል አበትዋ ሊጠይቅዋት ከክፍልዋ በገቡ ጊዜ የልጃቸው ፊት እንደ ክከብ በርቶና እጅግ በጣም ደስ ብሎአት አገኘዋት። ያኔ ጥንት በልጅነት ዘመንዋ ታሳየው የነበረው ፈገግታና የመንፈስ እርካታ ከገጽዋ ላይ ባይ ጊዜ ቁጣቸውና ቁጭታቸው ሁሉ የት እንደ ደረሰ ሳይታወቅ ሙሉ ለሙሉ እንደ ጉም ተነነ።

ከዚያ ቤት ውስጥ ዳግም ሰላም ሰፈነ። ቤቱም የደስታ ቤት ሆነ። ከቤቱ ውስጥ ሰፍኖ የነበረው ሀዘንና ተንሰራፍቶ የነበረው ጭንቀት ከተመለሰው ደስታ ውስጥ ለአንዴና ለመጪረሻ ጊዜ ተቀብሮ ቀረ።



Scan by Easy Scanner

ምዕራፍ ስልሳ አምስት

«ምን ያህል እንደ ተበቃየኝ አስበው!»

ኤሊኖርና ባልዋ ጸግም ከተገናኙ ዋቂት ዓመታት በኋላ አንድ ትልቅ ዜና እንግሊዝ አገር ውስጥ ተነገረ። ቻይና ከተባለ ሩቅ አገር ውስጥ ጓደኛ ሆኖ ላለ እንደ ጥሩ ነገር የሚቆጠር ባህል ነበራቸው። በባህላቸው ወንድ ልጅ ሲወለድ እንደ ትልቅ ፀጋ ይቆጠራል። ሴት ልጅ ስትወለድ ግን ጥቅም እንደሌላት ተደርጎ ስለሚቆጠር ወላጆችዋ የሴትዋ ልጅ መጥፊያ ይፈልጋሉ። ያቺን ጥቅመቢስ የሆነችውን ሴት ልጅ ለማስወገድ ብዙውን ጊዜ ከወንዝ አጠገብ እየወሰዱ ይጥልዋቸዋል። በዚህም ምክንያት አልፎ አልፎ የሕፃን ልጅ ሬሳ ከወንዝ ዳር ማግኘት የተለመደ ትርዒት ነበር።

ይህ አሳፋሪ ታሪክና ጨካኝ ድርጊት በተሰማ ጊዜ ብዙ አዛኝና ደጋግ ሰዎች ይህን አጉል ባህል ለመዋጋት ወደዚያ አገር ሄዱ። ብዙ የሃይማኖት ሰዎችም ወደዚያው ጎረፉ። ወደዚያ አገር ለመሄድ እንዲችሉም ብዙ ሰዎች ገንዘብ አዋጥተው ረድዋቸው። በተዋጣው ገንዘብም ከታላላቅ ወንዞች አካባቢ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶችና ሚሲዮኖች ተቋቋሙ። እነዚያ በጎ አድራጊዎች በወንዙቹ ውስጥም ሆነ ዳርቻ ሕፃናት እንዳሉ ከለሙ ከሥፍራው ፈጥነው ለመሄድ በሕይወት ያገኙዋቸውን ያሳድጓቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ግን ሕፃናቱ ሞተው እንጂ በሕይወት አያገኝዋቸውም። ስለዚህ እነዚያ በጎ አድራጊዎች የሞቱትን በክብር ሲቀብሯቸው በሕይወት ያገኝዋቸውን በቅድሚያ ካጠመቁዋቸው በኋላ እየተንከባከቡ ያሳድጓቸዋል። ይህን የመሰለ በጎ ተግባር ይሠሩ ከነበሩት በጎ አድራጊዎች መካከል አብዛኛዎቹ ሴሮች ነበሩ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ እነዚያ በአጉል እምነት የተተበተቡ አላዋቂዎች ሴሮቹ ይፈጽሙት የነበረውን በጎ ተግባር እንደ ክፋት እያዩ ይተናኰለዋቸዋል። የተንኰል ድርጊታቸውም ሴሮችን እስከ መግደል የሚያደርስ ነበር። ሴሮችን ብቻ ሳይሆን የረድዋቸው ሕፃናትም ሲያድጉ ይገድሏቸዋል። ይህ ዜና ነበር እንግዲህ ከእንግሊዝ አገር የደረሰውና ሕዝብ እንዲሰማው የተደረገው።

ከብድ ያለ የጭካኔ ሥራ ይሠራበትና ሴሮችና ያደጉ ሕፃናት በብዛት ይገደልበት የነበረው አካባቢ ቹሊንግ ሲባል ከዚያም የነበረው የሃይማኖት ተቋም የቹሊንግ ሚስዮን ይባል ነበር። በሚስዮን ውስጥ ይሠሩ የነበሩ

ሴሮች አለቃ ሲስተር ሜሪ ነበረች። በዚያ አካባቢ ስለሲስተር ሜሪ በጎ ተግባር የማያውቅ ሰው አልነበረም።

እንግሊዝ አገር ውስጥ ይታተሙ የነበሩ ጋዜጦችም ከፍ ብሎ ስለተጠቀሰው ታሪክ ሲጽፉ በለሲስተር ሜሪ በጎ ተግባር አጉልተው ይጠቅሳሉ። ምን ዓይነት ጠንካራ ሴትና ለሌሎች ደህንነት ስትል ራስዋን የምትበድል መሆንዋን፣ እንዲሁም ብዙ ሕይወት ማዳንዋን በግትት ስለእርስዋ ታላቅነት በዝርዝር ይጽፋሉ። ጋዜጦቹ ስለሞንት ታሪክዋ ግን ምንም አያውቁም። ገንዘብ ለማግኘት የምትጠቀምበትን ዘዴና የምታሳድጋቸው ልጆች በትምህርት ታንፀው እንዲያድጉ ስለምታደርገው ጥረት የተጻፈው በልዩ አቀራረብ ነበር። ከጥቂት እብሪተኞች በስተቀር የአካባቢው ሰው ሁሉ እንደ አምላክ ነበር የሚያያት። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ 'ይህቺ ሴት መልአክ እንጂ ሰው አይደለችም' እስክ ማለት ደርሰዋል።

ገንዘብ ለቸገረው ገንዘብ ትሰጣለች። የአላብ ድሃ የሆኑውን በበሰለ አላብ ትቀርጻለች፣ ትመክራለች። ተስፋ የቆረጠውን ታጽናናለች። የታመመውን ታከማለች፣ ትጠይቃለች። ቀን ላጨለመች ከብረት የጠነከረ ምርኩዝ በመሆን ቡተቃላት ሁሉ ትደግፋለች። ሰው ሲሞት በምንም ተሳምር ከቀብር አትቀርም። ለዚህ ነው እንግዲህ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩት ለሞች አከብሮት ያጎናጸፍዋት። ሥራዋ መቼም በጣም የሚደነቅ ነበር። ለልጆችማ የተለየ እንክብካቤ ነበር የምታደርገው። ሕፃናት ሁሉ የእርስዋን ፊት ሲያዩ ሰውነታቸው ይፈካል። ከጊዜ በኋላ በእርስዋ ስር የሚተዳደሩ ሕፃናትና አዋቂዎች እጅግ በረከቱ። ይህም ነው እንግዲህ በዚያ አካባቢ ስምዋ በይበልጥ ገናና እንዲሆን ያደረገው።

ስምዋ የገነነው በአገር ውስጥ ብቻ ላይሆን ከቻይና ውጭም ነበር። በዚህ የተነሳ ቁጥራቸው በዛ ያለ ሰዎች ከእርስዋ ጋር ለመሥራት ወደ ነበረችበት አገር ሄዱ። ከነአካቴው የቹሊንግ ሚስዮን በመላው ዓለም ታወቀ። ሲ/ር ማሪም በጎ ተግባርዋን በማስፋፋት ሥራው ተቀላጥፎ እንዲቀጥል ብዙ ጣረች። የሚስዮን ትምህርት ቤት አቋቋመች፣ ሆስፒታል ከፈተች። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች እንዲሆኑ አደረገች። ለዚህ ሁሉ ሥራዋ ሰዎች ገንዘብ እንዲሰጥዋት በለመነች ጊዜ ሁሉም እጁን ዘረጋላት።

በጥንት ዘመን የቻይና አገር ሰዎች እርስ በእርስ እየተጋጩ ብዙ የጭካኔ ሥራ ይሠሩ ነበር። በቹሊንግ አካባቢ ግን የዚያ ጭካኔ ሥራ

Scan by Easy Scanner

እጅግ ቀንሶ ነበር የሚታየው። በዚህም የተነሳ ከዚያ አገር ይሠሩ የነበሩ ሴሮች ያለ ፍርሃት ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር ቻሉ። አንድ ቀን ግን አጅግ ዘግናኝ የሆነ ዜና ከወደ ጁሊንግ ተሰማ። ያ ዜናም ብዙ ሰዎችን አስለቀሰ።

የሴቶች ልጆች አለመሞትና ማደግ በጅሊንግ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ጥቂት ሰዎችን አሰቆጣ። ቹሊንግ በሴት ብቻ ልትሞላ ስለሆነ ይህን መዋጋት አለብን ሲሉ እነዚያ ጥቂት ሰዎች አደሙ። ውጊያውም ከሴሮች ላይ እንዲያነጣጥር ተስማሙ። ለሴሮቹ ማስጠንቀቂያ ሰጥዋቸው። የሴት ልጅ ሕይወት ማዳናቸውን ካላቆሙ ሊገደሉ እንደሚችሉ ተነገራቸው። ሲ/ር ማሪ ማስጠንቀቂያው ሲደርሳት ሳቁች እንጂ የፍርሃት ስሜት አላሳየችም። እንዲያውም «መሞት አለብን፣ ሆኖም ግን የምንሞተው አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው። ከመሞት በሕይወት ኖሮ ሕፃናቱን መርዳት ይመረጣል» ስትል መከረች። በምክርዋም ተጠቅመው ትምህርትን በዘዴ በመቋቋም ያን መልካም ሥራ እየሠሩ ለተወሰነ ጊዜ ኖሩ።

አንድ ቀን ግን ወደ ማታ፣ ሦስት ሰዓት ገደማ ይሆናል፣ የአካባቢው ሰዎች ሦስት ሴት ሕፃናትን ከወንዝ ውስጥ ለመጣል መዘጋጀታቸውን ይሰማሉ። ስለዚህ ልጆቹን ለማዳን ሲ/ር ማሪና ሌሎች ሁለት ሴሮች ፈጥነው ወደ ወንዙ ወረዱ። ከወንዙ ሲደርሱ ጨረቃ ሙሉ ብርሃንዋን የሰጠችበት እለት ስለነበር ሴሮቹ በሩቁ የሚታይ አንድ ነገር ተመለከቱ። ብዙም ሳይቆይ የሕፃን ልጅ ልቅሶ ሰሙ። የሕፃን ልቅሶ ወደ ተሰማበት ሲያቅኑ ሦስቱ ሕፃናት በጨርቅ ተጠቅልለው ከቀርከሃ በተሠራ መቀመጫ ላይ ተንሳፍፈው አይዋቸው።

ሕፃናቱ ከዚያ ሥፍራ ከቆዩ ማዕበል መዋቱ ወደ ወንዙ መሃል ይዞአቸው እንደሚሄድ አወቁ። ደግነቱ ሕፃናቱ ከእይታ ከመሰወራቸው በፊት እህሲስተር ማሪ ደረሱላቸው። ተቀምጠውበት የነበረውን መቀመጫ ቀሰ ብለው በረጅም ቀርከሃ እነርሱ ወደ ነበሩበት ሥፍራ ስለጎተቱት ልጆቹን ለማዳናት ቻሉ። ነገር ግን በአካባቢው መሸግው ተቀምጠው የነበሩ ጦረኞች ብቅ አሉ። ወዲያው ጦረኞቹና ሴሮቹ ግብግብ ገጠሙ። በቅድሚያ ሁለቱ ሴሮች ይዘዋቸው የነበሩትን ሕፃናት ተጥተው ከወንዙ ውስጥ ወረወርዋቸው። ሲስተር ማሪ ግን የያዘችውን ሕፃን አልለቅም ብላ ብዙ ታገለች።

«የያዝሻትን ሕፃን ለወንዙ ገብሪ» ሲል አንዱ ጮኸባት። «ይህን ካደረግሽ ምንም አናደርግሽም። ቋንቋችን ስለምትናገሪና ከሕዝባችን ጋር አብረሽ ስለምትኖሪ በአንቺ ላይ ጉዳት እንዲደርስ እንፈልግም። እኛ እንደምናከብርሽ አንቺም ባህላችንና ሕጋችንን አክብሪ። ማህበረሰባችን የሚሠራውን የማያውቅ አይምሰልሽ። በእናንተ ምክንያት አገራችን በሴት ልጅ ልትወረር ነው። ድርጊታችሁ በዚህ ከቀጠለና ሴቶች ልጆች ሁሉ በሕይወት ከኖሩ ረሃብ ገብቶ ሁላችንም እናልቃለን። ይህ እንዲሆን ደግሞ እኛ አንፈቅድም። ስለዚህ አሁን ሕፃንዋን ስጪንና ወደ ወንዙ እንወርውራት። ይህን ካደረግሽ በሰላም ወደ ቤታችሁ ትመለሳላችሁ። ሥራሽ ጥሩ ስለሆነ በአንቺ ላይ ክፉ ነገር እንዲደርስ አንፈልግም» አልዋት።

ሲ/ር ማሪ ግን ያቀፈቻትንና የምታለቅሰዋን ሕፃን አሳልፋ ለመስጠት ፈቃደኛ ስላልሆነች በእምነትዋ አናኙ። እንዲያውም ሕፃንዋን አጥብቃ ይዛ በፍርሃት የተዋጡትን ሁለቱን ሴሮች አጽናንታ እነርሱ ሚስዮኑ ካለበት ሂደው እርዳታ እንዲጠይቁ አዘዘቻቸው። ሴሮቹ እነዚያን አረመኔዎች ሊያሸንፉ የሚችሉ ሰዎች ይዘው ሲደርሱ ሁሉም በተለያየ አቅጣጫ ለመሸሽ በሩጫ ፈረጠጡ። ሲስተር ማሪ የሞተችዋን ሕፃን እንደ ታቀፈች ከመሬት ወድቃ አይዋት። ለካስ ከጡትዋ ስር በጨቢ ተወግታ ኖሮ ሕይወትዋ አልፎአል። ነገር ግን ምንም እንኳን ሕይወትዋ ቢያልፍም ፈገግታዋ ከፊትዋ አልጠፋም።

አጆችዋና ክንድዋ ላይ የነበሩት ቁስሎች ሕፃንዋን ለማዳን ለመታገልዋ ምስክሮች ሆኑ። ከሞተች በኋላ እንኳን ፈገግታዋ ባለመጥፋቱ ሰዎች ያንን ሲያዩ ሁሉም በአምላ ተራጩ። አጅግ ስላሳዘኑቻቸው አምርረው አለቀሱላት። ከዚያም ሞቶ መቀበር የግድ ነውና ከሚስዮኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ቀበርዋት። ታሪክዋን የሚያውቅ ስላልነበረ ክስምዋ 'ከሲስተር ማሪ' በስተቀር ከመቃብርዋ ላይ የተጻፈ ሌላ ነገር አልነበረም። እስከ ዛሬ የሲ/ር ማሪ ስም በቅድስትነቱ ይነሳል። ለእነዚያ እንደ አነሲስተር ማሪ ላሉት ሴሮች ምስጋና ይግባውና ያ ጨካኝ ባህልም ከጊዜ በኋላ እየጠፋ ሄዶ ሴቶች ሕፃናት ወንዝ ውስጥ ከመጣል ዳኑ።

ይህን ታሪክ ካነበባችሁ በኋላ ማንኛችሁ ናችሁ በዚህች ሴት ላይ የምትፈርዱ? ድንጋይ ቢሰጣችሁ የትኛችሁ ናችሁ ያንን ድንጋይ ከመቃብርዋ ላይ የምትወረውሩ? ከወረወራችሁባትም ምፅዓት አስኪደርስ ያቺ ቆንጆ ከዚያው መቃብር ውስጥ ትተኛለች።

ራስዋን ለሕፃን ልጅ መሰዋእት ስላደረገች ቆንጆ ሴት በተለያየ መልኩ ታሪክ ተጽፎበታል። ያቺ ሴት በውበትዋ አገር ያደነቃት የሊንዋ እመቤት

Scan by Easy Scanner

ቪቫን መሆንዋን ማንም አላወቀም። እርስዋ መሆንዋን የሚያውቅ ግን አንድ ሰው ነበረ። እርሱም ሰር ልዮኔል ራይዳል ነው። አንድ ቀን ሰር ልዮኔል ራይዳል ደንዎልድ ከሚገኘው ቤቱ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሳለ ጋዚጣ ይመጣለታል። ልጆቹም ከቤቱ ውስጥ ነበሩ። ኤሊኖር ሰር ልዮኔል ከነበረበት ከፍል ስትገባ ባልዋ ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ቀብሮና ጠረጴዛ ተደግፎ ሲንበቀበቅ አየችው። እምባው ከጠረጴዛው ላይ ወርዶ ውሃ የፈሰሰ አስመስሎታል።

ከዚያ በኋላ ምስጢሩን ለመደበቅ አቅም ሰላነሰው ሆኖ ውስጥ አምቆ ያስቀረውን የቪቫን ታሪክ አንዱንም ሳያስቀር ለኤሊኖር ነገራት። ታሪካቸውን እንዳይናገር የተማጠነችው ሴት አሁን በሕይወት የለችም፣ ሞታለች። ስለዚህ በዚያች ሰዓት ሊያደርግላት የሚችለው ንጽህናዋንና ታላቅነትዋን ለማያውቁ ማሳወቅ ነበር።

ኤሊኖር ውብ የሆነ ሙዚቃ በሕልሙ እንደሚያደምጥ ሰው ዝም ብላ ሰማችው። ታሪኩን ሲጨርስ «ልዮኔል ምን ያህል እንደ ተሰቃየች አስበው» አለችው። አብረው በኖሩበት ዘመን የተናገረችውን ሁሉ አስታወሰች። እያንዳንዱን ነገር ባስታወሰች ቁጥር ሲ/ር ማሪ የተናገረችው ሁሉ ትርጉም እንደ ነበረው ኤሊኖር ገና አሁን ገባት።

ሰር ልዮኔል ከልጆቹና ከሚስቱ ጋር ደስ ብሎት ኖረ። ሆኖም ግን ሞቶ አፈር እስከ ተጫነው ድረስ ቪቫንን አልረሳትም። ያ በህዘን የቆሰለውና ለውበቱ ወደር ያማይገኝለት የቪቫን ፊት ዘውትር ከህሊናው ውስጥ በአሳብ እያየ አስታወሳት። የመስቀሉን ነገር ቢሰማማ ቁርሰን፣ ምሳውንና እራቱን በበላ ቁጥር ባስታወሳት፣ ቪቫን ሞታ ሴቶች ሲገንዝዋት ከአንጨት የተሠራና የደረቀ አበባ ምስል የተቀረጸበት መስቀል ከአንገትዋ ስር ተንጠልጥሎ አግኝተዋል። ከመስቀሉ ላይ 'ልዮኔል' የሚል ጽሑፍ ተቋፎበታል። በመጀመሪያ ሲገናኙ ልዮኔል የሰጣት መስቀል ነበር።

መስቀሉ አብሮአት ተቀብሮ እንጂ ከአንገትዋ አልወለቀም። «ኃጥያትዋ ህሊናዋ ታውሮ የፈጸመችው ስለሆነ ከይቅርታ በላይ ነው» ብሎ ዓለም ሁሉ ፈረደባት። ብዙ ጊዜ ግን የእግዚአብሔር ፍርድ ከሰዎች ፍርድ ጋር አይጣጣምም። «አትፍረድ እንዳይፈረድብህ»

መደምደሚያ

ልዮኔል 'ግድ የለም፣ ለአንድ ሰሞን ነው' በሚል አመለካከት ይመስላል ከቪቫን ጋር ግኙኝነት ጀመረ። የፍቅርዋን ጽናት በመግንዘብም ማድረግ ከሚገባው በላይ ቀረባት። የኋላ ኋላ ግን ግጣፊያው እጥሮት ከእርስዋ ለመራቅ ስላልቻለ የሚስቱን፣ የልጆቹንና የራሱን ሕይወት አበላሸ። ቪቫን ከለጋነት እድሜ ባሻገር ብልጭልጭ ነገር አታሎአት ከማይሆን ጋብቻ ውስጥ ተዘፈቀች። ከዚያ ከማይመጣጠንና ካልተባረከ ትዳር ለመላቀቅም የማይሆን እርምጃ ወሰደች። በዚህም የራስዋን ሕይወት አበላሽታ ለሌሎች ሰዎች ሕይወት መበላሸትም ምክንያት ሆነች። በስዚህ በሕይወት ዘመናችን የምንወስዳቸው እርምጃዎች በህሊና ዳኝነት መታገዝ እንዳለባቸው ይህ ታሪክ ትምህርት እንደሰጠን አተማመናለሁ።

ጋብቻ ከቡር ስለሆነ 'ለአንድ ሰሞን' በሚል ፊሊቃ የሚያበላሹት ጉዳይ አይደለም። 'ለአንድ ሰሞን' ብሎ ከማይሆን ነገር ውስጥ መዘፈቅ የሞቀ ትዳርን ሊያፈርስ ይችላል። ይህም ከእድሜ ልክ ጸጸት ውስጥ ይጨምራል። የዚህ ዓይነት አመለካከት የፈለጉትን ነገር ለማግኘት ሲባል የሚደረግ ራስን የማታለል ዘይቤ ነው። የማይሆነውን ጨብጠ ለመደሰት ከመሞከር የሚሆነውን መፈለግ ጨዋ ያስብላል። የደረሰውን ጥፋት ለማረም በሚደረግ ጥረትም ከባስ ጥፋት ውስጥ እንዳይወድቁ ማስተዋል እዋቂ ያሰኛል። አስቱውሉ መራመድም የራስን ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሕይወት ከማበላሸት ያድናል።

ቪቫን እግር አውጥታ ሕይወትዋን አበላሽች። ባል ወይም ሚስት እግር ማውጣት ካበዙ፣ ያለ ምክንያት የሚሆን ነገር የለምና 'ከቤት ያጡትን ለማግኘት ይሆን እግር ያወጡት?' ብሎ ራስን መጠየቅ ያስፈልጋል። ዋናው ነገር ደግሞ በእለት ተእለት ሕይወት የትዳር ጓደኛን የሚያስከፉ ነገሮችን በጥሞና መከታተል ነው። ሰምሳሌ ሳያስቡ መናገር ለወር የሚያስኮርፍ ወይም ከቤት የሚያርቅ ሁናቴን ሊፈጥር ይችላል። የትዳር ጓደኛን የሚያስቆጣ ወይም የሚያስደስት ነገር ወይም የፍቅር ጨዋታንና የፍቅርን ምንነት አለማወቅ፣ ተገቢውን ክብር ለትዳር ጓደኛ አለመስጠት፣ የቤ ተሰብ ኩተት ማብዛት፣ ትህትናን አርቆ ከእኔ ወዲያ ማለት፣ ከመጠን በላይ ቁጥጥር አብዝቶ አልባ ውስጥ ማስገባት፣ ባል ካገቡ በኋላ የሴቶች ራሳቸውን መጣል፣ ራስን ከመጠን በላይ መውደድ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች አለማገናዘብና ሌሎችም ምክንያቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ መጠንቀቁ ይበጃል። ይህም ከህሊና ወቃሳም ያድናል።

Scan by Easy Scanner

ስለሀሊና ካነሳን፣ ሀሊና እግዚአብሔር የሰጠን ትልቁ ዐጋ መሆኑን እየረሳን ከስህተት ላይ እንወድቃለን። የተሳሳተ መንገድ ይዘን ስንጓዝ 'ተው አይሆንም' እያለ ሀሊናችን ይመክረናል። እርሱ የሚነግረንን ካልሰማን ሰው መሆናችንን ረስተን እኛነታችንን ከእንስሳ ደረጃ አወረድን እንጂ ብልጥ ወይም አዋቂ የሆን አይምሰለን። ከእንስሳ የምንለየው በሀሊናችን ስለምንጠቀም በመሆኑ ሰጊዚያዊ ጥቅም ብለን ራሳችንን አናዋርድ።

ዛሬ ለግል ጥቅምና ለፍቅረ-ንዋይ ማደሩ እንደ ትልቅ ጉብዝናና ሙያ ከሚቆጠርበት ጊዜ ደርሰናል። ብዙ ገንዘብ ማግኘት፣ በተላይም አወጣጡን ካላወቁበት፣ ትርፉ ብዙ መብላት፣ ብዙ መጠጣት ሲሆን የዚህም ውጤት 'አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል' ይሆናል። ሰው ለሆዱ ሲል እንዴት ብሎ ይዋሻል፣ እንዴትስ ብሎ ይሰርቃል፣ ያላግባብ የተገኘ ገንዘብ ያላግባብ ስለሚያጠፉትና ከማይሆን ቦታም ስለሚወስድ በሽታ ያሸምታል። ከዚያም አልፎ ሕይወትን ያሳጣል። ደግሞም የደም ገንዘብ ስለሆነ ዘርማ ዘር ይተላለቅበታል። ታዲያ ትርፉ ምኑ ላይ ነው፤ ስለዚህ እናንተ ስም አይጠሪምች አገራችሁ ኬክ ብትሆንላችሁ፣ ለሌላው ምንም ሳታስተርፉ፣ ጨርሳችሁ አትብሏት። አሁን እንኳን አድሜ ለዶ/ር አብይ መንገዱን የዘጋባችሁ ይመስላል። የወያኔ ርዝራዞች ግን አሁንም በይሉኝታቢስነት ባህሪያቸው እየተጠቀሙ በዝርፊያው ቀጥለውበታው። የቀን ጉዳይ ነው እንጂ እነርሱም እንደሚጋለጡ አልጠራጠርም።

ይሉኝታቢስነት፣ ሌብነትና ውሸት ሀሊናን ከመሸጥ የሚገኙ ርካሽ ባህርዮች ሲሆኑ ራስንም የማዋረድ ምልክቶች ናቸውና እንወቅበት። ዛሬ በየመንገዱና በየመሥሪያ ቤቱ የሚታዩ ሀሊናቸውን የሸጡ ሰዎች መብዛት የማህበረሰብ መዝቀጥና የእገር መውደቅ ምልክቶች ናቸው። የዘመኑ ትልቁ በሽታ ሀሊናና ይሉኝታ ማጣት እንደሆነ ማንም የሚክደው አይደለም። በእሁኑ ጊዜ ስለመሰናኘ፣ ስለኪራይ ሰብሳቢነትና ስለመልካም አስተዳደር ብዙ ይወራል፣ ብዙ ይለፈፋል። እነዚህ ሁሉ ወያኔ ያስታሰቀፈን የሀሊና ማጣት ውጤቶች ስለሆኑ እባካችሁ የእለት ተእለት ሕይወታችንን በሀሊና ጻኝነት እየመራን ማህበረሰባችንንና አገራችንን ከውድቀት እናድን። አገራችን ውስጥ ሰውን እንደ ሰው ማየት ያልቻሉና ራሳቸውም ገና ሰው ያልሆኑ ቁጥራቸው የበዛ ሰው-መሰል ፍጡሮች ለመኖራቸው አይካድም። እነዚህ ሰው-መሰል ፍጡሮች በብዛት የተፈለፈሉት በዘመነ-ደርግና በዘመነ-ሕዋህት ሲሆን በተለይም ቅጥ ባጣውና አቅደቢስ በሆነው በሕዋህት ዘመነ-መንግሥት የኖሩት እነዚህ ሰው-መሰል ፍጡሮች የተንሰራፉትና ወያኔም ሆን ብሎ የኩተኩታቸው ናቸው። ስዚህም እቡይ ባህርይ በጊዜው

ሶበሩ በለሥልጣናት የፈጠሩት ሥርዓተ-ትምህርትና የሃይማኖት ተቋሞች መዛቱጥና የኩሣ ፖለቲካ መስፈን አስተዋጽዖ አድርገዋል።

ቤተሰብን እንዲመራ፣ ከቀበሌ እስከ አገር እንዲያስተዳድርና እንዲጠብቅ፣ የእለት ተእለት ሥራ እንዲያከናውን አደራ የተጣለበት ሁሉ ጋላፊነቱን ዘንግቶ ለግል ጥቅምና ለሥጋ ፍላጎት ከተሯሯጠ፣ ነጋዴ በመቶ ብር የገዛውን እቃ በሺህ ብር ከሸጠ፣ ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰው ሥጋ ከበሉና ከሙ፣ ሰዎች ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ላይ ተንኰል ከሸረቡ፣ ትንሹትንና ደግነትን አንግበው ወንድማቸውን እንደ ራሳቸው ለመውደድ ሳይችሉ ከቀሩና ኅሊናቸውን ከሸጡ የእነዚያ ሰዎች ቤተክርስቲያን ወይም መስጊድ ሄዶ መጸለይም ሆነ መስገድ ብዙም ዋጋ አልሰጠውም። ቤተ ክርስቲያን ወይም መስጊድ የመሄዱ፣ የያዎና የስግደቱ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ እኔ ትርጉም ያለው ሕይወት ብዬ የምጠራው የእለት ተእለት ሕይወት በኅሊና ጻኝነት በተገቢው መንገድ ሲመራና ከፍ ብለው የተጠቀሱትን መለኢም ነው። ኢባካችሁ ትኖንችም ሆነ ዛሬ ኢትዮጵያን ለማልማት ሳይሆን ለማጥፋት ታጥቆ የተነሳው ወያኔ ያስታቀፈንን ይሉኝታቢስነት፣ ሌብነትና ውሸት አሽቀንጥረን ከመጣል ወደ ኋላ እንበል። ኑሮአችንን በሀሊና ጻኝነት እንመራ። ስለሀሊና በተደጋጋሚ በተለያዩ ጽሑፎቼ ውስጥ የምጽፈው የጉዳዩን አሳሳቢነት ለመግለጥ ስለሆነ አትሰልቹኝ። ለዛሬው በዚሁ እናቁም።

አስተያየት

ከዛሬ አሥራ ሰድስት ዓመት በፊት ይህን መጽሐፍ ትርጉሜ ሰጨርስ ለባለቤቴ አባት ለመልአከ-ኀኑት ጋሻው ሚፈኛ ሳሳያቸው በቅድሚያ ዓይናቸው ያረፈው ከመጽሐፉ ርእስ ላይ ነበር። «ርእሱ ከመጽሐፉ ፍሬ አሳብ ጋር ይጣጣማል?» ብለው ሲጠይቁኝ መጣጣሙን አረጋገጥኩላቸው። 'በጣም ጥሩ ርእስ ነው፤ አንድ ቅጂ ስጠኝና ላንብበው' አሉኝ፤ እኔም በጠኋቸው። መጽሐፉን አንብበው ሲጨርሱ፤ እኔ ሳልጠይቃቸው፤ ቀጥሎ ያለውን አስተያየት ሰጡኝ።

ልዮኤል በህብትም ሆነ በተክለ-ሰውነት ከማንም የማያንስ ቢሆንም የዋህነትና ገርነት ያጠቃው ሰው ሲሆን ቂልነትም አሳጣውም ለማለት ይቻላል። ቪቫን በተክለ-ሰውነቱ ተማርካ ወደደችው። የሌኑ ክበርቴም በመጠኑ-ሰፊ ሀብታቸው ተመክተውና በጌጣጌጥ አባብለው አግብት። ጋብቻቸው ግን 'ያላቻ ጋብቻ» ስለነበር በሁለቱ መካከል የሀሊና ሚዛን አልነበረም። የዚህም ውጤት ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ እንደ ተነገረው

Scan by Easy Scanner

'በእርጌ ጨርቅ ላይ አዲስ ዕራፊ ቢለጠፍበት ጨርቁ እንደሚቀደድ ወይም በአሮጌ አቁማዳ ወይም ዕርካት አዲስ ጠጅ ቢጨምሩበት እንደሚፈነዳ' ባለማጤን ከበርቴው ሊን ቆንጆዪቱ ቪቫንን በሐር፣ በወርቅና በልዩ ልዩ ጌጣጌጥ እንድታንፀባርቅ አደረጉ። ቪቫን እንኳን አስጊጠዋት እንዲሁም በጣም ቆንጆ ስለነበረች ወንዶችን ሁሉ አሳበደች።

የዋሁና ሞኙ ልዮኤልም ከዚሁ ወጥመድ ውስጥ ጥልቅ ካሉት ወንዶች መካከል ቀንደኛው ነው። እዚህ ላይ የሚታየው የእርሱ እርሷን ማፍቀር ብቻ ሳይሆን ከእነዚያ ጉብል ወንዶች መካከል ሊመረጥ መጣጅቱን ለማጽደቅ ይመስላል ከቪቫን ጋር ለመቅበጥና ለመክነፍ የወሰነው። ልዮኤል ቤተሰቡንና ንብረቱን ጥሎ ከቆንጆዪቱ ቪቫን ጋር በኩባለለበት ሰዓት የተደበቀ ምሥጢር ሳይታሰብ በድንገት ገሃድ ወጣ። ልዮኤል ትዳር ያለው ሰው ሆኖ ሳለ እንዴት ብሎ ሊዳብቃት እንደቻለ ስትጠይቀው ፍቅርዋን እንዳያጣ ያደረገው መሆኑን ነገራት። ይህን ጊዜ ነው ቪቫን የሰው ትዳር በማፍረስዋ ከፍተኛ የሆነ ጸጸት ያደረባትና ኃጥያት መፈጸምዋን ያወቀችው። ለፈጸመችው ኃጥያትና ላደረሰቸው በደል ቤዛ እንዲሆናትም መነኰሰች። በሐሩ፣ በወርቁና በጌጣጌጡ ፈንታ ጥቁር ልብስ ለበሰች። ለአገልግሎት የሚያበቃ የነርስነት ትምህርትም ተማረች። ስምዋንም ቀየረች። መሳሳት የሚያስነቅፍ ቢሆንም ጥፋትን አውቆ ንስሐ መግባትና ዋጋ የማያስከፍል የጸጸት እርምጃ መውሰድ ደግሞ የሰው ብቻ ሳይሆን የፈጣሪንም ይቅርታ ያሰገኛል። ቪቫንም ያደረገችው ይኸው ሲሆን 'ህሊና ሲታወር' የተሰኘውም መጽሐፍ ይህንኑ ያስተምረናል።

የእምላክ ጥበብ ረቂቅ በመሆኑ የልዮኤል ባለቤትና ልጅ በታመሙ ጊዜ ቪቫን ልትረዳቸው ከቤታቸው ገባች። የቀድሞዋ ኃጥያተኛ የአሁንዋ እማሆይ ታማኝና እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት በመሆን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ስለረዳቻቸው ሕይወታቸው ዳነ። ኤሊኖርም 'እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለያየው አይችልም' በሚል እምነትዋ ሰለዘናጭና ለባልዋም ይቅርታን ስላወረደች የኋላ ኋላ የደስታ ሕይወት አገኘች። ቪቫን ግን ባና ከመነሻው ለዚህ ዓለም ተድላና ደስታ ስላልተፈጠረች ሕይወትዋን መስዋዕት እስከ ሚድረግ ብዙ ብትሰቃይም በበጎ ተግባርዋ የማይልፈውን የዘላለም ሕይወት አገኘች። ያቺ የቀድሞዋ ኃጥዕት የአሁንዋ እማሆይ ሚና ለሴቶች ልጆች ስትታገል ሕይወትዋ አልፎአል። የሕይወት ታሪኳ ከመቃብርዋ ድንጋይ ላይ ባይጻፍም እድሜ ለደራሲያንና ለተርጓሚዎች የዚህች ብዕዕት ታሪክ በዚህ መጽሐፍ አማካይነት ከአንባብያን ልብ ውስጥ

ተቀርጾ ሊኖበብ በቅቷል። ይህም ለእኛ ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ በመሆኑ 'ህሊና ሲታወርን' በጥሞና ማንበብ ከእንባቢ የሚጠበቅ ይሆናል።

ሌላው መረሳት የሌለበት መጽሐፉ የሆኅያትን አገባብ የጠበቀ መሆኑ ነው። ሊቃውንት ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸው ሦስት 'ሀ፣ሐ፣ኀ' ሁለት 'ሰ፣ሠ' እንዲሁም ሁለት 'ፀ፣ጸ' ከግዕዝና ከአማርኛ ፊደላት ውስጥ ያካተቱት ያለ ምክንያት ስላልሆነ ተማሪዎች ከዚህ መጽሐፍ ስለሆኅያት አገባብ ትምህርት ሊቀስሙበት ይችላሉ። ይህ መጽሐፍ በምርጥ የአማርኛ ቃላት ተቀነባብሮ የቀረበ በመሆኑ የእያንዳንዱ አንባቢ ዓይን በመስመሩ ላይ ከተተከለ በቀላሉ የማይነቀል ሐሳብን የሚመስጥ ሆኖ መገኘቱን አንባቢ ሁሉ ሊረዳው ይገባል።

መልአከ-ገነት ኃሻው ማፈኛ በላቸው



መልአከ-ገነት ኃሻው ማፈኛ በላቸው የቅኔ፣ የዚማ፣ የድጓና በሌሳም የቤተክርስቲያን ትምህርት የታወቁ ሊቅ ነበሩ። ይህንንም የምሰው ተወዳጅ ልጃቸውን ስለሰጡኝ ሳይሆን ትክክለኛና እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ሰው ስለነበሩ ነው። መልአከ-ገነት ኃሻው ማፈኛ ፈረሃ-እግዚአብሄር ያደረባቸው፣ የሚናገሩትን ያከበሩ፣ የሚሰብኩትን የኖሩ፣ የተማሩትን ሁሉ በትክክል ተግባር ላይ ያዋሉ ታላቅ የእግዚአብሄር ሰው እንደነበሩ እኔ ብቻ ሳልሆን በቤተክህነት አካባቢ፣ በተለይም ሐረርጌ ክፍለ-ሀገር ውስጥ የኖሩና ያሉ ሊቃነ-ጳጳሳትና ካህናት በገሃድ የተናገሩትና የሚናገሩት ነው። መልአከ-ገነት ኃሻው በእንድ ወቅት የሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ቤተክህነት ሥራ አስኪያጅ፣ የቁልቢ ገብርኤል ገዳምና የሐረር መድሐኒዓለም ብተክርስቲያን አስተዳዳሪ ሁነው አገልግለዋል። ቀደም ሲልም ትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ በአስተማሪነትና በተለያየ የኃላፊነት ደረጃ ሠርተዋል።

ተፈጸመ

Scan by Easy Scanner

ገበያ ላይ ያሉና የሌሉ ሌሎች የተርጓሚው ሥራዎች

'ምንጹቢን' ፍልስፍና ነው። 'ኑሮ በዘዴ' እና 'መንግሥትና ሕዝብ' እንዲሁ በመጠኑንም ቢሆን የፍልስፍና ባሕርይ አሳቸው። በሕይወት ሕይወትን ለማወቅ ለለሕይወት መፈላሰፍ፣ መመራመርና እውቀትን መሻት ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ግዴታ ሲሆን እንዳንዲም ከፍልስፍና ወጣ ብሎ የሚያዝናኑ ጽሑፎችን ማንበብ የመንፈስ ምግብ ስለሚሆኑ እነዚያንም ማንበብ የሚደገፍ ነው። ለዚህም ነው ከጎሊና ሲታወር በፊትና በኋላ ያዝናናሉ ብዬ የገመትኳቸውን 'የውበት ወጣመድ' እና 'ከመኒ'ን የተረጉምኩት። 'ምንጹቢን'፣ 'ከመኒ' እና 'መንግሥትና ሕዝብ' የተሰኙት መጻሕፍት ገበያ ላይ ስላሉ እንድታነቧቸው እጋብዛለሁ። በተለይ 'መንግሥትና ሕዝብ' የአስተዳደር ፍልስፍናና ታሪክ-ነክ ስለሆነ እውቀትን ያዳብራል የሚል ግምት አለኝ።

ሀ. ምንጹቢን

የመጽሐፉ ዋና ተዋናይ የሆነው ዣን ቫልጃ የሰው ሴቅ ሰብሮ ዳቦ በመስረቁ ቢታወርም በተደጋጋሚ ከእስር ቤት አምልጠ ሲወጣ ለማኅበረ-ሰብ የነበረው አመለካከት ጭካኔ የተሞላበት ቢሆንም በአጋጣሚ የተገናኛቸው ቅዳስ ዣን ቫልጃን ከአውሬነት ባህርይ ወደ ሰውነት ይመልሱታል። እርሱም በተራው የጉቬርን ግትርነት ቀይሮ ከመሞቱ በፊት እንዲፀፀትና ሕይወት በሕግ ብቻ ሳይሆን በሰብዓዊነትና በግብረገባዊነት ጭምር መመራት እንዳለበት እንዲያውቅ አድርጎታል። ሕግ፣ ሰብዓዊነትና ግብረገባዊነት ለሕይወት አስፈላጊዎች ሲሆኑ እነዚህ ነገሮች እርስ በእርስ ካልተደጋገፉ ሕይወት የተሟላች አትሆንም። ዮ'ምንጹቢን' ዋናው መልእክትም ይኸው ነው።

በዚህ ልብ እንጠልላይ ታሪክ ውስጥ ስለፈረንሳይ አብዮት ይወሳል። የፈረንሳይ አብዮት በተቀጣጠለበት ወቅት በነበረው የተዛባ ሥርዓት የተነሳ ይፈጸም የነበረውን ፍርደ-ገምድለነት ገሃድ አውጥቶ ሰዎች መመራት ያለባቸው ራሳቸው በደነገጉት ሕግ ብቻ ሳይሆን በጎሊና ዳኝነትም ጭምር እንደሆነ ይገልጻል። በመካከሉ ስለፍትር፣ ስለኑሮ ውጣ ውረድ፣ ስለሰዎች ጭካኔ፣ ስለስብዓዊ ኩብርና ስለመሳለሉት ነገሮች መጽሐፉ ሙስጥ ይተረካል። ዋናው ተዋናይ ዣን ቫልጃ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ጭምር ኖሮ በአሳዛኝ መልኩ ሞቶ ይቀበራል።

ለ. መንግሥትና ሕዝብ

ይህ መጽሐፍ የሚያተኩረው ከአስተዳደር ሥርዓት ላይ ሲሆን እግረመንገዱን ስለተለያዩ ታሪካዊ ሁነቶችም ያወሳል። የመጽሐፉ መሠረታዊ ዓላማ መልካም አስተዳደር ላይ ተመርኩዞ የዘመኑ የሳይንስ ጥብብ ያፈራቸው መልካም ነገሮች የጥቂቶች መገልገያ መሆናቸው ቀርቶ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲዳረሱ ምን መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብና ለማመላከት ነው። ለዚህም ሰዎች በዘር ሐረጋቸው ሳይሆን ሰው በመሆናቸቸው ብቻ በእኩልነት እንዲታዩ አድልዖ የተለየው የአስተዳደር ሥርዓት እንድሚያስፈልግ መጽሐፉ ያትታል። ከመጽሐፉ ውስጥ የተነባረውን ልጥቀስ፦

«ነፃነት የተለየው ሕይወት እርባነቢስ መሆኑን ስለምገነዘብ ሕይወታችንን ከሚያበላሹና ነፃነታችንን ከሚገድቡ አጥቂዎች እንድንከላከል ተፈጥሮ ራሱ ያስገደደናል። በራዎች አንበሳን የሚፈሩት፣ ወሾች ተኩላን የሚጠሉት፣ አይጦች ከድመት የሚርቁት የነፃነታቸውና የሕይወታቸው ፀሮች እንደሆኑ ስለሚያውቁ ነው። ስለዚህ እንደ ሕወሀት ያለ የሰው መብትንና ነፃነትን የሚገፍ ማንኛውም አመራር በስሜት እንድንጠላው ያስፈልጋል።»

'መንግሥትና ሕዝብ' እንደ ሕወሀት ያሉ ጨቋኝ ገዢዎች የተከተሉትን ርኩስ ያስተዳደር ዘይቤዎችንና መመሪያዎች፣ እንዲሁም ቅን ገዢዎች፣ እንደ አኔዶር አብይ ያሉ ልበል መሰለኝ፣ የሚጠቀሙበት የተቀደሰ የአስተዳደር ሥርዓትን ለማሳየት ይሞክራል። ሰለጉዳዩም እነአሪስቶትል፣ ፕሌቶ፣ ማክያቬሊ፣ ሽርሃም፣ ጆን ሃና፣ ዣን ቦዳና ሌሎችም ፈላስፎችና ምሁራን ያሉትን ያሣትሳል። በሌላ በኩልም አገር በቀል የሆኑ እንደ የጅከና የገዳ ሥርዓት ያሉት የመልካም አስተዳደር ሥርዓቶችን በምሳሌነት ያቀርባል። አንድ አገር ስለሚመሠረው የመሻሻል ፍላጎቶችና እንቅፋቶችም እሳብ ይሰነዝራል። ለዚህም በምሳሌነት ስለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደካማና ጠንካራ ጉን፣ ስለግርማዊነታቸው አወዳደቅ በተለይም ከመልጣን በተወገዱበት አለት ስለነበረው ሁናቴ የጓይን ምስክርነት፣ ስለእስር ቤት ሕይወታቸውና ስለአሟሟታቸው በዝርዝር ይገልጻል።

ስለለውጥ ዋዜማ፣ የአድማ ምልክቶችና ምክንያቶቹም 'መንግሥትና ሕዝብ' የሚለው አለው። የታሳቁ ፈላስፋና ደራሲ ከሊል ጊብራን

Scan by Easy Scanner

ጥቅሶችም በብዛት ተካትተዋል። በመጨረሻም ስለኅሊና ዳኝነትና ራስን ስለመምራት አሳብ ያካፍላልና መጽሐፉ እውታችን ያዳብራል የሚል እምነት ስላለኝ ገበያ ላይ አለና 'ከኅሊና ሲታወር' ቀጥላችሁ ብታነቡት ይጠቅማል ብዬ አገምታለሁ።

ሐ. 'ከመኒ'

«ከመኒ ሚስት ያለው እርሱም ከመኒ ነው፣ ከለው ሠርግ አይሄድም ከቤቱ ወርግ ነው። አሳዛ ሚስት ያለው እርሱም አሳዛ ነው፣ ከሰው ልቅሶ አይሄድም ከቤቱ ለቅሶ ነው።» መጽሐፉ ውስጥ የተነገረ ጥቅስ ነው።

የሚስማማ፣ የሚወዱትና የሚመች ማለት 'ከመኒ' የሆነ/የሆነች የትዳር ጓደኛ ለማግኘት ብዙ ያንከራትታል፣ ያለፋል፣ ያሰቃያልም። ስለዚያ ውጣ ውረድና ሰለሰው የተለያየ ባሕርይ 'ከመኒ'

አጉልቶ ያሳያል። የያታ ግኑኝነትን በተመለከተ የምዕራባውያን ባህል ምን ያህል እንደ ሀቀጠ የመጽሐፉ ደራሲ ዳንኤል አስቲል በሚገባ ታሳየናለች። ያ አጉል ባህል እኛም አገር እየገባ ስለሆነ መጠንቀቅ እንዳለብን ከ'ከመኒ' መማር የምንችል ይመስለኛል።

በ'ከመኒ' መጽሐፍ እንደ ተገለጸውነ የአንዲት ሴት ባል ሌላ ሴት ወድዶ ውድ ባለቤቱን ጥሎ ይሄዳል። ይህቺ ሴት መልካም ግለት ከመኒ የሆነ ባል ለማግኘት በምትታገልበት ጊዜ ስለሚገጥማት ስቃይ፣ መከራ፣ ውጣ ውረድና አመኔታ ማጣት በመጽሐፉ ውስጥ በሰፊው የተገለጠ ሲሆን ያም ከአሁን ታሁን ምን ሆነ፣ ምን ደረሰ በሚል ልብ ይሰቅላል። የሚመኙትን የትዳር ጓደኛ ለማግኘት በሚደረግ ጉዞ አንባቢ ትምህርት ያገኝበታል/ታገኝበታለች የሚል እምነት አለኝና 'ከመኒንም' አንድታነቡ አጋበዛለሁ።

ዮሐንስ ገብረ ጻድቅ

ያማርኛ ያለህ!

'እሪ በይ አገሬ' አሉ የታንዛንያው ፕሬዚዳንት ጁልየስ ኔሬሬ፣ እኔ ደግሞ 'እሪ በይ አማርኛዬ' ብዬ ልጨኽህ ይሁን! አሳስቦ። ይህ ርዕሰ ራሱን ችሎ መጽሐፍ የሚያጽፍ ቢሆንም በእኔ በኩል ግን ያን ለማድረግ አትሙ፣ እውቀቱና ችሎታው የለኝም። ቢሆንም በተገኘው አጋጣሚ ተጠቅሞ አሳብ መወርወሩ አይከፋም። የተሊያዩና የተራራቁ አሳቦችን 'ከኅሊና ሲታወር' መጽሐፍ ውስጥ በማካተቱ አንባቢ ከሰለቸኝ በቅድሚያ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

እኔ በምተረጉማቸውም ሆነ በምጽፋቸው መጻሕፍት፣ ችሎታዬ በፈቀደ መጠን፣ ስለጐሳያት እጠነቀቃለሁ። ሁልጊዜም እኔ ስጽፍ በተቻለ መጠን የጐሳያትን አገባብ ጠብቄና የጥንቱን የአማርኛ ሕግንና ሥርዓትን ተከትዬ ስለሆነ አንባቢ ከፈለገ ሊጠቀምባቸው ይችላል። የአማሪኛና የግዕዝ ቋንቋ ሊቃውንት ያለ ምክንያት አይደለም ሦስት (ሀ፣ ሐ፣ ኀ)፣ ሁለት (አ፣ ዐ)፣ ሁለት (ጸ፣ ፀ)፣ ዘፈደላት ውስጥ ያካተቱት። ጐሳያት ያለበታቸው ሲገቡ የተለየ ትርጉም ሊሰጡ እንደሚችሉ ሊቃውንቱ ይናገራሉ። ሆኖም የተሊያዩ ጸሐፊዎች በማይሆን ጐሳያት ሲጠቀሙ ማየትና ማንበብ እጅግ በጣም ያዎግል። ለምሳሌ ዓመት (አመት) መጽሐፍ (መፅህፍ)፣ ኃይለ ሥላሴ (ሀይለ ስላሴ)፣ ዐሐይ (ኣጎይ) እየተባለ ሲጻፍ ምን ዓይነት ስሜት ሊፈጥር እንደሚችል አስቡት። እነዚህ ፊደሎች የቋንቋው ውበት ስለሆኑ ጠቢባኑ እንደዚያ ያደረጉት ያለ ምክንያት አይደለምና እንወቅበት።

እኔ በቋንቋው ይህን ያህልም የጠለቀ እውቀት የለኝም። ሆኖም ስለዚህ ጉዳይ የምጽፈው፣ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ እንዲሁም ኮሌጅ በነበርኩበት ጊዜ በቀሰምኩት እውቀት መነሻነት ነው። ስለዚህ እኔም ራሴ ብሆን ልሳሳት እችላለሁ። ቢሆንም ግን አቅሜና ችሎታዬ በፈቀደ መጠን ስለምጠ ነቀቅና ጥረት ስለማደርግ በሙያው የጠለቀ እውቀት ከሌላቸው ካንዳንድ ወጣቶች/አሐፊዎች የምሻል ይመስለኛል። ስለዚህ እባካችሁ የአማርኛ ቋንጃ መምህራንና ጸሐፊዎች ስለጉዳዩ እጅግ አድርጋችሁ አስበቡበት፣ ትከረትም ስጡት። ስለአማርኛ ሰዋስው ቀደም ሲል የተዘጋጁትን መጻሕፍትንና መመሪያዎችን በማጣቀስ ጻፉ/አስተምሩ። ምናልባትም እኔ የጻፍኳቸውን መጻሕፍት ማየትም ሊጠቅም ይችል ይሆናል። የኔጠላና የድርብ ሰረዝ፣ እንዲሁም የአራት ነጠብ (፣ ፤ ።) ጉዳይም እንዲሁ ነው።

ያለችን አንድ የመግባቢያ ቋንቋ አማርኛ ስለሆነ ልናበላሸው አይገባም። አማርኛ፣ ከግዕዝ ወይም ከሳቢያን የመረሰነው የሌም ቋንጃ ይመስለኛል።

Scan by Easy Scanner

ስለአመጣጡና ሰለታሪኩ ለባለሙያ ሙተጪ ይሻላል። የእኔም ዓላማና ፍላጎት በለቋንቋው አመጣጥ ማስተማር አይደለም። ሆነም ቀረም የአማርኛ ቋንቋ የራሱ የሆነ ፊደል አለው። ያ ደግሞ እኛን አጅግ የሚያኰራ ሲሆን ሌሎች፣ ሁሉም የጥቁር ሕዝቦች ለማለት ይቻላል፣ የራሳቸው የሆነ ፊደል የላቸውም። ስለዝርዝሩ ምሑራን ይተቹበት። ስለዚህ ፊደሎቻችንን ብአግባቡ እንጠቀምባቸው። የእውቀት ሳይሆን የስሜት ተገዥ ሆነን እኛ ተዋርደን አገራችንንም አናዋርድ፣ የቋንቋችንንም ደረጃ አናውርድ። ለአማርኛ ቋንቋ የምንጠቀምባቸው የግዕዝ ፊደሎች የአማራ ብቻ ሳይሆኑ የሁሉም ጐሣና ነገድ ፊደሎች ስለሆኑ የኢትዮጵውያን ሁሉ ሀብቶች ናቸው።

በሕይወት ዘመኔ ካዘንኩባቸው ቀኖች አንዱ የኦሮሚፋ ቋንቋ ተናጋሪዎች በግዕዝ ፊደል ሳይሆን በላቲን ፊደል ለመጠቀም የመሰኑ እለት ነው። ከግዕዝ ፊደል የላቲን ፊደል ይቀርባል ያለው ማነው? ለምንስ ብለን ነው ሁለት መጻሕፍት ለማሳተም የምንችልበትን ፊደል ትተን በላቲን ፊደል በመጠቀም አንድ መጽሐፍ ብቻ የምናሳትመው? ዓላማው ምን እንደሆነ አይገባኝም። በአናባቢ ፊደሎች ብዛት ራሳችንን ከምናስጨንቅ ለምን የቋንቋው ድጋፍ ሊሆኑ በሚችሉ ምልክቶች አንጠቀምም? እባካችሁ የስሜት ተገዥ ሳንሆን ለዘለቄታው የሚጠቅመውን እንያዝ። ኤርትራውያን እንኳን በግዕዝ ፊደል ነው የሚጠቀሙት። ይልቁንስ ኦሮሚፋ ኢትዮጵያ ውስጥ በሰፊው የሚነገር ቋንቋ ስለሆነ ወጣቶች ሁሉ ከአንደኛ ደረጃ ጀምረው እንደ ቋንቋ እንዲማሩት ቢደረግ ስለሚጠቅም ትኩረታችን በዚያ ላይ ይሁን። ይህን ፊደል ትተህ በዚህኛው ተጠቀም ማለቱን ትታችሁ የኦሮሞዎች የእለት ተእለት ሕይወት የሚሻሻልበትን መንገድ አስተምሩ።

ሌላው እኔን የሚያሳምመኝ፣ ባለማወቅ ይሁን በማወቅ፣ ሰንናገርም ሆነ ስንጽፍ ፊደሎችን የብዙ ብዙ እያደረግን ቋንቋችንን የምናበላሽበት ፈሊጥ ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያውያኖች፣ ሕፃናቶች፣ ሰዓታቶች፣ መጻሕፍቶች፣ ትጉኃኖች፣ ምንዱባኖች..... እንላለን። ኢትዮያውያን፣ ሕፃናት፣ ሰዓታት፣ መጽሐፍት፣ ትጉኃን፣ ምንዱባን ብንል በቂ ነው። ከዚህም ሌላ፣ እጅግ የሚያሳዝነው የአማርኛ ቃል ሳይጠፋ በእንግሊዝኛ ቃላት የመጠቀማችን ጉዳይ ነው። አንዳንዴ በእንግሊዝኛ ቃላት የተሞሉ የሬድዮና ቦቴሌቪዥን ውይይቶችና ፕሮግራሞች መስማቱና ማየቱ ያምማል፣ ይለለቻል፣ ያስጠላል፣ ያናድዳል። እርስ በእርስ ሲጫወቱም እንዲሁ። 'አባባና እማማ' እያሉ 'ፋዘር፣ ማዘር' ምን ያስብላል?

በአንድ ወቅት ሁለት ሆነው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሲያቀርቡ ሴትዋ ፕሮግራም አቅራቢ ደግማና ደጋግማ 'ላይክ አደረጉን፣ ላይክ አደረግናቸው'

ትላለች። በእርስዋ ቤት አዋቂ መሆንዋ ነው። የራስን መካድ ያዋርዳል እንጂ እዋቂ አያሰብልም። 'ወደዱን፣ ወደድናቸው' ማለት ምን ገዶ ነው ወደ እንግሊዝኛው ቃላት የሚያስኬደው! አብሯት የነበረው ፕሮግራም አቅራቢም አነጋገሯን ለማስተካከል አልሞከረም፣ እንዲያውም ከነአካቴው እርስዋን በመደገፍ እርሱም በእንግሊዝኛ ቃላት ይጠቀም ጀመር።

ሌላው ለምሳሌ 'ስንት 'ትቸርጀሻለህ' የሚል ቃል ሲነገር እሰማለሁ። 'ዋጋው ስንት ነው? ብለን ብንጠይቅ ምን እንሆናለን? በዚህ አጋጣሚ በኢትዮጵያ ማሰራጫ አገልግሎት 'በኢ.ቢ.ኤስ ፖሊን ሾው' ፕሮግራም አዘጋጅንና አቅራቢን ለማመሰገን አፈልጋለሁ። ብዙ ሰዎች የእንግሊዝኛ ቃል ከንግግራቸው ውስጥ ሲዶሉ አንዳንዴ እርስዋ አባባሎቹን፣ በስሱ ቢሆንም፣ እየተረጐመች የአማርኛውን ቃል ወይም ሐረግ በማስገባት ተመልካችንና አድማጭን ለመርዳት ትሞክራለች። እባካችሁ ሌሎቻችሁም የእርስዋን ፈለግ በመከተል አማርኛችንን አክብሩ/አሰክብሩ።

በሃገራችን ላይ የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ራሱን 'ኢትዮጵያን ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን' እያለ የሚጠራው ለምን ይሆን? 'የኢትዮጵያ ማሠራጫ ተቋም ወይም ድርጅት' ማለት ተስኖት ይሆን? 'ኢቲቪ' ከማለትስ 'የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን' ቢባል ምን አለበት? ወይስ ሌላው የወያኔ ደባ ነው? እኔ አይገባኝም።

ሌላም ሌላም ብዙ ነገሮችን ማንሳት ይቻል ነበር። ነገር ግን የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ይህ ስላልሆነ ማሰለቢያውን በዚሁ ማቆሙ ይሻላል። ለማንኛውም እባካችሁ የሆነውን ነገና ያልሆነውን ለመሆን እንሞክር። የሆንነው ያስከብረናል እንጂ አያዋርደንም። በማያስፈልጉ የእንግሊዝኛ ቃላት በመጠቀም ያልሆነውን ለመሆን መሞከርም እኛነታችንን ከፍ አያደርገውም፣ አዋቂም አያስብለንም። እንዲያውም አላዋቂነታችንን ገሃድ ያወጣል።

በትዕግሥት አላቤን ስለተካፈላችሁ አመሰግናለሁ። እናንተ ግን በዚሁ አታቁሙ፣ ተወያዩ፣ በውይይቱም ቀጥሉበት። እኔ ከተሳሳትኩም አርሙኝ። ሌላው ቢቀር ፕሌቶ እንዳለው እኔ አለማወቄን አውቃለሁ።

Scan by Easy Scanner

ምስጋና

ምንም እንኳን እናቴ ነዘብ ተርማማ በልጅነቴ በሞት ብትለየኝም አብረን በቆየንባቸው ጥቂት ዓመታት በስጠኝ ምክር ለሕይወቴ መሠረት ጥላልኝ አልፋለች። ባለቤቴ ወ/ሮ ቅድስት ኃሻው ማፈኛም ከተገናኘን ጀምሮ ከጐኔ በመቆም በሥነ ጽሑፍ ሥራዬ እንድገፋና እንድበረታ የበሰለ አሳብና ምክር በመስጠት ረድታኛለች። ስለዚህ ለሁለቱም የማቀርበው ምስጋና የላቀ ሲሆን የዚህ መጽሐፍ ማስታወሻነትም ዘመትር ከህሊናዬ ለማትጠፋው ለውድ እናቴና ከልብ ለማፈቅራት ለውድ ባለቤቴ ይሁን። እስከ ዛሬ የጻፍኳቸውንና የተረጐምኳቸውን አነስተኛ መጻሕፍት ግዙት በማንበብ ያበረታቱኝን አንባቢያን ሳላመሰግን ማለፉ ደግሞ ትክክል ስለማይሆን እነርሱንም ከልብ አመሰግናለሁ።

አስጀምሮ ላስጨረሰንም አምላክ ምስጋና ይግባዋልና ይደልያ እንበል። — አሜን —

ዮሐንስ ገብረ ጻድቅ: 0911 69 80 23

Scan by Easy Scanner



ሀሊና ሲታወር

ኤሊኖር በባልዋና በልጆችዋ ረክታና ተደስታ የምትኖር ሴት ነበረች። የኋላ ኋላ ግን ባልዋ ምናልባት በፍቶተ-ሥጋ አምሮት ወይም በሌላ በውል ባልታወቀ ምክንያት ሀሊናው ታውሮ ለውበትዋ ወደር ከማይገኝላት ሴት ጋር የኮበለለው "ግድ የለም፣ ለአንድ ሰሞን ነው" በሚል ፈሊጥና የወደደችውን ሴት የፍቅር ጽናት በመገንዘብ ነበር። የኋላ ኋላ ግን ማጣፊያው አጥሮት ከአርሰዋ ለመራቅ ስላልቻለ የሚስቱን፣ የልጆቹንና የራሱን ሕይወት አበላሸ። አፍቃሪዋ ሴት ደግሞ ገና ከመጀመሪያው እድለ-ሰንኳላ ስለነበረች ብልጭልጭ ነገር አታለሎአት ከማይሆን ጋብቻ ውስጥ ተዘፈቀች። ከዚያ ካልተባረከ ትዳር ለመላቀቅም የማይሆን እርምጃ ወሰደች። በዚህም የራስዋን ሕይወት አበላሽታ ለሌሎች ሕይወት መበላሸትም ምክንያት ሆነች፤ እሷም ከሚገባት በላይ ተሰቃየች። ሀሊና ያለው ፍጡር ለምን እስከዚህ የስሜት ተገዥ ሆኖ ሕይወቱን ያበላሻል? ለምን አንዳንድ ሰው እድለቢስ ሆኖ ይፈጠራል? አንዳንዱስ መልካም ሰው ሆኖ ሳለ ለምን ያላግባብ ይሰቃያል? ዝርዝሩን ከዚህ ሲቃ ከሚያሲይዝ ታሪክ ያንብቡ።

"ሀሊና ሲታወር" ከጣማችሁ "ከመኒን" ቀጥሎ ያንብቡ። "ከመኒ ባል ያለው እርሱም ከመኒ ነው፣ ከሰው ሠርግ አይሄድም እቤቱ ሠርግ ነው፣ አጎዛ ሚስት ያለው እርሱም አጎዛ ነው፣ ከሰው ለቅሶ አይሄድም እቤቱ ለቅሶ ነው።" ከመኒ የሆነና የሚመኙት መልካም ሰው ለማግኘት ሲባል የሚደረገው ጥረት በአብዛኛው የማይረባ ማለት "ቢከፍቱት ተልባ" እየሆነ ብዙ ያንከራትታል፣ ያበሳጫል፣ ያስለፋል፣ የቁም ስቃይ ያሳያል። ለምን? እንዴት? ምክንያቱስ? ምሥጢሩን ለማወቅና ትምህርት ለመቅሰም ሌላኛው ትርጉሜን የ[illegible]ቱል "ከመኒን" ያንብቡ።

የተርጓሚው ሥራዎች

- ኑሮ በዘዴ
- መንግሥትና ሕዝብ
- የውበት ወሞመድ
- ምንዱባን
- ከመኒ
- ሀሊና ሲታወር

ዋጋው፡ ዘጠና አምስት ብር (95፡00)

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ
0113 691933

Scanned by Easy Scanner